# ነገዎቻችንን አዲስ እንደገና የትምህርት በጋራ ማጤን ማኅበራዊ ውል

**ክብርት ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**
አንቶኒዮ ኖቮአ፣ ማሳኖሪ አዎያጊ፣ አርጁን አፓዱሬ፣ ፓትሪክ ኤዋህ፣ አብደል ባሴት ቤን ሀሰን፣ ክሪስቶቫም ቡዋርክ፣ ኤሊዛ ጉዌራ፣ በድር ጃፋር፣ ዶ-ዮን ኪም፣
ጀስቲን ዩፉ ሊን፣ ዩቭጌኒ ሞሮዞቭ፣ ካረን ሙንዲ፣ ፌርናንዶ ኤም ሬይሜርስ፣ ታርሲላ ሪቬራ ዚያ፣ ሰሪን እምባይ ቲያም፣ ቫይራ ቪከ ፍሬይበርጋ፣ ማሃ ያህያ

### ዩኔስኮ - በትምህርት ዓለም አቀፍ መሪ

ትምህርት ዩኔስኮ ዋነኛ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ የሆነው መሠረታዊ የሰብአዊ መብት እና ለሰላምና ዘላቂ ልማት መሠረት ስለሆነ ነው። ዩኔስኮ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ የትምህርት ኤጀንሲ እንደመሆኑ፤ እድገትን ለማምጣት ዓለም አቀፍ እና ቀጣናዊ አመራር ይሰጣል፤ ሁሉንም ተማሪዎች ለማገልገል የብሔራዊ ሥርዓቶችን ጽናት እና ዕቅምን ያጠናክራል። የዩኔስኮ ለየጊዜው ዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶች በሥርዓተ ጾታ እኩልነት እና በአፍሪካ በሁሉም ተግባራት ላይ ልዩ ትኩረት ያደረጉ ለዋጭ የትምህርት ጥረቶችን ይመራል።

### የትምህርት ነገዎች ኢኒሼቲቭ

ኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ዕውቀት እና ትምህርት የሰውን ልጅ እና የፕላኔቷን የወደፊት ሁኔታ እንዴት እንደሚቀርጽ እንደገና ለማሰብ በ2019 በዩኔስኮ ተቋቋመ። ውጥኑ ሰፊ የሕዝብ እና የባለሞያዎች ተሳትፎን የሚያጠቃልል ሲሆን፤ ውስብስብነት፣ አላስተማማኝነት እና ደካማነት በበዛበት ዓለም ትምህርት እንዴት እንደገና መቃኘት እንዳለበት ዓለም አቀፍ ክርክርን ለመፍጠር ያለመ ነው።

unesco

የተባበሩት መንግስታት
የትምህርት፣ የሳይንስ
እና የባህል ድርጅት

በ2024 በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት ታተመ
7, place de Fontenoy, 75352 Paris 07 SP, France እና የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ
Gulele Subcity, Woreda 9, House No. 199, P. O. Box 32228, Addis Ababa, Ethiopia

© ዩኔስኮ እና የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ 2024

ISBN 978-92-3-000232-9
https://doi.org/10.54675/DDXA6216

CC BY SA

ይህ ኅትመት በAttribution-ShareAlike 3.0 IGO (CC-BY-SA 3.0 IGO) ፍቃድ በክፍት መዳረሻ ውስጥ ይገኛል።
(http://creativecommons.org/licenses/by-sa/3.0/igo/)። ተጠቃሚዎቹ የዚህን ህትመት ይዘት ሲጠቀሙ፣ ለዩኔስኮ ክፍት መዳረሻ ማከማቻ
(https://www.unesco.org/en/open-access/cc-sa) የአገልግሎት ውል እንደተስማሙ ይቆጠራል።

ዋናው ርእስ፡- *Reimagining our futures together: A new social contract for education*
በ2021 በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት ታተመ።

በዚህ ኅትመት ውስጥ የተካተቱት ስያሜዎች እና የክፍሎቹ አቀራረብ በዩኔስኮ የየትኛውም ሀገር፣ ግዛት፣ ከተማ ወይም አካባቢ ወይም የባለስልጣናት ሕጋዊ ሁኔታ ወይም የወሰኖችን ወይም የድንበሮችን ሁኔታ በተመለከተ ምንም ዓይነት አስተያየት መገለጹን አያመለክትም።

ኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን አባላት በኅትመቱ ውስጥ ለተካተቱት እውነታዎች እና በውስጡ ለተገለጹት አስተያየቶች ምርጫ እና አቀራረብ ተጠያቂ ናቸው። እነዚህ የግድ የዩኔስኮ አይሆኑም፤ ድርጅቱንም አይገልጹም።

የእንግሊዝኛው የቅጅ አርታዒ፡- ሜሪ ደ ሱሳ
ተርጓሚ፡- ቴዎድሮስ አጥላው ወልደገብርኤል

የአማርኛው የቅጅ አርታዒ፡- ፕሮፌሰር ዘላለም ልየው

በዩኔስኮ ዲዛይን ተደርጎ ታተመ

የአማርኛው ሌይአውት ዲዛይን፡- የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ

በፈረንሳይ የታተመ

ኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ሥራ በስዊድን ዓለም አቀፍ ልማት ትብብር ኤጀንሲ (ሲዳ)፣ በፈረንሳይ መንግሥት እና በባንኮ ሳንታንደር ልግስና ተደግፏል።

**አ ጭ ር   ጭ ም ቅ   ሐ ሳ ብ**

# አዲስ ማኅበራዊ ውል ለትምህርት

የሰው ልጅ እና ምድር ፕላኔታችን ስጋት ላይ ናቸው። ወረርሽኙ አቅመቢስነታችንን እና መተሳሰራችንን ለማረጋገጥ ብቻ አገልግሏል። አሁን አካሄዳችንን ለመቀየር እና መጻዒ ሕይወታችንን እንደ አዲስ ለማለም በጋራ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። ይህ የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ኮሚሽን ሪፖርት ትምህርት ጥልቅ ለውጥ ለማምጣት ላለው ኃይል ዕውቅና ይሰጣል። ለሁሉም ሕፃናት፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብትን ለማረጋገጥ እና ትምህርት ለዘላቂ የጋራ የወደፊት ጉዞዎች መንገድ በመሆን ያለውን የለዋጭነት አቅም ሙሉ በሙሉ ዕውን ለማድረግ የተገባውን እና ያልተፈፀመውን ቃል ለመፈጸም መንታ ፈተና ይገጥመናል። ይህንን ለማድረግ፣ የወደፊቱን እየለወጥን ኢ-ፍትሐዊነትን የምጠግንበት አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ያስፈልገናል።

ይህ አዲስ ማኅበራዊ ውል በሰብአዊ መብቶች ላይ የተተከለ እና በኢ-አድሎአዊነት፣ በማኅበራዊ ፍትሕ፣ ሕይወትን በማክበር፣ በሰብአዊ ክብር እና በባሕል ስብጥር መርሆዎች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። እርስበርስ የመተሳሰብን የመደጋገፍንና የመከባበርን ሥነ ምግባር ያቀፈ መሆን አለበት። ትምህርትንም እንደ ሕዝባዊ ጥረት እና የጋራ ጥቅም ማጠናከር አለበት።

አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎችን ባሳተፈ ዓለም አቀፍ የምክክር ሂደት ለሁለት ዓመታት ሲዘጋጅ የቆየው ይህ ሪፖርት፣ በዓለም ዙሪያ ያሉ መንግሥታት፣ ተቋማት፣ ድርጅቶች እና ዜጎች ለሁሉም ሰው ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ዘላቂ ነገዎችን ለመገንባት የሚረዳ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል እንዲፈጥሩ ይጋብዛል።

እዚህ የቀረቡት ራእዮች፣ መርሆች እና ምክረ ሐሳቦች መነሻዎች ብቻ ናቸው። እነሱን መተርጎም እና ከየአውዱ ጋር ማስማማት የጋራ ጥረት ነው። ብዙ ጭላንጭል ብርሃኖች ወትሮውኑም አሉ። ይህ ሪፖርት ጭላንጭሎቹን ይዞ፣ እነርሱን ለማስፋት ይሞክራል። ነገር ግን ሪፖርቱ መመሪያም ሆነ ንድፍ ሳይሆን፣ የወሳኝ ውይይት መክፈቻ ነው።

**የወደፊቱን እየለወጥን ኢ-ፍትሐዊነትን ለመጠገን አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ያስፈልገናል**

unesco

«ጦርነቶች በወንዶች እና በሴቶች አእምሮ ውስጥ ስለሚጀምሩ፣ የሰላም መከላከያዎችም መገንባት ያለባቸው በወንዶች እና በሴቶች አእምሮ ውስጥ ነው።»

# ነገዎቻችንን አዲስ እንደገና የትምህርት በጋራ ማጤን ማኅበራዊ ውል

የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ሪፖርት

# ቀዳሚ ቃል

**አድሪ አዙሌ**
የዩኔስኮ ዳይሬክተር ጄነራል

ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ውስጥ አንድ ነገር ካሰባሰበን፣ ያ የአሁን ተጋላጭነት እና ስለወደፊቱ እርግጠኛ ያለመሆን ስሜታችን ነው። የሰው ልጅን አካሄድ ለመለወጥ እና ፕላኔቷን ከተጨማሪ ምስቅልቅል ለማዳን አስቸኳይ እርምጃ እንደሚያስፈልግ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አሁን ዐውቀናል። ነገር ግን ይህ እርምጃ የረጅም ጊዜ እና ከስልታዊ አስተሳሰብ ጋር የተጣመረ መሆን አለበት።

ትምህርት እነዚህን አስጨናቂ ፈተናዎች ለመፍታት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ሆኖም፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝእንዳሳየው፣ ትምህርት አቅመ ደካማ ነው፡- ወረርሽኙ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰ ጊዜ፣ በመላው ዓለም ትምህርት ቤቶች በመዘጋታቸው 1.6 ቢሊዮን ተማሪዎች ተጎድተዋል።

በእጅ ያለ ነገር እስኪታጣ ድረስ እጅግም አይደነቅም። በዚህም ምክንያት፣ ዩኔስኮ በኢፌዲሪ ፕሬዝደንት ክብርት ወ/ሮ ሣህለ ወርቅ ዘውዴ መሪነት በኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን የተዘጋጀውን ይህንን ነገዎቻችንን እንደገና በጋራ ማጤን፤ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል የተባለ አዲስ ሪፖርት ተቀብሎታል።

ዩኔስኮ ከተመሠረተ ከ75 ዓመታት በፊት ጀምሮ በማኅበረሰባዊ ለውጥ ቁልፍ ጊዜያት ትምህርት የሚጫወተውን ሚና መልሶ መቃኘት የሚያስችሉ በርካታ ዓለም አቀፍ ሪፖርቶችን አሠርቷል። ይህም ለመሆን መማር፡- የትምህርት ዓለም ዛሬ እና ነገ በተባለው የፉውሬ ኮሚሽን የ1972 ሪፖርት ተጀምሮ፤ እና በ1996 በዴሎርስ ኮሚሽን በተሠራው መማር፡- በውስጥ የታመቀው ሀብት በተባለው ሪፖርት ቀጥሏል። እነዚህ ሁለቱም ሪፖርቶች ጥልቅ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ነበሩ፤ ይሁን እንጂ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ዓለም በመሠረቱ ተለዋውጧል።

እንደቀድሞዎቹ ሪፖርቶች ሁሉ፣ የሣህለ ወርቅ ኮሚሽን ሪፖርትም በዚህች ፕላኔት ላይ ያሉ ሕያዋንን በሙሉ ህልውናቸውን ለማሻሻል በሚያስችል መንገድ ትምህርትን ለመምራት ስለሚያስፈልጉ ፍልስፍናዎች እና መርሆዎች የሚደረጉ ውይይቶችን እያስፋፋ ነው። ሪፖርቱ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የተሠራ እና ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሰዎች ጋር በተከናወኑ ሰፊ ምክክሮች ላይ የተገነባ ነው።

ሪፖርቱ የሚያስተምረን አንድ ነገር ካለ ይህ ነው፡- አካሄዳችንን ለመቀየር አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አለብን፤ ምክንያቱም የሰዎች የወደፊት ዕጣ በፕላኔቷ የወደፊት ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው፤ ሁለቱም ደግሞ አደጋ ላይ ናቸው። ሪፖርቱ እርስበርስ፣ ከፕላኔቷ እና ከቴክኖሎጂ ጋር ያለንን ግንኙነት እንደገና ለመገንባት ያለመ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል እንዲገባ ምክረ ሐሳብ ያቀርባል።

ይህ አዲስ ማኅበራዊ ውል ያለፈውን ኢ-ፍትሐዊነት ለመጠገን እና የወደፊቱን ለመለወጥ የሚያስችለን ዕድላችን ነው። ከሁሉም በላይ፣ በሕይወት ዘመን ሁሉ ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብት ላይ የተመሠረተ፣ ማስተማር እና መማርን እንደ የጋራ ማኅበረሰብ ጥረቶች እና ስለዚህም እንደ የጋራ ጥቅሞች የሚቆጥር ነው።

ይህ የትምህርት ራዕይ ዕውን ለማድረግ የማይቻል ሥራ አይደለም። በተለይ በወጣቶች ዘንድ ተስፋ አለ። ነገር ግን፣ አካታችነት፣ ፍትሐዊነት፣ ሰብአዊ መብቶች እና ሰላም የወደፊት ሕይወታችንን የሚገልጹ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመላውን ዓለም ፈጠራ እና ብልኅነት እንፈልጋለን። በመጨረሻም፣ ይህ ሪፖርት እንድናደርግ የሚጋብዘንም ይህንኑ ነው። በዚህ ምክንያት ብቻ እንኳን፣ ለእያንዳንዳችን ጠቃሚ ትምህርቶች አሉት።



**ኦድሪ አዙሌ**

የዩኔስኮ ዳይሬክተር ጄነራል

# ቀዳሚ ቃል

**ክብርት ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**
የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ሊቀመንበር
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት

የምድራችን የወደፊት እጣ ፈንታ በአካባቢያዊ እና በዲሞክራሲያዊ መንገድ የታለመ መሆን አለበት። የምንፈልጋቸው ነገዎች ዕውን የሚሆኑት የሕዝቦቻችንን እና ባሕሎቻችንን የበለጸገ ስብጥር በውጤታማነት መጠቀም በሚያስችሉ የጋራ እና የግል ተግባራት ብቻ ነው።

የሰው ልጅ አንድ ፕላኔት ብቻ ነው ያለው፤ ሆኖም የፕላኔቷን ሀብቶች በአግባቡ አንጋራቸውም ወይም ዘላቂነት ባለው መንገድ አንጠቀምባቸውም። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች መካከል ተቀባይነት የሌለው መበላለጥ አለ። ለሴቶች እና ልጃገረዶች የጾታ እኩልነትን ከማረጋገጥ የራቅን ነን። የቴክኖሎጂ አቅም እርስበርስ ሊያገናኘን ተስፋ ቢሰጠንም፣ በተለይም በአፍሪካ፣ አሁንም ሰፊ የዲጂታል ተጠቃሚነት ልዩነቶች አሉ። በሰዎች ዕውቀትን የማግኘት እና የመፍጠር ችሎታ ረገድም፣ ሰፊ የአቅም አለመመጣጠኖች አሉ።

እነዚህን ሥር የሰደዱ ኢ-ፍትሐዊ መበላለጦች ለመፍታት ትምህርት ቁልፍ መንገድ ነው። የምናውቀውን መሠረት አድርገን፣ ትምህርትን መለወጥ አለብን። መማሪያ ክፍሎች እና ትምህርት ቤቶች አስፈላጊ ቢሆኑም፤ ወደፊት በተለየ መንገድ ሊገነቡ እና የሚገኝባቸው ተሞክሮም ሊለወጥ ይገባል። ትምህርት በ21ኛው ክፍለ ዘመን የሥራ ቦታዎች የሚያስፈልጉትን ክህሎቶች ማሳደግ አለበት፤ ይህም የሚሆነው የሥራውን ተለዋዋጭነት እና የኢኮኖሚ ደህንነትን በተለያዩ መንገዶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ከዚህ ባለፈም፣ ሁለንታዊ የትምህርት መብት መጠበቁን ለማረጋገጥ ለትምህርት ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍ መስፋፋት አለበት።

ሰብአዊ መብቶችን ማክበር እና ትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም መቁጠር የጋራ ዓለማችንን እና የተያያዙ ነገዎቻችን ማስተሳሰሪያ ዋነኛ ክሮች ሊሆኑ ይገባል። ይህ ሪፖርት እንደሚሞግተው፣ እነዚህ ሁለቱ ሁለንታዊ መርሆች በየትኛውም ሥፍራ ላለው ትምህርት መሠረቶች መሆን አለባቸው። ጥራት ያለው እና ግለሰቦች ለጋራ ጥቅም በጋራ ለመሥራት ያላቸውን አቅም የሚያጎለብት ትምህርት በየትኛውም ቦታ የማግኘት መብት መከበር፣ እያበቡ ለሚሄዱ ልዩ ልዩ የትምህርት መጻዒ ዕድሎች መሠረት ይሆናል። ለሰብአዊ መብቶች መከበር እና ለጋራ ጥቅም መረጋገጥ በምናሳየው ዘላቂ ቁርጠኝነት አማካይነት፣ የሰው ልጅ ባሕሎች እና ማኅበረሰቦች ወደ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ መማር ማስተማር፣ እንዲሁም ልናካፍለው እና ሰብስበን ልናደራጀው ወደምንችለው ዕውቀት የሚያመጧቸው እጅግ ሰፊ እና ልዩ ልዩ የማወቂያ እና የመኖሪያ መንገዶች ልናዘልቃቸው እና ልንጠቀምባቸው እንችላለን።

ይህ ሪፖርት በ2019 በዩኔስኮ የተቋቋመው ኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን የዓለም የጋራ ሥራ ውጤት ነው። ልዩ ልዩ ከሆነው እና መልክዓ ምድራዊ ስብጥር ባለው ቡድናችን አባላት በሙሉ ለታየው ቁርጠኝነት እና ለተበረከተው አስተዋጽኦ ዕውቅናዬን እየሰጠሁ፣ በተለይ የኮሚሽኑን የምርምር እና አርቃቂ ኮሚቴ በሰብሳቢነት የመሩትን በዩኔስኮ የፖርቹጋል አምባሳደር አንቶኒዮ ኖቮዋን ላመሰግን እወዳለሁ። ነገዎቻችንን እንደገና በጋራ ማጤን ውስጥ የቀረቡት ምክረ ሐሳቦች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመጣው የዓለም አይጨበጤነት፣ ውስብስብነት እና አይገመቴነት መሀል ፈጠራ፣ ጽናት እና ተስፋ መትረፍረፉን ከሚያሳይ ዓለም አቀፋዊ ተሳትፎ እና አብሮ የመገንባት ሂደት የመነጩ ናቸው። በተለይም እንደገና ማሰብ የሚያስፈልጋቸው የሚከተሉት ወሳኝ  አርእስተ ጉዳዮች የወደፊት ሁኔታ ተመርምሯል፡- ዘላቂነት፤ ዕውቀት፤

መማር ማስተማር፤ መምህራን እና ማስተማር፤ ሥራ፣ ክሂሎቶች እና ብቃቶች፤ ዜግነት፤ ዲሞክራሲ እና ማኅበራዊ አካታችነት፤ የሕዝብ ትምህርት፤ እንዲሁም ከፍተኛ ትምህርት፣ ምርምር እና ኢኖቬሽን።

ኮሚሽኑ ባለፉት ሁለት ዓመታት ያከናወናቸው ተግባራት በዓለም አቀፉ የጤና ወረርሽኝ የተቃኘ ሲሆን፤ የኮሚሽኑ አባላት ከትምህርት ቤቶች መዘጋት ጋር ለመጋፈጥ የተገደዱ ሕፃናት፣ ወጣቶች እና በሁሉም ዕድሜ ያሉ ተማሪዎች ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች ጠንቅቀው ያውቃሉ። ነገዎቻችንን እንደገና በጋራ ማጤንን መታሰቢያ የምናደርገው በኮቪድ ሕይወታቸው ለተናጋባቸው ተማሪዎች እና መምህራን፣ እንዲሁም በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ደህንነታቸውን፣ ዕድገታቸውን እና የመማር ማስተማሩን ሂደት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ላደረጓቸው አስደናቂ ጥረቶች ነው።

በዚህ ሪፖርት የተካተቱት ምክረ ሐሳቦች እና አስፈላጊነቱ የታመነበት ሕዝባዊ ውይይት እና የጋራ እርምጃ የሰው ልጅን እና የፕላኔታችንን መጻዒ ጊዜያት ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ዘላቂ እንዲሆን የመቅረጹን ጥረት የሚያፋጥኑ እንደሚሆኑ ተስፋ አለን።



**ክብርት ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**
**የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ሊቀመንበር**
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት

# ኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን

**ክብርት ሣህለ ወርቅ ዘውዴ፤** የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት እና የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ሊቀመንበር

**አንቶኒዮ ኖቮአ፤** በሊዝበን ዩኒቨርስቲ ኢንስቲቲዩት ኦፍ ኤጁኬሽን ፕሮፌሰር እና የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን የምርምር ማርቀቅ ኮሚቴ ሰብሳቢ

**ማሳኖሪ አዎያጊ፤** በቶኪዮ ዩኒቨርስቲ ኢሜሪተስ ፕሮፌሰር

**አርጁን አፓዱሬ፤** , በኒው ዮርክ ዩኒቨርስቲ የሚዲያ፣ ካልቸር ኤንድ ኮሙኒኬሽን ኢሜሪተስ ፕሮፌሰር እና በኒው ዮርክ የባርድ ግራጁዌት ሴንተር የማክስ ዌበር ግሎባል ፕሮፌሰር

**ፓትሪክ ኤዋህ፤** በጋና የአሼሲ ዩኒቨርስቲ መሥራች እና ፕሬዝደንት

**አብደል ባሴት ቤን ሀሰን፤** በቱኒዚያ የአረብ ኢንስቲቲተት ኦፍ ሂዩማን ራይትስ ፕሬዝደንት

**ክሪስቶቫም ቡዋርከ፤** በብራዚሊያ ዩኒቨርስቲ ኢሜሪተስ ፕሮፌሰር

**ኤሊዛ ጉዌራ፤** በሜክሲኮ የኮሌጂዮ ቫሌ ደ ፊላደልፊያ፣ መምህርት እና መሥራች

**በድር ጃፋር፤** , በዩናይድ አረብ ኤሚሬትስ፣ የክሬሰንት ኢንተርፕራይዝስ ዋና ሥራ አስኪያጅ

**ዶ-ዮን ኪም፤** በሴኡል ናሽናል ዩኒቨርስቲ ኢሜሪተስ ፕሮፌሰር እና የቀድሞ የኮርያ ሪፐብሊክ የትምህርት፣ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር

**ጀስቲን ዪፉ ሊን፤** ፕሮፌሰር፣ በፔኪንግ ዩኒቨርሲቲ የኢንስቲቲዩት ኦፍ ኒው ስትራክቸራል ኢኮኖሚክስ ዲን

**ዩቭጌኒ ሞሮዞቭ፤** ደራሲ

**ካረን ሙንዲ፤** በዩኔስኮ የኢንተርናሽናል ኢንስቲቲዩት ፎር ኤጁኬሽናል ፕላኒንግ ዳይሬክተር እና በቶሮንቶ ዩኒቨርስቲ፣ የኦንታሪዮ ኢንስቲቲዩት ፎር ስተዲስ ኢን ኤጁኬሽን ፕሮፌሰር (ፈቃድ ላይ ያሉ)

**ፌርናንዶ ኤም ሬይሜርስ፤** በሐርቫርድ ግራጁዌት ስኩል ኦፍ ኤጁኬሽን ፕሮፌሰር፣ ዩኤስኤ

**ታርሲላ ሪቬራ ዚያ፤** የCHIRAPAQ ሴንተር ፎር ኢንዲጂኒየስ ካልቸርስ ኦፍ ፔሩ ፕሬዝደንት

**ሰሪን እምባይ ቲያም፤** የሴኔጋል የውኃ እና የንጽሕና አጠባበቅ ሚኒስትር

**ቫይራ ቪከ ፍሬይበርጋ፤** የላትቪያ የቀድሞ ፕሬዝደንት፣ የኒዛሚ ጋንጃቪ ኢንተርናሽናል ሴንተር የወቅቱ ተባባሪ ሊቀመንበር፣ ባኩ

**ማሃ ያህያ፤** የካርኒጌ ሚድል ኢስት ሴንተር ዳይሬክተር፣ ሊባኖስ

# ምስጋና

የበርካታ ግለሰቦች፣ ኔትወርኮች እና ድርጅቶች ጠቃሚ አስተዋጽኦዎች ባይኖሩ ኖሮ፣ ይህ ሪፖርት ዕውን ሊሆን አይችልም ነበር።

ኮሚሽኑ ገለልተኛ ሪፖርቶችን እና መነሻ ጥናቶችን ያበረከቱትን፣ እንዲሁም በትምህርት የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ በተካሄደው ዓለም አቀፍ ምክክር ላይ የተሳተፉትን ግለሰቦች፣ ድርጅቶች እና ኔትወርኮች ላደረጉት ሁሉ ማመስገን ይፈልጋል (የአስተዋጽኦ አበርካቾችን እና የአስተዋጽኦዎቻቸውን ዝርዝር ከአባሪው ይመልከቱ)።

በዓለማቀፋዊ ትምህርት፣ ምርምር እና ኢኖቬሽን ውስጥ ግንባር ቀደም ሰዎች እና ቁልፍ ስትራቴጂካዊ አጋሮች ከተወከለው የፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን አማካሪ ቦርድ የተገኘው ግብአት በዋጋ አይተመንም (የግለሰቦቹን እና የድርጅቶቹን ሙሉ ዝርዝር ከአባሪው ይመልከቱ)።

በመተንተን እና በማርቀቅ ሂደት ውስጥ ከዩኔስኮ ጽሕፈት ቤት ጋር በቅርበት ለሠሩት እና የረቂቁን ቀዳሚ ቅጂዎች ለገመገሙት ለሚከተሉት ኤክስፐርቶች ልዩ ምስጋና እናቀርባለን:- ትሬሲ በርንስ፣ ፖል ኮሚን፣ ፒተር ሮናልድ ዴሶዛ፣ ኢኔስ ደስል፣ ኬሪ ፌሰር፣ ሂዩ ማክሊን፣ ኤብሪማ ሳል፣ ፍራንሷ ታዴይ፣ ማላክ ዛሎክ እና ሃቪየር ሮግላ ፑይግ።

በመጨረሻም፣ ኮሚሽኑ ዩኔስኮን እና በተለይም ሚስ ስቴፋኒያ ጂያኒኒ፣ የትምህርት ረዳት ዋና ዳይሬክተር፣ ለሰጡት አመራር፣ እንዲሁም ለኮሚሽኑ ሥራ ላደረጉት ያላሰለሰ ድጋፍ፤ የወደፊት የትምህርት እና ኢኖቬሽን ቡድን ዳይሬክተር ሶብሂ ጠዊል እና ቡድናቸውን ከልብ ማመስገን እንፈልጋለን። የቡድኑ አባላት አይዳ አልሃብሺ፣ አሌሃንድራ ካስታኔዳ፣ ካታና ሰርኬራ፣ አኔት ዶሚትር፣ ኬት ሆልምስ፣ ያሮስላቫ ካርኮቫ፣ ስቴፋኒ ማጋሌግ፣ ጃክ ማክኔል፣ ፌንግቹን ሚያዎ፣ ሚቼላ ፓጋኖ፣ ማያ ፕሪንስ፣ ኖዋ ደብልዩ ሶቤ፣ ኤሌና ቶካን እና ማርክ ዌስት ይገኙበታል። ቡድኑ ለፊውቸር ኦፍ ኤጁኬሽን ፕሮጀክት በተለያዩ መንገዶች አስተዋጽኦ ካደረጉ የድርጅቱ በርካታ ባልደረቦች ድጋፍ አግኝቷል።

# ማውጫ

**ቀዳሚ ቃል** **v**
የዩኔስኮ ዳይሬክተር ጀነራል ኦድሪ አዙሌ

**ቀዳሚ ቃል** **vii**
ክብርት ሣህለ ወርቅ ዘውዴ

**ኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን** **ix**

**ምስጋና** **x**

**ዓቢይ ጭምቅ ሐሳብ** **1**

## መግቢያ 7

የሰው ልጅ፣ የሰብአዊ ሙብቶች እና የሕያው ፕላኔት ህልውና አደጋ ላይ ነው 8
የአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል አስፈላጊነት 10
የትምህርትን ዓላማዎች እንደገና መበየን 11
የሪፖርቱ አደረጃጀት 14

## ክፍል አንድ
## ባለፉ ተስፋዎች እና ባልተረጋገጡ ነገዎች መሀል 17

**ምዕራፍ 1 ይበልጥ ፍትሐዊ ወደሆኑ የትምህርት ነገዎች** **19**

ያልተሟላ እና ኢፍትሐዊ የትምህርት መስፋፋት 20
የማያቋርጥ ድህነት እና እየተባባሰ ያለ ኢ-እኩልነት 24
የማግለል ድር 25

**ምዕራፍ 2 መናጋቶች እና አዳዲስ ለውጦች** **29**

በአደጋ ላይ ያለች ፕላኔት 30
የሚያገናኘው እና የሚያለያየው ዲጂታል ቴክኖሎጂ 34
ዲሞራሲያዊ መንሸራተት እና አዳጊው ዋልተኝነት 38
ያልተረጋገጠው የሥራ መጻዒ ሁኔታ 40

## ክፍል ሁለት

**ትምህርትን ማደስ** 46

**ምዕራፍ 3 የትብብር እና የአጋርነት ሥነ ትምህርቶች** 49

ሥነ ትምህርታዊ አቀራረቦችን እንደገና ማጤን 51
በእያንዳንዱ ዕድሜ እና ደረጃ ላይ ያሉ ሥነ ትምህርታዊ ጉዞዎች 55
የከፍተኛ ትምህርትን ተልእኮ ማደስ 59
የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች 60

**ምዕራፍ 4 ሥርዓተ ትምህርት እና እያደገ ያለው የጋራ ዕውቀት** 63

የጋራ ዕውቀት ተሳትፎ 65
የከፍተኛ ትምህርት የአስቻይነት ሚና 74
የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች 76

**ምዕራፍ 5 የመምህራን ለዋጭ ሥራ** 79

ማስተማርን እንደ የትብብር ሙያ መልሶ መቅረጽ 80
ከሕይወት ጋር የተቆራኘው የመምህር ዕድገት ጉዞ 84
ትምህርትን ለመቀየር ሕዝባዊ አጋርነት 87
ዩኒቨርስቲዎች ከመምህራን ጋር ያላቸው ቀጣይነት ያለው ግንኙነት፣ 88
የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች 90

**ምዕራፍ 6 ትምህርት ቤቶችን መጠበቅ እና መለወጥ** 93

የትምህርት ቤቶች የማይተካ ሚና 95
የትምህርት ቤቶች አስፈላጊ ለውጥ 96
ሽግግር ከትምህርት ቤት ወደ ከፍተኛ ትምህርት 101
የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች 103

**ምዕራፍ 7 ትምህርት በልዩ ልዩ ጊዜያት እና ሥፍራዎች** 105

የትምህርት ዕድሎችን ወደ አካታችነት እና ዘላቂነት መምራት 108
የትምህርትን “መቼ” ማስፋፋት 113
የትምህርት መብትን ማስፋት 115
የውይይት እና የድርጊት መርሆዎ 117

## ክፍል ሦስት
## አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ማስጀመር 119

**ምዕራፍ 8 የምርምር እና የፈጠራ ጥሪ** **121**
ለትምህርት አዲስ የምርምር አጀንዳ 123
ዕውቀትን፣ ውሂብን እና ማስረጃን ማስፋፋት 125
የትምህርትን ወደፊቶች መፍጠር 128
የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች 131

**ምዕራፍ 9 የዓለም አቀፍ ኢጋርነት እና የዓለም አቀፍ ትብብር ጥሪ** **133**
ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ ለሆነ የዓለም ሥርዓት ምላሽ መስጠት 134
ለጋራ ዓላማዎች፣ ግዴታዎች፣ ደንቦች እና ደረጃዎች 136
የዕውቀት ማመንጨት እና የማስረጃ አጠቃቀም ትብብር 137
የፋይናንስ ድጋፍ፣ የትምህርት ስጋት ባለበት 138
የዩኔስኮ ሚና 139
የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች 140

## ማሳረጊያ ቃል እና ቀጣይነት
## የትምህርትን ወደፊቶች በጋራ መገንባት 143

**አዲስ ማኅበራዊ ውል የመገንባት ምክረ ሐሳቦች** **145**
**የተግባር ጥሪዎች** **150**
**ውይይት እና ተሳትፎ** **153**
**ለመቀጠል የቀረበ ግብዣ** **155**

## አባሪዎች 157

**የተመረጡ ማጣቀሻዎች** **159**
ገለልተኛ ሪፖርቶች *159*
የዳራ ጥናቶች *161*
የዓለም አቀፍ ምክክር ግብዓቶች *163*
የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ኅትመቶች *164*

**የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን** **165**
ሥልጣን *165*
አባላት *165*

**የትምህርት ወደፊቶች ኢኒሼቲቭ** **170**

**የዓለም አቀፍ ምክክር አስተዋፅዖ አበርካቾች** **171**

# ዓቢይ ጭምቅ ሐሳብ

ዓለማችን ወሳኝ የለውጥ ምዕራፍ ላይ ነች። ዕውቀት እና መማር ለመታደስና ለመለወጥ መሠረት እንደሆኑ ቀድሞውንም እናውቃለን። ነገር ግን ዓለም አቀፋዊ ልዩነቶች - እና ለምን፣ እንዴት፣ ምን፣ የት እና መቼ መማር እንዳለብን መልሶ የመቃኘት እጅግ አስፈላጊነት - ትምህርት ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ዘላቂ ነገዎቻችንን መቅረጽ እንድንችል ሊረዳን የገባልንን ቃል ገና እየፈጸመ አለመሆኑን ያሳዩናል።

ለዕድገትና ለልማት በምናደርገው ጥረት፣ እኛ ሰዎች የተፈጥሮ አካባቢያችንን በመጉዳት የራሳችንን ሕልውና አደጋ ላይ ጥለናል። ዛሬ ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ከጥልቅ አለመመጣጠኖች ጋር አብሮ ይኖራል። በአደባባይ ሕይወት የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥር እየበዛ የመጣ ቢሆንም፤ የሲቪል ማኅበረሰብ እና የዲሞክራሲ መዋቅር ግን በመላው ዓለም በብዙ ቦታዎች እየፈራረሰ ነው። ፈጣን የቴክኖሎጂ ለውጦች የሕይወታችንን ብዙ ገጽታዎች እየቀየሩት ይገኛሉ። ሆኖም እነዚህ ኢኖቬሽኖች በበቂ ሁኔታ በፍትሐዊነት፣ በአካታችነት እና በዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አቅጣጫ የተቃኙ አይደሉም።

ዛሬ ሁሉም ሰው - ዓለማችን የተትረፈረላት እንጂ እጥረት የሌለባት መሆኗን እና ሁሉም ሰው እኩል ሰብአዊ መብቶችን በተሟላ መልኩ የሚጠቀምባት መሆኗን ለአሁኑም ሆነ ለወደፊት ትውልዶች የማረጋገጥ ከባድ ግዴታ አለበት። ምንም እንኳን አጣዳፊ እርምጃ መውሰድ የሚያስፈልግበት ጊዜ ላይ እና እርግጠኛነትን በእጅጉ የሚያሳጡ ሁኔታዎች ውስጥ ብንሆንም፤ **በተስፋ የተሞላንበት ምክንያት አለን**። እንደ አንድ ዝርያ፣ በጋራ ታሪካችን ውስጥ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ዕውቀትን እና እንድንተባበር የሚያስችሉንን መሳሪያዎች በስፋት ለማግኘት የምንችልበት ደረጃ ላይ እንገኛለን። የተሻለ ነገን በጋራ ለመፍጠር የሰው ልጅን የማሳተፍ ዓቅማችንም ከዚህ የላቀ ሆኖ አያውቅም።

ይህ የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ዓለም አቀፍ ሪፖርት በ2050 እና ከዚያ ወዲያ አርቀን በምናየው ጊዜ፣ ትምህርት የጋራ ዓለማችንን እና የጋራ ነጋችንን በመቅረጽ ረገድ ምን ሚና ሊጫወት እንደሚችል ይጠይቃል። የቀረቡት ምክረ ሐሳቦችም እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች - ሕፃናት፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች - በዚች የጋራ ፕላኔታችን ላይ **የተሳሰርን መሆናችንን** እና **ተባብረን መሥራታችን** የግድ መሆኑን ጠንቅቀው እንደሚገነዘቡ ካየንበት የሁለት ዓመታት ዓለም አቀፍ ተሳትፎ እና የጋራ ግንባታ ሂደት የመነጩ ናቸው።

አሁንም ቢሆን፣ ብዙ ሰዎች እነዚህን ለውጦች በማምጣት ጥረት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ይህ ሪፖርት የመማሪያ ቦታዎችን እንዴት እንደገና ማጤን እንደሚቻል ከሚተነትነው፣ ሥርዓተ ትምህርትን ከቅኝ አገዛዝ ነጻ ስለማውጣት እና ስለ የማኅበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርት አስፈላጊነት እስከሚያጠይቁት ድረስ ካበረከቷቸው አስተዋጽኦዎች ጋር አሰናስሎ አቅርቧል። እንዲሁም ስለ አየር ንብረት ለውጥ፣ እንደ ኮቪድ-19 ወዳሉ ቀውሶች፣ ወደ ሐሰተኛ ዜናዎች እና ወደ ዲጂታል መረጃዎች የተደራሽነት ልዩነት እና በገሃድ እየታዩና እየጨመሩ ወደሄዱ ፍራቻዎቻቸው ዘልቆ ገብቷል።

ትምህርት - መማር ማስተማርን በሕይወት ዘመን ሰፍረን ባደራጀነው መልኩ - ማኅበረሰቦችን በመለወጥ ሂደት ውስጥ ለረጅም ጊዜ መሠረታዊ ሚና ሲጫወት ቆይቷል። ከሌላው ዓለም ጋር እና እርስበርስ ያገናኘናል፤ አዳዲስ ዕድሎች ይከፍትልናል፤ እንዲሁም የውይይት እና የድርጊት አቅማችንን ያጠናክርልናል። **ነገር ግን ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ቀጣይነት ያለው ነገን ለመቅረጽ፣ ትምህርት ራሱ መለወጥ አለበት።**

## አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል

ትምህርት በማኅበራዊ ውልነት፣ ማለትም በማኅረሰብ አባላት መካከል ለጋራ ጥቅም ለመተባበር እንደተገባ ኢቀጥተኛ ስምምነት ሊታይ ይችላል። ማኅበራዊ ውል በሕግ የተደነገጉ እና በባሕልም የተካተቱ ደንቦችን፣ ግዴታዎችን እና መርሆዎችን ስለሚያንጸባርቅ፣ ከግብይት በላይ ነው። **መነሻው ለትምህርት ሕዝባዊ ዓላማዎች የታለመ የጋራ ራዕይ ነው።** ይህ ውል የትምህርት ሥርዓቶችን የሚያዋቅሩ መሠረታዊ እና ድርጅታዊ መርሆችን፣ እንዲሁም እነሱን ለመገንባት፣ ለመጠገን እና ለማጥራት የተሠሩትን ሥራዎች ያካተተ ነው።

በሃያኛው ክፍለ ዘመን፣ የሕዝብ ትምህርት በዋነኛነት ለሕፃናት እና ወጣቶች በሚሰጥ አይተዌ ትምህርት አማካይነት ብሔራዊ የዜግነት እና የልማት ጥረቶችን ለመደገፍ ያለመ ነበር። ዛሬ ግን በሰው ልጅ እና በምንኖርባት ፕላኔት የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ከባድ አደጋዎች መጋረጣቸውን በምናይበት ዘመን፣ ትምህርት የጋራ ተግዳሮቶቻችንን ለመፍታት በሚረዳን መልኩ በአስቸኳይ እንደገና ልንፈጥረው ይገባል። ይህ እንደገና **የማሰብ ተግባር ማለት የጋራ እና እርስበርስ የሚደጋገፉ የወደፊት ሁኔታዎችን ለመፍጠር በጋራ መሥራት ማለት ነው።** አዲሱ የትምህርት ማኅበራዊ ውል በጋራ ጥረቶች ዙሪያ አንድ ሊያደርገን እና በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከባቢያዊ ፍትሕ ላይ ለተመሠረቱ ሁሉ ዘላቂ እና ሰላማዊ ነገን ለመቅረጽ የሚያስፈልገንን ዕውቀት እና ኢኖቬሽን ሊሰጠን ይገባል። ይህ ሪፖርት እንደሚያደርገው፣ ውሉ የመምህራንን ሚና መደገፍም አለበት።

ወደ 2050 ስናማትር፣ ልናነሣቸው የሚገቡ ሦስት የትምህርት ወሳኝ ጥያቄዎች አሉ:- **ምን ማድረግ መቀጠል አለብን? ምን መተው አለብን? ምንስ እንደ አዲስ መፈልሰፍ አለብን?**

### *መሥራች መርሆች*

*ማንኛውም ዐዲስ ማኅበራዊ ውል ሰብአዊ መብቶችን በሚደግፉ ሰፋፊ መርሆዎች፣ ማለትም - በአካታችነት እና ፍትሐዊነት፣ በትብብር እና አጋርነት፣ እንዲሁም በጋራ ኃላፊነት እና ትስስር ላይ መገንባት እና በሚከተሉት ሁለት መሥራች መርሆች መመራት አለበት:-*

- **በሕይወት ዘመን ሙሉ ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብትን ማረጋገጥ፤** በዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 26 ላይ የተደነገገው የትምህርት መብት ለአዲሱ የማኅበራዊ ውል መሠረት ሆኖ መቀጠል እና በሕይወት ዘመን ሁሉ ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብትን ለማካተት መስፋፋት አለበት። በተጨማሪም የመረጃ፣ የባሕልና የሳይንስ መብቶችን፣ እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተጠራቀሙ ያለማቋረጥ እየተለወጡ ያሉ የሰው ልጅ የጋራ ሀብቶች የሆኑትን የወል ዕውቀቶች የማግኘት እና ለእነርሱም የማበርከት መብትን ማካተት አለበት።
- **ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ ጥረት እና የጋራ ጥቅም ማጠናከር፤** ትምህርት እንደ የማኅበረሰብ የጋራ ጥረትነቱ፣ የጋራ ዓላማዎችን በመገንባት ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች አብረው እንዲያብቡ ያስችላቸዋል። አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ለትምህርት ሕዝባዊ የገንዘብ ድጋፍ ማረጋገጥን ብቻ ሳይሆን፤ ሁሉንም ሰው ስለ ትምህርት በሚደረጉ ሕዝባዊ ውይይቶች ላይ ለማሳተፍ የሚያስችል ሕብረተሰብ አቀፍ ቁርጠኝነትንም ማካተት አለበት። ይህ ለሕዝባዊ ተሳትፎ የሚሰጥ አጽንዖት ነው ትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም እና በጋራ እንደተመረጠ እና እንደተሳካ የጋራ ደህንነት የሚያጠናክረው።

እነዚህ መሥራች መርሆች የሰው ልጅ በትምህርት ኃይል እስካሁን በደረሰበት ደረጃ መሠረት ላይ የተገነቡ ሲሆን፤ ወደ 2050 እና ከዚያ ወዲያ ስንሻገር ደግሞ፣ ትምህርት የወደፊት ትውልዶች ሕይወታቸውን እንደገና እንዲቃኙ እና ዓለሞቻቸውን እንዲያድሱ የሚያስችል መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳሉ።

## ባለፉት ተስፋዎች እና ባልተረጋገጡት ነገዎች መሀል

የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አለመመጣጠንና መስፋፋት፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የብዝኃ ሕይወት መጥፋት፣ በፕላኔት ድንበር እንኳን ያልተገደበ የሀብት አጠቃቀም፣ የዲሞክራሲያዊነት መሸርሸር እና የሚያናጋ የቴክኖሎጂ አውቶሜሽን ያለንበት ታሪካዊ ምዕራፍ መገለጫዎች ናቸው። እነዚህ በርካታ ተደራራቢ ቀውሶች እና ተግዳሮቶች ግላዊ እና የጋራ ሰብአዊ መብቶቻችንን የሚገድቡ ከመሆናቸውም በላይ፣ በምድር ላይ ባለው አብዛኛው ሕይወት ላይ ጉዳት አድርሰዋል። የትምህርት ሥርዓቶች መስፋፋት ለብዙዎች ዕድሎችን የፈጠረ ቢሆንም፣ ሰፊ ቁጥር ያለው ሕዝብ ግን አሁንም ዝቅተኛ ጥራት ባለው ትምህርት ብቻ እንዲወሰን አድርጓል።

የወደፊቱን ጊዜ ስንመለከት፣ ከአሁኑ ይበልጥ የጨለመ ምስል መገመት በጣም ቀላል ነው። ለሰዎች መኖሪያ የሚሆን ትንሽ ቦታ የተረፋትን የተዳከመች ፕላኔት በምናብ መሳል ይቻላል። ከዚህ የከፋው የወደፊት ምስል ደግሞ ጥራት ያለው ትምህርት ለልሂቃን ብቻ የሚሰጥ ልዩ ዕድል የሆነበት እና እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ሰዎች አስፈላጊ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን መግዛት ስለማይችሉ በሰቆቃ ውስጥ የሚኖሩበትን ዓለም ያጠቃልላል። ሥርዓተ ትምህርት ተዛማጅ እስካልሆነ ድረስ፣ አሁን ያለው የትምህርት ተደራሽነት አለመመጣጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ይሄዳል? እነዚህ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ለውጦችስ በመሠረታዊ ሰብአዊነታችን ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራሉ?

የትኛውም አዝማሚያ ዕጣ ፈንታን አይወስንም። ብዙ አማራጭ ያላቸው ነገዎች ሊኖሩ ከመቻላቸውም በላይ፣ የሚያናጉ ለውጦች በብዙ ቁልፍ ቦታዎች ተለይተው ሊታወቁ ይችላሉ፦

- ፕላኔቷ በአደጋ ላይ ነች። ነገር ግን የካርበን ልቀትን የመቀነስ እና እና ኢኮኖሚዎችን አረንጓዴ የማድረግ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። በዚህ ረገድ፣ ሕፃናት እና ወጣቶች ትርጉም ያለው እርምጃ እንዲወሰድ በመወትወት እና የሁኔታውን አንገብጋቢነት ለመጋፈጥ አሻፈረኝ የሚሉትን አክርሮ በመገሰጽ ካሁኑ መንገድ መምራት ይዘዋል። .
- ባለፈው ዐሥርት ዓመት በዓለም ላይ የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ወደ ኋላ መንሸራተት እና በማንነት ላይ የተመሠረተ ሕዝበኝነት እያደገ መምጣት ታይቷል። ከዚያው ጎን ለጎን ግን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ አድሏዊነትን እና ኢ-ፍትሐዊነትን የሚገዳደር የዜጎች ተሳትፎ እና ንቅናቄ እያደገ መጥቷል።
- በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ውስጥ ግዙፍ የለዋጭነት ዓቅሞች ቢኖሩም፤ እነዚህን በርካታ ተስፋዎች እንዴት ዕውን ማድረግ እንደምንችል ግን እስካሁን አላወቅንም።
- ሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI)፣ አውቶሜሽን እና መዋቅራዊ ለውጦች በዓለም ዙሪያ ያሉ የሥራ መልኮችን እየቀየሩ ባለበት ሁኔታ፣ ሰውን ያማከለ ልከኛ ሥራ የመፍጠር ተግዳሮት የበለጠ እየከበደ መጥቷል። ከዚያው ጎን ለጎን ግን፣ ብዙ ሰዎች እና ማኅበረሰቦች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመንከባከብ ሥራ ያለውን ጠቀሜታ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት የግድ ሊረጋገጥ የሚችልባቸውን በርካታ መንገዶች ተገንዝበዋል።

እነዚህ እየተከሰቱ ያሉት መናጋቶች በሙሉ በትምህርት ላይ ጉልሕ አንድምታ አላቸው። በትምህርት ላይ በጋራ የምንሠራው ሥራ ደግሞ በተራው፣ ትምህርት ራሱ ለመናጋቶቹ ምላሽ የሚሰጥበትን መንገድ ይቀርጻል።

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዙሪያ ትምህርትን የምናደራጅባቸው መንገዶች ፍትሐዊ እና ሰላማዊ ማኅበረሰቦችን፣ ጤናማ ፕላኔትን እና ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ የጋራ ዕድገትን ለማረጋገጥ በቂ አይደሉም። **አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል** ስለ መማር ማስተማር እና በተማሪዎች፣ በመምህራን፣ በዕውቀት እና በዓለም መካከል ስላለው መስተጋብር **በተለየ መንገድ እንድናስብ ያስችለናል።**

## ትምህርትን የማደስ ምክረ ሐሳቦች

***ሥነ ትምህርት በሕብረት፣ በትብብር እና በአጋርነት መርሆዎች ዙሪያ መደራጀት አለበት።*** *ተማሪዎች በሕብረት እንዲሠሩ እና ዓለምን በሙሉ ልብ በመረዳት እና በልዩ ተነሣሽነት እንዲቀይሩ አእምሯዊ፣ ማኅበራዊ እና ግብረገባዊ ችሎታዎቻቸውን ማሳደግ አለበት። በዚህ ሂደት ቀድሞ የተማሯቸውን አድልዎን፣ ጭፍን ጥላቻን እና ከፋፋይነትን ከአእምሮ ማስወገድም ያስፈልጋል። ምዘናቸውም እነዚህን ሥነ ትምህርታዊ ግቦች ለሁሉም ተማሪዎች ትርጉም ያለው ዕድገት እና ትምህርትን በሚያበረታቱ መንገዶች ማንጸባረቅ አለበት።*

***ሥርዓተ ትምህርት ተማሪዎች ዕውቀትን እንዲያገኙ እና እንዲያፈሩ ለሚረዳቸው፣ በዚያውም የመመዘን እና የመተግበር ዓቅማቸውን ለሚያዳብርላቸው ሥነ ምህዳራዊ፣ በይነ-ባሕላዊ እና በይነ-ዲሲፕሊናዊ ትምህርት አጽንኦት መስጠት አለበት።*** *ሥርዓተ ትምህርት ከምድር ጋር እንደ ሕያው ፕላኔት እና ብቸኛ ቤታችን ቆጥረን የምንዛመድበትን ግንኙነት የሚያስተካክለውን የሰው ልጅ ሥነ ምህዳራዊ ግንዛቤ መቀበል አለበት። ውሸትን ከዕውነት የመለየት ዓቅምን በሚያዳብሩ ሳይንሳዊ፣ ዲጂታል እና ሰብአዊ በሆኑ ዕውቀቶች አማካይነት የተሳሳቱ መረጃዎች መስፋፋትን መከላከል አለበት። በትምህርት ይዘት፣ ዘዴዎች እና ፖሊሲ አማካይነት ንቁ ዜግነትን እና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን ማበረታታት አለብን።*

***ማስተማር መምህራን ዕውቀት አምራቾች እና በትምህርታዊ እና በማኅበራዊ ለውጥ ውስጥ ቁልፍ ሰዎች መሆናቸው የሚታወቅበት የትብብር ጥረት ሆኖ ሙያዊነቱን የበለጠ መጠበቅ አለበት።*** *ትብብር እና የቡድን ሥራ ለመምህራን ሥራ መለዮዎች መሆን አለባቸው። ሐሳብን ማንጸባረቅ፣ ጥናትና ምርምር እና ዕውቀትና አዳዲስ ሥነ ትምህርታዊ ልምምዶችን መፍጠር የማስተማር ወሳኝ ክፍሎች መሆን አለባቸው። ይህም ማለት ውሳኔ ሰጭነታቸው እና ነጻነታቸው ሊደገፍ ይገባል፤ የትምህርትን መጻዒ ዕድል በሚመለከቱ ሕዝባዊ ክርክሮች እና ውይይቶች ላይ በምልዓት መሳተፍ አለባቸው ማለት ነው።*

***ትምህርት ቤቶች በሚደግፉት አካታችነት፣ ፍትሐዊነት እና የግል እና የጋራ ደህንነት ምክንያት ጥብቅ የትምህርት ቦታዎች መሆን፣ እንዲሁም ዓለም ይበልጥ ወደ ፍትሐዊ፣ ሚዛናዊ እና ዘላቂ መጻዒ ሁኔታዎች የምታደርገውን ለውጥ እንዲደግፉ ተደርገው እንደገና መቃኘት አለባቸው።*** *ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ቡድኖችን አንድ ላይ አሰባስበው፣ ሌላ ቦታ ከማይገኙ ተግዳሮቶች እና ዕድሎች ጋር የሚያገናኟቸው ሥፍራዎች ሊሆኑ ይገባል። የትምህርት ቤት ኪነ ሕንፃዎች፣ ሥፍራዎች፣ ጊዜዎች፣ የጊዜ ሰሌዳዎች እና የተማሪዎች አቦዳደኖች ግለሰቦች ተባብረው እንዲሠሩ የማበረታታት እና የማስቻል አቅም እንዲኖራቸው ተደርገው በአዲስ መልክ መቀየስ አለባቸው። የዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ዒላማም ትምህርት ቤቶችን መተካት ሳይሆን፣ መደገፍ ሊሆን ይገባል። ትምህርት ቤቶች ሰብአዊ መብቶችን በማረጋገጥ እና የዘላቂ አሠራር እና ከካርበን ልቀት ነጻ የመሆን ተምሳሌቶች በመሆን፣ የምንመኘውን የወደፊት ጊዜ መምሰል አለባቸው።*

***በሕይወት ዘመን ሙሉ እና በተለያዩ ባሕላዊ እና ማኅበራዊ ሥፍራዎች ውስጥ የሚከናወኑትን የትምህርት ዕድሎች ልናጣጥማቸው እና ልናስፋፋቸው ይገባል።*** *ሰዎች በሁሉም የሕይወት ዘመናቸው ትርጉም ያላቸው፣ ጥራታቸው የተጠበቀ የትምህርት ዕድሎች ሊያገኙ ይገባል። የተፈጥሮ፣ የተገነቡ እና ቨርቹዋል የመማሪያ ቦታዎችን አቀናጅተን የእያንዳንዳቸውን ምርጥ አቅም በጥንቃቄ መጠቀም አለብን። በዚህ ረገድ ቁልፍ ኃላፊነቶች የሚጣሉት የገንዘብ እና የትምህርት ቁጥጥር ዓቅማቸው ሊጠናከርላቸው በሚገባው በመንግሥታት ነው። የትምህርት መብት የሕይወት ዘመን መብት ሆኖ ሊሰፋ እና የመረጃ፣ የባሕል፣ የሳይንስ እና የእርስበርስ ግንኙነት መብቶችን ሊያጠቃልል ይገባል።*

## የትምህርትን አዲስ ማኅበራዊ ውል ማፋጠን

መጠነ ሰፊ ለውጥ ማምጣትእና ኢኖቬሽንን ዕውን ማድረግ ይቻላል። በሚሊዮኖች በሚገመቱ የልበሙሉነት፣ የአመራር፣ የተቃውሞ፣ የፈጠራ እና የእንክብካቤ ግላዊ እና የጋራ ተግባራት አማካይነት አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል እንገነባለን። አዲሱ ማኅበራዊ ውል አድልዎን፣ ማግለልን እና መነጠልን ማሸነፍ አለበት። ለሥርዓተ ጾታ እኩልነት፤ እንዲሁም ዘር፣ ጎሳ፣ ሃይማኖት፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ወሲባዊ ዝንባሌ፣ ዕድሜ እና የዜግነት ሁኔታን መሠረት ሳናደርግ ለሁሉም ሰው መብቶች መረጋገጥ ራሳችንን መስጠት አለብን። ለማኅበራዊ ውይይት፣ አብሮ ለማሰብ እና ለመሥራት ትልቅ ቁርጠኝነት ያስፈልጋል።

**የምርምር እና ኢኖቬሽን ጥሪ፡-** አዲስ ማኅበራዊ ውል በሕይወት ዘመን ሁሉ የመማር መብት ላይ የሚያተኩር የትብብር የምርምር መርሐ ግብር ያስፈልገዋል። ይህ መርሐ ግብር የመማር መብትን ያማከለ እና የተለያዩ ዓይነት ማስረጃዎችን እና፤ አግድሞሻዊ ትምህርት እና የዕውቀት ልውውጥን ጨምሮ፣ የተለያዩ የዕውቀት መንገዶችን ያካተተ መሆን አለበት። ከመምህራን እስከ ተማሪ፣ ከትምህርት ተቋማት እና የምርምር ማዕከላት እስከ መንግሥታት እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ድረስ የሁሉንም ሰው አስተዋጽኦ ሊቀበልም ይገባል።

**የዓለም አቀፍ ሕብረት እና የዓለም አቀፍ ትብብር ጥሪ፡-** አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ለዓለም አቀፍ ትብብር ትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም በመደገፍ፤ በመንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተዋናዮች መካከል በሚኖር የበለጠ ፍትሐዊ እና ከአድሎ ነጻ ትብብር ላይ የተመሠረተ አዲስ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ለትምህርት ከሚደረጉ የሰሜን-ደቡብ የእርዳታ ፍሰቶች ባሻገር፣ በደቡብ-ደቡብ እና በሦስት ማዕዘን ትብብር አማካይነት ዕውቀት እና ማስረጃ ማመንጨት መጠናከር አለበት። ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ዕውን ለማድረግ መንግሥታት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በጋራ ዓላማዎች፣ ደንቦች እና ደረጃዎች ዙሪያ እንዲጣጣሙ የመርዳት ቁልፍ ሚና መጫወት አለበት። በዚህም ውስጥ በቀጥተኛ ተገቢነት ላይ የተመሠረተ የውሳኔ አሰጣጥ መርህ መከበር ይኖርበታል፤ አካባቢያዊ፣ ብሔራዊ እና ቀጣናዊ ጥረቶችም ሊበረታቱ ይገባል። በተለይ የጥገኝነት ጠያቂዎች፣ የስደተኞች፣ የአገር አልባ ሰዎች እና የፍልሰተኞች የትምህርት ፍላጎቶች በዓለም አቀፍ ትብብር እና በዓለም አቀፍ ተቋማት ሥራ መደገፍ አለባቸው።

**በአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ግንባታ ውስጥ ዩኒቨርስቲዎች እና ሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሁሉም ዘርፎች ንቁ ተሳታፊ መሆን አለባቸው፡-** ፈጠራ የተካኑ እና ትምህርትን እንደ የጋራ ጥቅም ለማጠናከር ቁርጠኛ የሆኑ ዩኒቨርስቲዎች ምርምርን እና የሳይንስን ዕድገት ከመደገፍ ጀምሮ፣ በማኅበረሰባቸው እና በዓለም ዙሪያ ላሉ ሌሎች የትምህርት ተቋማት እና መርሐ ግብሮች አስተዋጽኦ አድራጊ አጋር እስከመሆን ድረስ የትምህርትን የወደፊት እጣዎች በመወሰን ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ።

**የትምህርትን ነገዎች በመገንባት ተግባር የሁሉም ሰው መሳተፍ መቻል አስፈላጊ ነው፡-** ልጆች፣ ወጣቶች፣ ወላጆች፣ መምህራን፣ ተመራማሪዎች፣ አክቲቪስቶች፣ አሠሪዎች፣ የባሕል እና የሃይማኖት መሪዎች ሊሳተፉ ይገባል። መነሻ መሠረት የሚሆኑን ጥልቅ፣ የበለጸጉ እና ሥብጥር ያላቸው ባሕላዊ ትውፊቶች አሉን። ሰዎች የሚጋሯቸው ታላላቅ ተግባሮች፣ ዕውቀት እና ፈጠራ አላቸው። እንግዲህ አሁን አንድ ከባድ ምርጫ አጋጥሞናል፡- ዘላቂነት በሌለው መንገድ የመቀጠል ወይም አካሄድን የመቀየር ምርጫ።

ይህ ሪፖርት ምን ማድረግ መቀጠል አለብን? ምን መተው አለብን? እንዲሁም የትኛውስ ነው በአዲስ መንገድ እንደገና መታሰብ ያለበት? ለሚሉት ሦስት ወሳኝ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። ነገር ግን **እዚህ ውስጥ ያሉት ምክረ ሐሳቦች መነሻዎች ብቻ ናቸው።** ይህ ሪፖርት ከዕቅድነት ይልቅ፣ ለማሰብ እና በምናብ ለመሳል የቀረበ ግብዣ ነው። በመላው ዓለም በማኅበረሰቦች፣ በአገሮች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በሁሉም ዓይነት የትምህርት መርሐ ግብሮች እና ሥርዓቶች እነዚህ ጥያቄዎች ተነሥተው መመለስ አለባቸው።

**ለአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል መፍጠር የወደፊት ሕይወታችንን እንዳዲስ በጋራ ለመቃኘት ወሳኝ እርምጃ ነው፡-**

# መግቢያ

ህልውናዊ ምርጫ ከፊትለፊታችን ተደቅኖብናል፦ ዘላቂነት በሌለው መንገድ መቀጠል ወይም አካሄዳችን ላይ ሥር ነቀል ለውጥ ማድረግ። አሁን ባለው መንገድ መቀጠል ለማሰብ የሚከብዱ ኢ-እኩልነቶችን እና ብዝበዛን፣ የብዙ ዓይነት ጥቃቶችን መባባስ፣ የማኅበራዊ ትስስር እና የሰብዓአዊ ነጻነቶችን መሸርሸር፣ ቀጣይ ከባቢያዊ ውድመትን እና አደገኛ እና ምናልባትም አስከፊ የሆነ የብዝኃ ሕይወት መጥፋትን መቀበል ማለት ነው። አሁን ባለው መንገድ መቀጠል ከማኅበረሰቦቻችን የቴክኖሎጂ እና ዲጂታል ለውጦች ጋር ሊመጣ የሚችለውን አደጋ አስቀድሞ መገመት እና መፍታት አለመቻል ማለት ነው።

ይልቁንም በአስቸኳይ በጋራ ወደፊቶቻችንን መልሰን ልናጤናቸው እና እነሱን ዕውን የምናደርግበትን እርምጃ ልንወስድ ይገባል። ዕውቀት እና መማር የዕድሳት እና የለውጥ መሠረቶች ናቸው። ነገር ግን ዓለም አቀፋዊ ልዩነቶች - እና ለምን፣ እንዴት፣ ምን፣ የት እና መቼ መማርን እንደገና የማጤን አንገብጋቢ አስፈላጊነት - ትምህርት ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ዘላቂ ወደፊቶችን ለመቅረጽ የሚችለውን እያደረገ አለመሆኑን ማሳያዎች ናቸው።

ሁላችንም ዓለማችን የተትረፈረፈላት እንጂ እጥረት የሌለባት መሆኗን እና ሁሉም ሰው እኩል ሰብአዊ መብቶችን በተሟላ መልኩ የሚጠቀምባት መሆኗን ለአሁኑም ሆነ ለወደፊት ትውልዶች የማረጋገጥ ግዴታ አለብን። ምንም እንኳን አጣዳፊ እርምጃ መውሰድ የሚያስፈልግበት ጊዜ ላይ እና እርግጠኛነትን በእጅጉ የሚያሳጡ ሁኔታዎች ውስጥ ብንሆንም፤ በተስፋ የተሞላንበት ምክንያት አለን። እንደ አንድ ዝርያ በጋራ ታሪካችን ውስጥ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ዕውቀትን እና እንድንተባበር የሚያስችሉንን መሳሪያዎች በስፋት ለማግኘት የምንችልበት ደረጃ ላይ እንገኛለን። የተሻለ ነገን በጋራ ለመፍጠር የሰው ልጅን የማሳተፍ ዓቅማችንም ከዚህ የላቀ ሆኖ አያውቅም።

ትምህርት የሕይወት ዘመን መማር እና ማስተማርን በምናደራጅባቸው መንገዶች እና በማኅበረሰቦች ለውጥ ውስጥ ለረጅም ጊዜ መሠረታዊ ሚና ተጫውቷል። ትምህርት የዕውቀት ስርጭትን እና የአብሮ-ፈጠራን በይነ-ትውልዳዊ ዑደት የምናደራጅበት መንገድ ነው። ትምህርት ከዓለም እና ከሌሎች ጋር ያገናኘናል፤ ለአዳዲስ ዕድሎች ያጋልጠናል፣ እንዲሁም የውይይት እና የተግባር ዓቅማችንን ያጠናክርልናል። ነገር ግን የምንፈልጋቸውን ወደፊቶች ለመቅረጽ እንድንችል፣ ትምህርት ራሱ መለወጥ አለበት።

ይህ የኢንተርናሽናል ኮሚሽን ኦን ዘ ፊውቸርስ ኦፍ ኤጁኬሽን ዓለም አቀፍ ሪፖርት በ2050 እና ከዚያም ወዲያ አርቀን በምናየው ጊዜ፣ ትምህርት የጋራ ዓለማችንን እና የጋራ ነጋችንን በመቅረጽ ረገድ ምን ሚና ሊጫወት እንደሚችል ይጠይቃል። የቀረቡት ምክረ ሐሳቦችም እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች - ሕፃናት፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች - በዚህች የጋራ ፕላኔታችን ላይ የተሳሰርን መሆናችንን ጠንቅቀው እንደሚገነዘቡ ካየንበት የሁለት ዓመታት ዓለም አቀፍ ተሳትፎ እና የጋራ ግንባታ ሂደት የመነጩ ናቸው። እርስበርስ በመያያዛችን ምክንያትም የዓለም ችግሮች ሁላችንንም ይነኩናል። ከዚህ እኩል፣ ስብጥርን እና ልዩነትን ከማድነቅ ተነሥተን፣ ተባብረን መሥራት እንዳለብን በመላው ዓለም፣ በብዙዎች ዘንድ የሆነ ጠንካራ ግንዛቤ አለ።

የወደፊቱን መተንበይ እንደ ሰው ሁልጊዜ የምናደርገው ነገር ነው። ስለወደፊት የሚታሰቡ ሐሳቦች በትምህርታዊ አስተሳሰብ፣ ፖሊሲ እና አፈጻጸም ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ከተማሪዎች እና ቤተሰቦች የዕለት ተዕለት ውሳኔ አሰጣጥ ጀምሮ የትምህርት ሚኒስትር መሥሪያ ቤቶች እስከሚነድፏቸው በትምህርት ላይ ለውጥ የሚያመጡ ታላላቅ ዕቅዶች ድረስ ሁሉንም ነገር ቅርጽ ያስይዛሉ።

ይህ ሪፖርት ከትምህርት ጋር በተያያዘ ከሥር ነቀል ለውጥ እስከ ጥልቅ ቀውስ ያሉ በርካታ የወደፊት ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገነዘባል። በትምህርት ውስጥ ስለወደፊቱ ጊዜ የምናስብበት ዋናው ዓላማ የአሁኑን በተለየ ማዕቀፍ እንድናየው፣ አዳዲስ ሊሆኑ የሚችሉ አቅጣጫዎችን ለመለየት እና እየተከፈቱልን ወይም እየተዘጉብን ያሉ ዕድሎችን እንድናስተውል ለማስቻል እንደሆነ ሪፖርቱ አመልክቷል። ሊሆኑ የሚችሉ እና አማራጭ የወደፊት ሁኔታዎችን የሚፈትሽ ኀሣሳ ሁሉ የሥነ ምግባር፣ የፍትሐዊነት እና የርትእ ጥያቄዎችን ያስነሳል - ምን ዓይነት ወደፊቶች ናቸው ተፈላጊዎቹ፣ ለማን? ደግሞም ትምህርት በውጫዊ ሁኔታዎች ተጽዕኖ የሚያርፍበት ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁንም በሁሉም የዓለም ማዕዘናት ውስጥ የወደፊት ዕድሎችን ለመክፈት ቁልፍ ሚና ስለሚጫወት፤ የወደፊት እጣ ፈንታችንን በጋራ ማጤን አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ማካተቱ ግዴታ ካልሆነ ተፈጥሯዊ ነው

> *ሊሆኑ የሚችሉ እና አማራጭ የወደፊት ሁኔታዎችን የሚፈትሽ ኀሣሳ ሁሉ የሥነ ምግባር፣ የፍትሐዊነት እና የርትእ ጥያቄዎችን ያስነሳል - ምን ዓይነት ወደፊቶች ናቸው ተፈላጊዎቹ፣ ለማን?*

# የሰው ልጅ፣ የሰብአዊ መብቶች እና የሕያው ፕላኔት ህልውና አደጋ ላይ ነው

የእያንዳንዱ ሰው ክብር ውድ ነው የሚለው ሐሳብ፤ ሁሉም ሰዎች መሠረታዊ መብቶች አላቸው የሚለው ቁርጠኝነት፤ የነጠላ ቤታችን፣ የምድር ጤና - ሁሉም አደጋ ላይ ናቸው። አካሄዳችንን ለመቀየር እና አማራጭ የወደፊት ሁኔታዎችን ለማለም፤ እርስበርሳችን፣ ከሕያው ፕላኔት እና ከቴክኖሎጂ ጋር ያለንን ግንኙነት በአስቸኳይ ማመጣጠን አለብን። እርስበርስ መደጋገፋችንን እና ሰዋዊ ሥፍራችንን እና ተጽዕኖአችንን ከሰው ዓለምነት በላይ በሆነ ዓለም ውስጥ እንደገና መማር አለብን።

ብዙ፣ ተደራራቢ ቀውሶች ያጋጥሙናል። የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አለመመጣጠን መስፋፋት፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የብዝኃ ሕይወት መጥፋት፣ በፕላኔት ድንበር እንኳን ያልተገደበ የሀብት አጠቃቀም፣ የዲሞክራሲያዊነት መሸርሸር እና የሚያናጋ የቴክኖሎጂ አውቶሜሽን ያለንበት ታሪካዊ ምዕራፍ መገለጫዎች ናቸው።

እርስበርስ የሚጋጩ የሚመስሉ የዕድገት አዝማሚያዎች ዘላቂነት ወደሌለው የወደፊት ጎዳና እየመሩን ነው። ዓለም አቀፍ የድህነት ደረጃዎች ቢወርዱም፤ በአገሮች መካከል ያለው አለመመጣጠን ግን አድጓል። ከፍተኛው የኑሮ ደረጃ በታሪክ ከታዩት ሁሉ ከበለጡ ጥልቅ አለመመጣጠኖች ጋር አብሮ ይኖራል። የአየር ንብረት ለውጥ እና የአካባቢ መራቆት የሰውን ልጅ እና በፕላኔት ምድር ላይ ያሉ ሌሎች ዝርያዎችን ሕልውና አደጋ ላይ ጥሏል። በአደባባይ ሕይወት የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥር እየበዛ የመጣ ቢሆንም፤ የሲቪል ማኅበረሰብ እና የዲሞክራሲ መዋቅር ግን በመላው ዓለም በብዙ ቦታዎች እየፈራረሰ ነው። ቴክኖሎጂ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ቢያገናኘንም፤ ለማኅበራዊ መበታተን እና ውጥረቶችም አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። ዓለም አቀፋዊው ወረርሽኝ ብዙ ደካማ ጎኖቻችንን የበለጠ አጉልቶ አሳይቷል። እነዚህ ቀውሶች እና ተግዳሮቶች የግል እና የጋራ ሰብአዊ መብቶቻችንን ይገድባሉ። ደግሞም በአብዛኛው የሰው ልጅ ምርጫዎች እና ድርጊቶች ውጤቶች ናቸው። ከፈጠርናቸው ከረጅም ጊዜ ይልቅ የአጭር ጊዜ ጥቅም ቅድሚያ ከሚያገኝባቸው እና የጥቂቶች ፍላጎት የብዙዎችን ፍላጎት ከሚሸርባቸው ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች የመነጩ ናቸው።

የአየር ንብረት እና ከባቢያዊ አደጋዎች ዘላቂ ባልሆኑ የሀብት አጠቃቀም ደረጃዎች ላይ በተመሠረቱ የኢኮኖሚ ሞዴሎች አማካይነት ይፋጠናል። ለአጭር ጊዜ ትርፍ እና ከልክ ላለፈ ሸማችነት ቅድሚያ የሚሰጡ የኤኮኖሚ ሞዴሎች በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ማኅበረሰቦቻችንን ከሚያሳዩት ግለሰባዊ ስግብግብነት፣ ፉክክር እና ርህራሄ ማጣት ጋር በጥብቅ የተሳሰሩ ናቸው። የዓለም ሀብት በከፍተኛ ሁኔታ ተከማችቷል፤ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ አለመመጣጠንም የማኅበረሰቦቻችንን ቁርኝት እያናጋ ነው።

የፖለቲካ ድንበርን የማያውቁ እና የማያከብሩ የጋራ ችግሮቻችንን ለመፍታት የተጠናከረ ትብብርና ሕብረት በሚያስፈልገን በዚህ ወቅት የአምባገነንነት፣ አግላይ ሕዝበኝነት እና የፖለቲካ ጽንፈኝነት መግነን ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን በትክክል

እየተፈታተኑ ናቸው። ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ማኅበረሰቦች የሚያደርጓቸውን ጥረቶች ለመደገፍ ለዐሥርት ዓመታት የተከናወኑ ሥራዎች ቢኖሩም፣ ዛሬ የዓለም መለያ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ጽንፍ ረገጥነት ነው። በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እየጎሉ ያሉት የጥላቻ ንግግር፣ ኃላፊነት የጎደለው የሀሰት ዜና ስርጭት፣ የሃይማኖት ጽንፈኝነት፣ አግላይ ብሔርተኝነት መጨረሻቸው የጥቂቶችን ፍላጎቶችን ለማሟላት ስልታዊ ጥቅም ላይ ይውላሉ። በዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ላይ በተገለጹት የጋራ እሴቶች ላይ የተመሠረተው የዓለም ሥርዓት እየተዳከመ ነው። ዓለማችን የእሴቶች ቀውስ ተጋርጦባታል፤ ለዚህም ማስረጃዎቹ ጎልተው እየታዩ የመጡት ሙስና፣ መጨካከን፣ አለመቻቻል እና ጭፍን ጥላቻ፣ እንዲሁም ጥቃትን እንደጤናማ ጉዳይ የመቁጠር አዝማሚያ ናቸው።

የተፋጠነ ግሎባላይዜሽን እና እያደገ የሚሄደው የሰው ልጅ ዝውውር፣ ከግዳጅ ስደት እና መፈናቀል ጋር ተዳምረው፣ በጣም ብዙ ጊዜ የዘረኝነትን፣ የጭፍን ጥላቻን፣ የአለመቻቻልን እና የአድልዎን ሰብአዊነት የጎደለው ተጽዕኖ ያባብሳሉ። እነዚህ በሰው ልጅ ክብር ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ከመተባበር እና ነጻ ከማውጣት ይልቅ የበላይ ለመሆን እና ለመቆጣጠር የሚጥሩ የሥልጣን መዋቅሮች መገለጫዎች ናቸው። የትጥቅ ግጭት፣ ወረራ እና ፖለቲካዊ ጭቆና ሕይወትን ከማውደም ባለፈ፣ የሰብአዊ ክብር ፅንሰ ሐሳብንም ያዳክማል።

ብዙ ጊዜ፣ ልዩ መብቶችን የሚያገኙ እና የአንድ ወገን የበላይነትን በሚያሰፍኑ ሥርዓቶች የሚጠቀሙ አካላት በጾታ፣ በዘር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ወይም በወሲባዊ ዝንባሌ ላይ የተመሠረተ አድልዎ ይፈጽማሉ፤ እንዲሁም ቀደምት ሕዝቦች፣ ሴቶች፣ ስደተኞች፣ ፍልሰተኞች፣ የእንስታዊነት አቀንቃኞች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፣ የአካባቢ ጥበቃ ተሟጋቾች ወይም የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ይሁኑ ወይም ሌሎች አስጊ ናቸው የሚሏቸውን ቡድኖች ይጨቁናሉ።

የማኅበረሰቦቻችን ዲጂታል ለውጥ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በሕይወታችን ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው። ኮምፒውተሮች ዕውቀት የሚፈጠርበትን፣ የሚገኝባቸውን፣ የሚሰራጭባቸውን፣ የሚመዘንባቸውን እና ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን መንገዶች በፍጥነት እየለዋወጡ ነው። ይህ በአብዛኛው መረጃ ይበልጥ ተደራሽ እያደረገ እና አዳዲስ እና ተስፋ ሰጪ የትምህርት መንገዶችን እየከፈተ ነው። ነገር ግን የሚያስከትላቸው አደጋዎችም ብዙ ናቸው፡- መማር በዲጂታል ሥፍራዎች ሊያጠብብም ሊያሰፋም ይችላል፤ ቴክኖሎጂ ሊጨቁን ወይም ነጻ ሊያወጣ የሚችል አዲስ የሥልጣን እና የቁጥጥር መሳሪያዎችም ይሰጣል፤ እንዲሁም ፊትን መለየት በሚያስችለው ቴክኖሎጂ እና በሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI)፣ ከዐሥር ዓመታት በፊት ሊታሰቡ በማይችሉ መንገዶች ግላዊ መረጃችንን የመጠበቅ ሰብአዊ መብታችንን ሊጥስ ይችላል። በመካሄድ ላይ ያሉ ቴክኒካል ለውጦች እንድንበለጽግ የሚረዱን እንጂ፣ እና የተለያዩ የዕውቀት መንገዶቻችንን ወይም የአእምሯዊ እና የፈጠራ ነጻነታችንን ወደፊት ሥጋት ላይ እንዳይጥሉ ለማድረግ በንቃት መጠበቅ አለብን።

የአኗኗር ዘይቤዎቻችን የአሁኑንና የወደፊቱን ደህንነታችንን እና ቀጣይ ህልውናችንን አደጋ ላይ በመጣል፣ ከፕላኔቷ እና ከምትደግፋቸው ብዙ ሕይወቶች ጋር ሚዛናቸውን የሳቱ ናቸው። ሳንመዝን ቴክኖሎጂን መቀበላችን ብዙ ጊዜ በአደገኛ ሁኔታ እያለያየን፣ ውይይቶቻችንን እያሳጠረ እና የጋራ መግባባታችንን እያላላብን ነው፤ ምንም እንኳን ተቃራኒውን የማሳካት ዓቅም ቢኖረንም። ደግሞም እነዚህ ፕላኔታዊ እና የቴክኖሎጂ ሚዛን መሳቶች ለሦስተኛ እና እኩል አደገኛ ለሆነ መለያየት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡- የእርስበእርስ ሚዛን መሳታችን አለመመጣጠንን በማስፋፋት፣ እምነትና በጎ ፈቃድን መጠቀሚያ በማድረግ፣ ለ'ሌላው' አጋንንታዊ ምስል በመስጠት፣ እና ይህን እያደገ የመጣውን የዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶች ሰልፍ የበለጠ ትርጉም ባለው መልኩ ተባብሮ ለመጋፈጥ ባለመፈለግ ይገለጻል።

የወደፊቱን ጊዜ በመመልከት ምስሉን ጥቀርሻ መቀባት በጣም ቀላል ነው። ለሰዎች መኖሪያ የሚሆን ትንሽ ቦታ የተረፋትን የተዳከመች ፐላኔት በምናብ መሳል ይቻላል። ከዚህ የከፋው የወደፊት ምስል ጥራት ያለው ትምህርት ለልሂቃን ብቻ የሚተው ልዩ ዕድል የሆነበት እና እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች አስፈላጊ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን መግዛት ስለማይችሉ በመከራ ውስጥ የሚኖሩበትን ዓለም ያጠቃልላል። ሥርዓተ ትምህርት ይበልጥ ተገቢነቱን እያጣ መጥቶ፣ አሁን ያለው የትምህርት ተደራሽነት አለመመጣጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ይሄዳል? እነዚህ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ለውጦችስ በመሠረታዊ ሰብአዊነታችን ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራሉ? ሰብአዊነታችንስ ይበልጥ እየተሸረሸረ ይሄዳል?

*ዛሬ በጋራ የምናደርጋቸው ምርጫዎች የጋራ የወደፊት ዕጣዎቻችንን ይወስናሉ።*

ዛሬ በጋራ የምናደርጋቸው ምርጫዎች የጋራ የወደፊት ዕጣዎቻችንን ይወስናሉ። መትረፍ መጥፋታችን፣ በሰላም መኖር ወይም ሁከት ሕይወታችንን እንዲወስን መፍቀዳችን፣ ከምድር ጋር ዘላቂ በሆነ ወይም ባልሆነ መንገድ መዛመዳችን ሁሉ በዛሬ ምርጫዎቻችን እና የጋራ ግቦቻችንን ለማሳካት ባለን ዓቅም በጥልቀት የሚቀረጹ እና የሚወሰኑ ጉዳዮች ናቸው። በጋራ፣ አካሄዱን መቀየር እንችላለን።

# የአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል አስፈላጊነት

ትምህርት ለማኅበረሰቦቻችን መታደስ እና መለወጥ መሠረት ነው። በመለወጥ ላይ ያለችውን ያልተጨበጠች ዓለም ለመፈተሽ እንዲረዳን ዕውቀትን ያደራጅልናል። የትምህርት ኃይሉ እኛን ከዓለም እና ከሌሎች ጋር ለማገናኘት፣ ከምንኖርባቸው ሥፍራዎች ባሻገር ለማንቀሳቀስ እና እኛን ለአዳዲስ ዕድሎች ለማጋለጥ ባለው ዓቅሙ ላይ ነው። በጋራ ጥረቶች ዙሪያ በሕብረት እንድንቆም ይረዳናል፤ የጋራ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚያስፈልገንን ሳይንስ፣ ዕውቀት እና ኢኖቬሽን ይሰጠናል። ትምህርት ግንዛቤዎቻችንን በማዳበር፤ የወደፊት ሕይወታችን ይበልጥ ማኅበራዊ አካታችነት፣ ኢኮኖሚያዊ ፍትሐዊነት እና ከባቢያዊ ዘላቂነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዱ ችሎታዎችን ይገነባልናል።

ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ሥርዓቶች ድክመቶች ቢኖሩባቸውም፣ ዕድሎችን መፍጠር እና ለግል እና ለጋራ ዕድገት መንገዶችን መክፈት እንደሚችሉ፣ በዓለም ዙሪያ ያሉ ቤተሰቦች፣ ማኅበረሰቦች እና መንግሥታት፣ በሚገባ ያውቃሉ። ትምህርት ብቸኛው ባይሆንም፣ ቁልፍ ቢሆንም ወደ ተፈላጊ የዕድገት ውጤቶች የሚያደርሱ መሻሻሎችን ለማምጣት፣ የሥራ ክህሎትና ብቃቶችን ለማጎልበት፣ ተሳታፊ እና ዴሞክራሲያዊ ዜግነትን ለመደገፍ የሚያግዝ ቁልፍ ሚና እንዳለው በመንግሥት እና በሲቪል ማኅበራት ዘንድ በሰፊው ይታወቃል። ትምህርት - የሰው ልጆችን ሁሉ ደህንነት፣ ፍትሕ እና ሰላም ለማላቅ፣ እንዲሁም ከአካባቢ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ዘላቂነት ለማሳደግ የሚያስችል አካታች ራዕይ ለሆነው የ2030 የዘላቂ ልማት ማዕቀፍ ምሶሶ ነው።

ሆኖም በመላው ዓለም ያለው ትምህርት ከምንጠብቀው በታች ማሽቆልቆሉን ተያይዞታል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የትምህርት ተደራሽነት ጉልሕ መስፋፋት ቢያሳይም፤ በበርካታ ማግለያዎቹ ምክንያት በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕፃናት፣ ወጣቶች እና አዋቂዎች ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መሠረታዊ መብታቸውን እንደተነፈጉ ናቸው። በጾታ፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በባሕል እና በዕውቀት ማግኛ መንገዶች ሰበብ የሚፈጸመው መድልዎ፣ ያውም ብዙ ጊዜ መዋቅራዊ ሆኖ፣ ቀጥሏል። የተደራሽነት እጦት በይዘት እና ፍላጎት አለመጣጣም ቀውስ ይባባሳል፡- በጣም ብዙ ጊዜ መደበኛ ትምህርት የሕፃናትን እና ወጣቶችን እና የማኅበረሰባቸውን ፍላጎቶች እና ምኞቶች አያሟላም። ዝቅተኛ ጥራት ያለው የማስተማር ዘዴ ፈጠራን እና የማወቅ ጉጉትን ያዳክማል። በሁሉም የትምህርት እርከኖች የሚታየው የተማሪዎች ፍላጎት የማጣት እና ትምህርት የማቋረጥ/ለማቋረጥ የመገደድ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት ያለው የትምህርት ቤት ሞዴል ለሕፃናት እና ለወጣቶች ትርጉም ያለው ትምህርት የመስጠት እና ብቃትንና ግብን የማስታጠቅ አቅም የሌለው መሆኑን ያመለክታል። ትምህርት የሚያገኙትም ሰዎች ለአሁኖቹም ሆነ ለወደፊቶቹ ፈተናዎች ዝግጁ ያለመሆናቸው ነገር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው።

በተጨማሪም የትምህርት ሥርዓቶች የጋራ የወደፊት ዕጣ ፈንታችንን አደጋ ላይ የሚጥሉ፣ እንደ መድልዎ እና መገለል ወይም ዘላቂነት የሌለው የአኗኗር ዘይቤ ያሉ ሁኔታዎችን ስለሚያራቡና ስለሚያስቀጥሉ የትምህርትን ዕውነተኛ የለዋጭነት ዓቅም ይገድባሉ። እነዚህ የጋራ ውድቀቶች በትምህርት አዲስ የጋራ ራዕይ እና ተግባሮቻችንን ቅርጽ ሊያሲዙ እና ሊመሩ የሚችሉ የታደሱ መርሆችን እና የቁርጠኝነትን አስፈላጊነት ያጠናክራሉ።

የማንኛውም የትምህርት ማኅበራዊ ውል መነሻው ስለትምህርት ሕዝባዊ ዓላማዎች ያለ የጋራ ራዕይ ነው። የትምህርት ማኅበራዊ ውል የትምህርት ሥርዓቶችን የሚያዋቅሩ መሠረታዊ እና ድርጅታዊ መርሆችን፣ እንዲሁም እነሱን ለመገንባት፣ ለመጠገን እና ለማጥራት የተሠሩትን ሥራዎች ያካትታል።

በሃያኛው ክፍለ ዘመን፣ የሕዝብ ትምህርት በዋነኛነት ለሕፃናት እና ወጣቶች በሚሰጥ አይተዌ ትምህርት አማካይነት ብሔራዊ የዜግነት እና የልማት ጥረቶችን ለመደገፍ ያለመ ነበር። ዛሬ ግን፣ ከባድ አደጋዎች መጋረጣቸውን በምናይበት ዘመን፣ ትምህርትን የጋራ ተግዳሮቶቻችንን ለመፍታት በሚረዳን መልኩ በአስቸኳይ እንደገና ልንፈጥረው ይገባል። ይህ አዲሱ የትምህርት ማኅበራዊ ውል በጋራ ጥረቶች ዙሪያ አንድ ሊያደርገን እና በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከባቢያዊ ፍትሕ ላይ ለተመሠረቱ ሁሉ ዘላቂ እና ሰላማዊ ነገን ለመቅረጽ የሚያስፈልገንን ዕውቀት እና ፈጠራ ሊሰጠን ይገባል።

አዲስ የማኅበራዊ ውል መገንባት ማለት ስለ ትምህርት፣ ዕውቀት እና ስለመማር ሥር የያዙ የአስተሳሰብ መንገዶች አዳዲስ መንገዶችን ከመክፈት እና ወደምንፈልገው የወደፊት ሕይወት እንዳንሄድ እንዴት እንደሚያግዱን መመርመር ማለት ነው። አሁን ያለውን የትምህርት ልማት ሞዴል ማስፋፋት ብቻ ወደፊት አያራምደንም። ችግሮቻችን የውሱን ሀብቶች እና ዘዴዎች ውጤቶች ብቻ አይደሉም። ተግዳሮቶቻችን ከምናስተምርበት ዓላማ እና ዘዴ፣ እንዲሁም መማርን ከምናደራጅባቸው መንገዶች የመነጩ ጭምር ናቸው።

# የትምህርትን ዓላማዎች እንደገና መበየን

የትምህርት ሥርዓቶች የአጭር ጊዜ ልዩ ጥቅሞች እና ምቾቶች ከረጅም ጊዜ ዘላቂነት የበለጠ አስፈላጊ ናቸው የሚል እምነት በተሳሳተ መንገድ ፈጥረዋል። ሕብረታችንን፣ የእርስበርስ ተደጋጋፊነታችንን የመረዳት አቅማችንን እና አንዳችን ለአንዳችን እና ለፕላኔታችን መጠንቀቃችንን በሚጎዳ መልኩ ለግለሰቦች ስኬት፣ ለብሔራዊ ተፎካካሪነት እና ለኢኮኖሚ ልማት እሴቶች የተጋነነ ትኩረት ሰጥተዋል።

ትምህርት በጋራ ጥረቶች ዙሪያ አንድ ሊያደርገን እና በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከባቢያዊ ፍትሕ ላይ ለተመሠረቱ ሁሉ ዘላቂ እና ሰላማዊ ነገን ለመቅረጽ የሚያስፈልገንን ዕውቀት፣ ሳይንስ እና ፈጠራ ሊሰጠን ያለመ ሊሆን ይገባል። በአድማሳችን ላይ ለሚከሰቱ የአካባቢ፣ የቴክኖሎጂ እና የማኅበራዊ ለውጦች እያዘጋጀን፣ ያለፈውን ዘመን ኢ-ፍትሐዊነት ማስተካከል አለበት።

አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል በሁለት መሥራች መርሆች ላይ መተከል አለበት፡- (1) የመማር መብት እና (2) ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ የማኅበረሰብ ጥረት እና የጋራ ጥቅም የሚቆጥር ቁርጠኝነት።

## ጥራት ያለው ትምህርት ዕድሜ ልክ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ

አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ለመገንባት የሚያስፈልገው ውይይት እና እርምጃ ለሰብአዊ መብቶች መከበር በሚደረገው ቁርጠኝነት ላይ ጸንቶ የቆመ መሆን አለበት። እ.ኤ.አ. በ1948 የወጣው ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ለሁሉም የሰብአዊ ቤተሰባችን አባላት የማይጣሱ መብቶችን ከማስቀመጡም በላይ፣ አዳዲስ የወደፊት የትምህርት ዕድሎችን ለማየት የሚያስችል የተሻለውን ኮምፓስ ይሰጣል። ሌሎቹን ሁሉንም ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባሕላዊ መብቶችን ዕውን ለማድረግ

ወሳኝ የሆነው ትምህርት የማግኘት መብት ለአዲሱ ማኅበራዊ ውል እንደ መሪ ብርሃን እና መሠረት ሆኖ መቀጠል አለበት። ይህ የሰብአዊ መብት መነጽር ገቢ፣ ጾታ፣ ዘር ወይም ጎሳ፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ባሕል፣ ወሲባዊ ዝንባሌ፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ አካል ጉዳተኝነት ወይም ሌላ ለመድልዎ እና ለማግለያነት ጥቅም ላይ ሊውል በሚችል ሰበብ ልዩነት ሳይደረግ ትምህርት ለሁሉም መዳረስ እንዳለበት ያስገድዳል።

*አዲሱ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ለሰብአዊ መብቶች መከበር በሚደረገው ቁርጠኝነት ላይ ጸንቶ መቆም አለበት።*

የትምህርት መብት በሕይወት ዘመን ሁሉ ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብትን ማካተት አለበት። ለረጅም ጊዜ የሕፃናት እና የወጣቶች ትምህርት ቤት የመግባት መብት ተብሎ ሲተረጎም የቆየው፣ ወደፊት የትምህርት መብትን በሁሉም ዕድሜ እና በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ማረጋገጥ አለበት። በዚህ ሰፊ አተያይ መሠረት፣ የትምህርት መብት ከመረጃ፣ ከባሕል እና ከሳይንስ መብቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። የሰውን ዓቅሞች ለመገንባት ጥልቅ ቁርጠኝነት ያስፈልጋል። የትምህርት መብት የሰው ልጅ የሚጋራቸውን እና እየተስፋፉ ያሉ የመረጃ፣ የዕውቀት እና የጥበብ ሀብቶች የሆኑትን የወል ዕውቀቶች ከማግኘት እና ለእነርሱም ከማበርከት መብት ጋር በቅርበት የተሳሰረ ነው።

በውድድር፣ በውይይት እና በክርክር እየተከወነ ያለው የዕውቀት ፈጠራ ዑደት ተግባራትን ለማስተባበር፣ ሳይንሳዊ ዕውነቶችን ለማምረት እና ፈጠራን ለማነቃቃት የሚረዳ ነው። ይኸውም ከሰው ልጅ እጅግ በጣም ጠቃሚ፣ የማይነጥፉ ሀብቶች እና ከትምህርትም ቁልፍ ገጽታዎች አንዱ ነው። የወል ዕውቀት የሚያገኙ ሰዎች በበዙ ቁጥር፣ ይበልጥ እየተትረፈረፈ ይመጣል። የቋንቋ፣ የሒሳብ እና የአጻጻፍ ሥርዓቶች መዳበር፣ ዕውቀት በጊዜ እና በሥፍራ ሳይወሰን እንዲስፋፋ አድርጓል። ይህ ደግሞ ማኅበረሰቦች ታይቶ የማይታወቅ የጋራ ዕድገትና የሥልጣኔ ግንባታ ከፍታ ላይ እንዲደርሱ አስችሏቸዋል። በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የወል ዕውቀት ዕድሎች ገደብ የለሽ ናቸው። በወል ዕውቀት አማካይነት የተከፈተው ስብጥር እና ኢኖቬሽን የተገኘው ከመዋዋስ እና ከመበዳደር፣ የዲሲፕሊን ድንበሮችን ከሚሻገር ሙከረት፣ እንዲሁም አሮጌውን ዳግም ከመተርጎም እና አዲሱን ከመፍጠር ሂደት ነው።

እንደ አለመታደል ሆኖ፣ እንቅፋቶች የወል ዕውቀትን የማግኘት እና የማበርከት ፍትሐዊነትን ይከለክላሉ። በሰው ልጅ የተከማቸ ዕውቀት ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው እና ሊታረሙ የሚገባቸው ጉልሕ ክፍተቶች እና መዛባቶች አሉ። አገር በቀል አተያዮች፣ ቋንቋዎች እና ዕውቀቶች ለረጅም ጊዜ ተገልለው ቆይተዋል። ሴቶች እና ልጃገረዶች፣ አነስተኛ ቁጥርና የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ማኅበረሰቦች እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቡድኖች በአስከፊ ሁኔታ ውክልና የላቸውም። አጥሮቹ የንግድ ልውውጥ እና በገዳቢነታቸው ለከት የሌላቸው የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ሕግጋት - እንዲሁም ለማኅበረሰብ እና የወል ዕውቀትን የሚያስተዳድሩ ሥርዓቶችን የሚቆጣጠር በቂ ደንብ እና ድጋፍ ያለመኖሩ - ውጤት ነው። የከያንያንን፣ የደራሲዎችን፣ የሳይንቲስቶችን እና የኢኖቬተሮችን አእምሯዊ እና ኪነጥበባዊ ንብረት መብትን መጠበቅ አለብን። በተመሳሳይም፣ ዕውቀትን ለመተግበር እና ለመፍጠር የሚያስችሉ ነጻ፣ ፍትሐዊ ዕድሎችን ለመደገፍ ቁርጠኝነት ያስፈልገናል። ለጋራ አእምሯዊ ንብረት መብቶች ዕውቅና መስጠትን የሚያካትተው መብቶችን መሠረት ያደረገው አካሄድ፣ የቀደምት ሕዝቦችን እና ሌሎች የተገለሉ ወገኖችን ዕውቀቶች በሕገወጥ መንገድ እና ያለፈቃዳቸው መጠቀሚያ እንዳይሆኑ ለመከላከል ሲባል በወል ዕውቀት አስተዳደርም ውስጥ ሊተገበር ይገባል።

በሕይወት ዘመን ሁሉ ትምህርት የማግኘት የተስፋፋ መብት እንቅፋቶችን ማፈራረስ እና የወል ዕውቀት ልዩ ልዩ የማወቂያ እና በዓለም የመኖሪያ መንገዶችን የሚያንጸባርቅ ነጻ እና ዘላቂ ሀብት መሆኑን ማረጋገጥ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል።

## ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ ጥረት እና የጋራ ጥቅም ማጠናከር

ትምህርት እንደ የማኅበረሰብ የጋራ ጥረትነቱ፣ የጋራ ዓላማዎችን በመገንባት ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች አብረው እንዲያብቡ ያስችላቸዋል። አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ለትምህርት በቂ እና ዘላቂ ሕዝባዊ የገንዘብ ድጋፍን ማረጋገጥን ብቻ ሳይሆን፤ ሁሉንም ሰው ስለ ትምህርት በሚደረጉ ሕዝባዊ ውይይቶች ላይ ለማሳተፍ የሚያስችል ሕብረተሰብ አቀፍ ቁርጠኝነትንም ማካተት አለበት። ይህ ለሕዝባዊ ተሳትፎ የሚሰጥ አጽንዖት ነው ትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም - በጋራ እንደተመረጠ እና እንደተሳካ የጋራ ደህንነት - የሚያጠናክረው።

ትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም የሚያስቀጥሩት ሁለት መሠረታዊ ባሕርያት አሉ። በመጀመሪያ፣ የትምህርት ተመክሮ የሚገኘው ሰዎችን ሰብስቦ ከሌሎች እና ከዓለም ጋር እንዲገናኙ በማድረግ ነው። በትምህርት ተቋማት፣ መምህራን፣ የትምህርት ባለሙያዎች እና ተማሪዎች ግላዊም እና የወልም በሆነ የጋራ ተግባር ላይ ይገናኛሉ። ትምህርት ሰዎች የሰው ልጅን የዕውቀት ቅርስ እንዲጠቀሙበት እና እንዲጨምሩበት ያስችላቸዋል። እንደ የወል አብሮ የመፍጠር ተግባርነቱ፣ ትምህርት የግለሰቦችን እና ማኅበረሰቦችን ክብር እና ዓቅም ያረጋግጣል፤ የጋራ ዓላማዎችን ይገነባል፤ ለጋራ ተግባር የሚውሉ ችሎታዎችን ያዳብራል፤ እንዲሁም የጋራ ሰብአዊነታችንን ያጠናክራል። ስለዚህ የትምህርት ተቋማት የተቻለውን መጠን ያህል የተማሪዎችን ስብጥር ማካተታቸው፣ ተማሪዎቹ በየልዩነታቸው አንዳቸው ከአንዳቸው እንዲማማሩ ስለሚያስችል አስፈላጊ ነው።

ሁለተኛ፣ ትምህርት የሚተዳደረው በጋራ ነው። እንደ ማኅበራዊ ፕሮጀክት፣ ትምህርት በአስተዳደር እና በመጋቢነት ተግባር ብዙ የተለያዩ ተዋናዮችን ያካትታል። የተለያዩ ድምፆች እና አመለካከቶች በፖሊሲዎች እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ መካተት አለባቸው። በትምህርት ፖሊሲ፣ አቅርቦትና ክትትል ላይ አሁን ያለው መንግሥታዊ ያልሆነ ተሳትፎ ወደ የላቀ እና ብዝኃነቱ የሰፋ የመሆን አዝማሚያ፣ እንደ የሕዝብ ጉዳይነቱ በትምህርት ውስጥ የመደመጥ፣ የግልጽነት እና የተጠያቂነት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱን የሚያሳይ ነው። የመምህራን፣ የወጣቶች ንቅናቄ፣ የማኅበረሰብ አቀፍ ቡድኖች፣ ባለአደራዎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ኢንተርፕራይዞች፣ የሙያ ማኅበራት፣ በጎ አድራጊዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት እና የማኅበራዊ ንቅናቄዎች ተሳትፎ የትምህርትን ፍትሐዊነት፣ ጥራት እና ተገቢነት ያጠናክራል። መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት የአድሎየለሽነት፣ የእኩል ዕድል እና የማኅበራዊ ፍትሕ መርሆዎችን ሲያስጠብቁ፣ የትምህርት መብትን በማረጋገጥ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።

የትምህርት ሕዝባዊ ባሕርይ አቅርቦቱ፣ የገንዘብ ወጭው እና አስተዳደሩ በመንግሥት ባለሥልጣናት ከመሠጠቱ በላይ ነው። የሕዝብ ትምህርት ማለት (1) በሕዝብ ቦታ የሚከወን፣ (2) የሕዝብን ጥቅም የሚያበረታታ፣ እና (3) ለሁሉም ተጠያቂ የሚሆን ትምህርት ነው። ሁሉም ትምህርት ቤቶች፣ ማንም ያደራጃቸው ማን፣ ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር፣ የስብጥርን ዋጋ ለማጉላት እና መድልዎን ለመከላከል ማስተማር አለባቸው። የሕዝብ ትምህርት ሕዝብን እንደሚያስተምር መዘንጋት የለብንም። ልዩነታችንን እና ብዝኃነታችንን አክብሮ፣ የአንድ የሰው ዘር እና የአንዲት ፕላኔት አካላት ለመሆናችንን አጽንዖት ይሰጣል።

በሕዝባዊ ማኅበረሰባዊ ጥረትነቱ እና በጋራ ጥቅምነቱ ለትምህርት ቁርጠኛ መሆን ማለት በአካባቢ፣ በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ የትምህርት አስተዳደር መንገዶች አካታች እና አሳታፊ መሆን አለባቸው ማለት ነው። መንግሥታት በቁጥጥር እና ትምህርትን ከመሸቀጫነት በመጠበቅ ላይ ትኩረት የማድረጋቸው አስፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። ገበያዎች ትምህርት እንደ ሰብአዊ መብት ሊደርስበት በሚገባው ስኬት ላይ የሚፈጥሩትን እንቅፋት እንዲገፉበት መፍቀድ አይገባም። ይልቁንም ትምህርት የሁሉንም ሰው ሕዝባዊ ፍላጎት ለማሟላት ማገልገል አለበት።

አዲሱ ማኅበራዊ ውል ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከባቢያዊ ፍትሐዊነት እና ዘላቂነት ያላቸውን የወደፊት መንገዶች ለመገንባት እንዲረዳን ከተፈለገ፤ ዕድሜ ልክ ትምህርት በማግኘት መብት እና ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ እና የጋራ ጥቅም በሚቆጥር ቁርጠኝነት ማዕቀፍ መቃኘት አለበት። እነዚህ መሠረታዊ መርሆች ከሥነ ትምህርት እና ከሥርዓተ ትምህርት እስከ ምርምር እና ዓለም አቀፍ ትብብር ድረስ ቁልፍ የሆኑትን የትምህርት አውታሮች ለማደስ የሚያስፈልገውን ውይይት እና ተግባርን ለመምራት ይረዳሉ።

# የሪፖርቱ አደረጃጀት

ይህ ሪፖርት በርካታ ምዕራፎችን ባቀፉ ሦስት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ለመገንባት የሚያስችሉ ምክረ ሐሳቦችን እና በርካታ የውይይት እና የድርጊት መምሪያ መርሆችን ያቀርባሉ። ምክረ ሐሳቦቹ በተለያዩ አውዶች ወደ ተግባር የሚተረጎሙባቸውን መንገዶች ባቀረበበት ድኅረ ቃልም ይደመደማል። ሪፖርቱ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ የምርምር ማስረጃዎችን ቢያመለክትም፣ በጽሑፉ ውስጥ ማጣቀሻዎችን አላስገባም። በተለይ የዚህ ኢኒሼቲቭ አካል ሆነው እንዲሠሩ የተደረጉ የዳራ ጥናቶች በአባሪው ውስጥ ተዘርዝረዋል።

የሪፖርቱ ክፍል አንድ፣ ባለፉት ተስፋዎች እና ባልተረጋገጡት ነገዎች መሀል፣ በትምህርት ማግለልን ለማስተካከል እና ዘላቂ ነገን ለማረጋገጥ የሚረዳ አዲስ የማኅበራዊ ውል አስፈላጊነት የሚያረጋግጠውን የትምህርት ዓለም አቀፍ የኢ-ፍትሐዊነት እና የተገቢነት መንታ ተግዳሮት ያቀርባል። ሁለት ምዕራፎችን ያቀፈ ነው።

ምዕራፍ 1 በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 26 ላይ የተደነገገውን የትምህርት መብት ባሳካቸው እና ባላሳካቸው ተስፋዎች አማካይነት ያሳያል። ምዕራፍ 2 የሚያተኩረው በቁልፍ መናጋቶች እና አዳዲስ ለውጦች ላይ ሲሆን፤ ይህም አራት የተደራረቡ ሰፋፊ የለውጥ መስኮች ማለትም ከባቢያዊ ለውጥ፣ የቴክኖሎጂ ማፋጠን፣ አስተዳደር እና ማኅበራዊ መበታተን እና አዲስ የሥራ ዓለሞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው። ይህ ምዕራፍ ወደ 2050 በማስመልከትም፣ በእነዚህ መናጋቶች እና ለውጦች ምክንያት ትምህርት እንዴት እንደሚጎዳ እና እነሱን በተሻለ ሁኔታ ለመፍታት እንዴት ሊለወጥ እንደሚችልም ይጠይቃል።

የሪፖርቱ ክፍል ሁለት፣ ትምህርትን ማደስ፣ ትምህርትን በአምስት ቁልፍ አውታሮች እንደገና እንዲበየን እና እንዲታደስ ይሞግታል፤ አውታሮቹም ሥነ ትምህርት፣ ሥርዓተ ትምህርት፣ ማስተማር፣ ትምህርት ቤቶች፣ እና በሕይወት ዘመንና በተለያዩ ባሕላዊ እና ማኅበራዊ ሥፍራዎች የሚገኙ ሰፊ የትምህርት ዕድሎች ናቸው። እያንዳንዱ አውታርም በየተመደበለት ውይይት እና ድርጊት መምሪያ መርሆችን ያካተተ ምዕራፍ ውስጥ ተብራርቷል።

ምዕራፍ 3 ሌሎችን መረዳትን፣ ልዩነትን ማክበርን እና ርህራሄን የሚያጎለብት እና ራሳቸውን እና ዓለምን ለመለወጥ በጋራ የሚሠሩበትን የግለሰቦችን ዓቅም የሚገነቡ የትብብር እና የአጋርነት ሥነ ትምህርቶችን አስፈላጊነት ያስገነዝባል። ምዕራፍ 4 ተማሪዎች ዕውቀትን እንዲያገኙ እና እንዲያፈሩ የሚረዳቸውን፣ በዚያውም የመመዘን እና የመተግበር ዓቅማቸውን የሚያዳብርላቸውን ሥነ ምህዳራዊ፣ በይነ-ባሕላዊ እና በይነ-ዲሲፕሊናዊ ሥርዓተ ትምህርት ያበረታታል። ምዕራፍ 5 ለመምህራን የለውጥ ሥራዎች ወሳኝነት አጽንዖት በመስጠት፤ ማስተማር የትብብር ጥረት ሆኖ ሙያዊነቱ ይበልጥ እንዲጠበቅ ይመክራል። ምዕራፍ 6 ትምህርት ቤቶች አካታችነትን፣ ፍትሐዊነትን እና የግል እና የጋራ ደህንነትን የሚደግፉ ሥፍራዎች እንደመሆናቸው ጥበቃ ሊደረግላቸው እና በዚያውም ፍትሐዊ እና ሚዛናዊ መጻዒ ሁኔታዎችን ዕውን እንዲያደርጉ ሊለወጡ እንደሚገባ ያስረዳል። ምዕራፍ 7 ትምህርት ይህም በመደበኛ ተቋማት ብቻ የሚከወን ሳይሆን፣ በብዙ ማኅበራዊ ቦታዎች፣ ዕድሜ ልክ ሊያጋጥም የሚችል መሆኑን በመገንዘብ፤ ትምህርት በተለያዩ ጊዜያት እና ሥፍራዎች አስፈላጊ መሆኑን ያብራራል።

የሪፖርቱ ክፍል ሦስት፣ የትምህርትን አዲስ ማኅበራዊ ውል ማፋጠን፣ ለምርምር እና ለዓለም አቀፍ ትብብር እና ሕብረት ጥሪዎችን በማቅረብ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ግንባታን ማስጀመር የሚያስችሉ ሐሳቦችን ያቀርባል።

ምዕራፍ 8 አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ለመገንባት የሚያስፈልገውን ዕውቀት በማመንጨት፣ በማምረት እና በመደራደር ረገድ እያንዳንዱ ሰው የሚጫወተው ሚና እንዳለው በማመልከት፤ በሕይወት ዘመን ሁሉ ትምህርት የማግኘት መብት የጋራ የምርምር አጀንዳ እንዲሆን ያበረታታል። ምዕራፍ 9 በጽናት፣ በልበሙሉነት እና በቁርጠኝነት እና እስከ 2050 እና ከዚያም ባሻገር በሚታለም ራዕይ አማካይነት ዓለም አቀፋዊ ሕብረትን እና ዓለም አቀፍ ትብብርን ለመገንባት እና ለማጠናከር የታደሰ አስቸኳይ ፍላጎት ስለመኖሩ ይናገራል።

ሪፖርቱ በጽሑፉ ውስጥ የተነሡ ሐሳቦች እና ምክረ ሐሳቦች በተለያዩ መንገዶች እና በተለያዩ አውዶች ወደ መርሐ ግብሮች፣ ግብዓቶች እና ድርጊቶች ሊተረጎሙ እንደሚገባ በድጎረ ቃሉ እና በቀጣይ ሂደት ማመላከቻው በመሞገት ያጠቃልላል። እንዲህ ዓይነቱ ለውጥ የሚመጣው እነዚህን ሐሳቦች ወደ ዕቅድ እና ተግባር ለመተርጎም ተሳትፏቸው አስፈላጊ ከሆኑት ከሌሎች ጋር በጋራ ግንባታ ሂደቶች በመተባበር እና በመነጋገር ነው። የትምህርት ዕድሳት ብየና እና ትግበራ በተለያዩ የመንግሥት ኃላፊነት እርከኖች ላይ ባሉ መሪዎች፣ የትምህርት አስተዳዳሪዎች፣ በመምህራን እና ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ ማኅበረሰቦች እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ይወሰናል።

ከፊታችን የሚጠብቀን ተግባር በትምህርት እና በጥቅሉም በዓለም ላይ ወደፊት መውሰድ፣ መተው እና በጥበብ መልሰን ማሰብ ስላለብን የሚነጋገር የጋራ፣ ቀጣይነት ያለው ዓለም አቀፍ ውይይትን ማጠናከር ነው። ይህንን እንደ ዕድሳት ተግባር እንቆጥረዋለን፡- ሰው ሆነን ከሰው በላይ በሆነው ዓለም እየኖርን በጋራ የሚገጥሙንን ችግሮች አስከፊነት የመረዳት እና ተራ ድግግሞሽን የሚቋቋም የወደፊት መንገድ የመፈለግ ተግባር። ዕውነቱን ከተናገርን፣ ተመሳሳይ ነገር በዝቶ፣ እና ይበልጥ ፈጥኖ፣ ገዝፎ እና ቀልጥፎ ወደ ገደል እየገፋፋን እንደሆነ እናውቃለን፡- ለዚህ ደግሞ የአየር ንብረት መበላሸት እና የሥነ ምህዳር መዳከም በጣም ግልጽ እና ጉልሕ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ዕድሳት የትምህርት ሥርዓቶቻችንን አነቃቅቶ ለማላቅ በልፋት በተገኘ ዕውቀት እና ተመክሮ ወንፊት ማጥራትን ያመለክታል። አዲስ እና የበለጠ ተስፋ ሰጭ አካሄድ መቅረጽ የሚታወቀውን መጠቀም እና ማደራጀትን ያካትታል።

*ይህ ሪፖርት ያንን ግብ ለማሳካት ለውይይት እና ለድርጊት የቀረበ ግብዣ እና የታቀደ አጀንዳ ነው።*

አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ከተጀመረ የተወሰነ ጊዜ ሆኖታል። አሁን ውሉን ዕውን ለማድረግ የሚያስፈልገው ሰፊ መሠረት ያለው፣ አካታች እና ዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ ውይይት እና ንቅናቄ ነው። ይህ ሪፖርት ያንን ግብ ለማሳካት ለውይይት እና ለድርጊት የቀረበ ግብዣ እና የታቀደ አጀንዳ ነው።

# ክፍል አንድ

## ባለፉ ተስፋዎች እና ባልተረጋገጡ ነገዎች መሀል

በትምህርት የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ ለማሰላሰል መጀመሪያ ትምህርት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ እና አሁን ያሉ ተግዳሮቶች እና አዳዲስ ለውጦች የሚያመለክቱትን ሊሆኑ የሚችሉ የወደፊት ዕጣዎች መመርመር አለብን። በትምህርት፣ እንደሌሎች የሕይወት ዘርፎች ሁሉ፣ ትናንት በብዙ መልኩ ከእኛ ጋር ነው። የረጅም ጊዜ ታሪካዊ አዝማሚያዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብን። የትናንቶቹን ማግለሎች እና ድክመቶች ስንመረምር፣ ትምህርት ከተስፋዎቻችን አንጻር ምን ያህል ከጠበቅነው በታች እንደዋለ በደንብ መረዳት እንችላለን።

የዚህ ሪፖርት የመጀመሪያ ክፍል ለእኩል ዕድል፣ ለፍትሕ እና ለዘላቂነት ከተገባው መደበኛ ቁርጠኝነት ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የትምህርት ሁኔታ ያሳያል - እንዲሁም እነዚህ ጉዳዮች ወደፊት እንዲዳብሩ የምንጠብቅባቸውን መንገዶች ይመለከታል። ትምህርት ባለፉ ተስፋዎች እና ባልተረጋገጡ ነገዎች መሀል ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንዳለም ያመለክታል።

የዚህ ክፍል የመጀመሪያ ምዕራፍ ባለፉት 50 ዓመታት በትምህርት በኩል በተገኘው ዕድገት ላይ ያተኩራል። እንደ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ድህነት፣ እና የሥርዓተ ጾታ መድልዎ ያሉ ሁኔታዎች ከትምህርት ዕድገቶች ጋር እንዴት እንደሚገናኙ (እና እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያርፍባቸውም) ይዳስሳል። ያለፈው ጊዜ ችላ ሊባል እንደማይችል፣ ይልቁንም የሚመጣው ነገር የሚወሰነው ዛሬ እና በሚቀጥሉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ በምናደርጋቸው ምርጫዎች እና በምንወስዳቸው እርምጃዎች ስለመሆኑ ይሞግታል።

በዚህ ክፍል ቀጣዩ ምዕራፍ እየታዩ ያሉ ለውጦችን ከአራት ቁልፍ ጉዳዮች አንጻር ይመለከታል፤ ማንጸሪያዎቹም አካባቢ፣ ቴክኖሎጂ፣ የፖለቲካ ምህዳር እና የሥራ የወደፊት ሁኔታ ናቸው። ስለ ነገ ለመተንበይ ባይቻልም፣ ነገር ግን በዚህ ኢኒሼቲቭ የተሳተፉት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በጣም አደገኛው እና መናጋትን የሚያስከትለው መንገድ እነዚህን በሂደት ላይ ያሉ ለውጦች ችላ ማለት እንደሆነ ትልቅ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

# ምዕራፍ 1

# ይበልጥ ፍትሐዊ ወደሆኑ የትምህርት ነገዎች

*የትምህርት ሥርዓታችን ማበረታታት ያለበት ይህንን ነው። ለጋራ ጥቅም አብሮ የመኖር እና አብሮ የመሥራትን ማኅበራዊ ግቦች ማሳደግ አለበት። ሁሉም አባላት ክፋውንም ደጉንም ፍትሐዊ በሆነ መልኩ የሚካፈሉበት እና ዕድገት በግለሰብም ይሁን በመንግሥት የተቀናጡ ሕንፃዎች፣ መኪናዎች ወይም ሌሎች እንደዚህ ባሉ ነገሮች ሳይሆን፣ በሰው ልጅ ደህንነት የሚመዘንበት የሕብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ወጣቶቻችን ንቁ እና ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ማዘጋጀት አለበት። ስለዚህ ትምህርታችን በጠቅላላው ማኅበረሰብ ውስጥ የቁርጠኝነት ስሜትን መትከል እና ተማሪዎችም ለወደፊታችን ተስማሚ የሆኑትን እሴቶች እንዲቀበሉ መርዳት አለበት።*

ጁሊየስ ኔሬሬ፣ *Education for Self-Reliance,* 1967.

ባለፉት ሠላሳና አምሳ ዓመታት በትምህርት ምን ያህል ተጓዝን? ትምህርት በአሁኑ ጊዜ ምን ላይ ደርሷል? የረጅም ጊዜ የወደፊት ሁኔታን ስንመለከት የት ላይ ነው አካሄዱን በፍጥነት መቀየር ያለበት?

ይህ ምዕራፍ ያለፈውን ግማሽ ምዕተ ዓመት ትምህርት ከሁለት አቅጣጫዎች ያስቃኛል። በመጀመሪያ፣ የትምህርት አመላካቾች በክልል፣ በገቢ ምድብ፣ በጾታ፣ በዕድሜ ምድብ እና በሌሎች ነገሮች ያላቸውን አከፋፈል ለመረዳት በተቻለ መጠን ከአማካይ በላይ በመሄድ፣ በጊዜ ሂደት ላይ ሊታዩባቸው የሚችሉ አዝማሚያዎችን በዝርዝር ይገልጻል። ሁለተኛ፣ ስለ እነዚህ እና ሌሎች የትምህርት አዝማሚያዎች ይበልጥ ዓይነታዊ ውይይት ያቀርባል፤ ይህም በእኩል ተደራሽነት፣ በፍትሐዊነት፣ በጥራት እና እንደግጭት እና ፍልሰት ያሉ አንዳንድ ጉልሕ መናጋቶች ሲያጋጥሙ በሚኖረው ምላሽ አሰጣጥ ላይ ያተኩራል።

የረጅም ጊዜ የስታቲስቲክስ አዝማሚያዎች ምን ሊለካ፣ ምንስ ላይለካ ይችላል በሚሉ ጥያቄዎች የተቃኙ እና ከፊል ታሪኮችን ብቻ የሚያሳዩ ናቸው። ሆኖም በሁለንተናዊ መልኩ ሲታዩ ሊሆኑ የሚችሉ የወደፊት አቅጣጫዎችን እና የለውጥ መንገዶችን ያሳያሉ። የትምህርት ዕድል ማግኘት፣ የተገለሉ ሕዝቦችን ማካተት፣ የማንበብና መጻፍ ክህሎት ዕድገት፣ እና የዕድሜ ልክ የትምህርት ሥርዓቶችን መፍጠር አንዳንድ የጋራ ጉዳዮችን ቢጋሩም፤ ነገር ግን እንደየአገሩ፣ ክፍለ ዓለሙ እና እንደየገቢ መደቡ የሚወሰን ከፍተኛ ልዩነት አላቸው። በተጨማሪም፣ የአዝማሚያ ትንተናዎች የትኞቹ ጉዳዮች ከፍተኛ ትኩረት እንዳገኙ እና የትኞቹ ደግሞ አዲስ እና አስቸኳይ ምላሽ እንደሚያስፈልጋቸው አጉልተው ያሳያሉ። ሊሆኑ የሚችሉ ትምህርታዊ የወደፊት ሁኔታዎችን ከታሪካዊ እና ወቅታዊ ተግዳሮቶች አንጻር መመልከታችን፣ ሊከሰቱ ስለሚችሉ ሌሎች የወደፊት ሁኔታዎች እንድናስብ ይረዳናል።

> *ዛሬ በተደራሽነት፣ በተሳትፎ እና በውጤት ላይ የሚታዩ ክፍተቶች በትናንናዎቹ ማግለሎች እና ጭቆናዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው።*

ያለፉት አምሳ ዓመታት ዕድገቶች እጅግ በጣም ያልተመጣጠኑ እንደመሆናቸው፤ ዛሬ በተደራሽነት፣ በተሳትፎ እና በውጤት ላይ የሚታዩ ክፍተቶች በትናንናዎቹ ማግለሎች እና ጭቆናዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። የነገው ግስጋሴ የሚመሠረተው በእርምታቸው ላይ ብቻ ሳይሆን፤ እነዚህን እኩል ያልሆነ ተጠቃሚነትን እና አለመመጣጠንን ያስከተሉትን ግምቶች እና ስምምነቶች በመፈተሽም ላይ ጭምር ነው። ለምሳሌ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት በራሱ እንደ ግብ ብቻ ሳይሆን፤ የነገን ዘላቂ ትምህርት ለማረጋገጥ እንደ ቅድመ ሁኔታ መታየት አለበት።

# ያልተሟላ እና ኢፍትሐዊ የትምህርት መስፋፋት

በብዙ መመዘኛዎች፣ ትምህርት እንደ ሰብአዊ መብት ከተቆጠረ ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ የትምህርት ተደራሽነት ያሳየው መስፋፋት አስደናቂ ነው። ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ በ1948 ሲፀድቅ፣ የዓለም ሕዝብ 2.4 ቢሊዮን ነበር። ከዚህ ውስጥ 45% ብቻ ነበሩ የትምህርት ቤት ደጃፍ የረገጡት። ዛሬ፣ ከ8 ቢሊየን የዓለም ሕዝብ ከ95% በላይ የሚሆኑት ትምህርት ተከታትለዋል። በ2020 የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር የመጀመሪያ ደረጃ ከ90%፣ በታችኛው ሁለተኛ ደረጃ ከ85% እና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ65% ዐልፈዋል። በዚህም ምክንያት ባለፉት አምሳ ዓመታት ውስጥ በዓለም ዙሪያ ከትምህርት ውጭ የነበሩ ሕፃናት እና ወጣቶች መጠን ጉልሕ ቅናሽ ታይበቶታል። ይህንን የተደራሽነት መስፋፋት በከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር መጨመር ወቅት መከሰቱ የበለጠ አስደናቂ ያደርገዋል። በ1970 ከአራት ልጆች ውስጥ ከአንድ በላይ የሚሆኑት ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውጭ የነበሩ ሲሆን፤ በ2020 ግን ከትምህርት ቤት ውጭ ያሉ ሕፃናት ድርሻ ከ10 በመቶ በታች ወርዷል። በ1990 ከትምህርት ገበታ ውጭ ከነበሩ ሕፃናት ሁለት ሦስተኛውን ይሸፍኑ በነበሩት ሴቶች ልጆች ላይ ጉልሕ መሻሻሎች ታይተዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ወደ መረጋገጥ በመድረሱ፣ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው አገሮች እና ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገሮች በስተቀር፣ ልጃገረዶች ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከትምህርት ቤት ውጭ የሚሆኑበት ሁኔታ ቀርቷል።

በተለይም ከ2000 ጀምሮ፣ በቅድመ መደበኛ ትምህርት በዓለም አቀፍ ደረጃ፣ በሁሉም ቀጣናዎች እና የአገር የገቢ ቡድኖች ተሳትፎ ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል። የዓለም የተሳትፎ መጠን በ1970 ከ15% ከፍ ያለ ከነበረበት ተነሥቶ፣ በ2000 ወደ

35% አድጎ፣ በ2019 ደግሞ 60% ደርሷል። ከፍተኛ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች የተሳትፎው ምጣኔ በ2050 በዓለም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ይደረስበታል ተብሎ ከሚጠበቀው ተሳትፎ ጋር ተቀራርቧል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሥርዓተ ጾታ ልዩነቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠበቡ የመጡ ሲሆን፤ እንዲያውም የቅድመ መደበኛ የትምህርት ቤት ተሳትፎ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ወይም ቅሩብ እኩልነት ላይ ደርሷል። ይህም በመጪዎቹ ዓመታት የሥርዓተ ጾታ እኩልነት በአንደኛ ደረጃም ጥሩ እንደሚሆን ያመለክታል፤ ምክንያቱም የቅድመ መደበኛ ትምህርት የዕድሜ አቻዎች ወደ አንደኛ ደረጃ ይሸጋገራሉ፤ በትምህርት ቤት ስኬታማ ለመሆንም በተሻለ ሁኔታ ዝግጁ ይሆናሉ።

የትምህርት ተሳትፎ መስፋፋት በ1990 እና 2020 መካከል የዕድገት ደረጃቸው ምንም ያህል ይሁን ምን በሁሉም ሀገራት የወጣቶች እና የጎልማሶች መሠረተ ትምህርት ምጣኔ እየጨመረ እንዲሄድ አድርጓል። ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት መሠረታዊ ትምህርት ያገኙ ወጣቶች ምጣኔ ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ከደረሱበት ከ90+ በመቶ ጋር ተቀላቅሏል። ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ በሁሉም ሀገራት መሠረታዊ ትምህርት ባገኙ ሴት ወጣቶች ምጣኔ ላይ ከፍተኛ መሻሻልታይቷል፤ ይህም የሥርዓተ ጾታ ልዩነቱን አጥብቧል። አሁን በወጣቶች መሠረታዊ ትምህርት ምጣኔ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ከፍተኛ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት የተስተዋለ ሲሆን፤ በሌሎች አገሮችም የሥርዓተ ጾታ ልዩነት ወደ እኩልነት እየጠበበ ነው። ይህም በተመሳሳይ፣ ወደፊት ወጣቶች ወደ ጉልምስና ሲሸጋገሩ፣ የሚደረስበትን የተሻለ ዓለማቀፍ የጎልማሶች ትምህርት ምጣኔ ያበሥራል።

የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎም ባለፉት አምሳ ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። በ1970 በዓለም አቀፍ ደረጃ 10% የነበረው የወጣቶች እና ጎልማሶች ተሳትፎ ወደ 40% አድጓል። የቅበላው ዕድገትም፣ ባለፉት አምሳ ዓመታት ውስጥ የሴቶችን የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ አምጥቷል። በ1970ዎቹ እና 1980ዎቹ አብዛኛው የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ የወንዶች የነበረ ቢሆንም፤ በ1990 ገደማ የጾታ እኩልነት ላይ በመደረሱ፣ የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች በበለጠ ፍጥነት ማደጉን ቀጥሏል። ይህም 7% ሴት ተማሪዎች እና 10% ወንድ ተማሪዎች ከሚሳተፉባቸው ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት እና ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገሮች በስተቀር በሁሉም የገቢ መደቦች እና በሁሉም ክፍላተ ዓለም ዕውነት ሆኖ ታይቷል። ከ1970 ጀምሮ ባሉት አዝማሚያዎች ላይ የተመሠረቱ ትንበያዎች እንደሚያመለክቱት፣ በ2034 ከፍተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት የተሳትፎው መጠን 100% ሊደርስ የሚችል ሲሆን፤ መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ደግሞ በ2050 የተሳትፎ መጠን ከ60 እስከ 80% ይደርሳል። በሌላ በኩል፣ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2050 ወደ 35% ገደማ ብቻ ሲደርስ፣ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ደግሞ ከ15% በታች ይሆናል።

ባለፉት ዐሥርት ዓመታት የትምህርት ዕድልን በማስፋፋት ረገድ ይህ አስደናቂ ዕድገት ቢመዘገብም፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽነት ያልተሟላ እና ኢፍትሐዊ እንደሆነ ነው። ከትምህርት ዕድሎች መገለል እስካሁንም በጣም በግልጽ የሚታይ ችግር ነው። ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ ከአራት ወጣቶች አንዳቸው ዛሬም ማንበብና መጻፍ አይችሉም። መካከለኛ ገቢ ባላቸውና ከፍተኛ ገቢ ባላቸው አገሮችም ቢሆን፣ የኢኮኖሚያዊ ትብብር እና ልማት ድርጅት (OECD) የዓለም አቀፍ ተማሪዎች ምዘና መርሐ ግብር እንደሚያሳየው፣ በዚህ የሲቪክ እና የኢኮኖሚ ተሳትፎ ጥያቄዎች ይበልጥ ውስብስብ እየሆኑ በመጡበት ዓለም፣ ትምህርት ቤት ካሉ በ15 ዓመት ዕድሜ ላይ ያሉ ታዳጊዎች መሀል ቀላል የማይባል መጠን ያላቸው ተማሪዎች በጣም መሠረታዊ ከሆኑ ደረጃዎች ውጭ ያነበቡትን መረዳት አይችሉም። ያም ሆኖ፣ በተለመዱ ብያኔዎች እንኳን፣ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት ምጣኔ ከ75 በመቶ በታች፣ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ደግሞ ከ55 በመቶ ከፍ ያለ ነው። ምንም እንኳን ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት ውስጥ ያሉት የሥርዓተ ጾታ ልዩነቶች እየጠበቡ ቢመጡም፣ በተለይ በድሆች ዘንድ አሁንም ጉልሕ ክፍተቶች ናቸው። ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ከ5 ሴቶች ከ2 በላይ የሚሆኑት ማንበብና መጻፍ አይችሉም። ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ ከሚገኙት ከአምስት ሕፃናት አንዱ እና በመላው ዓለም ደግሞ ከዐሥሩ አንዱ፣ ወይም 250 ሚሊዮን የሚሆኑ ሕፃናት ዛሬም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አያገኙም። በዓለም አቀፉ የትምህርት ስኬት ምዘና ማኅበር እና በኢኮኖሚያዊ ትብብር እና ልማት ድርጅት (OECD) በተሠሩ ድንበር ተሻጋሪ ጥናቶች እንዳመለከቱት፤ በመሠረታዊ የንባብ፣ የስሌትና የሳይንስ ትምህርቶች ከሚታዩት ክፍተቶች ባሻገር፣ በሥነ ዜጋ መሠረታዊ ትምህርት፣ በዓለም አቀፋዊ ብቃትና በማኅበረ-ሥነልቡናዊ ክህሎቶች ላይ ተመሳሳይ ክፍተቶች ተስተውለዋል፤ እነዚህ ሁሉ ደግሞ በሲቪክ እና በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ለመሳተፍ ያላቸው አስፈላጊነት እየጨመረ ያሉ ብቃቶች ናቸው።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሁኔታው የበለጠ አስገራሚ ነው። ምንም እንኳን በ2030 ነጻ፣ ፍትሐዊ እና ጥራት ያለው የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመላው ዓለም መሟላቱን ለማረጋገጥ ቃል የተገባ ቢሆንም፤ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ከሚገኙ አምስት ታዳጊዎችና ወጣቶች መካከል ሦስቱ በአሁኑ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አይከታተሉም። ልዩነቶቹ በግልጽ ተለይተዋል። ከፍተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ዝቅተኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ከሞላ ጎደል (98%) ቢሆንም፤ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ግን በጉርምስና ዕድሜ ላይ ከሚገኙት ታዳጊዎች ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት (40% ሴቶች እና 34% ወንዶች) ለዝቅተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አልተመዘገቡም። በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ላይ ያለው ልዩነት ይበልጥ ጎልቶ የሚታየው፤ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች የተመዘገቡትን ከ35% ያነሱ ልጃገረዶች እና 45% ወንዶች፣ ከ90% በላይ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ትምህርት ገበታቸው ላይ ከሚገኙባቸው ከፍተኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር ነው።

ከተደራሽነት እና ከምዝገባ ባሻገር፣ ትምህርትን የማጠናቀቅ አዝማሚያዎች በትምህርት አቅርቦት ጥራት እና ተዛማጅነት ላይ ያሉ ተግዳሮቶችን ያመለክታሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከአራት የዝቅተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከአንድ በላይ እና ከሁለት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከአንድ በላይ የሚሆኑት የትምህርት ዑደቱን አያጠናቅቁም። ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ 60% ገደማ የሚሆኑት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ 90% ገደማ የሚሆኑት ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ዑደቱን ሳያጠናቅቁ ትምህርት ያቋርጣሉ። እንዲህ ዓይነቱ ከፍተኛ የወጣቶች አቅም እና ችሎታ ኪሳራ ተቀባይነት የለውም። በከፍተኛ መጠን ያለ ጊዜው ትምህርት ማቋረጥ በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱለት ይችላሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ የትምህርት ይዘቱ ደካማ ተዛማጅነት፣ ለሴቶች ልዩ ማኅበራዊ ፍላጎቶች እና ለድሆች ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ትኩረት አለመስጠት፣ ባሕል እና እሴትን ከግምት ባለማስገባት ተዛማጅነት ማጣት፣ እንዲሁም ከወጣቶች ዕውነታዎች ጋር የተጣጣሙ በቂ የሥነ ትምህርት ዘዴዎች እና ሂደቶች በበቂ አለመኖር ይገኙበታል። ይህ በሰፊው ችላ የተባለ እና በብዙዎች ዘንድ ዓለም አቀፍ "የትምህርት ቀውስ" ተብሎ የሚጠራው የትምህርት ገጽታ ነው።

የማስተማር ጥራት ማነስ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ከሚያደርጓቸው ቁልፍ "ገፊ" ምክንያቶች አንዱ ነው። በቂ ዕውቅና፣ ዝግጅት፣ ድጋፍ፣ ግብአት፣ በራስ የመወሰን ነጻነት እና ለቀጣይ ዕድገት የሚያግዙ ዕድሎች እስካገኙ ድረስ፤ መምህራን በትምህርት ጥራት ውስጥ ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው። ተገቢውን ድጋፍ ካገኙ፣ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ውጤታማ፣ ባሕልን ያገናዘቡ፣ እና ፍትሐዊ የመማር ዕድሎችን ማረጋገጥ ይችላሉ። ተማሪዎች በሲቪክ እና በኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ለመሳተፍ የሚያስፈልጓቸውን ሙሉ አቅሞች እንዲያዳብሩ ለመርዳት፣ የማስተማር ሙያን ማበልጸግ አስፈላጊ ነው። ይህም ብቃት ያላቸውን እጩዎችን መምረጥን፣ ለእነርሱም ከፍተኛ ጥራት እና አግባብነት ያለው የመነሻ ዝግጅት ማቅረብን፣ በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ዓመታት ውጤታማ በሆነ መንገድ መደገፍን እና ተከታታይ የሙያ ማዳበሪያዎችን እንዲያገኙ ማድረግን፣ እንዲሁም በትብብር ላይ የተመሠረተ ሙያዊ ልህቀትን በሚያሳድግ መንገድ የመምህራንን ሥራዎች ማዋቀርን፣ ትምህርት ቤቶችን የመማሪያ ተቋማት ማድረግን፣ በማስተማርም ሆነ በአስተዳደር ውስጥ እያደገ ለሚሄደው ልህቀት ዕውቅና እና ሽልማት መስጠት የሚያስችል የመምህራን የሙያ እርከኖችን መፍጠርን እና የሙያውን እና የትምህርትን የወደፊት ሁኔታ በመቅረጽ የመምህራን ድምፅ የሚሰማበት፣ ሙያን የሚያግዝ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ መፍጠርን ይጠይቃል። እንዲህ ዓይነቱን ተከታታይነት ያለው ድጋፍ መፍጠር ደግሞ እነዚህ የተለያዩ አካላት እርስበርስ ተቀናጅተው እንዲሠሩ ማድረግ የሚያስችል የጋራ አመራርን ይፈልጋል። ብዙ ባሕላዊ ደንቦች የማስተማርን የተከበረ ሙያነት ያናንቃሉ፤ ለምሳሌ የመምህራንን ምደባ ከተማሪዎች ፍላጎቶች ውጭ እንደ የፖለቲካ ድጋፍ ላሉ ጉዳዮች መጠቀሚያነት  እንዲውሉ ማድረግ፣ የመምህራን ትምህርት መርሐ ግብሮች በሚያስተዳድሯቸው ተቋማት "ገንዘብ እንደምትታለብ ላም" መቆጠራቸው፣ መምህራኑ በተማሪው ትምህርት ላይ ለሚያሳድሩት ተጽዕኖ ዕውቅና የማይሰጡ የሙያ መዋቅሮች መኖራቸው፣ የአሠራር መመዘኛዎች ወይም ለመምህራን ማሰልጠኛ/ማዘጋጃ ተቋማት መመዘኛዎች አለመኖር፣ ተመሳሳይ የዝግጅት እና የሥራ ደረጃዎች ከሚያስፈልጋቸው ሌሎች ሙያዎች በታች የሆኑ ቁሳዊ ሁኔታዎች፣ መምህራን የሙያቸውን ክብር በሚያሳንስ ተግባር ላይ እንዲሳተፉ የሚደርስባቸው ጫና - ለምሳሌ በፖለቲካ ዘመቻዎች ላይ እንዲሳተፉ መጠየቅ ወይም ላላመኑበት ዓላማ ገንዘብ እንዲያዋጡ ማስገደድ፣ ወይም ነጻነታቸውን፣ ማንነታቸውን እና ሰብአዊ መብቶቻቸውን

*በመላው ዓለም የብቁ የአንደኛ ደረጃ መምህራን ድርሻ በአሳሳቢ ደረጃ እየወደቀ ነው።*

መጣስ፣ በሥራ ቦታ ላይ ወሲባዊ ትንኮሳ መፈጸም፣ ወይም ሃይማኖታዊ ወይም ፖለቲካዊ ታማኝነት እንዲያሳዩ ማስገደድ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ሆኖም፣ የትምህርት ዕድል እያደገ በመምጣቱ እና የመምህራን ተፈላጊነት እየሰፋ ሲሄድ፣ በመላው ዓለም የብቁ የአንደኛ ደረጃ መምህራን ድርሻ በአሳሳቢ ደረጃ እየወደቀ ነው። ይህ በበርካታ ቀጣናዎች የታየ ሲሆን፤ በተለይም ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ድርሻ በ2000 ከነበረው 85%፣ በ2020 ወደ 65% ዝቅ ብሏል። ማሽቆልቆሉ ከዚህ በፊት ብቃት ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ድርሻ ከፍተኛ በነበረባቸው ቀጣናዎችም ታይቷል። ለምሳሌ በአረቡ ዓለም በ2004 ከነበረበት 98% በ2020 ወደ 85% ወርዷል። ከሰሃራ በታች ባሉ አገሮች የመምህራን ድርሻ ማሽቆልቆል በሁለተኛ ደረጃ ይብሳል። በ2015 ከሰሃራ በታች ካሉት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን መካከል ዝቅተኛውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉት ግማሽ ያህሉ ሲሆኑ፤ ይህም ከዐሥር ዓመት በፊት ከነበረው 80 በመቶ ገደማ ድርሻ አሽቆልቁሏል።

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የወጣቶች ተሳትፎም በብዙ የዓለም ክፍሎች ዝቅተኛ ነው። ከ2000 እስከ 2020 ባለው ጊዜ ውስጥ ከ15-24 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ወጣቶች ውስጥ እስከ 15 በመቶው በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በተመዘገቡባቸው የመካከለኛው እስያ፣ የመካከለኛው እና ምሥራቅ አውሮፓ፣ እንዲሁም የምሥራቅ እስያ እና የፓስፊክ አካባቢዎች በሙያ ትምህርት ምዝገባ ላይ የተወሰነ መሻሻል ታይቷል። ነገር ግን ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች በተለይም ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ አገሮች እና በደቡብ እስያ በሚገኙ አገሮች፣ በተጠቀሰው የዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተሳትፎ እጅግ በጣም ዝቅ ያለ እና 1% ላይ የቆመ ነው። የሙያ ክህሎት ማሳደግ በመደበኛ ትምህርት እና ሥልጠና ላይ ብቻ የተገደበ እንዳልሆነ እና ኢመደበኛ ኢኮኖሚ በሚጎላባቸው በብዙ ሀገራት ያሉ ወጣቶች ባሕላዊ የክህሎት መቅሰሚያ ወይም ኢመደበኛ የክህሎት ማሳደጊያ ዕድሎች ሊያገኙ እንደሚችሉ ማስታወስ ያስፈልጋል። ሆኖም ከዓለም አቀፉ የሠራተኞች ድርጅት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በመላው ዓለም ከአምስቱ ወጣቶች (16-24) ከአንድ በላይ የሚሆኑት በትምህርት፣ በሥልጠና ወይም በሥራ ላይ የማይገኙ ሲሆኑ፤ ከእነዚህ ውስጥ ሁለት ስተኛ የሚሆኑት ወጣት ሴቶች ናቸው።

እነዚህ አኀዞች ቢያንስ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ተደጋጋሚ ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖች ቢደረጉም፤ ለሁሉም ሕፃናት፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች ሁሉን አቀፍ የትምህርት መብትን በማረጋገጥ ረገጥ ያለንበትን የጋራ ውድቀት ጥርት አድርገው ያሳያሉ። ይህ በተለይ በልጃገረዶች እና በሴቶች፣ በሕፃናት እና በአካል ጉዳተኛ ወጣቶች፣ ከድኃ ቤተሰብ፣ ከገጠር ማኅበረሰቦች፣ ከቀደምት ማኅበረሰቦች እና አነስተኛ ቁጥርና የዕድገት ደረጃ ላይ ከሚገኙ ቡድኖች በተገኙ፣ እንዲሁም የአስከፊ ግጭት እና የፖለቲካዊ መዘዝ ሰለባዎች በሆኑት ዘንድ ዕውነት ነው። የተገለሉ ማኅበረሰቦች በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባሕላዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ድምር ተጽዕኖ መገለላቸው ቀጥሏል።

ትምህርት ነገን ለመለወጥ እንዲረዳ ከተፈለገ፣ በመጀመሪያ ላለፉ ኢ-ፍትሐዊነቶች በመቅረፍ፣ የበለጠ አካታች መሆን አለበት። ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች የተገለሉ ተማሪዎችን፣ በተለይም የተወሳሰቡ ጉዳቶች የሚያጋጥሟቸውን እንዲደግፉ ከተፈለገ፤ እነዚህን ኢ-ፍትሐዊነቶች እና ማግለያዎች የሚቀርፁ ነገሮች በግልጽ ተለይተው ሊታወቁ ይገባል።

# የማያቋርጥ ድህነት እና እየተባባሰ ያለ ኢ-እኩልነት

ድህነት በትምህርት ዕድል ተደራሽነት ላይ ቁልፍ ወሳኝነት ኖሮት ዘልቋል። ሴት ተማሪዎች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አለመረጋጋት እና ግጭት ውስጥ ያሉ፣ እና በጎሳ፣ በቋንቋ ወይም በመኖሪያቸው ርቀት ምክንያት የተገለሉ ተማሪዎች ያሉባቸውን አለመመጣጠኖች የሚያባብስ ውስብስብ ምክንያት ነው።

በምሥራቅ እስያ እና በፓስፊክ አገሮች፣ በተለይም በቻይና፣ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በመመዝገቡ እና ከፍተኛ ገቢ እና ከፍተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት ኢኮኖሚዎች በተከታታይ በመስፋፋታቸው ምክንያት የዓለም ኢኮኖሚ በ1990 እና 2020 መካከል በሁለት ተኩል ጊዜ በመጠን አድጓል። በሌላ በኩል፣ ዝቅተኛ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት በ2020 ከዓለም ሕዝብ የግማሽ ያህሉ መኖሪያ ቢሆኑም፤ ከዓለም አቀፉ ምርት አንድ ዐሥረኛውን ብቻ ነው የሚያዋጡት። ይህም የሆነው ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ በክፍላተ ዓለሞች መካከል ሰፊ የዕድገት ፍጥነት ልዩነት በመፈጠሩ የተነሣ ነው። በ1990 የቻይና እና ከሰሃራ በታች ያሉ አገሮች ኢኮኖሚዎች ተቀራራቢ መጠን ነበራቸው፤ ይኸውም በቅደም ተከተል የዓለምን ኢኮኖሚ 2% እና 1.5% ይወክል ነበር። ከሠላሳ ዓመታት በኋላ ቻይና 16 በመቶውን የዓለም የአገር ውስጥ ምርት ስትሸፍን፤ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች ደግሞ 2 በመቶ ብቻ ይወክላሉ።

የዓለም ኢኮኖሚ ዕድገት የግለሰብ ገቢ እና የኑሮ ሁኔታ መሻሻልን እና የዓለም የድህነት መጠን መቀነስን አምጥቷል። የዓለም ባንክ መረጃ እንደሚያሳየው፣ ከ1990 እስከ 2020 ባለው ጊዜ ውስጥ የዓለም የነፍስ ወከፍ ገቢ በ75% ጨምሯል። በ1990 ከሲሶ በላይ የሚሆነው የዓለም ሕዝብ ደሃ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር፤ ዛሬ ግን የዓለም የድህነት መጠን ከ10% በታች ነው። ይሁን እንጂ፣ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ፍጥነት መቀነስ የድህነት ቅነሳ እርምጃን እና የገቢ አለመመጣጠን የሚቀንስባቸውን ተስፋዎች ያደናቅፋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ድህነትን የማጥፋት ጥረት ያለበት ተግዳሮት አሁንም በርትቶ እንደቀጠለ ነው። በእርግጥ፣ ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የድህነት ቅነሳ ቢመዘገብም፣ በዓለም ዙሪያ ወደ 690 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች አሁንም በቀን ከሁለት የአሜሪካ ዶላር በታች እያገኙ፣ በድህነት ውስጥ ይኖራሉ። በዓለም ባንክ መረጃ መሠረት፣ ከዓለም ሕዝብ ውስጥ አንድ አራተኛው ወይም 1.8 ቢሊዮን ሰዎች የሚኖሩት በቀን 3.20 ዶላር ወይም ከዚያ ባነሰ ገቢ እያገኙ ነው። አስከፊ ድህነት በአብዛኛው ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ፣ በዋነኝነትም በገጠር የተከማቸ ሲሆን፤ በተለይ ሴቶችን ያለልክ ይጎዳል። ከድሆቹ መካከል 2/3ኛው በዕድሜ ከ25 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት እና ወጣቶች ናቸው።

በማደግ ላይ ባሉ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ኢኮኖሚዎች ከ1980ዎቹ ጀምሮ የታየው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በአገሮች መካከል ያለው ልዩነት በጥቅሉ እንዲቀንስ አድርጓል። በዚያው ጊዜ ግን፣ በተለያየ ፍጥነት ቢሆንም፣ በአገሮች ውስጥ ኢ-እኩልነት ጨምሯል። ከ1980ዎቹ ጀምሮ የገቢ አለመመጣጠን በቻይና፣ በሕንድ፣ በሰሜን አሜሪካ እና በሩሲያ ፌዴሬሽን በከፍኛ ደረጃ ጨምሯል፤ በአውሮፓም መጠነኛ ጭማሪ ታይቷል። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በአረቡ ዓለም፣ እንዲሁም ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች፣ እና ልክ በብራዚል እንደሆነው፣ ኢ-እኩልነት ቀድሞውንም ከፍተኛ ነበር፤ አሁንም በዚያው ቀጥሏል። በ2018 የዓለም ኢ-እኩልነት ሪፖርት መሠረት ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች እና በአረብ አገሮች ወይም እንደ ብራዚል እና ሕንድ ባሉ አገሮች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ገቢ የሚሰበስቡት ከተከፋዮች/ገቢ አግኚዎች የላይኞቹ 10 በመቶዎች ብቻ ናቸው። በሁሉም አገሮች ማለት ይቻላል ካፒታል ከሕዝብ ወደ የግል ባለቤትነት ተሸጋግሯል። ኢኮኖሚው እየሰፋ ሲሄድ፣ መንግሥታት እየደኸዩ በመምጣታቸው፣ የገቢ ማደላደል እና ኢ-እኩልነትን የመቀነስ ዕድሎች ተገድበዋል።

የሀብት አለመመጣጠን በትምህርት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ገጸብዙ ነው። አለመመጣጠኑ በድሆች ላይ ወደሚደርስ ማኅበራዊ ማግለል ተቀይሮ፣ ለማኅበረሰቦች ዕድገት እና መልካም አስተዳደር እንዲኖር አስፈላጊ የሆነውን ማኅበራዊ ትስስር ይጎዳል። አለመመጣጠን በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ወደ ተወለዱ እና ደረጃው በጣም የተለያየ የትምህርት ድጋፍ ወደሚያገኙ ልጆችም ይተረጎማል፤ ይህም የትምህርት ቤቶችን የመጫወቻ ሜዳውን ለሁሉም እኩል የማድረግ ኃላፊነት አስቸጋሪ ያደርገዋል። ያሉበት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን፣ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ልጆች እኩል የትምህርት ዕድሎችን መስጠታቸው፣ ይበልጥ ፍትሐዊ እና ያልተዛቡ ነገዎችን ለማረጋገጥ መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ ነው።

ይህ በይበልጥ እኩል ባልሆኑ ማኅበረሰቦች ውስጥ ፈታኝነቱ ይጎላል። በእርግጥም የተጋነነ አለመመጣጠን በትምህርት ውስጥ ሙስና እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ይኸውም ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የመብለጥ ጉጉት ሕገወጥ አቋራጭ መንገዶችን ወደመጠቀም ሊተረጎም እና ይህንኑም በአግባቡ የመቆጣጠር አቅም ሊያሳንስ ይችላል። የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የ2013 ዓለም አቀፍ የሙስና ሪፖርት በትምህርት ላይ ሙስና ሊገለጽ ይችልባቸዋል ብሎ ከዘረዘራቸው መንገዶች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡- ለግዢ እና አቅርቦት የሚውሉ ሀብቶችን ለሌላ ጥቅም ማዋል፣ ከክፍል ክፍል ለማሻገርና ለቅበላ ጉቦ መቀበል፣ በቅጥር እና በትምህርት ዕድል አሰጣጥ ላይ በዘመድ መጠቃቀም፣ በጥናትና ምርምር ላይ የሚፈጸም አካዳሚያዊ ስርቆሽ እና በምርምር ላይ ያልተገባ የፖለቲካ እና የንግድ ተጽዕኖ ማሳደር። የተዳከመ ማኅበረሰባዊ እና ተቋማዊ ተአማኒነት በትምህርት ዋጋ እና ታማኝነት ላይ ያለውን እምነት ሊያሳንስ ከመቻሉም በበለጠ፣ ከልጅነት ጀምሮ ሙስናን እንደ ማኅበራዊ ደንብ መቀበልን ሊያስለምድ ይችላል።

# የማግለል ድር

ድህነት እና የገቢ አለመመጣጠን ከሌሎች የትምህርት ማግለልን ከሚያስከትሉ የአድልዎ ምክንያቶች ጋር ይገናኛሉ። የሥርዓተ ጾታ መድልዎ፣ ለምሳሌ፣ ሴት ልጆችን ከትምህርት መብታቸው የበለጠ ለማግለል እንደ ድህነት፣ የጎሳ ማንነት እና አካል ጉዳተኝነት ካሉ ሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች ጋር በእጅጉ ይተባበራል። አብዛኛዎቹ የገቢ ቡድኖች እና ክፍላተ ዓለሞች በትምህርት ቤት ምዝገባ ረገድ የጾታ ማመጣጠን ላይ ቢደርሱም፤ በጣም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ወይም ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች ውስጥ ያለው ዕውነታ ግን ይህ አይደለም። የዩኔስኮ ኢንስቲትዩት ፎር ስታትስቲክስ (UIS) መረጃ እንደሚያሳየው፣ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መግቢያ ዕድሜ ሆነው ነገር ግን ትምህርት ቤት ባልገቡ በእያንዳንዳቸው 100 ወንዶች ልጆች ልክ፣ 123 ሴት ልጆችም ከትምህርት የተገለሉ ናቸው። ልጃገረዶችን ማግለል በታችኛው እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ውስጥ የበለጠ ጎልቶ ይታያል። ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ውስጥ በ9ኙ በጣም ድሃ የሆኑ ልጃገረዶች በትምህርት ቤት የሚያሳልፉት ጊዜ በአማካይ በ2 ዓመት ከወንዶች ያነሰ ነው። ይህ በተለይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚታይ ሥርዓተ ጾታዊ ማቋረጥ፣ ልጃገረዶችን ሙሉ የትምህርት ዘመናቸውን ሳያቋርጡ እንዲከታተሉ ለማስቻል ምን ያህል ከፍተኛ ጥረት መደረግ እንዳለበት ይጠቁማል። የመነሻው ተደራሽነት ብቻ በቂ አይደለም። ልጃገረዶች ሙሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ የማድረግ ኃላፊነት ለትምህርት ቤቶች ብቻ የሚተው አይደለም። እንደ ያለ ዕድሜ ጋብቻ ወይም ያለ ዕድሜ እና ያልታሰበ እርግዝና፣ የቤት ውስጥ ሥራ እና የወር አበባ ጤና እና መገለል ካሉ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ልጃገረዶች፣ በተለይም በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙት፣ በዓለም ላይ እያጋጠሟቸው ካሉ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች ጋር ይዛመዳል።

የትምህርት ሥርዓቶች አካታች ፖሊሲዎች እስከሌሏቸው ድረስ፣ አካል ጉዳተኝነት በሁሉም ክፍላተ ዓለም እና የገቢ ቡድኖች የትምህርት ተደራሽነትን ይነካል። አካል ጉዳተኞች የሚያጋጥሟቸው የትምህርት መሰናክሎች ድህነት ሲጨመርባቸው ደግሞ በእጅጉ የከፉ ይሆናሉ። አብዛኞቹ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሕፃናት በጣም ደሃ በሆኑ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። በሁሉም ዕድሜዎች፣ የመካከለኛ እና ከባድ የአካል ጉዳት ምጣኔ ከበለጸጉ አገሮች በላይ ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ከፍ ያለ ነው። ድህነት የአካል ጉዳት መንስኤ እና መዘዝ ነው፤ የትምህርት ሥርዓቶች ደግሞ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የመማር መብት የመደገፍ ግዴታ አለባቸው፤ እንዲሁም በተቻለ መጠን ገዳቢነቱ ባነሰ የትምህርት ከባቢ ውስጥ ሊያካትቷቸው ይገባል።

ግጭት በአስከፊ ሁኔታ ከትምህርት ቤት ውጪ ከቀረው የዓለም ሕዝብ የግማሹን ምክንያት ነው። አስከፊ ግጭት የትምህርት ቤቶችን ሥራ ማካሄድንም ሆነ፣ ትምህርት መከታተልን አደገኛ ከማድረጉም በላይ፣ ሁሉንም ሕዝብ ሊያፈናቅል ይችላል። የትምህርት ተቋማት፣ ሠራተኞች እና ተማሪዎች ዒላማ ሊሆኑ እና የአፈና፣ የአስገድዶ መድፈር እና የታጣቂነት ምልመላ ሰለባ ሊሆኑ ይችላሉ።

ከቀደምት ሕዝቦች እና አነስተኛ ቁጥርና የዕድገት ደረጃ ካላቸው ብሔሮች የተገኙ ልጆች እና ወጣቶች ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት ዕድልን የሚገድቡ በርካታ መሰናክሎች በሁሉም እርከኖች ያጋጥሟቸዋል። ከኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ ልሳናዊ

እና ጂኦግራፊያዊ መሰናክሎች ባሻገር፣ እንደ ዘረኝነት፣ መድልዎ እና የባሕል አግባብነት ማጣት ያሉ ጉዳዮች በቀደምት ነዋሪዎች ልጆች እና ወጣቶች ከፍተኛ የትምህርት ማቋረጥ ምክንያቶች ናቸው። በጥቅሉ ሲታይ፣ መደበኛ ትምህርት ለአገር በቀል ዕውቀትና የትምህርት ሥርዓቶች ዕውቅና ካለመስጠቱም በላይ፣ በገጠርም ሆነ በከተማ ላሉ ቀደምት ሕዝቦች ነባራዊ ሁኔታዎች እና ምኞቶች ምላሽ አይሰጥም።

በታሪክ እንደታየው፣ ትምህርት የሕፃናት ባሕላዊ እና ሃይማኖታዊ መብቶች ለመጣስም አገልግሏል፤ ለምሳሌ ቀደምት ማኅበረሰቦችን እና አነስተኛ ቁጥርና የዕድገት ደረጃ ያላቸውን ብሔረሰቦች የበላይነት ካላቸው ማኅበረሰቦች ጋር ለማዋሐድ ወይም አነስተኛ ቁጥርና የዕድገት ደረጃ ያላቸውን ማኅበረሰቦች ሕፃናት ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ማንነቶች በሃይማኖት አስተምህሮ ለማስካድ ወይም ለማጥፋት በመሳሪያነት አገልግሏል። የቀደምት ማኅበረሰቦችን ልጆች እና ቤተሰቦች ለመጉዳት ትምህርትን በመሣሪያነት መጠቀም አሁንም በሥርዓታዊ መድልዎ እና ቸልተኝነት መገለጡን ቀጥሏል። ለምሳሌ ርቀው ከሚኖሩ ቀደምት ማኅበረሰቦች እና አነስተኛ ቁጥርና የዕድገት ደረጃ ካላቸው ማኅበረሰቦች የተገኙ ልጆች ብዘውን ጊዜ ትምህርታቸውን ለመቀጠል አካባቢያቸውን ለቀው እንዲሄዱ፣ በሆስቴሎች ወይም በአዳሪ ትምህርት ቤቶች እንዲኖሩ ይገደዳሉ፤ ይህም ከቤተሰቦቻቸው እና ከማኅበረሰባቸው ይነጥላቸዋል፤ እንዲሁም ከባሕል የሚያገኙትን ድጋፍም ያሳጣቸዋል።

ኢኮኖሚያዊ ግሎባላይዜሽን ተማሪዎች ምን እና እንዴት እንደሚማሩ የሚወስን ተጽዕኖው እየጨመረ ነው። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሥራ ለማግኘት ሕፃናትና ወጣቶች ምን ሊያውቁ እንደሚገባ የሚሰጡ ግምቶችን አስለውጧል። ለሥራ መዘጋጀት ጠቃሚ የትምህርት ግብ ነው። ነገር ግን፣ የትምህርትን ግቦች በጣም አጥብቦ፣ በተለይም ከተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ሕይወት እና ዕድሎች ዕውነታዎች ጋር በማይጣጣሙ መንገዶች መግለጽ ችግሮች አሉበት። ማወቂያ መንገዶችን አስፍቶ ማየት ዕውቀት በተለያዩ አውዶች፣ ባሕሎች እና ሁኔታዎች ውስጥ ሊተገበር፣ ሊመነጭ እና ሊሰራጭ በሚችልባቸው መንገዶች ላይ ሰፊ ስብጥር እንዳለ ይገነዘባል። እነዚህ በመሠረታዊ የማንበብ መጻፍ እና የስሌት ችሎታዎች ላይ ብቻ ሳይሆን፤ ለዓለም አቀፋዊው፣ አካባቢያዊው፣ በትውልድ ውርስ ለተገኘው፣ ለሥጋዊው፣ ለባሕላዊው፣ ለሳይንሳዊው እና ለመንፈሳዊው ዕውቅና በሚሰጡ በሁሉም ባሕሎች በሚገኙ የበለጸጉ የዕውቀት ቅርሶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

> *የትምህርት ፍትሐዊነት የሰው ልጅን ብዙ የዕውቀት ዓይነቶች እና መገለጫዎቹን ማካተት አለበት።*

ይህ በተለይ፣ ከትምህርት ቤት ውጭ ካሉት መካከል ሊቆጠሩ ከሚችሉት፤ ከቀደምት፣ ጥቂት ተናጋሪ ያለውን ቋንቋ ከሚናገሩ እና የተለያየ ጎሳ ካላቸው ማኅበረሰቦች የተገኙትን ተማሪዎች በተመለከተ ዕውነት ነው። የትምህርት ፍትሐዊነት የሰው ልጅን ብዙ የዕውቀት ዓይነቶች እና መገለጫዎቹን ማካተት አለበት። መጠነ ሰፊ የመማሪያ ምዘናዎች ብዙ ጊዜ የአፍ መፍቻ ብቃቶችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይሳናቸዋል፣ ይህም አነስተኛ ቁጥርና የዕድገት ደረጃ ያላቸው ቡድኖችን እና የቀደምት ማኅበረሰብ ተማሪዎችን ይበልጥ በማግለል ቀድመው ትምህርት እንዲያቋርጡ ሊያደርጋቸው ይችላል። በዓለም አቀፍ የትምህርት ቤት የንባብ ዳሰሳ ምርምር መርሐ ግብር (PIRLS) ውጤቶች መሠረት፣ ለምሳሌ የፈተናውን ቋንቋ በቤት ውስጥ የማይናገሩ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ ዝቅተኛው የንባብ ብቃት ደረጃ ላይ የመድረስ ዕድላቸው ከሌሎች ተማሪዎች ያነሰ ነው። ነጠላ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ራዕይ ከመጫን ይልቅ፣ ብዙ የተኖሩ ዕውነታዎችን ያካተተውን ዓለም መቀበል አለብን። የግለሰብ እና የወል መብቶች ሙሉ በሙሉ መተግበራቸውን ማረጋገጥ፣ ለተለያዩ ዓይነት የሰው ልጅ አቅሞችን ትክክለኛ ግምት መስጠትን ይጠይቃል።

ሰብአዊ መብት አዲሱን የትምህርት ማኅበራዊ ውል እንዲመራው ከተፈለገ፣ የተማሪዎች በተለይም በቀደምትነታቸው፣ በሃይማኖት፣ በባሕልና በሥርዓተ ጾታ ሕዳጣንነታቸው ምክንያት ሥርዓታዊ መገለል የሚደርስባቸው ተማሪዎች የማንነት መገለጫ - ባሕላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ እና ሥነ ልሳናዊው ማንነት- ዕውቅና እና ድጋፍ ሊያገኝ ይገባዋል። በሥርዓተ ትምህርት፣ በሥነ ትምህርት እና በተቋማዊ አቀራረቦች ውስጥ ማንነት አግባብ ያለው ዕውቅና ማግኘቱ ተማሪን በትምህርት ገበታ ላይ በማቆየት፣ በአእምሮ ጤና፣ በራስ ከበሬታ እና በማኅበረሰባዊ ደህንነት ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

ሌሎች መፍትሔዎች በቂ ለማይሆኑላቸው ለመድረስ የተለያዩ ዘዴዎች እና እርምጃዎች ያስፈልጋሉ። ነገር ግን እነዚህ ጥረቶች ከአየር ንብረት ለውጥ፣ ከዓለም አቀፍ ወረርሽኝ እና ከደህንነት እጦት የተነሣ በሚያጋጥሙ ተጨባጭ እና አሁናዊ ማኅበራዊ እና ትምህርታዊ ችግሮች አንጻር የበለጠ ፈታኝ ይሆናሉ። በ2020 የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ብቻ በዓለም ዙሪያ 1.6 ቢሊዮን ሕፃናት እና ወጣቶች የሚማሩባቸው የትምህርት ተቋማት እንዲዘጉ በማስገደዱ ጎድቷቸዋል። ትምህርት ቤቶች ቢከፈቱም እንኳን፣ በተለይም ከድሆች እና የተገለሉ ማኅበረሰቦች ይመጡ የነበሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት አይመለሱም። የትምህርት ዕድል አለመመጣጠን የበለጠ ተባብሷል።

በማቆጥቆጥ ላይ ካሉ ሕብረተሰባዊ ለውጦች እና በዓለም ላይ ካሉ ሥር ነቀል መስተጓጎሎች አንጻር፣ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል መፍጠር ከምንም ነገር በላይ አጣዳፊ ነው። ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር ዘላቂነት፣ እና ማኅበራዊ ፍትሐዊነት እና አካታችነት ያላቸው የጋራ ነገዎችን ለመቅረጽ እየረዳ፤ ትምህርታዊ እና ማኅበረሰባዊ መገለልን የሚያስቀጥሉትን የአለመመጣጠን ድሮች መፍታት አለበት።

# ምዕራፍ 2

# መናጋቶች እና አዳዲስ ለውጦች

*እዚህ ላይ፣ ሕይወቴ ካስተማረኝ ታላላቅ ትምህርቶች አንዱ የአሁኑን ቋሚነት፣ የመሆንን ቀጣይነት እና የወደፊቱን ተተንባይነት ማመን ማቆም መሆኑን በአጽንዖት መግለጽ እፈልጋለሁ። አጭር እና ያልተጠበቁ ድንገተኛ ፍንዳታዎች አንዳንድ ጊዜ ደስ በሚል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሚያስከፉ ሁኔታ፣ ግላዊ ሕይወታችንን፣ የዜጋነት ሕይወታችንን፣ የአገራችንን ሕይወት እንዲሁም የሰው ልጅን ሕይወት ለማንቀጥቀጥ ወይም ለመለወጥ ያለማቋረጥ ይመጣሉ።*

*ኤድጋር ሞሪን፣ Leçons d'un siècle de vie,* 2021.

ወደ ምዕተ ዓመቱ አጋማሽ ወሳኝ ምዕራፍ ወደ 2050 ስንገሰግስ፣ የሚያስፈልገን የትምህርት ዓይነት በቤተሰቦች፣ በማኅበረሰቦች፣ በአገሮች እና በክፍላተ ዓለሞች መካከል ካሉ ከፍተኛ ልዩነቶች አኳያ ዓለም ምን እንድትመስል መጠበቅ በምንችለው ልክ ይወሰናል።

ይህ ምዕራፍ ብዙ ጊዜ እርስበርስ ተሳስረው በሚገኙ በአራት መስኮች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚጠበቁትን መናጋቶች በማጉላት የወደፊቱን ይመለከታል፤ አራቱ መስኮች አካባቢ፣ ከቴክኖሎጂ ጋር የምንኖርባቸው እና የምንግባባባቸው መንገዶች፣ የአስተዳደር ሥርዓቶቻችን እና የሥራ ዓለም ናቸው።

አርቆ የማየት ሥራ እርግጠኛ ባያደርግም፣ ልዩነት ፈጣሪ አምጪ ለውጦችን አስቀድሞ መገመት ግን በሚቀጥሉት ዐሥርት ዓመታት እና ከዚያም በላይ ትምህርትን ከሰው ልጅ ፍላጎቶች ጋር ማስማማት የሚያስችሉ አማራጭ ቢሆኖችን ለማቀድ እና ለመገንባት መሠረት ይሰጣል።

# በአደጋ ላይ ያለች ፕላኔት

ወደ 2050 የሚያደርሱን ዐሥርት ዓመታት እና በተለይም 2020ዎቹ ከሰዎች እና በምድር ላይ ካሉት ሕያዋን የወደፊት ዕጣ አኳያ ወሳኝነት እንዳላቸው ሳይንሳዊ መግባባት ላይ ተደርሷል። የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ የምንወስዳቸው - ወይም የማንወስዳቸው - እርምጃዎች በ2030ዎቹ እና 2040ዎቹ ሊሆኑ የሚችሉትን ሁኔታዎች ከመወሰናቸውም በላይ፣ በሙቶ ሺዎች እንዲያውም በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ዓመታት የሚዘልቅ ውጤት ይኖራቸዋል። ምድር ላይ የምናደርጋቸው ለውጦች መጠን እና ፍጥነት ምንም ታሪካዊ ቀዳሚ ምሳሌ የላቸውም፤ ሥነ ምድራዊ ቀዳሚ ምሳሌዎቻቸውም በጣም ጥቂቶች ናቸው። የከባቢ አየር ኬሚካላዊ ቅንብር በአጥቢ እንስሳት ዕድሜ ዘመን ውስጥ ከታዩት እጅግ በጣም ከፍተኛ ለውጦች እንኳን በዐሥር እጥፍ ፍጥነት እየተቀየረ እንዳለ ይገመታል። ከ125,000 ዓመታት በፊት ከጀመረው የመጨረሻው የበረዶ ዘመን አንሥቶ፣ ምድር አሁን ከየትኛውም ጊዜ የበለጠ ሞቃታማ ሆናለች። ደግሞም የተከሰቱት የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎች ሥርዓታችን ውስጥ በመተከላቸው፣ ለሚቀጥሉት ሡላሳ ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት የፕላኔቷ ሕያዋን ሕይወት መልክ ይወስናሉ። ስለዚህ የአየር ንብረት ለውጥን ያገናዘበ ምላሽ መስጠት፣ ለውጡን ማቅለል እና ወደነበረበት መመለስ አለብን፤ እንዲሁም ስለ የአየር ንብረት ለውጥ የሚሰጥ ትምህርት ከእነዚህ ሦስት ግቦች ጋር መጣጣም አለበት።

የ2015 የፓሪስ የአየር ንብረት ስምምነት መፈረም ከኢንዱስትሪ ዘመን መባቻ ጀምሮ እየተስፋፋ የመጣውን እንደ CO2 እና ሚቴን ያሉ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት ለማረጋጋት እና በመቀነስ ላይ ለመሥራት ታሪካዊ ዓለም አቀፍ ቁርጠኝነትን አሳይቷል። የዓለም መንግሥታት ፕላኔቷ ከቅድመ-ኢንዱስትሪ የሙቀት መጠኗ ከ2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በላይ (እና ከተቻለም ከ1.5 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በላይ) አለመሞቋን ለማረጋገጥ ለመርዳት ቃል ገብተዋል። ሆኖም የቅሪተ አካል ነዳጆችን ቃጠሎ ለመቀነስ ቃል ቢገባም፣ የልቀት መጠኑ እየጨመረ መሄዱን ቀጥሏል። የ2021 የአየር ንብረት ለውጥ የበይነ መንግሥታት ፓነል ሪፖርት እንደሚያሳየው የዓለም ሙቀት መጨመር ፍጥነት ከጥቂት ዓመታት በፊት ከተጠበቀውም በላይ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሙቀት አማቂ ጋዞችን መጠን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ይቅርና ውጤታቸውን ማረጋጋት እንኳን አለመቻላችንን አረጋግጠናል። የዚህ እርምጃ ያለመውሰዳችን ተጽዕኖው በዙሪያችን አለ፤ በአብዛኛውም አስከፊ በሆነ ሙቀት ይገለጣል፤ ተደጋጋሚ እና ተራዛሚ ድርቆች፣ ጎርፎች፣ እሳቶች እና ጥፋትን ማፋጠን የተለመደ እየሆነ መጥቷል። ደግሞም፣ ምንም እንኳን የማያቋርጡ ማስጠንቀቂያዎች ቢኖሩም፣ በጣም ብዙ ሰዎች ለዘመናዊው ዓለም ኃይል አቅርቦት ሲባል የሚከወኑ እንደ ማዕድን ማውጣት እና ካርቦን ማቃጠል ያሉ የሰው ልጅ እንቅስቃሴዎች የሚያስከትሉትን መዘዝ ገና አልተረዱም። የሰው ልጅ እንቅስቃሴ የአየር ንብረት ለውጥ አስከትሏል፣ ይህም በፕላኔታችን ላይ ከሚገኙት ሞቃታማ ኮራል ሪፎች መካከል ግማሽ ያህሉ እንዲሞቱ፣ 10 ትሪሊዮን ቶን በረዶ እንዲቀልጥ እና በአስደናቂ ሁኔታ የውቅያኖስ አሲዳማነት እንዲጨምር አድርጓል። የአየር ንብረት ለውጥን አስከፊ ተጽዕኖዎች ለመከላከል የካርቦን ልቀት ሚዛንን የተጣራ ዜሮ ማድረሱ እስከ 2050 ጊዜ የሚሰጠን መስሎ ቢቆይም፣ የቅርብ ጊዜ ሳይንሳዊ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ግን ከዚያ ጊዜ በጣም መቅደም የግድ ነው። በሚቀጥሉት በርካታ ዓመታት ውስጥ - ከምድር ታሪክ ስፋት አንጻር በናኖ ሰከንድ ውስጥ - የሚፈጠሩት ነገሮች አይጨበጤነቱ እየተባባሰ

ወደሚመጣ እና አደገኛ የአየር ጠባይ ወዳለው አስፈሪ የሕይወት ጎዳና ሊወስዱን፤ ወይም ወደሚለዋወጥ፣ ነገር ግን አስከፊነቱ ቀነስ ወዳለ እና ለሰው ልጆች አንጻራዊ ተስማሚነት ወዳለው የአየር ሁኔታ ሊመሩን ይችላሉ።

የሁኔታው አጣዳፊነት በመላው ዓለም ባሉ ቤቶች፣ የንግድ ተቋማት፣ የአምልኮ ቦታዎች እና ትምህርት ቤቶች ዘንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየታወቀ መጥቷል። በግልጽ እንደታየው፣ ሕፃናት እና ወጣቶች፣ እርምጃዎች እንዲወሰዱ አንዳንድ በጣም ኃይለኛ ጥሪዎችን መርተዋል፤ የዘመናችንን አሳሳቢ ሁኔታ ላይ መሆን በማይቀበሉት እና ትርጉም ያለው የእርምት እርምጃ በማይወስዱት ላይም ከባድ ተግሣጽ ሰንዝረዋል። ለዚህ ሪፖርት ግብአት በሆኑት ምክክሮች፣ ከወጣቶች ጋር እና በወጣቶች በተደረጉት የትኩረት ቡድን ውይይቶች፣ እና በወጣቶች ላይ በተደረጉ ቅኝቶች ላይ እንደታየው፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና የአካባቢ ውድመት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

## ፕላኔታዊ ድንበሮችን ማለፍ

የምድር ከባቢ አየር እና የውቅያኖሶች ሙቀት ፕላኔቷን ወደ ጥፋት አፋፍ ከሚገፋት የተፈጥሮ ሀብት ብዝበዛ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ የሚጓዝ ነው። ከ1950 እስከ 2020 ባለው ጊዜ ውስጥ የሰው ልጅ ቁጥር በሦስት እጥፍ አድጎ፤ ከ2.5 ቢሊዮን ሰዎች ወደ 8 ቢሊዮን ገደማ ደርሷል፤ ይህም በወሊድ መጠን መጨመር እና በሕይወት የመቆያ ዕድሜ ጣራ በፍጥነት ማደግ የተነሣ ነው። በ2020 በምድር ላይ ያለው አማካይ ሰው በ1920 ከነበረው እጥፍ ዕድሜ ኖሯል - ይህም አስደናቂ ስኬት ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ማኅበራዊ እና ሳይንሳዊ ስኬቶችን ያንጸባርቃል። እንደሚገመተው፣ ይህ የሕዝብ ቁጥር መናር ከሀብት ፍላጎቶች መጨመር ጋር ተመሳስሏል። ከቅርብ ምዕተ-ዓመታት ባነሰ ፍጥነት ቢሆንም የሕዝብ ቁጥር መስፋፋቱን ቀጥሏል። አሁን ያሉት ትንበያዎች በ2050 የሕዝብ ቁጥር ዕድገት 9.7 ቢሊዮን እና ከዚያም በ2100 ወደ 11 ቢሊዮን አካባቢ ደርሶ እንደሚረጋ ይጠቁማሉ።

ይህ ዕድገት ከፍጆታ እና የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴን ፈጣን መስፋፋት ጋር ተዳምሮ በሀብቶች ላይ ከፍተኛ ፍላጎት ከመቀስቀሱም በላይ በአካባቢ ላይ ተደጋጋሚ ጫናን ያስከትላል። ከ1950 ጀምሮ የሰው ልጅ የውኃ አጠቃቀም በእጥፍ ጨምሯል፤ የምግብ ምርት እና ፍጆታ በ2.5 እጥፍ፣ የእንጨት ፍጆታ ደግሞ በሦስት እጥፍ አድጓል። በ2050 የምግብ ፍላጎት በ35%፣ የውኃ ፍላጎት ከ20-30% እና የኃይል ፍላጎት ደግሞ በ50% ይጨምራል ተብሎ ይገመታል።

> *ዛሬ በቁሳቁስ ምርት፣ በፍጆታ እና ማስወገድ ፕላኔታዊ ድንበሮችን ዐልፈናል።*

ዛሬ በቁሳቁስ ምርት፣ በፍጆታ እና ማስወገድ ፕላኔታዊ ድንበሮችን ዐልፈናል። በአንዳንድ ግምቶች፣ አሁን ያለው የሰው ልጅ ሥነ ምህዳራዊ አሻራ እኛን ለመደገፍ እና ቆሻሻችንን ለመምጠጥ 1.6 ምድሮች እንደሚያስፈልጉን ያሳያል። ይህ ማለት የሀብት አጠቃቀማችን እያደገ በመሄዱ፤ ፕላኔቷ አሁን በአንድ ዓመት ውስጥ የምንጠቀመውን እንደገና ለመፍጠር፣ አንድ ዓመት ከስምንት ወር ያስፈልጋታል ማለት ነው። አካሄዳችንን ካላረምን፣ በ2050 ለማገገም አራት እጥፍ ጊዜ የሚፈጁ ሀብቶችን ስለምንጠቀም፤ ለመጪው ትውልድ በአስከፊ ደረጃ የተሟጠጠች ፕላኔት እናስረክባለን።

የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀማችን እና ብዝበዛችን ተረፈ ምርት የሆነው የከባቢ አየር ብክለት በፍጥነት ትልቁ አካባቢያዊ የበሽታ እና ሞት መንስኤ ሆኗል፤ በዓመት ለ9 ሚሊዮን ያለዕድሜ ሞቶች ምክንያት ነው ተብሎ ይገመታል፤ ይህም ኤድስ፣ ወባ፣ ቲቢ እና ጦርነት ተደምረው ከሚያመጡት ሞት መጠን በእጅጉ የላቀ ነው። ብክለት የፕላኔታችን ትልቁ የማኅበረሰብ ጤና ቀውስ ተብሎ የሚጠራ ብቻ ሳይሆን፤ ከመማር ችግር እና ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ተያይዞም ይነሣል። ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እና መምጣት ብቻ በብዙ ሁኔታዎች ለሰው ልጅ ጤና አደገኛ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም በአየር ብክለት አደገኛ ደረጃ ላይ ከመድረሱም በላይ፤ እና ብዙዎቹ የትምህርት ተቋማት የሚሠራ የአየር ማጣሪያ፣ ተገቢ የፍሳሽ ማስወገጃ እና ንጹህ ውሐ የላቸውም። ሌሎቹ የመማሪያ ተቋማት ደግሞ አደገኛ የኬሚካል ብክነት እና ሌሎች መርዛማ ብክለት ባለባቸው አካባቢዎች ይገኛሉ።

ምንም እንኳን ነገ ዜሮ ልቀት ቢሳካ እና 100% የንፁሕ ኢነርጂ ሥርዓቶች ቢኖሩን እንኳን፤ በሥርዓታችን ውስጥ በተተከሉ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎች ላይ ከሚጨመሩ እንደ ደን መጨፍጨፍ፣ ለከትየለሽ ዓሳ ማጥመድ፣ ኢንዱስትሪያዊ ግብርና፣ ማዕድን ማውጣት እና ቆሻሻ ያሉ ዘላቂነት የሌላቸው ተግባራት ከሚያስከትሏቸው ጎጂ ሥነ ምሕዳራዊ መዘዞች ጋር እንጋፈጣለን። እነዚህ ሰንሰለታማ መዘዞች ገና መታየት መጀመራቸው ነው። የምድር ባዮስፌር የተቀናጀ ሥርዓት ነው - ሰውን የሚያካትት እና ከፍተኛ ጫናዎችን የሚቋቋም - ነገር ግን ጥገኞች የሆንንባቸው ሥርዓተ ምህዳሮች ላይ ጫና ባበዛንባቸው ቁጥር ወደማይቀለበስ ውድመት ወደሚያመራው ጫፍ እንጠጋለን።

ለዚህ ተጠያቂው የሰው ልጅ ቢሆንም፤ ሁሉም ሰዎች ግን እኩል ተጠያቂ አይደሉም። ልዩ ተጠቃሚነት ያላቸው ቡድኖች እና የፕላኔቷ ሀብታም አካባቢዎች በሚያስደንቅ ሁኔታ ብዙ ሀብቶችን ይጠቀማሉ፤ ከሌሎች የበለጠም ካርቦን ያቃጥላሉ። አቅጣጫ ለመቀየር በጋራ ስንሠራ፣ ማኅበራዊ ፍትሕ ሥነ ምህዳራዊ ፍትሕን፣ ሥነ ምህዳራዊ ፍትሕ ደግሞ ማኅበራዊ ፍትሕን ማካተት አለባቸው። በፕላኔቷ ላይ እነዚህን ውጥረቶች ለማድረስ ዝቅተኛ ተጠያቂነት ያላቸው ወገኖች፣ ከጥፋታቸው ጋር የማይመጣጠን ዋጋ መክፈላቸውን እንዳይቀጥሉ ማረጋገጥ አለብን።

## የአየር ንብረት ለውጥ በትምህርት ላይ የሚያሳድራቸው ተጽዕኖዎች

በአሁኑ ጊዜ የአየር ንብረት ለውጥ እና የሥርዓተ ምህዳር መዛባት ትምህርትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ይጎዳል። የከባድ የአየር ሁኔታ ክስተቶች እና ተጓዳኝ የተፈጥሮ አደጋዎች መጠናከር የትምህርትን ተደራሽነት ሊያግድ፣ ዐልፎ ተርፎም ጭራሽ ሊከለክል ይችላል። ልጆች፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች ተማሪዎች በቂ የትምህርት ተቋማት ከሚገኙባቸው አካባቢዎች ርቀው ወደሚገኙ ሥፍራዎች ሊፈናቀሉ ይችላሉ። የትምህርት ቤት ሕንፃዎች ሊወድሙ ወይም ወደመጠለያነት ወይም ወደ ሌሎች አገልግሎቶች መስጫነት ሊቀየሩ ይችላሉ። ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርስቲዎች ሥራ ቢቀጥሉም፣ በመፈናቀል ምክንያት የሚያጋጥም የመምህራን እጥረት፣ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ከሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች ውጤቶች አንዱ ነው።

የሙቀት መጨመር በትምህርት ላይ ልዩ አደጋዎችን ይጋርጣል። ብዙ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሙቀት በመማር እና በመገንዘብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ እንዳለ ሆኖ፤ አብዛኛዎቹ የዓለም ትምህርት ቤቶች እና መኖሪያ ቤቶች በአሁኑ ጊዜ የሙቀት መጠንን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስ እና የአየር ንብረት ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ቁሳቁሶች፣ ኪነ ሕንፃ እና ቴክኖሎጂዎች የሏቸውም። ይህም ከፍተኛ ሙቀት ባለባቸው አገሮች እና ብዙዎቹ ሀብታም በሆኑ፣ ወቅት እየጠበቀ ከፍተኛ የሙቀት መጠን መጨመር በሚከሰትባቸው አገሮች የሚታይ ዕውነት ነው። የቅርብ ጊዜ ትንበያዎች እንደሚጠቁሙት፣ በሙቀት አማቂ ጋዞች ምርት ከፍተኛ ለውጥ ካልተካሄደ በቀር፣ እስከ አንድ ሦስተኛ የሚሆነው የዓለም ሕዝብ በ2070 ከሞቃታማነታቸው የተነሣ ለሰው ልጆች ተስማሚ አይደሉም በሚባሉ አካባቢዎች ይኖራሉ። በመላው ዓለም ያሉ ተማሪዎች በአደገኛ የሙቀት መጠኖች እና በሌሎች በመጠን፣ በደረጃ እና በድግግሞሻቸው እየተባባሱ እንደሚሄዱ በሚገመቱ ከባድ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ምክንያት ከትምህርት ቤት ከመቅረት እና በቤት ውስጥ ከመቆየት መመሪያዎች ጋር ተላምደዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ እና ብክለት በተማሪዎች፣ በመምህራን እና በትምህርት ቤት ማኅበረሰቦች ላይ ከሚያደርሷቸው ቀጥተኛ ተጽዕኖዎች ባሻገር፣ በኑሮ እና በደህንነት ላይ ቀጥተኛ ያልሆኑ ተጽዕኖዎች ያደርሳሉ። የምግብ ዋስትና እጦት፣ የበሽታ መስፋፋት እና የተባባሰ የኢኮኖሚ አይጨበጤነት መጨመር፣ የመማር መብትን ለማረጋገጥ በሚደረጉ ጥረቶች ላይ አዳዲስ ፈተናዎችን ይፈጥራሉ። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥም እንኳን፣ ተጽዕኖዎቹ ያልተመጣጠኑ መሆናቸውን እናውቃለን።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ በተለይም በጣም ድሆች እና የተገለሉ እንዲሁም በከእጅ ወዳፍ ግብርና ላይ ጥገኛ በሆኑት ዘንድ የአየር ንብረት ለውጥ የሥርዓተ ጾታ አለመመጣጠኖችን ያባብሳል። እጥረት ባለባቸው ቦታዎች ሀብቶች ባልተመጣጠነ መንገድ ይከፋፈላሉ። ሴቶች እና ልጃገረዶች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ሲፈናቀሉ፣ በድህነት ወጥመድ ውስጥ የመውደቅ ዕድላቸው ከፍ ያለ ነው። ትምህርትን ጨምሮ፣ ወደ ቀድሞ ሕይወታቸው የመመለስ እና ሕይወታቸውን ወደነበረበት የመመለስ ዕድላቸው ከወንዶች አቻዎቻቸው ያነሰ ነው። የአየር ንብረት ለውጥ የወንዶችን ፍልሰትም ከፍ በማድረግ፣ በሴቶች ላይ የቤተሰብን ህልውና የማስቀጠልን ጫና ሊጨምር ይችላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የልጃገረዶችን ያለዕድሜ ጋብቻ ማመቻቸትን ቤተሰቦች የራሳቸውን ሕልውና ለማቆየት ከሚኖሯቸው ጥቂት አማራጮች አንዱ ያደርጉታል፤ በዚህ ደግሞ

የልጃገረዶች የወደፊት የትምህርት ተስፋ ያበቃለታል። በዚያው ልክ፣ ሴቶች ለአየር ንብረት ፍትሕ - እንደ እናቶች፣ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ ውሳኔ ሰጪዎች እና የማኅበረሰቡ አባላት እና መሪዎች - በለውጥ ወኪሎችነት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፤ ደግሞም አብዛኛውን ጊዜ በማላመድ እና በመቀነስ ተግባራት ግንባር ቀደም ናቸው።

የአገሬው ተወላጅ ሴቶች የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮችን ለመቀነስም ይሁን እና ለመላመድ የሚያግዝ፣ እንደ ዘላቂ የደን አስተዳደር፣ ውኃ ማቆር፣ ብዝሃ ሕይወት፣ የሰብል ለውጥን መቋቋም፣ ዘር ጥበቃና ምርጫን የመሳሰሉ ዕውቀቶች ቢኖሯቸውም የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ብዙ ጊዜ ችላ ይባላል።

በጣም ብዙ ጊዜ በአየር ንብረት ይበልጥ የሚጎዱት በዓለም አቀፍ ደረጃ፣ በአገራቸው እና በቀያቸው ውስጥ በሚደረጉ ሕዝባዊ ክርክሮች ውስጥ ውክልና የሌላቸው ናቸው። ከዚህ ባለፈ፣ በትምህርት ዘርፍ ትልልቅ የሚባሉት እና ተማሪዎችን፣ መምህራንን እና ቤተሰቦችን ያቀፉት ማኅበረሰቦች ስለአየር ንብረት ለውጥ እና በትምህርት ላይ ስለሚያስከትላቸው ተጽዕኖዎች በሚደረጉ ውይይቶች ላይ በወጉ አለመሳተፋቸው ብዙ ጊዜ በግልጽ ይታያል። ትምህርት ምላሽ የሚሰጥባቸውን መንገዶች በመቅረጽ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና መጫወታቸው በጣም አስፈላጊ ነው። የአሳታፊ ዘዴዎች ፍላጎት ከትምህርት ፖሊሲ እና ዕቅድ ዐልፎ፤ በፕላኔቷ እና በትምህርት ላይ በሰዎች ምክንያት ስለሚከሰቱ ለውጦች በሚደረግ ምርምር እና የዕውቀት ፈጠራ ላይም ይሠራል።

በአሁኑ ጊዜ በትምህርት ከፍተኛ ደረጃ መድረስ እና ማጠናቀቅ ዘላቂ ካልሆኑ ልምምዶች ጋር ይዛመዳል። በዓለም ላይ በጣም የተማሩ ሀገሮች እና ሕዝቦች በጣም የአየር ንብረት ለውጡን እያፋጠኑ ጣሉት ናቸው። ትምህርት ለሰላም፣ ለፍትሕ እና ለሰብአዊ መብቶች መንገዶችን ይጠርጋል ብለን ተስፋ ብናደርግም፣ አሁን መጠበቅ እና በእርግጥም መጠየቅ እየጀመርን ያለነው መንገዶችን እንዲከፍት እና የዘላቂነት አቅሞችን እንዲገነባ ነው። ይህ ሥራም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። የተማረ መሆን ማለት ዘላቂነት የሌለው ኑሮ መኖር ማለት ከሆነ፣ ስለትምህርት ተግባር እና የተማረ ስለመሆንም ምንነት ያሉንን ሐሳቦች እንደገና ማቃናት ይኖርብናል።

## ሰበበ ተስፋ

በጣም ለረጅም ጊዜ ትምህርት ራሱ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ባተኮረ የዘመናዊነት ልማት ዕይታ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ቆይቷል። ነገር ግን በምድር ላይ የአኗኗራችንን መንገድ ሊያስተካክልና እርስበርስ ለሚደጋገፉ ሥርዓቶቿ እና ገደቦቿ ዕውቅና ሊሰጡ በሚችሉ ግንዛቤዎች ላይ ወደተመሠረተ አዲስ ሥነ ምህዳር ተኮር ትምህርት እንደምንሄድ የሚያሳዩ ፍንጮች አሉ። በየሚያዝያ ወር የሚከበረው የምድር ቀን ዓመታዊ በዓል በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ካሉ ታላላቅ ዓለማዊ በዓላት አንዱ ሆኗል። የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ያተኮሩ እንቅስቃሴዎች ሕፃናት ስለ ራሳቸው ወደፊት የሰነቋቸው ራዕዮች መደመጣቸውን እና መተግበራቸውን ለማረጋገጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አነሳስቷል። ተግባራቸው ለተለየ ዓይነት ነገን ለመቀበል የሚደረጉ ዝግጅቶች ናቸው።

> *ተማሪዎች የአየር ንብረት ለውጥን የመላመድ እና የመከላከል አቅሞችን እንዲያዳብሩ ለመርዳት የተሻሻሉ እና የበለጠ ውጤታማ የሆኑ አካሄዶች ያስፈልጉናል።*

ከዚህ ባሻገር፣ ዘላቂ ልማት የትምህርት መሪ ዓላማ እና የሥርዓተ ትምህርት ማደራጃ መርህ ተደርጎ መታየቱ እየጨመረ ነው።

በ2050 ሥር ነቀል ለውጥ ይታይበታል ተብሎ የተገመተው የሰው ልጅ ንቃተ ምህዳር እና ከሕያው ምድር ጋር ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ የመኖር ዘዬአችን ዕውን መሆን መጀመሩን ችላ ማለት አንችልም።

የአካባቢ ትምህርት አስፈላጊነት ለበርካታ ዐሥርት ዓመታት ዕውቅና ተሰጥቶት እና በብዙ የመንግሥት ፖሊሲዎች ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም፤ በፖሊሲ እና በተግባር መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፤ እና ከውጤቶች አንጻር ደግሞ ከዚያም የሰፋ ልዩነት አለ። በአየር ንብረት ለውጥ ትምህርት ውጤታማነት ላይ የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው፣ ትምህርቱ በአብዛኛው የሚያተኩረው በሳይንሳዊ አስተምህሮ ላይ ብቻ

በመሆኑ፤ ተማሪዎችን በውጤታማ ተግባር ለማሳተፍ አስፈላጊ የሆኑትን የተሟሉ ክህሎቶች አያስጨብጥም። ተማሪዎች የአየር ንብረት ለውጥን የመላመድ እና የመከላከል አቅሞችን እንዲያዳብሩ ለመርዳት የተሻሻሉ እና የበለጠ ውጤታማ የሆኑ አካሄዶች ያስፈልጉናል። ስትራቴጂዎቻችንም ጥልቅ ትምህርትን ማጎልበት እና የዜግነት ብቃትን ማዳበር ስለሚቻልባቸው መንገዶች ጊዜው በደረሰበት ዕውቀት እና ስለ የሕይወት እና የሥራ ክህሎቶች ዕድገት በቅርብ በተደረጉ ጥናቶች ላይ መመሥረት አለባቸው።

# የሚያገናኘው እና የሚያለያየው ዲጂታል ቴክኖሎጂ

ያለንበት ታሪካዊ ዘመን በቴክኖሎጂ ለውጥ መፋጠን፣ በሂደት ላይ ባለ ዲጂታል አብዮት እና በባዮቴክኖሎጂ እና በኒውሮሳይንስ ዕመርታ ተለይቶ ይታወቃል። የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች የምንኖርበትን እና የምንማርበትን መንገድ ከመቀየራቸውም በላይ፣ በዚሁ መቀጠላቸው አያጠራጥርም።

ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች፣ መሳሪያዎች እና መድረኮች ሰብአዊ መብቶችን ለመደገፍ፣ ሰብአዊ አቅምን ለማጎልበት እና ለሰላም፣ ለፍትሕ እና ለዘላቂነት የጋራ እርምጃን ለማመቻቸት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። እንደሚታወቀው፣ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መሠረታዊ ዲጂታል ትምህርት እና ተደራሽነት መሠረታዊ መብቶች ሆነዋል፤ እነርሱን ሳይጨብጡ በሲቪክ እና በኢኮኖሚ መስኮች መሳተፍ በጣም አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል። በዓለም አቀፉ ወረርሽኝ ከታዩ አሳዛኝ ዕውነታዎች አንዱ ትምህርት ቤቶች ቢዘጉ እንኳን ኢንተርኔት እና የዲጂታል ችሎታዎች ተደራሽነት ያላቸው ተማሪዎች በርቀት መማር (እና በቀጥታ ከሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ተጠቃሚ ለመሆን) መቻላቸው፤ እንደዚህ ያለ ተደራሽነት እና ችሎታ የሌላቸው ግን መማር ካለመቻላቸው በተጨማሪ፣ ሌሎች ከትምህርት ተቋማት በአካል ያገኟቸው የነበሩ ጥቅሞችንም ማጣታቸው ነው። በዚህ ዲጂታል ልዩነት ምክንያት በዜጎች እና በአገሮች መካከል ያለው የትምህርት ዕድል እና ውጤት ክፍተቶች ጨምረዋል። የመጀመሪያው ሥራ ይህንን መለያያ ዘግቶ፤ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ወሳኝ በሆነው ዲጂታል መሠረተ ትምህርት ተማሪዎች እና መምህራንን ለማብቃት ማሰብ ነው።

ነገር ግን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሰው ልጅን አቅሞች በማጎልበት ዓለምን የበለጠ አሳታፊ እና ዘላቂ ማድረግ የተቀመጠለት ዓላማ እና ማበረታቻ ያስፈልገዋል። ቴክኖሎጂ መብቶቻችን ላይ ጫና የማሳደር እና አቅሞቻችንን የመገደብ፣ ዐልፎ ተርፎም የማኮሰስ ረጅም ታሪክ አለው። አዳዲስ ቴክኖሎጂያዊ ለውጦችን በችኮላ እንደ "ተአምራዊ" መፍትሔዎች መቀበል ብዙም አላዋጣም። የተሻለ ውጤት ያስገኙት እያደጉ የሚሄዱ ማሻሻያዎች ማድረግን የሚሹ ለውጦች እና ሥጋቶቹን ተገንዝቦ እና ቀላል፣ ሁለንታዊ መፍትሔዎች እንደሌሉ ተረድቶ የቴክኖሎጂ ሙከራዎችን የሚያበረታታ ባሕል ናቸው።

ዲጂታሉ - በኮምፒዩተር ለሚደረግ ስርጭት፣ ክምችት እና ትንተና ወደ አኃዛዊ ድርድሮች የተቀየረው ሁሉ - የሰውን እንቅስቃሴ በስፋት አጥለቅልቋል። ዲጂታል ቴክኖሎጂ እንደ አንድ የመሠረተ ልማት (አያያዥ) አካልነቱ እኛን "በማገናኘት" ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ሆኖም፣ በኢንተርኔት ተደራሽነት እና ቴክኖሎጂን ለጋራ እና ግላዊ ዓላማዎች ለመጠቀም ከሚያስፈልጉት ክህሎቶች እና ብቃቶች አኳያ አሁንም "ዲጂታል አለመመጣጠን" አለ።

በዲጂታላይዜሽን እና በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ውስጥ ተፈጥሯዊ ተቃርኖዎች አሉ። ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች አንዳንዶቹ ትልቅ ነጻ የማውጣት አቅም ያመቁ፣ ሌሎች ደግሞ ትልቅ ተፅእኖዎች እና ሥጋቶች የሚያስከትሉ ብዙ ተጠየቃዊ መርሆች አሏቸው። በዚህ ረገድ "ዲጂታል አብዮት" እንደ ግብርና እና ኢንዱስትሪያል አብዮቶች ካሉ ሌሎች ታላላቅ የቴክኖሎጂ ለውጦች አይለይም። ዋና ዋና የጋራ ጥቅሞች አሳሳቢ የአለመመጣጠን እና የማግለል ሁኔታዎችን አስከትለው ነው የሚመጡት። ፈተናው እነዚህን ድብልቅ ውጤቶች ለመቆጣጠር ሰብአዊ መብቶችን እና እኩል ዕድሎችን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ዕድገቶች የመንደፍ ነው።

ቴክኖሎጂ ገለልተኛ አይደለም - ዓለምን እና የሰው ልጅን ግንዛቤ እና ተግባር በሚከፋፍሉ እና በሚቀርጹ መንገዶች የድርጊቶችን እና ውሳኔዎችን አቅጣጫ ሊያስቀይር ይችላል።

የዲጂታል ቴክኖሎጂ አንዳንድ ባሕርያት ዕውቀትን እና መረጃን መጋራትን እንደሚያመቻቹ ሁሉ፣ የተወሰኑት ባሕርያቱ ደግሞ በዕውቀት ስብጥር፣ በባሕላዊ አካታችነት፣ በግልጽነት እና በአእምሯዊ ነጻነት ላይ ከፍተኛ ስጋት ሊፈጥሩ ይችላሉ። በአሁኑ ጊዜ የአልጎሪዝም ውሳኔ አሰጣጥ፣ ፕላትፎርም ኢምፔሪያሊዝም እና የዲጂታል መሠረተ ልማቶች የአስተዳደር ዘይቤዎች ትምህርትን አንድ የጋራ ጥቅም አድርጎ በማዝለቅ ላይ ከባድ ፈተናዎችን ጋርጠዋል። የሚያነሷቸው ጉዳዮች ስለትምህርት፣ በተለይም ስለትምህርት ዲጂታላይዜሽን እና በዐዲስ መንገድነት ሊመጡ ስለሚችሉት ድብልቅ ወይም ቨርቹዋል-ብቻ የትምህርት ቤት ሞዴሎች በሚደረጉ የዘመኑ ሙግቶች ውስጥ ቁልፍ ጉዳዮች ሆነዋል።

ለበርካታ ዐሥርት ዓመታት የትምህርቱ ዓለም ከዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ጋር በተለያዩ፣ ጊዜያዊ እና አዳጊ ግንኙነቶች ውስጥ ተይዞ ቆይቷል። ኮምፒውተሮች በዓለም ዙሪያ ባሉ ብዙ የመማሪያ ክፍሎች እና ቤቶች ውስጥ ጥቅም ላይ ይውላሉ፤ ሞባይል ስልኮች በተለያዩ የትምህርት አውዶች ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥቅም ላይ እየዋሉ የመጡ ሲሆን፣ በተለይ የግል ኮምፒዩተሮች በቀላሉ በማይገኙባቸው በደሃ አካባቢዎች፣ በተለይም ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ወሳኝ ሚና በመጫወት ላይ ናቸው። ኢንተርኔት፣ ኢሜል፣ የሞባይል ዳታ፣ የቪዲዮ እና ኦዲዮ ዥረት እና በርካታ የተራቀቁ የትብብር እና የመማሪያ መሳሪያዎች ሰፊ እና አስደሳች የትምህርት ዕድሎችን እና አቅሞችን ፈጥረዋል።

እነዚህ በመካሄድ ላይ ያሉ ለውጦች ትምህርት በማግኘት መብት ላይ እንዲሁም ከቋንቋ፣ ቅርስ እና ምኞት ጋር በተያያዙ የባሕል መብቶች ላይ ጉልሕ አንድምታ አላቸው። የመረጃ፣ የውሂብ እና የዕውቀት መብቶች እና የዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ መብቶችም ከፍተኛ ተፅዕኖ ደርሶባቸዋል። እንደ የግላዊነት መብት እና የራስን ዓላማ የመከተል መብት ያሉ የሰው ልጅ ክብር መሠረታዊ መርሆች የሚመጡትደግሞ ዲጂታላይዜሽን ያመጣቸውን አስተጓጓይ ለውጦች ስንመለከት ነው።

በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ላይ የሚታዩት ዕድገቶች የመማርን ዋጋ፣ ትምህርት የሚካሄድባቸውን መንገዶች እና የትምህርት ሥርዓቶችን አደረጃጀት እየተለወጡ ነው። ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች መረጃን ለመሰብሰብ እና ለመጠቀም የሚያስፈልጉትን ወጪዎች በእጅጉ ቀንሰዋል። በተጨማሪም፣ በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ ብዙ ሰዎች እንዲሳተፉ አስችለዋል። የዜጎች ሳይንስ እና የክፍት ሳይንስ ፕሮጀክቶች የዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚሰበሰበውን እና የሚተነተነውን የመረጃ መጠን እና በዚህ ሥራ ውስጥ የሚሳተፉትን ሰዎች ቁጥር እና ልዩ ልዩነት ለማስፋት እንዴት እንደሚረዳ የሚያሳዩ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። የመረጃ ማመንጨት፣ ስርጭት እና አጠቃቀም እና መረጃ በዲጂታል ሂደቶች ሊገኝ የመቻሉ ዕውቀት የሳይንስ ዕድገት እና የልዩ ሙያ ተክህኖ የሚዳብርባቸውን፣ እንዲሁም መረጃ እና ዕውቀት በመላው ዓለም ላሉ ሕዝቦች ተደራሽ የሚሆኑባቸውን ወይም የማይሆኑባቸውን መንገዶች ቀይሯል። በተመሳሳይም፣ በኮምፒዩተር የተደገፈ የውሂብ አሰባሰብ እና ትንተና ቀላልነት ሌሎች የማመዛዘን እና ትርጉም የመስጠት አማራጮችን ጋርዷል፤ ይህም ለምሳሌ ከግል ተመክሮ እና ሌሎች አስፈላጊ ቢሆኑም በአኀዝ ለመለካት አስቸጋሪ ከሆኑ መረጃዎች ይልቅ ለአኀዛዊ ውሂብ ስብስቦች ቅድሚያ ይሰጣል።

በኪስ በምንይዘው ተንቀሳቃሽ ስልክ በሺሕ ዓመታት ባደራጀናቸው ታላላቅ የአካል አቢያተ መጻሕፍት ካሉት ክምችቶች ድምር የበለጠ የጽሑፍ እና የግራፊክስ መረጃ ወዲያውኑ ከሚገኝበት ዓለም ጋር እየተላመድን በመምጣታችን፤ ትምህርት ዕውቀትን ከማስፋፋትና ከማስተላለፍ ዐልፎ፣ ይልቁንም ዕውቀት ራሱ የተማሪዎችን አቅም እንደሚያጎለብት እና ያንን ዕውቀትም በኃላፊነት እንደሚጠቀሙበት ማረጋገጥ አለበት። ከቁልፍ የትምህርት ተግዳሮቶች አንዱ ሰዎች በጥቂት ዳበሳዎች ወይም የቁልፍ መጫኖች የሚያገኟቸውን የመረጃ ውቅያኖሶች እንዲገነዘቡ የሚያስችሏቸውን መሳሪያዎች ማስታጠቅ ነው።

## ዲጂታል ዕውቀት እና ተገላዮቹ

ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች የድኅረ ሬነሳንስ ምዕራብ ዓለም መለዮ የሆነውን፣ ብዙ አገር በቀል ዕውቀቶችን ወደ ዳር የገፋውን ውሱን እና ገዢ የዕውቀት መልክ እያንጸባረቁ መጥተዋል። የዓሣ አጥማጆች፣ የመርከበኞች እና የጀብደኞች የአየር ንብረት እና የአሰሳ ዕውቀት ከእሱ የተገኘን ቴክኖሎጂ እና መረጃ በታጠቁ የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች፣ የአየር ንብረት ተመራማሪዎች እና የሜትሮሎጂ ባለሙያዎች ተገልሏል። እንደዚሁም ለምዕተ ዓመታት ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየው የገበሬዎች፣ የአዳኞች፣ የፍራፍሬ ለቃሚዎች እና የአርብቶ አደሮች ዕውቀት በግብርና ሳይንስ ባለሙያዎች፣ በደን ልማት ባለሙያዎች፣ በባለሙያ ደን ጠባቂዎች፣ በመድኃኒት አምራች ኩባንያዎች እና በሥነ ምግብ ባለሙያዎች የቴክኒክ ብቃቶችና ቴክኖሎጂዎች ተገልሏል። ይህ ከቴክኖሎጂ ውጪ ያሉ የዕውቀት መንገዶችን የማግለል አካሄድ የሰው ልጅ ሰው ስለመሆኑ፣ ስለ ተፈጥሮ፣ ስለ አካባቢ እና ስለ ሥነ ፈለክ የነበረውን ሰፊና መልከ ብዙ መዛግብተ ዕውቀት አሳጥቶታል። የትምህርት ባለሙያዎች የሰው ልጅን የባሕል ስብጥር ዲኤንኤ ለያዙት ለእነዚህ ዕውቀቶች ዕውቅና ለመስጠት፣ መልሶ በባለቤትነት ለመያዝ እና ወደ ሥፍራቸው ለመመለስ ብዙ ሊሠሩ ይችላሉ። ሆኖም፣ የሥነ ትምህርት ሳይንስ ራሱ ኢ-መደበኛ፣ አገር በቀል እና በቀላሉ የማይገኙ ዕውቀቶችን ብዙ ጊዜ የሚገፋ ወይም በጥርጣሬ የሚያይ የባለሙያ ብቃት ሆኗል።

በዲጂታላዊነት መግነን ሥጋት ከተጋረጠባቸው ውድ የዕውቀት ዓይነቶች አንዱ ማኅበራዊው ዓለም ራሱ ነው። ምንም እንኳን ስለ መጋራት፣ ትስስር እና ግንኙነቶች አቅሙ ቢኩራራም፣ አብዛኛው በትርፍ የሚመራ ዲጂታል ዕውቀት የሚወሰነው ግለሰብ - ተጠቃሚ፣ ገዢ ወይም ተመልካች - ላይ ነጥሎ በማተኮር ሲሆን፤ በዚህም ብቸኝነትን፣ ራስ ወዳድነትን እና ራስ አፍቃሪነትን በቀላሉ ሊያበረታታ ይችላል። ደግሞም፣ እቅጩን ለመናገር የዲጂታል መሠረተ ትምህርት፣ መሳርያዎቹ፣ መድረኮቹ እና የመተላለፊያ ፍጥነቱ በአገሮች መካከልም ሆነ በአገር ውስጥ በጣም ባልተመጣጠነ ሁኔታ ስለተሰራጩ፤ ለአገር በቀል፣ አነስተኛ ቴክኖሎጂ ለሚፈልጉ፣ ጊዜያዊ እና ሽቀጥ ላልሆኑ የዕውቀት ዓይነቶች ዋጋ ለሚሰጡ እና በእሱም ላይ ለሚተማመኑ ሰዎች ንቀት ይታያል።

በአንድ ወገን ሲታይ፣ “ዲጂታል አለመመጣጠን” የመኖሩ ምክንያት፣ በሥሪቱ ከራሱ ዓለም ውጪ ያሉትን እና የመለኪያ፣ የማከማቻ እና የመተንተኛ ዘዴዎቹን የሚተዉትን ሁሉ ችላ ማለቱ ነው። በዚህ ረገድ፣ አለመመጣጠኑ “ፕላትፎርም ኢምፔሪያሊዝም” (የዲጂታል መድረክ ጫና) ተብሎ ቢጠራ አግባብነት አለው። መፍትሔውም አካታች ዲጂታላይዜሽን ብቻ አይደለም።

> *ትረካዎች የሌሏቸው ቁጥሮች፣ ባሕላዊ አካታችነት የሌለው ትስስር፣ አቅም ያልጎለበተበት መረጃ እና በትምህርት ውስጥ የጠሩ ዓላማዎች የሌሉት ዲጂታል ቴክኖሎጂ በሰው ልጅ ዕድገት ውስጥ አስፈላጊ አይደሉም*

ይልቁንም መፍትሔው ዲጂታሉ ከራሱ ዓለም ውጭ ለተቀረው ጥረት ከሚኖረው አዲስ አድናቆት ጋር ደምሮ የጋራ ጥቅምን ለመደገፍ መዋል የሚችልባቸው መንገዶች ላይ ያተኮረ የበለጠ ውስብስብ፣ ሕዝባዊ ተሳትፎ ነው።

በተለይም በአኀዛዊ፣ ስልተ ቀመራዊ እና “ቴክኒካዊ መፍትሔያዊ” የዕውቀት ብያኔዎች ላይ አተኩረው በ2050 በእጅጉ ተስፋፍተው ሊገኙ የሚችሉትን የዲጂታላዊነት አሉታዊ ገጽታዎች የመቋቋም አቅምን ሁላችንም በጋራ መደገፍ እና ማጎልበት አለብን። ነገር ግን እነዚህን አሉታዊ ዝንባሌዎች መቃወም በራሱ ዲጂታላይዜሽንን መቃወም ማለት አይደለም።

በኮቪድ-19 ጊዜ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ለሕብረተሰብ ጤና እና ለሕዝብ ትምህርት አስፈላጊ መሆናቸውን ዐይተናል፡- ለርቀት ትምህርት፣ ለግንኙነት እና ለክትባት ክትትል፣ ስለ ቫይረሱ አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት እና ለሌሎችም መተኪያ የሌላቸው መሣሪያዎች ነበሩ። ነገር ግን፣ ትረካዎች የሌሏቸው ቁጥሮች፣ ባሕላዊ አካታችነት የሌለው ትስስር፣ አቅም ያልጎለበተበት መረጃ እና በትምህርት ውስጥ የጠሩ ዓላማዎች የሌሉት ዲጂታል ቴክኖሎጂ በሰው ልጅ ዕድገት ውስጥ አስፈላጊ መለኪያዎች ወይም አጋዦችም አይደሉም።

በዲጂታል አብዮት ላይ ብዙ አስተያየቶችን የሚያጅበው የድግስ መንፈስ ቢሆንም፣ ሁኔታው እንዲህ ባሉት ቴክኖሎጂዎች የቀረቡትን ጥልቅ የለውጥ ዕድሎች መጠቀም አለመቻል ተብሎ ሊተረጎምም ይችላል። አሁን ባለው አጠቃቀም፣ ዲጂታል መድረኮች በአብዛኛው ሰፊ የንግድ ዓላማዎችን ከሚያራምዱ ግቦች ጋር የተስማሙ ናቸው። ንድፍ አውጪ ቡድኖቻቸውም ሴቶችን እና የቋንቋ፣ የጎሳ እና የዘር ሕዳጣንን እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ዕድል የተነፈጉ ማኅበረሰቦችን በማግለል፤ በአጠቃላይ የሰው ልጅን የማይወክሉ አድሏዊ እና አሳሳች መረጃዎችን ያሰራጫሉ። ሆኖም ግን፣ በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ የሚገኙት ኃያል የዲጂታል ቴክኖሎጂዎች እጣ ፈንታ መሆን የለበትም። ከሠራንላቸው እና እንዲሆኑም ከምንጠብቅባቸው ከተለመደው የንግድ ቅርጽ ይበልድ የሰዎችን አቅም በማጎልበት እና ሰዎችን በማስተሳሰር ረገድ ብዙ ሊሠሩ ይችላሉ።

ይበልጥ ምቹ የሆነ ዲጂታል አካባቢ ለመፍጠር በአሁኑ ጊዜ አወንታዊ ዕድገቱን እና ሊፈጥር የሚችለውን የጋራ ጥቅም የሚገድቡ መሠረታዊ መሠረተ ልማቶቹን ከንግድ ሞዴሎች እና ከአምባ ገነናዊ የሥልጣን ቁጥጥር ፍላጎቶች ማላቀቅ ያስፈልጋል።

## የተማሪዎችን ቅኝት ማስተካከል

የባዮቴክኖሎጂ እና የኒውሮሳይንስ ዕድገቶች ይሆናሉ ተብለው ሊታሰቡ በማይችሉ መንገዶች የሰውን ልጅ የዘረመል ምህንድስና ነጻ የመልቀቅ አቅም አላቸው። በሰው ልጅ ዘረመል አወቃቀር እና በኒውሮኬሚስትሪ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የቴክኖሎጂ ዕድገቶች ዘላቂ፣ ፍትሐዊ እና ሰላማዊ የወደፊት ሁኔታዎችን እንደሚደግፉ ለማረጋገጥ ትክክለኛ የሥነ ምግባር አስተዳደር እና ሕዝባዊ ውይይት ከጊዜ ወደ ጊዜ አጣዳፊነታቸው እየጨመረ ይመጣል።

አዳዲሶቹ የኒውሮሳይንስ መሳሪያዎች ተመራማሪዎች የሰውን አንጎል ሥራ በባሕርይ መነሻነት ለማወቅ ይሞክሩ የነበረውን አስቀርተው፣ በቀጥታ መረምረው እንዲረዱት አስችለዋቸዋል። ነገር ግን፣ አብዛኞቹ የዘመኑ የአንጎል ቀረጻ ዘዴዎች፣ ከዕውነተኛ ሕይወት የትምህርት አውዶች እና መስተጋብሮች ርቀው በሚገኙ ከፍተኛ ቁጥጥር በሚደረግባቸው ሁኔታዎች ላይ የተመረኮዙ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ዝነኛ ከሆኑት የምርምር ተግባራት አንዱ፣ እንደ ቋንቋ መረዳት ወይም ሒሳባዊ አስተሳሰብ ባሉ በተለያዩ የትምህርት ተግባራት ተለይተው የሚነቁ የአንጎል ክፍሎችን መለየት ነው። ሆኖም፣ እስካሁን ድረስ፣ ምርምሩ የትምህርቱን መመሪያ መንደፍ የሚቻልበትን መንገድ የሚያሳየው በጣም በጥቂቱ ከመሆኑም ባሻገር፣ መመሪያዎቹን መተርጎም የሚያስችል ተጨማሪ ምርምር ያስፈልገዋል።

የሆነ ሆኖ አንጎልን ባነሰ ወይም በላቀ ሁኔታ ለመማር የተመቹ ሁኔታዎች ውስጥ ሊሆን እንደሚችል ሥነ ሕይወታዊ አካል ከሚወስዱ ጥናቶች ጠቃሚ ግንዛቤዎች እየተሰበሰቡ ነው። የአንጎል ጤና በሰውነት አካላዊ ጤና አካልነቱ ያለው ወሳኝነት፣ በመማር እና በአጠቃላይ የሰው ልጅ ደህንነት መካከል ያሉትን ተደጋጋፊነቶች ያጠናክራል - ከዚያም አልፎ በትምህርት መብት እና እንደ የጤና መብት ባሉ ሌሎች መብቶች መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ ያጎላል።

የሰውን አንጎል የነርቭ ፕላስቲክነት (ኒውሮፕላስቲሲቲ) የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች እየበረከቱ ነው - ይህም ማለት አንጎል በሰው ልጅ የሕይወት ዘመን ተደጋጋሚ አካላዊ ለውጦች ያካሂዳል። የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ወሳኝ የመፈጠሪያ ጊዜ ቢሆኑም፣ አሁን ግን አንጎላችን በሁሉም ዕድሜ ብዙ የመማር እና የ"መልሶ ዝርጋታ" (የመታደስ) አቅም እንዳለው እና አንዳንድ ኬሚካሎችም የሰውን አንጎል መልሶ ዝርጋታ የማመቻቸት ሚና እንደሚጫወቱ ተረድተናል፤ ለምሳሌ ህሙማንን ከአእምሮ ጠባሳ እንዲፈወሱ በማስቻል። እነዚህ ግንዛቤዎች ወደፊት በጎልማሶች ትምህርት እና ሥልጠና ወሳኝ ፋይዳ ይኖራቸዋል።

*የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ወሳኝ የመፈጠሪያ ጊዜ ቢሆኑም፣ አሁን ግን አንጎላችን በሁሉም ዕድሜ ብዙ የመማር እና የ"መልሶ ዝርጋታ" (የመታደስ) አቅም እንዳለው ተረድተናል።*

የነርቭ ፕላስቲክነት የሰው ልጅ ከአካባቢያዊ እና ቴክኒካዊ ለውጥ በሚላመድበት ሁኔታም ላይ ወሳኝ አንድምታ አለው። ይህ ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ ሕፃናት ብቻ ሳይሆኑ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች በተጎዳች ፕላኔት ውስጥ መኖርን ለመልመድ ይገደዳሉ። በዓለም ዙሪያ በዲጂታል ስክሪን ላይ በተመሠረተ ንባብ የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ

ሲመጣም ኒውሮፕላስቲክነት የሚጫወተው ሚና ይኖረዋል። በቀላሉ የትኩረት መበታተን፣ ረዘም ላለ ጊዜ በንቃት የመከታተልን አስቸጋሪነት እና የሰንጠረዣዊ፣ የ'ዐየት ዐየት' የንባብ ሁኔታዎች መግነንን በተመለከተ አሳሳቢ ጉዳዮች እየተከሰቱ ነው። አሁን አንጎል የሚቀርቡለትን ተግባራት የማከናወን አቅሙን ለማሻሻል ራሱን በአዲስ መልክ ስለሚሠራበትን መንገድ ያለን ግንዛቤ፣ ከሕትመት ጋር የተያያዘው መስመራዊ ንባብ በራሱ እጅግ ውስብስብ የሆነ የነርቭ ተግባር መሆኑን ያስታውሰናል። ይህ ክስተት ለሰው ልጅ ያለው ባሕላዊ እና ሥነ ሕይወታዊ ጠቀሜታ በበርካታ የሰው ልጅ ባሕሎች ውስጥ ከቃላዊነት ወደ ጽሑፋዊነት የተደረገውን ሽግግር በሚገልጹ ብዙ ምሁራን ተጠቁሟል። በአንድ በኩል፣ እኛ ሰዎች ራሳችንን “ሀክ ስናደርግ” (ስንቃኝ) ለረጅም ጊዜ ቆይተናል። ብዙዎች አሁን ከፊትለፊታችን ካሉት አዳዲስ የንባብ ቴክኖሎጂዎች ጋር መላመድ እንደምንችል በትክክል ይናገራሉ። ለነገው ትምህርት ምርጫው ዲጂታል ወይም የህትመት ንባብ ብቻ ተብሎ መቅረብ የለበትም - ይልቁንም የማንበብና መጻፍን ክህሎት ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት መምህራን ተማሪዎቻቸው ከመስመራዊ እና ከሰንጠረዣዊ ንባብ ጋር መተዋወቃቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ህትመት እና ዲጂታል ተመጋጋቢ እና አስፈላጊ የምንባብ ቅርጾች ተደርገው መታየት አለባቸው።

በኒውሮሳይንስ እና ባዮቴክኖሎጂ ውስጥ እየታዩ ያሉትን ዕድገቶች በአግባቡ መምራት በክፍት መረጃ፣ ክፍት ሳይንስ እና የትምህርት መብት የግንኙነት፣ የውሂብ፣ የመረጃ እና የግለጉዳይ ጥበቃ መብቶችን ሊያካትት ይገባል በሚለው ሰፊ መረዳት ይወሰናል።

# ዲሞራሲያዊ መንሸራተት እና አዳጊው ዋልተኝነት

ምክንያታዊ አስተሳሰብ፣ ኢኖቬሽን እና የግለሰባዊ እና የጋራ ዓላማዎች ዕውን መሆን ሰብአዊ መብቶች በተከበሩባቸው አሳታፊ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታዎች ውስጥ ያብባሉ። ሆኖም፣ ባለፈው ዐሥርት ዓመት በዓለም ላይ ጉልሕ የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ወደ ኋላ መንሸራተት እና በማንነት ላይ የተመሠረተ አግላይ ሕዝበኝነት እያየለ መምጣት ታይቷል። እንዲህ ዓይነቱ ስሜት በግሎባላይዜሽን ዓለም ሥርዓት ወደ ኋላ በተተዉት ሰዎች አለመደሰት አማካይነት የሚዳብር ነው - ሥርዓቱ ግድግዳዎች ሲፈርሱ፣ ድንበሮች ሲጠፉ፣ እና የሰዎች፣ የሸቀጦች እና ሐሳቦች እንቅስቃሴ በዘመናዊው ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መንገድ ሲስፋፋ ታይቶበታል። በሕዝብ ፍልሰት እና በግጭት፣ በኢኮኖሚ ችግር እና በአየር ንብረት ለውጥ ግፊቶች ሳቢያ በሚከሰት መፈናቀል የበለጠ ተቀጣጥሏል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲሞክራሲን ሁኔታ የሚመረምሩ እና የሚከታተሉ ድርጅቶች የእነዚህን ለውጦች ተጽዕኖ በተለያዩ መንገዶች ገልፀውታል። ዘ ኢኮኖሚስት የዜና መጽሔት ከሙሉ ዴሞክራሲ እንከን ወደበዛበት የዲሞክራሲ ሥርዓት ሽግግር መደረጉን አመልክቷል። ፍሪደም ሃውስ ከነጻ ወደ ከፊል ነጻ የፖለቲካ ሥርዓቶች የተደረገውን ለውጥ ሲመለከት፤ ቪ.ዴም ደግሞ ከየምርጫ ዲሞክራሲ ወደ ምርጫ አውቶክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግሮች መደረጋቸውን ይገልፃል። የአሰያየሙን ልዩነት ብንተወው፣ ብዙዎች የሚጋሩት ዴሞክራሲ ከቅርብ ጊዜ በፊት ከነበረበት ሁኔታ ዛሬ የበለጠ ደካማ መምሰሉን ነው።

መገለጫዎቹም ከሕዝበኛ መሪዎች መነሣት እና በብሔርተኝነት ስም የተወላጅነት ስሜት መግነን አንሥቶ፣ ሆን ብሎ “አሳሳች ዜናዎች”ን በቅፅበት የማሰራጨት አቅም እስካለው የማኅበራዊ ሚዲያ ኃይል፣ እንዲሁም ማኅበራዊ ባሕርይ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር እስከሚያስችል መረጃ ማዛባት እና ለመልእክቶች ጥቃቅን ዒላማዎችን እስከማበጀት የሚደርሱ ናቸው። የልሂቃን የተጋነነ ግብዝነት እና ሰው በዓለም ላይ ስላለው ቦታ የሚፈጠርበት እና እየተባባሰ ስለሚሄደው የወደፊቱ ዓለም አጠራጣሪነት እያየለ የሚመጣው ጭንቀት የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ።

ብዙ የዴሞክራሲ ተቋማት ጥቃት እየተፈጸመባቸው ዓለም እየተከፋፈለ እና እየተቃረነ ይመስላል። ተቋማቱ ዲሞክራሲ የገባውን ቃል አላስገኘም በሚሉ እና እንዲያውም ከልክ ዐልፏል ብለው በሚሰማቸው ሰዎች ይሞገታሉ። የበላይነት አስተሳሰቦች እና ትምክህተኝነቶች ገጸ ብዙ ማንነቶችን እንዲሁም ውይይትን እና መረዳትን በሚጎዳ ልክ ጉልበት እያገኙ ነው። የዜግነት፣ ማኅበራዊ፣ ሰብአዊ፣ አካባቢያዊ መብቶች ፍርሐቶችን፣ ጭፍን ጥላቻን እና አድሎዎችን በማነሣሣት በሚገዙ አምባገነን መንግሥታት እየተፈናቀሉ ወይም እየተጋረዱ ነው።

የሕዝባዊ ንግግሮች መክሰም እና ሐሳብን በነጻነት መግለጽ ላይ የሚፈጸሙ ጥሰቶች ማየል፤ በአካባቢ፣ በአገር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰብአዊ መብቶች፣ በዜግነት እና በዜጎች ተሳትፎ ውስጥ ሥሩ በተተከለው በትምህርት ላይ ትልቅ ተጽዕኖዎችን ያስከትላል።

ይህ በእንዲህ እንዳለም፣ በብዙ አካባቢዎች ዜጎችን የማስተባበር ቅስቀሳ እና ንቅናቄ እየጨመረ ነው። እነዚህ የአፀፋ ንቅናቄዎች ተቋቁሞሽን እና የአሳታፊ ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካን አዳዲስ መጻዒ ሁኔታዎች ያመለክታሉ። እነዚህ ንቅናቄዎች ብዙ ጊዜ በወጣቶች ከሚመሩት የሥነ ምህዳር ንቅናቄዎች፣ አነስተኛ ቁጥርና የዕድገት ደረጃ ያላቸው ማኅበረሰቦችን መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶችን ከሚገፍፉ ኀዥዎች ጋር እስከሚደረጉ የዜጎች ትግሎች ይደርሳሉ። በመላው ዓለም ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲመለሱ እና የሕግ የበላይነት እንዲከበር የሚቀርቡ ጥያቄዎችንም ያካትታሉ። ይህ ቅስቀሳ እንደ “ብላክ ላይቭስ ማተር” (“የጥቁር ሕዝቦች ሕይወት ዋጋ አለው”) ያሉትን ጸረ ዘረኝነት ንቅናቄዎች፣ እንደ “#ሚቱ” (“እኔም/እኔንም ይመለከተኛል”) ያሉትን በሥርዓተ ጾታ ላይ የተመሠረተ ትንኮሳ እና ጥቃትን የሚገዳደሩ እንቅስቃሴዎች፣ እንዲሁም ሥርዓተ ትምህርትን እና የትምህርት ተቋማትን ከቅኝ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት የሚቀርቡ ጥሪዎችን ያጠቃልላል።

*የሕዝባዊ ንግግሮች መክሰም እና ሐሳብን በነጻነት መግለጽ ላይ የሚፈጸሙ ጥሰቶች ማየል በትምህርት ላይ ትልቅ ተጽዕኖዎችን ያስከትላል።*

የእነዚህ እንቅስቃሴዎች ማተኮሪያ ጉዳዮች በወደፊት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። ትምህርት ጠንካራ ዲሞክራሲያዊ ዜግነትን፣ የመወያያ ቦታዎችን፣ አሳታፊ ሂደቶችን፣ የትብብር ተግባራትን፣ በመተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ ግንኙነቶችን እና የጋራ ነገዎችን በማበረታታት እና በማረጋገጥ ረገድ የሚጫወተው ሚና አለው።

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ የተቀሰቀሰው ዓለም አቀፍ የጤና ቀውስ በብዙ ማኅበረሰባዊ ምሳሌዎች በታየው የአጋርነት መነቃቃት አማካይነት ከዚህ ለአብዛኛው ሕዝባዊ ተሳትፎ እና ንቅናቄ መነሣሻ ግፊትን እና ቁርጠኝነትን ሰጥቷል። ብዙ መንግሥታት ሰዎች በራሳቸው በሚወስዱት ኃላፊነት እና በጋራ መተሳሰብ አማካይነት የሕብረተሰቡን እገዛ ካላገኙ በቀር የማኅበረሰብ ጤና እና ሌሎች ድንገተኛ ችግሮችን ለብቻቸው መፍታት እንደማይችሉ ተገንዝበዋል። የማኅበረሰብ ሚና ተመልሶ ዕውቅና አግኝቷል።

በዚያው ልክ ግን፣ ወረርሽኙ የዲሞክራሲን የወደኋላ ሽርተቴ አባብሷል። የአስፈጻሚ ኃይሎችን መስፋፋት፣ የክትትል ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን መጨመር፣ በሕዝባዊ ስብሰባዎች እና በነጻነት መንቀሳቀስ ላይ የተጣሉ እገዳዎችን፣ በሲቪል አካባቢዎች የወታደራዊ ኃይሎችን መሰማራት፣ የምርጫ መርሐ ግብር መስተጓጎልን እና ሌሎች ተፅዕኖዎችንም ዐይተናል። የሕዝብ ጤናን ለማረጋገጥ ምንም ዓይነት ምክንያት ቢኖር፤ በሕዝብ ድንገተኛ ችግሮች ወቅት የሚከሰተው ሁኔታ የመንግሥታዊ አስተዳደር መገለጫ መሆኑን ማስታወስ ይጠቅማል።

የእነዚህ የፖለቲካ ለውጦች ያልታወቁ አቅጣጫዎች ቢያንስ ለበርካታ ዐሥርት ዓመታት አብረውን ይቆያሉ፤ ይህም በትምህርት ላይ ብዙ አንድምታዎች አሉት፤ ምክንያቱም አንድም መናጋቱ የትምህርት አጀንዳዎችን መልክ ያስቀይራል፤ አንድም ደግሞ በትምህርት ተደራሽነት፣ በሥርዓተ ትምህርት እና በሥነ ትምህርት ላይ የሚከሰቱት ነገሮች ደግሞ በመልሱ፣ በዓለም ዙሪያ የሚደረጉ ፖለቲካዊ ለውጦችን መልክ ይቀይራሉ።

ዓለም በከፊል በማኅበራዊ ድረገጾች አካሄድ ምክንያት እየቀነሰ በመጣ አነስተኛ ትዕግስት የፖለቲካ ተሳትፎ ያለው ሕዝብ ከሚፈጠርበት መንገድ አኳያ ዓለም አዲስ ምዕራፍ ላይ ነች። እርስበርሳችን መደማመጥ ሲያቅተን፣ ሕዝባ ሕይወት በእጅጉ ይጋረዳል። ሌሎችን መንከባከብ እና መከባበር ተግባራዊ ሊደረጉ እና ሊጠናከሩ ይገባል - በዚህ ረገድ ትምህርት በደንብ ሊያግዝ ይችላል፤ የተማሪዎችን የነቃ ዜግነት እና የዲሞክራሲ ተሳትፎ አቅም በመገንባትም ጭምር።

# ያልተረጋገጠው የሥራ መጻዒ ሁኔታ

ወደፊት ትምህርት ግለሰቦችን፣ ማኅበረሰቦችን እና ሕብረተሰቦችን ትርጉም ላለው ሥራ እና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና ለማብቃት በምን መልኩ የተሻለ ድጋፍ ይሰጣል?

ሰውን ያማከለ የወደፊት ሥራን በማረጋገጥ ዙሪያ የአይኤልኦ ዓለም አቀፍ መጻኢ የሥራ ዕድል ኮሚሽን በ2019 ያወጣቸው የይሁንታ ሐሳቦች ጠቃሚ መነሻ ናቸው። ይህ አጀንዳ ሰዎችን እና ሥራዎቻቸውን በኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፖሊሲ እና በምርጥ የሥራ ተመክሮ ማዕከል ላይ ያስቀምጣቸዋል።

ዛሬ ሥራ አጥነት ተቀባይነት በሌለው ደረጃ ከፍተኛ ነው። በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በአደገኛ ኢመደበኛ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። ከ300 ሚሊዮን በላይ ደመወዝተኛ ሠራተኞች አሁንም በከፋ ድህነት ውስጥ ይኖራሉ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወንዶች፣ ሴቶች እና ሕፃናት በዘመናዊ ባርነት ውስጥ ተይዘው ይገኛሉ። የሥራ ቦታ ደህንነት እና ትንኮሳ ጉዳይ አሁንም መሻሻል አለበት። በአብዛኛዎቹ የዓለም ክፍሎች ከሰው ኃይል ተሳትፎ እና ለወንዶች እና ለሴቶች ከሚከፈል ካሳ አንጻር አሁንም ትልቅ የሥርዓተ ጾታ ክፍተቶች አሉ።

ከ1990 ጀምሮ በሁሉም የዓለም ክልሎች እና የገቢ ቅንፎች የሠራተኛ ኃይል ተሳትፎ መጠን ቀስ በቀስ እየቀነሰ ነው። ይህ በተለይ በ1990 ከነበረው 50% ወደ 33% ባሽቆለቆለው የወጣቶች (15-24) ተሳትፎ በተግባር ታይቷል። የዚህ ከፊል ምክንያቱ ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ እና በከፍተኛ ትምህርት የሚደረስባቸው እርከኖች መሻሻል ሊሆን ቢችልም፤ ዛሬም ከአምስት ወጣቶች አንዳቸው በሥራ፣ በትምህርት እና በሥልጠና ላይ አይገኙም። እንዲሁም ከአራት ወጣቶች አንዳቸው በዝቅተኛ ሥራ ላይ ነው የተሰማሩት።

በሥራ ገበያ ተሳትፎ እና ዕድሎች ውስጥ በሥርዓተ ጾታ ላይ የተመሠረቱ ጉልሕ ልዩነቶች አሁንም ቀጥለዋል። ላለፉት በርካታ ዐሥርት ዓመታት የሴቶች የሥራ ገበያ ተሳትፎ በየጊዜው እየጨመረ በመምጣቱ፣ የሥርዓተ ጾታ ልዩነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠበበ ቢመጣም፤ ከዝቅተኛ ምጣኔ በመነሣቱ ልዩነቶቹ እስካሁንም በአሳሳቢ ደረጃ በጣም ሰፊ ናቸው። በ2019 የሠራተኛ ኃይል ተሳትፎ ለሴቶች ከ50% በታች ሲሆን፣ ለወንዶች ደግሞ ወደ 75% ይጠጋ ነበር። በከፍተኛ መጠን ለትምህርት መመዝገባቸው በሴቶች የሥራ ተሳትፎ ምጣኔ ላይ ተጽዕኖ አለው። የተሻለ የኑሮ ደረጃ ሴቶች በፈቃደኝነት ከሥራ ገበያ እንዲወጡ ሊያበረታታቸው ይችላል። ነገር ግን፣ ብዙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ሴቶች የሚያገኙት በጥራት ዝቅተኛውን ሥራ ነው። ክፍያ የማያስገኝ እና የቤት ውስጥ ሥራ ሴቶች ደመወዝ በሚያከፍሏቸው የሥራ ገበያዎች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ መጠን እንዳይጨምር የሚያግዱ ቋሚ እንቅፋቶች ናቸው።

ሰፊ የሥርዓተ ጾታ ልዩነቶች አሁንም ስለመኖራቸው አንዱ ማሳያ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው የሙያ መለያየት ቀጣይነት ነው። በአጠቃላይ፣ በመደበኛነት 'ሥራ' ተብሎ የሚወሰደው እና እንደ 'ምርታማነት' የሚለካው እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ሥራ እንዳይታይ ይጋርደዋል። ይህ ለሕብረተሰቡ ወሳኝ የሆነውን፣ ነገር ግን ብዙ ጊዜ የሴት ተደርጎ የሚቆጠረውን እና በተለይ በቤት ውስጥ የሚሠራ ሥራን ይጨምራል። ቤተሰብ መንከባከብ፣ ልጅ ማሳደግ፣ ሕመምተኞችን ማስታመም፣ ጽዳት፣ ምግብ ማብሰል እና ለሌሎች አካላዊ እና ስሜታዊ ድጋፍ መስጠት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ይህ ሥራ መደበኛ ሲሆን፤ እነዚህ ሙያዎች ብዙውን ጊዜ ዝቅተኛ ክፍያ የሚመደብላቸው እና ዝቅተኛ ደረጃ የሚሰጣቸው ናቸው።

የሥራ ጥራትን ማሻሻል እና ግለሰቦች የኢኮኖሚ ደኅንነታቸውን በሚፈልጉት መንገድ የማረጋገጥ ምርጫ እና ነጻነትን ማስፋት፣ በተለይ በኮቪድ-19 ምክንያት በተፈጠሩት መናጋቶች እና እንቅፋቶች የተነሣ ለተወሰነ ጊዜ ዓለም አቀፍ ፈተና ሆኖ ሊቆይ ይችላል። ይህ ዓለም አቀፋዊ ቀውስ ገና እስካሁንም ጥርት ብለው ባልታወቁ መንገዶች የሥራውን ዓለም አናግቷል፤ ስለዚህም ብዙዎች ገና አስከፊ የረጅም ጊዜ መዘዝ እንደሚያከትል ይጠብቃሉ። የሥራ ቦታ መዘጋት እና የሥራ ሰዓት ኪሳራ በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ጎድቷል። አሁን ባለው የዓለም ሥራ ድርጅት ግምት እስከ 150 ሚሊዮን የሚደርሱ ሥራዎች ሳይጠፉ አልቀሩም።

ኮቪድ-19 የሥርዓተ ጾታ ክፍተቱን ለማጥበብ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሥርዓተ ጾታ አለመመጣጠን ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀልበስ በሚደረገው ትግል ላይ ትልቅ እንቅፋት ፈጥሯል። መጀመሪያ ላይ ከቤት ወደመሥራት የተደረገው ሽግግር ለባለሙያ ሴቶች ጠቃሚ ሊሆን ይችላል የሚል ተስፋ የነበረ ቢሆንም፣ በትክክል የሆነው ግን ተቃራኒው ነው። በሁሉም ክፍላተ ዓለማት እና በአብዛኛዎቹ አገሮች፣ በየትኛውም የገቢ ደረጃ የሚገኙ ሴቶች ሥራቸውን በማጣት ረገድ ከወንዶች የበለጠ ተጎድተዋል።

*ኮቪድ-19 የሥርዓተ ጾታ ክፍተቱን ለማጥበብ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሥርዓተ ጾታ አለመመጣጠን ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀልበስ በሚደረገው ትግል ላይ ትልቅ እንቅፋት ፈጥሯል።*

የወደፊቱን ሥራ አቅርበው ሲመለከቱት ፈታኝ ምስል ወደ ዕይታ ይመጣል። እንደ አርቴፊሻል አስተውሎት፣ አውቶሜሽን እና ሮቦቲክስ ያሉ የቴክኖሎጂ ዕድገቶች አዳዲስ ሥራዎች ቢፈጥሩም፣ በዚያው ልክ ብዙዎችን ከሥራ ያፈናቅላሉ፤ ደግሞም በዚህ ሂደት ሥራቸውን የሚያጡ ሰዎች አዳዲስ ዕድሎችን ለመጠቀም የሚኖራቸው ዝግጁነት በጣም ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል።

ኢኮኖሚዎቻችንን ወደ አረንጓዴ ኢኮኖሚዎችነት ለመቀየር ዘላቂነት ያላቸውን አሠራሮች እና ከብክለት ንፁሕ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀማችን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሥራዎችን ይፈጥራል፤ ሆኖም ሀገራት ከፍተኛ ካርበን እና የተፈጥሮ ሀብት ይጠቀሙ የነበሩ ኢንዱስትሪዎቻቸውን እየቀነሱ ስለሚሄዱ፣ ሌሎች ሥራዎች ይጠፋሉ። ፕላትፎርም ኢኮኖሚ የአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የሥራ ልምዶችን መልሶ ሊፈጥር እና የወደፊት ትውልዶችን "የዲጂታል ቀን ሠራተኞች" አድርጎ ሊሠራቸው ይችላል። ዛሬ የካበቱ ክህሎቶች የነገው ሥራ ከሚፈልጋቸው ችሎታዎች ጋር ያለመጣጣም ዕድላቸው ሰፊ በመሆኑ፣ ብዙዎች ጊዜ ያለፈባቸው ይሆናሉ። በእነዚህ ለውጦች ምክንያት የሥራ ገበያ ሽግግሩ በቀጥታ ለሚነካቸው ወገኖች የሚሰጠውን ድጋፍ ለማሳደግ፣ በትምህርት እና ሥልጠና ሥርዓቶች ላይ ተጨማሪ ፍላጎቶች ይፈጠራሉ።.

## ትምህርት፣ ክህሎት ማዳበር፣ እና ከትምህርት ቤት ወደ ሥራ ሽግግሮች

እነዚህ ተደጋጋሚ ተግዳሮቶች እና የቅርብ ጊዜ እንቅፋቶች ሁሉ በትምህርት እና ሥልጠና ዓለም ላይ አንድምታ አላቸው። ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች የትምህርት ተቋማት ግለሰቦች ነጻነት እና ክብራቸው ተጠብቆ፣ ኢኮኖሚያዊ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ እንዲሠሩ በማዘጋጀት እና በመደገፍ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ይህ ስኬትን እና እርካታ የሚያስገኘው በመደበኛው ኢኮኖሚ ሆነ በኢመደበኛው ኢኮኖሚ፣ ወይም ለምሳሌ፣ በቤት ውስጥ ሥራ ሆነ በእንክብካቤ ሥራ እና በሌሎች የሥራ ዓይነቶች ውስጥ፣ በየትኛውም መስክ ቢሆን፤ ትምህርት እኩል የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ዕድል እንዲኖር እና ሰዎች ትርጉም ባላቸው ሙያዎች እና ሥራዎች እንዲሰማሩ የማስቻል ሚና እንዲጫወት እንጠብቃለን።

ያም ሆኖ፣ ትምህርት ሌሎች የፖሊሲ መስኮች የፈጠሯቸው - እየፈጠሯቸው ያሉት - ጉድለቶች ያስከተሏቸውን የሥራ ጥራት ማሽቆልቆል እና እንዲሁም ሰፊ ሥራ አጥነት ሊያካክስ አይችልም። ትምህርት የጥምሩ አንዱ አካል ቢሆንም፤ ነገር ግን የማክሮ ኢኮኖሚ፣ የኢንዱስትሪ እና የሥራ ስምሪት ፖሊሲ በተለይ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ጥራት ያለው ሥራ በመፍጠር ረገድ የበለጠ ውጤታማ መሳሪያዎች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ የትምህርት እርከን ማጠናቀቅ እና የወጣቶች ሥራ አጥነት በአንድ ላይ ይጨምራል። ከአቅም በታች በሆነ ሥራ መሰማራት፣ ከምኞቶች፣ ክህሎቶች እና አቅም ጋር የሚዛመድ ሥራ ማግኘት አለመቻል በበለፀጉ የዓለም ሀገራት ውስጥ ባሉ የዩኒቨርስቲ ምሩቃንን ጭምር የሚያጋጥም፣ ቀጣይ እና እያደገ ያለ ዓለማቀፍ ችግር ነው። ይህ አለመጣጣም ተቀጣጣይነት አለው፡- ማኅበራዊ ሳይንቲስቶች በከፍተኛ ደረጃ የተማረ ሕዝብ ክህሎቱን እና ብቃቱን በሚመጥን ሥራ ላይ ማዋል ሳይችል መቅረቱ ወደ ቅሬታ፣ ውጥረት እና አንዳንዴም ወደ ፖለቲካዊ እና የእርስበርስ ግጭት ያመራል።

ከትምህርት ቤት ወደ ሥራ በሚደረግ ሽግግር፣ የሚያጋጥመውን የክህሎት አለመጣጣም አቃልሎ ማየት አይቻልም። ትምህርት ከሥራው ዓለም ጋር የተዛመደ መሆን አለበት። ወጣቶች ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ወደ ሥራ ገበያ እንዲገቡ እና እንደ አቅማቸው ለማኅበረሰባቸው እና ለሕብረተሰባቸው አስተዋፅኦ ማድረግ እንዲችሉ ጠንካራ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ተማሪዎች ከሥራ ዓለም እና ከተለያዩ የሥራ ዘርፎች ጋር እንዲተዋወቁ የኢንዱስትሪ እና የማኅበረሰብ መሪዎች በተሻለ ሁኔታ ወደ ሁለተኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ትምህርት እንዲመጡ ማድረግ ይገባል። የትምህርት ተቋማት የሙያ ምክር መስጠት ብቻ ሳይሆን፤ ለመምህራን በሙያቸው እና በሥራው ዓለም ላይ ካሉ ለውጦች ጋር እንዲጣጣሙ ለማድረግ የሚያስችሉ የዕድሜ ልክ የትምህርት ዕድሎች ድጋፍ መስጠት አለባቸው። በሁለተኛ ደረጃም ሆነ በከፍተኛ ትምህርት የሚሠጠው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥራ ተኮር እንዲሆን ከሚያስችሉ የመማር ዕድሎች ጋር መቀናጀት አለበት። ይህ ለተማሪዎች የገሃዱን ዓለም ተመክሮ ከማስተዋወቁ ባሻገር፣ የትምህርት እና ሥልጠናን ጥራት እና ተገቢነት ሊያሻሽል ይችላል። የመማሪያ መንገዶች የሙያ ትምህርት አማራጮችን ማመቻቸት ያለባቸው የወደፊት የመማር ዕድሎችን ሳይዘጉ መሆኑን ማረጋገጥ ያፈልጋል። ትምህርት በራሱ የሠራተኛ ኃይል ፍላጎትን አያመጣም። መዋቅራዊ የሥራ አጥነት ችግሮችንም መፍታት አይችልም። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እና በክህሎት ልማት ላይ ተጽዕኖ ያሳደረው "የአቅርቦት ጎን" ማሻሻያ በራሱ ሥራን ወይም የሥራ ዕድገትን አይፈጥርም።

ነገር ግን ትምህርት ሰዎች ፈጠራን እንዲፈጥሩ፣ ዕውቀታቸውን እንዲተገብሩ፣ ችግሮችን እንዲፈቱ እና ውስብስብ ተግባራትን እንዲፈጽሙ አድርጎ መቅረጽ ይችላል። በተለይም በከፍተኛዎቹ ደረጃዎች ትምህርት ቤት የተራቀቀ ዕውቀት እና የግንዛቤ ክህሎት ያላቸውን ሰዎች ያፈራል፤ እንዲሁም ዕውቀታቸውን እና ክህሎቶቻቸውን ለመጠቀም የሚያስችላቸው ዕድል ያገኛሉ የሚል ተስፋንም ያጭራል። ትምህርት ለሥራ ወይም የሥራ ፈጠራ ክህሎቶችን ለማዳበር የሚል ነጠላ ግብ ላይ ያኮረ ጥረት ቦታውን የሣተ ነው። ትምህርት ሰዎች ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው እና ለማኅበረሰባቸው የረዥም ጊዜ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን እንዲፈጥሩ በሚያስችል መልኩ መቀረጽ አለበት።

> *ትምህርት ሰዎች ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው እና ለማኅበረሰባቸው የረዥም ጊዜ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን እንዲፈጥሩ በሚያስችል መልኩ መቀረጽ አለበት።*

ከቴክኖሎጂ ጋር ተስማምቶ መኖርን መማር ለወደፊቱ ሥራ በጣም አስፈላጊ ነው። ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ እና ከካርቦን ለፀዳ ነገ ለመዘጋጀት ከሚያስፈልጉ ምርጥ ስልቶች ውስጥ አንዱ የብቃት ማረጋገጫዎች፣ መርሐ ግብሮች እና ሥርዓተ ትምህርቶች አዲስ በሚመጡ ሙያዎች እና ዘርፎች ወይም ወደ ካርቦን ቀናሽ ኢኮኖሚ እየተሸጋገሩ ባሉ ዘርፎች "አረንጓዴ ክህሎት"ን ማካተታቸውን ማረጋገጥ ነው። ሌላው ወሳኝ እርምጃ፣ የመማሪያ አካባቢያችንን ሙሉ በሙሉ አረንጓዴ ማድረግ ነው። ተማሪዎችን ከካርቦን ነጻ የትምህርት ሥርዓትን በመፍጠር ሂደት ግንባር ቀደም እንዲሆኑ ማበረታታት በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ውስጥ ትርጉም ያለው ሥራ እንዲሠሩ ለማዘጋጀት አንዱ ተስፋ ሰጪ ስትራቴጂ ነው።

## በለውጥ ላይ ያሉት የትምህርት ማስረጃዎች ወደፊት

የትምህርት ማስረጃዎች የትምህርት እና የሥራ ገበያዎች መገናኛ ላይ ናቸው። የትምህርት ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎች እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሐ ግብሮች ቁልፍ ሚና የተማሪዎቻቸውን የክህሎት፣ የብቃት እና የዕውቀት አቅም ማረጋገጥ ነው። መደበኛ ባልሆኑ እና በኢመደበኛ የትምህርት አውዶችም ቢሆን ግለሰቦች ትምህርታቸው ዕውቅና እና ማረጋገጫ እንዲያገኙ የመጠየቅ መሠረታዊ መብት እንዳላቸው ግንዛቤያቸው እየጨመረ መጥቷል።

ማረጋገጫው ላይ ብቻ ማተኮር በራሱ በቂ አይደለም። ስለ ውጤቶቹ ማሰብ አስፈላጊ ቢሆንም፣ የትምህርት ዋነኛ አካል የሆኑት ማኅበራዊ ሂደቶች እና መስተጋብሮች መዘንጋት የለባቸውም። ማረጋገጫዎች ምንጊዜም ቢሆን በዋነኝነት በማኅበራዊ እምነት ላይ የተመሠረቱ የሰው አቅም እና ችሎታ "ወኪሎች" ናቸው፤ በትምህርት ዓላማዎች እና ትግበራዎች ላይ መተማመን ያለውን ዋጋ የሚያሳዩ ማስረጃዎች።

የሙያ እና የሥራ መስክ ለውጦች በጣም እየተለመዱ እና እየቀለሉ ሲመጡ፣ ሰዎች በተዛማጅ ሥራዎች መካከል ተንቀሳቅሰው በተሻለ ሁኔታ እንዲሠሩ ለማድረግ ተጨማሪ ጥናት ያስፈልጋል። መንግሥታት፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ አሠሪዎች እና ሕብረተሰቡ ማኅበረሰባቸው ተንከባክቦ የሚያዳብራቸውን የሙያ ዓይነቶችና ሥራዎችን ለመለየት በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። የሥራ ገበያ ለውጦችን የሚከታተሉ እና የሚተነትኑ ሥርዓቶች እና የሙያ እና የሥራ ቦታዎች ተለዋዋጭ የክህሎት ፍላጎቶች እየተወሳሰቡ መጥተዋል፤ ስለዚህ የትምህርት እና የሥልጠና ሥርዓቶች መርሐግብሮቻቸውን በማስተካከል ለሥራው ዓለም ተገቢ የትምህርት አማራጮችን ለማቅረብ ይህንን መረጃ በተሻለ ሁኔታ መጠቀም አለባቸው። ተቋማት ወደ የብቃት ማረጋገጥ፣ የሥርዓተ ትምህርት እና የመርሐ ግብር አነዳደፍ ዘዴዎቻቸውን ሲቀርጹ የበለጠ ውጫዊ ዕይታ ሊኖራቸው እና ተራማጅ ሊሆኑ ይገባል።

## የሥራ ገበያዎች መዋቅራዊ ለውጥ

ከቴክኖሎጂ እና የአካባቢ ለውጥ ጎን ለጎን የተለያዩ መዋቅራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የሥራ ገበያን ቅርጽ በመቀየር ላይ ናቸው። የ"ጊግ"፣ የፍሪላንስ እና የኮንትራት ኢኮኖሚዎችን ዕድገት እና በቢሊዮን ለሚቆጠሩ የዓለም ሕዝቦች ኢ-መደበኛው ኢኮኖሚ ላለው ፋይዳ ሊያንሰብት የሚችል የወደፊት ተስፋ እያየን ነው። እንደነዚህ ያሉት አዳዲስ የሥራ ስምሪት ሞዴሎች እያደገ በመጣው ሠራተኞችን አዲስ ክህሎት የማስጨበጥ እና ያሏቸውን ክህሎቶች የማሳደግ ፍላጎት ላይ ተጨማሪ ጫና ይፈጥራሉ። የትምህርት እና የሥልጠና ሥርዓቶች የበለጠ ተለዋዋጭ የመማር አማራጮችን መስጠታቸውን መቀጠል ይኖርባቸዋል፤ በዚህም ምክንያት ተቋማት እና መርሐ ግብሮች የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት፣ በመረጡት ቦታ እና በፈለጉ ጊዜ ለሚማሩ በርካታ የዕድሜ አቻ ተማሪዎች ተደራሽ ይሆናሉ።

የሥነ ሕዝብ ለውጥም የሥራን ወደፊት በመወሰን ረገድ ቁልፍ ተጽዕኖ አለው፤ ተጽዕኖውም በ2050 የጎላ ይሆናል። በአንዳንድ ቀጣናዎች በፍጥነት እያደገ የሚሄደው የወጣቶች ቁጥር የወጣቶችን ሥራ አጥነት እና የስደት ጫና ማባባሱ አይቀርም። ሌሎች ቀጣናዎች ደግሞ የሕዝቦች እርጅና ይፈጠርባቸውና፣ በማኅበራዊ ደህንነት እና ሌሎች የእንክብካቤ ሥርዓቶች ላይ ተጨማሪ ጫና ይገጥማቸዋል።

በአሁኑ ጊዜ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከጠቅላላው ሕዝብ ቁጥር ምርታማ ነው ተብሎ ከሚታሰበው እና ሕፃናት እና አረጋውያንን ከሚደግፈው ከ15-64 ዓመት የዕድሜ እርከን ጋር የሚያነጻጽርበትን የ"ጥገኝነት ምጣኔ" ስሌት ይጠቀማል። የጥገኝነት ምጣኔዎች በ2050 በአውሮፓ፣ በሰሜን አሜሪካ እና በእስያ በከፍተኛ ደረጃ፤ በላቲን አሜሪካ እና በካሪቢያን ደግሞ በመጠኑ ይጨምራል ተብሎ ይጠበቃል - ይህም ማለት ትናንሽ የሠራተኞች ቡድኖች ሠራተኞች ያልሆኑ ትላልቅ ቡድኖችን (በዋነኛነት ጡረተኞችን) ይደግፋሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ከአፍሪካ አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት ግማሹ ከ25 ዓመት በታች ስለሚሆን፤ አጠቃላይ የአህጉሩ የጥገኝነት ምጣኔ ይቀንሳል ተብሎ ይጠበቃል።

በወጣቶች ብዛት ምጣኔ እና በአረጋውያን ምጣኔ ዕድገት የታየባቸው እነዚህ የሥነ ሕዝብ አወቃቀር ቅየራዎች፣ በሥራው ዓለም እና በትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቶች ላይ ጉልሕ አንድምታዎች አሏቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እና የጎልማሶች ትምህርት ዕድሎችን የማስፋት እና የዕድሜ ልክ ትምህርትን የማጠናከር አዝማሚያዎች ይታያሉ። የሰው ልጅ በሕይወት መቆያ ዕድሜ ሊጨምር እና ምናልባትም በዚያም የተነሣ፣ ቢያንስ ለአንዳንዶች፣ ሥራ ላይ መቆያ ዘመንም ሊራዘም ይችላል። በዕድሜ የገፉ ሰዎች ንቁ ሆነው በሥራ ላይ እየተሳተፉ ከቀጠሉ፣ በክህታቸው እና በተመክሯቸው ሕብረተሰቡንና ኢኮኖሚውን ያበለጽጋሉ። ወጣቶች ሙሉ አቅማቸውን ወደ መጠቀም እንዲደርሱ እና አዳዲስ ዕድሎችን እንዲያገኙ ማስቻል, የነገ የለውጥ አራማጆች ያደርጋቸዋል። ይህ ማለት በሰዎች አቅም ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ፣ አዳዲስ ክህሎቶችን እንዲማሩ፣ የነበሯቸውን እንዲቀይሩ እና ያሏቸውን ክህሎቶች እንዲያልቁ ማስቻል፣ እና በሕይወታቸው በሚያጋጥሟቸው የተለያዩ ሽግግሮች ውስጥ መደገፍ እንደማለት ነው።

እነዚህ ለውጦች እየተከሰቱ ባሉበት ወቅት የትምህርት ፍላጎቶች ይቀያየራሉ፤ አንዳንዶቹ ሊታቀዱ የሚችሉ ሲሆኑ (ለምሳሌ በአንዳድ ቀጣናዎች እንዳለው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን የመክፈት እና ተጨማሪ መምህራንን የመቅጠር ፍላጎት)፤ ነገር ግን ሌሎች ደግሞ ከእርስበርስ ትስሥራቸው ውስብስብነት እና ለውጦቹ ከማይታወቁ አቅጣጫዎች ሊመጡ ከመቻላቸው

የተነሣ ሊገመቱ እና ሊታቀዱ አይችሉም። በዚህ ምክንያት የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ከአካባቢያቸው ማኅበረሰቦች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በማጠናከር ራሳቸውን መልህቅ ተቋማት አድርገው መትከል አለባቸው። ከሌሎች የአካባቢ ተቋማት ጋር ተቀራርቦ መሥራት ትምህርት ቤቶች እና ተቋማቱ የማኅበረሰባቸውን የመማር ፍላጎቶች በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እና ለማሟላት ያስችላቸዋል።

## ወደፊት ዋጋ የሚኖረው ምን ዓይነት ሥራ ነው?

ወደ 2050 ስንቃረብ፣ ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የሚፈጸም ፍቺን ሊወክል የሚችል ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡- የሠራተኞች ክህሎቶች ጥልቀት ምንም ያህል ቢሆን፣ በሥር ነቀል የቴክኖሎጂ ዕድገቶች ምክንያት ዓለም በመደበኛው ኢኮኖሚ ውስጥ በቀላሉ ሥራ ሊያልቅባት ይችላል። አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች መደበኛ ሥራ በሚያገኙበት ማኅበረሰብ ውስጥ ትምህርት እንዴት ይሠራል? ሰዎች ያለ መደበኛ ሥራ ለመኖር ምን ዓይነት አዲስ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል?

ማኅበረሰቦች ለግለሰብ ሥራ ዋጋ ወደመስጠት አድገዋል። ሳይለፉ ሳይደክሙ የሚኖርበት ወርቃማ ጊዜ ሕልም ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ የኖረ ነው። ዛሬ ግን በመጠኑ ተቀዳሚ አምሳያ የሌለውን ትርፍ ጊዜ ችግሩ ከዚህ በፊት ታይቶ የማያውቅ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያን ከመቆጣጠር ብዙም የማይገናኝ ይመስላል። ላለፉት ዐሥርት ዓመታት በድሃ ሀገራት የታየው የጅምላ ሥራ አጥነት በበለጸጉ አገሮችም ላይ እያንዣበበ ነው። ብዙ ነገሮች እንደገና ሊታሰብባቸው ይገባል። የሰውን ልጅ የአምራችነት እና የፈጠራ ተነሳሽነት ወደ ሌሎች ማኅበረሰባዊ እና ግለሰባዊ ጠቀሜታ ወዳላቸው አቅጣጫዎች በምን ዓይነት የተሻለ ዘዴ ማሸጋገር ይቻላል?

> *ሰዎች ያለ መደበኛ ሥራ ለመኖር ምን ዓይነት አዲስ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል?*

ደግነቱ፣ ለእንደዚህ ዓይነት ድንገተኛ አጋጣሚዎች የሚቀርቡ አንዳንድ ምርጥ ምክረ ሐሳቦች ጥሩ ሥራ ለመፍጠር እየተደረጉ ላሉ የትምህርት ጥረቶችም እኩል ያገለግላሉ። ሥለ ወደፊት የሥራ እና የፕላኔቷ ሁኔታ ያሉን በርካታ ንብርብር ጥርጣሬዎች ለተማሪዎች የማገናዘብ ችሎታ ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን ያመለክታሉ።

እንደ ዕውነቱ ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ እሴት መፍጠር ምን ማለት እንደሆነ እንደገና በጥልቀት ማጤን ሊያስፈልገን ይችላል። ስለወደፊቱ ሥራ እና ትምህርት ስናስብ አንድ ምርጫ ይገጥመናል፡- ከትምህርት በጣም ብዙ እና በጣም ትንሽ የሚጠብቀውን እርስበርሱ በሰፊው የሚጋጨውን የአስተሳሰብ ልማድ ይዘን መዝለቅ - ወይም ትምህርት ሊያደርግ በሚችለው ጥሩ ነገር ላይ ማተኮር።

ወደፊት፣ ዋጋ የምንሰጥበት እና ዋጋ የምሰጠውም ነገር የሰው ልጅ በከእጅ ወደ አፍ፣ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ እና በድህረ ኢንዱስትሪ ኢኮኖሚዎቹ ካጋጠሙት የትኞቹም ነገሮች በጣም የተለየ ሆኖ ሊለወጥ ይችላል።

የኢኮኖሚ ደህንነት ለመደበኛው ኢኮኖሚ ትኩረት በመስጠት ብቻ አይመጣም። በቤተሰብ ውስጥ የሚከናወነውን የእንክብካቤ ሥራ፣ የጋራ ጥቅም ሀብት አቅርቦትን እና በመንግሥታት የቀረቡ አስቻይ መሠረተ ልማቶችን (ቁሳዊም ሆነ ሕጋዊ) ጭምር ማጤን አለብን። ምንም እንኳን ብዙዎቹ ተለምዷዊ የተከፋፈሉ አካሄዶቻችን እና የታጠሩ ፍላጎቶቻችን መንገዳችን ላይ ቢቆሙም፤ ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን የሚያበረታቱትን ነገሮች ለመረዳት የሚሞክሩ ሰፋ ያሉ ዘዴዎች በ2050 እየተለመዱ ሊመጡ ይችላሉ።

ትምህርት ለግለሰቦች፣ ለቤተሰባቸው እና ለማኅበረሰባቸው የረዥም ጊዜ ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን መፍጠርን የሚደግፈው መደበኛ፣ ደመወዝ የሚያስገኘውን ሥራ እና ከዚያም ባሻገር በደንብ መመልከት የሚያስችል ሰፊ ዕይታ ሲኖረው ነው። እርግጠኛ ባልሆኑ የሥራ ዕድሎች ፊት እንደሁኔታው ተለዋዋጭነት ከአዲሱ የወደፊት የትምህርት ማኅበራዊ ውል ጋር መቀናጀት አለበት።

# ክፍል ሁለት

## ትምህርትን ማደስ

በ1921 ከመላው ዓለም የተውጣጡ የትምህርት ባለሙያዎች ሥራው በሚቀጥሉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ ባደገው እና ለዩኔስኮ ምሥረታ እና ትምህርትን በተመለከተ ለሚኖረው ኃላፊነት መቀረጽ ባገዘው በኒው ኤጁኬሽናል ፌሎውሽፕ የመጀመሪያ ጉባኤ ላይ ለመካፈል በካሌይ፣ ፈረንሳይ ተሰብስበው ነበር። በመጀመሪያው ስብሰባቸው "ለአዲስ ዘመን አዲስ ትምህርት" መከሰቱን አስታውቀዋል።

የዚህ ሪፖርት ግብም ከዚህ ያነሰ ጉጉት የለውም። ሆኖም፣ ይሄ እንደገና ለመጀመር የሚደረግ ሌላ ጥሪ ብቻ አይደለም። አዳዲስ ሥነ ትምህርቶች፣ አዳዲስ የሥርዓተ ትምህርት ዘዴዎች፣ የታደሰ የመምህራን ቃል ኪዳን፣ አዲስ የትምህርት ቤት ራዕይ፣ እና አዲስ የትምህርት ጊዜ እና ቦታዎች አድናቆት ያስፈልገናል። ይህ ማለት ግን ያለንን እናስወግዳለን ማለት አይደለም። ይልቁንም ምርጥ ምርጦቹን ሥነ ትምህርታዊ እና ትምህርታዊ ትውፊቶች መመርመር፣ ይህን ቅርስ ማደስ እና እርስበርስ የተሳሰሩ የሰው ልጅ እና የሕያው ፕላኔት ነገዎችን ለመቅረጽ የሚረዱንን ተስፋ ሰጪ አካላት ማከል ይኖርብናል።

ባለፈው ክፍለ ዘመን እና ከዚያም በላይ፣ ማኅበረሰቦች እና ቤተሰቦች የትምህርት ቃል ኪዳን በልጆቻቸው ተፈጽሞ ለማየት አይተዌ ትምህርት ላይ ተስፋቸውን አሳርፈዋል። በሚያስደንቅ ሁኔታ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተመሳሳይ መንገድ ሲደራጁ ቆይተዋል። እነዚህ ባሕርያት በተለያዩ ቀጣናዎች እና ባሕሎች የተለያየ አወቃቀሮች ቢኖራቸውም፣ የቀደምት ዘመናት መለዮዎች የነበሩትን ትምህርታዊ ተመክሮዎች መልከ ብዙነት አመሳስለው በመላው ዓለም ተሰራጭተዋል፤ ሰፍነዋል። በዐሥራ ዘጠነኛው እና በሃያኛው ክፍለ ዘመን የተቋቋመው የትምህርት ማኅበራዊ ውል ትምህርትን ለማደራጀት ወደሚከተሉት መርሆች ተተርጉሟል፡- በመጀመሪያ ደረጃ፣ ትምህርት በክፍል እና በመማሪያ ክፍሎች መዋቅር ውስጥ በመምህራን በሚሰጡ ትምህርቶች ላይ እንደተመሠረተ ሥነ ትምህርታዊ ፕሮጀክት ታይቷል፤ ምንም እንኳን ትምህርት በጋራ የመማሪያ ዐውድ ቢሰጥም፣ ቅድሚያ የሚሰጠው ግን ለግለሰብ ስኬት ነበር። ሁለተኛ፣ ትምህርት የሚሰጠው የትምህርት ዓይነቶች ማዕቀፍ ሆኖ በተደራጀ ሥርዓተ ትምህርት ነው። በሦስተኛ ደረጃ፣ ማስተማር የሚታሰበው አንድ መምህር ውጤታማ ትምህርትን ለማቀናጀት ባለው ሙያዊ ብቃት ላይ እንደሚመረኮዝ፣ ብዙ ጊዜም በሙያ ማዕቀፍ እንደሚወሰን የብቻ ተግባር ነው። አራተኛ፣ በየትኛውም ዐውድ ቢሆን፣ ት/ቤቶች የተደራጁት በታላቅ የኪነ ሕንፃ፣ ድርጅታዊ እና የአሠራር ተመሳሳይነት ባለው ሞዴል በመመሥረት ነው።

አምስተኛ ደግሞ፣ ትምህርት በተመሳሳይ ዕድሜ የሚገኙ ተማሪዎችን ከቤተሰቦቻቸው እና ከማኅበረሰቡ አንጻራዊ ርቀት ላይ በሚገኙ ልዩ ተቋማት ለማስተማር የተደራጀ እና ሕፃናት እና ወጣቶች ለወደፊት ሕይወታቸው ዝግጁ እንደሆኑ ሲታሰብ የሚጠናቀቅ ነው።

አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ ጥረት፣ የጋራ ማኅበራዊ ግዴታ፣ በጣም ወሳኝ ከሆኑት ሰብአዊ መብቶች እንደአንዱ እና ከቀጣናዎች እና ከዜጎች በጣም ወሳኝ ኃላፊነቶች እንደአንዱ ተቀብሎ ማጠናከር አለበት። በእርግጥ፣ የትምህርት አንዱ ቁልፍ ሚና ለሰብአዊ መብቶች መከበር የሚቆሙ ዜጎችን ማስተማር ነው። ይህም ተማሪዎች ራሳቸውን የቻሉ፣ በሥነ ምግባር የታነፁ አሳቢዎች እና አድራጊዎች የሚያደርጓቸውን አቅሞች መገንባትን ያካትታል። ከሌሎች ጋር እንዲተባበሩ፤ የድርጊት አቅማቸውን፣ የኃላፊነት ስሜታቸውን፣ ርህራሄያቸውን፣ ምክንያታዊ እና የፈጠራ አስተሳሰባቸውን፣ እንዲሁም በርካታ ማኅበራዊ እና ስሜታዊ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማዘጋጀት ማለት ነው። ትምህርትን ከዚህ ታላቅ ራዕይ ጋር ለማጣጣም አዳዲስ የትምህርት አደረጃጀት መንገዶችን መፍጠር ያስፈልጋል። ትምህርት የሰው ልጅ እርስበርሱ እና ከምድር ጋር ሰላም እንዲያወርድ ለመርዳት ከሚያስችሉ ቁልፍ ነገሮች እንደ አንዱ ሊወሰድ ይችላል። የዚህ ሪፖርት ክፍል ሁለት የትምህርት መብትን የሚያጎለብተውን፣ እና ትምህርትን የሰው ልጅን የመተሳሰብ እና የመተባበር አቅም እንደሚያጎለብት አንድ የጋራ ጥቅም እና የጋራ ጥረት የሚያጠናክረውን አዲስ ማኅበራዊ ውል ዕውን የምናደርግባቸውን መንገዶች ያቀርባል።

በእነዚህ አምስት ምዕራፎች ውስጥ የተቀመጡት የውይይት እና የድርጊት መመሪያ መርሆች የመነጩት፣ ኮሚሽኑ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ባደረገው እና በተለይም ለወጣቶች አስተዋጽኦዎች ትኩረት ከሰጠው ዓለም አቀፍ ምክክር ነው። ነገር ግን እነዚህ የመመሪያ መርሆች በትምህርት መስክ በአካዳሚያዊ እና በሙያዊ ማኅበረሰቦች ውስጥ በምርምር እና ማሰላሰል ከተገነባው ሥር ከያዘ ሳይንሳዊ የዕውቀት መሠረት ጭምር የተገኙም ናቸው።

እነዚህን የመመሪያ መርሆች ወደ ፖሊሲ እና ተግባር መቀየር ይህንን ሪፖርት በሚያነቡ ሁሉ ይወሰናል። እያንዳንዱ ተማሪ፣ ዜጋ፣ አስተማሪ እና ወላጅ የዕለት ከዕለት የትምህርት ልምምዶችን፣ ተቋማትን እና ሥርዓቶችን ለመቀየር በአካባቢው የመሥራት፣ እና ከሌሎች በቅርብም በሩቅም ካሉት ጋር የመገናኘት አቅም እና ዕድል አለው። እነዚህ ብዙ ትላልቅ እና ትናንሽ የትብብር እና የአጋርነት ተግባራት ናቸው በመጨረሻ፣ የወደፊቱን የሚቀይሩት። የኮሚሽኑ ይህንን ሪፖርት የማዘጋጀት ዓላማው ውይይቱን ለዚህ ለውጥ በሚያግዙ ሐሳቦች እና መርሆች ማስፋት ነው። የሪፖርቱ ዝግጅት የትብብር ሥራ ነበር። ሐሳቦቹን ዕውን ማድረግ ደግሞ ሌላ የትብብር ሥራ ይሆናል።

# ምዕራፍ 3

# የትብብር እና የአጋርነት ሥነ ትምህርቶች

*ትክክለኛ  ትምህርት የተማሪዎችን ዓላማዎች እና አቅሞች ግምት ውስጥ በማስገባት ማሳተፍ ይኖርበታል።  እንደዚህ ዓይነቱን ተሳትፎ ለማረጋገጥ መምህራን በመተሳሰብ እና በመተማመን ላይ የተመሠረቱ ግንኙነቶችን መገንባት አለባቸው። በእንዲህ ዓይነት ግንኙነቶች ውስጥ ደግሞ ተማሪዎች እና መምህራን በትብብር ትምህርታዊ ዓላማዎችን ይገነባሉ።*

ኔል ኖዲንግስ፣ *Philosophy of Education.*

**በአዲሱ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ውስጥ ሥነ ትምህርት በትብብር እና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ፣ ተማሪዎች እና መምህራን በመተማመን ዓለምን ለመለወጥ የሚተባበሩበትን አቅም የሚያጎለብት መሆን አለበት።**

የወደፊቱን መልሶ በጋራ ማጤን ማሰብ መተባበርንና መተሳሰብን የሚያበረታቱ ሥነ ትምህርቶችን ይፈልጋል። እንዴት እንማር የሚለው ለምን እና ምን እንማር በሚለው መወሰን አለበት። ሰብአዊ መብቶችን ለማስተማር እና ለማበልጸግ መሠረታዊ ግዴታ አለብን ማለት፣ የተማሪን መብቶች ማክበር አለብን ማለት ነው። በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በወሲባዊ ማንነት፣ በማኅበራዊ መደብ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በዜግነት፣ ወዘተ ባሉት ልዩነቶች ሁሉ ውስጥ ሰዎች እርስበርሳቸው የሚማሩባቸውን እና የሚከባበሩባቸውን አጋጣሚዎች መፍጠር አለብን። የሰዎችን ክብር ማክበር ማለት ምን እና እንዴት ማሰብ እንዳለባቸው ማሳወቅ ሳይሆን፣ በራሳቸው እንዲያስቡ ማስተማር ነው። ይህም ማለት ተማሪዎች የራሳቸውን ዓላማ እንዲያውቁ እና ለእነርሱ የተሳካ ሕይወት እንዴት ያለ እንደሚሆን እንዲወስኑ ዕድሎችን መፍጠር ማለት ነው። በተመሳሳይም፣ እንደዚህ ዓይነት ሕይወቶች ዕውን የሚሆኑበትን ዓለም በጋራ መገንባት አለብን፤ ይህ ማለት ደግሞ ዓለምን ለማሻሻል የሚያስችሉ አቅሞች እንዲገነቡ መተባበር ማለት ነው።

የትብብር እና የአጋርነት ሥነ ትምህርቶች በአድሎ አልባነት፣ ልዩነትን በማክበር እና በሚክስ ፍትሕ፣ የጋራ መርሆዎች ላይ የተመሠረቱ፤ እንዲሁም በመተሳሰብ እና በመደጋገፍ ሥነ ምግባር የታነጹ መሆን አለባቸው። አሳታፊ፣ ትብብራዊ፣ ችግር ፈቺ፣ እና በይነ-ዲሲፕሊናዊ፣ በይነ ትውልዳዊ እና በይነ ባሕላዊ አስተምህሮ የግድ ይጠይቃሉ። እንደነዚህ ያሉት ሥነ ትምህርቶች በወል ዕውቀት የሚበለጽጉ እሱንም የሚያበለጽጉ፣ በዕድሜ ልክ የሚዘልቁ፣ በእያንዳንዱ ዕድሜ እና የትምህርት ደረጃ የሚኖሩ ልዩ ዕድሎችን ከግንዛቤ የሚያስገቡ ናቸው።

ንቁ ትምህርት ፅንሰ ሐሳባዊ እና የአሠራር ዕውቀትን ማዳበር አስፈላጊ መሆኑን ይገነዘባል። ዕውቀትን ለማዳበር በዕውቀት እና በስሜት መሳተፍ፣ ዕውቀትን ወደ ተግባር የመተርጎም ችሎታ እና የመተግበር ጠባይ ማስፈለጉን ይቀበላል። ሥነ ትምህርታዊ ልምምዶች ከአሁኑ እና ከወደፊቱ አጣዳፊ ፍላጎቶች አንጻር በየጊዜው መታደስ ባለባቸው የዘመናት ተመክሮ፣ ማሰላሰል እና ጥናት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ኃይለኞቹ የመማር ማበረታቻዎች ትክክለኛነት (የተማርነው ከምንኖርበት ዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት መረዳት) እና አግባብነት (የተማርነው ከእሴቶቻችን ጋር ያለውን ግንኙነት መረዳት) ናቸው። በፕሮጀክት እና በችግር ላይ የተመሠረተ ትምህርት ለትክክለኛ፣ ተገቢ ትምህርት ብዙ ዕድሎችን ከመስጠቱም በተጨማሪ፣ ተፈጥሯዊ የማወቅ እና የመረዳት ፍላጎታችንንም ያነቃቃል።

የዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ አጋማሽ በትብብር እና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ ሥነ ትምህርትን የሚያሳይ ሲሆን፤ ይህም የሕብረት፣ በይነ-ዲሲፕሊናዊ እና ችግር ተኮር፤ ስብጥርን የሚያከብር እና የሚያቀጥል፤ ተማሪዎች የጭፍን ጥላቻ እና የመከፋፈልን ትምህርታቸውን እንዲያራግፉ የሚጋብዝ፤ በፍትሕ መጓደል የደረሱ ቁስሎችን የሚፈውስ፤ እና ለትምህርታዊ ጥቅም ሲባል ትርጉም ያለው ግምገማ የሚጠቀም ሥነ ትምህርትን ያካትታል። እነዚህ ዘዴዎች ለምሳሌ እንደ ሙዚየሞች፣ ቤተ መጻሕፍት፣ የክረምት ካምፖች እና የማኅበረሰብ ማዕከላት ያሉ ኢመደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ቦታዎችን ጨምሮ በሁሉም ቦታዎች በሚሰጡ ትምህርቶች ላይ ይሠራሉ። በመቀጠልም ምዕራፉ እነዚህ በትምህርት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ለመደበኛ ትምህርት የተለዩ ፍላጎቶች እና ዕድሎች በእያንዳንዱ የሕይወት ደረጃ መተግበራቸውን ይመረምራል፦ የሊጋ ሕፃንነት መሠረቶችን እና በሙሉ የልጅነት ጊዜ የሚደረግ ትብብርን በመደገፍ፣ የጎረምሶችን እና ወጣቶችን ልዩ ችሎታዎች በማውጣት እና የከፍተኛ ትምህርት ተልእኮን በማደስ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይፈትሻል። ምዕራፉ የሚጠናቀቀው ወደ 2050 በተቃኙ የውይይት እና የድርጊት መሪ መርሆች ሲሆን፤ እነዚህም በተለይ በትምህርት ባለሙያዎች እና የትምህርት ሥርዓቶች አስተዳዳሪዎች እና ዕቅድ አውጪዎች ፍላጎቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፤ ከእነሱም መካከል ቀጣዮቹ ይገኙበታል፦ ከሰፊው ዓለም ጋር ጥልቅ ግንኙነት መፍጠር፣ ትብብርን ማጎልበት፣ የሥነ ምግባር መሠረቶችን መገንባት፣ መተሳሰብን ማዳበር እና መማማርን ለመደገፍ ግምገማን መጠቀም።

# ሥነ ትምህርታዊ አቀራረቦችን እንደገና ማጤን

ሥነ ትምህርት ተዛምዷዊ ነው። መምህራን እና ተማሪዎች እርስበርሳቸው በሚማሩበት ጊዜ በሥነ ትምህርታዊው ዐውድ አማካይነት ይለወጣሉ። ሥነ ትምህርታዊ ዐውድ በአንድ ጊዜ የግለሰብ እና የወል ለውጥ በሚያስከትለው ውጤታማ ትስስር ይበየናል። ውስጣዊ ሕይወቶቻችን በአካባቢዎቻችን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፤ በዚያው ልክም የአካባቢዎቻችን ጥልቅ ተጽዕኖ ያርፍባቸዋል።

ተማሪዎች፣ መምህራን እና ዕውቀት የታወቀውን ሥነ ትምህርታዊ ሕብረ ሦስት ይመሠርታሉ። ማስተማር እና መማር ከጋራ ዕውቀት ይመገባሉ፣ እሱንም ይመግባሉ። በሥነ ትምህርታዊ አውዶች ትምህርት፣ እንዲሁ ከሰው ልጅ የጋራ የተከማቸ ዕውቀት ቅርስ ጋር ያገናኘናል እና እሱን ለማበልጸግም ዕድሎችን ይሰጠናል።

ዛሬ ይህ ሕብረ ሦስት ከሰፊው ዓለም አንጻር ሊታለም ይገባል። በዓለም ውስጥ እና ከዓለም ጋር ለመማር እና ዓለምንም ለማሻሻል የሚረዱን ሥነ ትምህርቶች ያስፈልጉናል። እንደነዚህ ያሉት ሥነ ትምህርቶች ስለ እያንዳንዱ ሰው ክብር እና በሕሊና እና በአስተሳሰብ ነጻነት የተወከለውን ታላቅ ስኬት መማር እንድንቀጥል ይጠይቃሉ - ነገር ግን ሰዋዊ የተለየሁ ነኝ ባይነት እና የበላይነት የተጸናወተውን ግለኝነት መተውንም ይፈልጋሉ። እርስበርስ በመደጋገፍ እና በመተሳሰብ ሥነ ምግባር ላይ መመሥረት እና በግለሰቦች፣ በቡድኖች እና በዝርያዎች መካከል ያለውን ተደጋጋፊነት መገንዘብ አለባቸው። በጋራ ስለምንካፈለው ነገር እና እርስበርስ እና ከፕላኔቷ ጋር ስለሚያስተሳስሩን ሥርዓታዊ ተደጋጋፊነት አስፈላጊነት እንድንገነዘብ ሊያበረታቱን ይገባል።

መምህራን እና ተማሪዎች ተባብረው ከሰው ልጅ የጋራ ዕውቀት የሚመገብ እና እሱንም የሚመግብ የዕውቀት ፈላጊዎች እና ገንቢዎች ማኅበረሰብ መፍጠር አለባቸው። ይህም ስላለው እና ስለሚገነባው ነገር ማሰላሰል፤ እንዲሁም ሁሉም ሰው፣ መምህራን እና ተማሪዎችን ጨምሮ፣ ራሱን ከሌሎች ጋር ተባብሮ ዕውቀት ማመንጨት እንደሚችል የማሰብ መብት እንዳለው መቀበልን ያካትታል።

> *መምህራን እና ተማሪዎች ተባብረው የዕውቀት ፈላጊዎች እና ገንቢዎች ማኅበረሰብ መፍጠር አለባቸው።*

ከሁሉም የትምህርት ዓላማዎች በስተጀርባ የትርጉም እና የዓላማ ጥያቄዎች አሉ። መምህራን እንደ ተግባር እና መስተጋብር ለተማሪዎች ምን፣ ለምን ዓላማ ያቀርባሉ? ተማሪዎች ለራሳቸው የመማር ጥረት ምን ትርጉም ይሰጣሉ?

ለዋጭ ሥነ ትምህርታዊ አውዶች ከክፍል ጓደኞች፣ ከእኩዮች እና ከማኅበረሰብ አባላት ጋር ለመወያየት ያስችላሉ። የማስተማር ጥበብ፣ ሳይንስ እና ክህሎት ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚገለገሉት፣ በተማሪዎች ላይ ጉጉትን እና ፍላጎትን እየጫሩ ተማሪዎቻቸው የታወቀውን እና ያልታወቀውን እንዲመረምሩ፣ እንዲፈጥሩ እና እንዲገናኙ ዕድል በሚሰጡ መምህራን ነው። የሚከተሉት ክፍሎች አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ወደ ሥነ ትምህርታዊ አውዶች ለመተርጎም የሚያስችሉ ተስፋ ሰጭ ስልቶችን ያቀርባሉ።

## በይነ-ዲሲፕሊናዊ ችግር ተኮር የሕብረት ትምህርት

መጪው ጊዜ ለተማሪዎች አዳዲስ ችግሮችን እና ዕድሎችን ይዞ ይመጣል። ይሆነኝ ብሎ የተማሪዎችን ችግርን የመለየት እና ችግርን የመፍታት አቅሞች በማጎልበት፣ ዓለም መለወጧን ትቀጥላለች የሚለውን ግንዛቤ በሥርዓተ ትምህርት እና በሥነ ትምህርት ውስጥ ማስረጽ ይቻላል። ችግር ተኮር ሥነ ትምህርት ተማሪዎችን መፈልሰፍን እና ሕብረትን በሚፈልጉ ፕሮጀክቶች፣ ኢኒሼቲቮች እና ተግባራት ላይ ያሳትፋል። ተማሪዎች ግልጽ የሆኑ ግቦችን እና ዓላማዎችን ሲጋፈጡ፣ አዋጭ እና ምናባዊ መፍትሔዎችን ለማግኘት የዲሲፕሊን ድንበሮችን ማለፍ ይኖርባቸዋል። በትምህርት ችግሮች እና ፕሮጄክቶች ላይ ማተኮር ተማሪዎችን በግል ተመክሯቸው ላይ መሠረት ሊያስይዛቸው፣ ዓለም እንደ ቋሚ ሳይሆን ተለዋዋጭ እንደሆነ

እንዲመለከቱ ሊረዳቸው፣ ዕውቀትን እና ማስተዋልን ሊገነባ እና የተማሪዎችን የመሠረታዊ ትምህርት ክህሎቶች እና ትርጉም ያለው አገላለጻቸውን ኃይል ማዳበር ይችላል።

የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳ ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ሰፋ ባሉ ተጓዳኝ ዘዴዎች ማጤን እንደሚኖርባቸው ይገነዘባል። የዘላቂ ልማት ግቦች፣ በተለይም ዒላማ 4.7፣ ተማሪዎችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ተደጋጋፊነቱ እየጨመረ በመጣው ዓለም ውስጥ ዘላቂ ነገዎችን ለመገንባት ዕውቀት እና ብቃቶችን የሚሹ ዓለም አቀፋዊ ዜጋ አድርጎ ያውቃቸዋል። 2050ን እና ከዚያ ወዲያ ያለውን ጊዜ ስንመለከት፣ እነዚህን አቅሞች ማጎልበት የበለጠ አስፈላጊ ይሆናል። የዘላቂ ልማት ግቦች ራሳቸው፣ ተማሪዎች የተሟላ ግቦችን የሚያጎለብቱባቸውን ችሎታዎች እንዲያዳብሩ የሚያግዛቸውን በችግር እና በፕሮጀክት ላይ የተመሠረተ በይነ-ዲሲፕሊናዊ ትምህርት የሚዋቀርበትን ማዕቀፍ ይሰጣሉ።

በጋራ ችግሮች እና ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ማድረግ ማለት ለጥናት፣ ለምርመራ እና ለጋራ ግንባታ ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው። የግለሰቦች ዕውቀት እና አቅም ከሌሎች ጋር ተዛምዶ ነው የሚዳብረው፤ ተግባርን እንዴት እንደሚጋሩት፣ እንዲሁም የዕውቀትን የራሱን ልዩ ልዩ እና የተሳሰሩ አውታሮች አጉልቶ በማሳየት። በፕሮጀክት እና በችግር ላይ የተመሠረቱ አካሄዶች የዕውቀት ፍላጎትን አይቀንሱም፤ ይልቁንም ዕውቀትን በሕያው ተለዋዋጭ ሂደቶች እና አተገባበሮች ማዕቀፍ ያስቀምጣሉ።

ብዙዎቹ በጣም ፍሬያማ የትምህርት ዓይነቶች የሚካሄዱት ከተለመዱ የዲሲፕሊን ድንበሮች ባሻገር ባለ የማያቋርጥ የሐሳብ ፍሰት በበለፀጉ አካባቢዎች ነው። የፕላኔቷ ችግሮች እና እንቆቅልሾች ራሳቸውን በዲሲፕሊን ድንበሮች ውስጥ እንደማይገድቡ ሁሉ፣ ሥነ ትምህርቶች በይነ-ዲሲፕሊናዊነትን ማንጸባረቅ አለባቸው። ሆኖም፣ ለአንድ ችግር ብዙ መፍትሔዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ፣ የመደጋገፍ እና የመተሳሰብ እሴቶችን እና መርሆዎችን የሚያዳብሩ ሥነ ትምህርታዊ አካሄዶች መመረጥ አለባቸው። አገልግሎት ተኮር ትምህርት እና ማኅበረሰባዊ ተሳትፎ በክፍል እና በማኅበረሰብ መካከል ያሉ ግድግዳዎችን አሳስተው፣ የተማሪዎችን ግምቶች በመፈተን፤ ተማሪዎች ከራሳቸው ልምድ ባለፈ ከሰፊ ሥርዓቶች፣ ሂደቶች እና ልምዶች ጋር ያገናኛቸዋል። ተማሪዎች በተለይም የተለያዩ ቁሳዊ ችግሮች ሊያጋጥሟቸው ከሚችሉ ሰዎች ጋር ሲገናኙ አገልግሎትን በትህትና መንፈስ፣ ያለ የበላይነት ስሜት መፈጸማቸው በጣም አስፈላጊ ነው። አገልግሎት ተኮር ትምህርት ለታደሉት ብቻ የተገደበ መሆን የለበትም፤ ሁሉም ተማሪዎች የማኅበረሰባቸውን ደህንነት ለማላቅ በሚደረግ የውይይት ሂደት አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላሉ። አገልግሎት ተኮር ትምህርት ለችግር ፈቺ ሥነ ትምህርት በጣም ጠቃሚ ወደ ሆኑት ወይም የግል ፍላጎት ላይ ወደተመሠረቱት መፍትሄዎች ከማድላት ይልቅ ሕብረትን እንደ ዋነኛ መርህ ይቆጥራል።

## ስብጥር እና ብዙኀነትን አክብሮ ማዝለቅ

መጪውን ጊዜ እንደገና በጋራ ማጤን ስብጥር እና ብዝሃነት የተጠናከረበትን ማኅበረሰብ ማለም እና የጋራ ሰብአዊነታችንን ማበልጸግ ነው። ካለንበት ሥፍራ አሻግረን መሄድ የሚያስችለን እና ወደማናውቀው የሚሸኘን ትምህርት ያስፈልገናል።

የአጋርነት ሥነ ትምህርት አካታች እና በይነ ባሕላዊ በሆነ ትምህርት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት - ይኸውም ሁሉንም ዓይነት የተደራሽነት አድልዎ እና ማግለልን የሚመለከት፣ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት እና ወጣቶችን ጨምሮ፣ እንዲሁም በዘር፣ በጾታ ማንነት፣ በመደብ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በሃይማኖት ወይም በዜግነት ጭፍን ጥላቻ የሚፈጸምባቸውን ሁሉ የሚያካትት ነው። በእያንዳንዱ ሰው የተለያዩ ዕውነታዎች ላይ የተመሠረተ የመካተት መብት በጣም ወሳኝ ከሆኑት ሰብአዊ መብቶች መካከል አንዱ ነው። ሥነ ትምህርት ተማሪዎችን ወደ የትምህርት ማኅበረሰቡ ሊቀበላቸው እና ሁሉንም አካታች እንዲሆኑ እና የሌሎችን ክብር ማድነቅ እንዲችሉ ሊረዳቸው ይገባል። አካታችነት የሌለበት ሥነ ትምህርት እንደ አንድ የጋራ ጥቅም የሚታየውን ትምህርት ያዳክማል፤ እናም የሁሉም ክብር እና ሰብአዊ መብቶች የሚከበሩበትን ዕድል ያዳክማል።

ስለዚህ መማር ራሱ ለስብጥር፣ ለልዩነት እና ለብዝሃነትን ዋጋ በመስጠት መነሻ መሆን እና ተማሪዎች ጭፍን ጥላቻን እና አድልዎን እንዲጋፈጡ ማስቻል አለበት። በፕላኔታችን ላይ ለተጋረጡ ውስብስብ፣ መልከ ብዙ ተግዳሮቶች የትኛውም ሰው ወይም አተያይ ሁሉም መፍትሄዎች ሊኖሩት አይችልም። የአጋርነት ሥነ ትምህርቶች በዓለም ዙሪያ በዘረኝነት፣ በጾታዊ አድልዎ፣ በቅኝ አገዛዝ እና በአምባ ገነን ገዥዎች የተጫኑትን ስልታዊ ማግለያዎች እና ማጥፋቶች መገንዘብ እና ማረም

አለባቸው። የተለያዩ ባሕሎች እና የዕውቀት ንድፈ ሐሳቦችን፣ የተለያዩ የአኗኗር ዘይቤዎች እና ንጽርዖተ ዓለሞችን ሳያከብሩ የአጋርነት ሥነ ትምህርትን መገንባት አይቻልም። የአጋርነት ሥነ ትምህርት እነዚህን ልዩነቶች በአንድ ጊዜ ያስተባብራል።

በምርጫም ይሁን በግዳጅ መፈናቀል በዓለም ላይ እየጨመረ የመጣው የሰው ልጅ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የዓለምን የባሕል እና የዘር ስብጥር በቀጥታ ወደ መማሪያ ክፍሎች እና ትምህርታዊ አውዶች የሚያመጡ አዳዲስ ትምህርታዊ ዕውነታዎችን ፈጥሯል። መምህራን የተለያየ የትምህርት ዳራ፣ ቋንቋ እና ባሕል ካላቸው ተማሪዎች ጋር በአዳዲስ ሁኔታዎች እየሠሩ ነው። የመከባበር፣ የማካተት፣ የወገንነት፣ የሰላም ግንባታ እና የግጭት ለውጥ ሥነ ትምህርቶች ልዩነቶችን ከመቀበል ወይም ከመቻቻል የዘለሉ ናቸው። ተማሪዎች ጎን ለጎን ተቀምጠው፣ አብረው እንዲሠሩ መደገፍ አለባቸው። ወጣቶች ያለፈውን፣ የአሁኑን እና የወደፊት ሕይወታቸውን እንዲረዱ እና እንዲያስተሳስሩ፣ ተመክሮዎቻቸውን የሚቀርጹትን ኢ-ፍትሐዊነቶች እንዲተነትኑ፣ መገፋት እና መገለልን እንዲቋቋሙ የሚያስችል ትምህርት ለማይታወቁ ወደፊቶች ከሚደረጉ ዝግጅቶች አንዱ ነው።

*የአጋርነት ሥነ ትምህርቶች በዓለም ዙሪያ በዘረኝነት፣ በጾታዊ አድልዎ፣ በቅኝ አገዛዝ እና በአምባ ገነን ገዥዎች የተጫኑትን ስልታዊ ማግለያዎች እና ማጥፋቶች መገንዘብ እና ማረም አለባቸው።*

ዓለም በመድብለ ባሕላዊ እና በመድብለ ጎሳዊ ሕብረተሰቦች የበለፀገች እንደመሆኗ፣ ትምህርት በይነ-ባሕላዊ ዜግነትን ማበረታታት አለበት። ስለ ስብጥር ዋጋ ከመማማር ባለፈ፣ ትምህርት ከተለያየ ቡድኖች፣ የዕውቀት ሥርዓቶች እና ልምምዶች ጋር የጎን ለጎን ዲሞክራሲያዊ ውይይት ለማድረግ የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን፣ እሴቶችን እና ሁኔታዎችን ማሳደግ ይኖርበታል። ለበይነ-ባሕላዊ ዜግነት መሠረቱ የራስን ባሕላዊ ማንነቶች ማረጋገጥ ነው። ማን እንደሆንክ ማወቅ ሌሎችን ለማክበር መነሻ ነው። በይነ-ባሕላዊ ትምህርት አነስተኛ ቁጥርና የእድገት ደረጃ ያላቸውን ብሔረሰቦችን፣ ቀደምት ሕዝቦችን ወይም ሌሎች የተገለሉ ቡድኖችን ወደ ብዙኃኑ ማኅበረሰብ ለማዋሃድ እንደ መሳሪያ ማገልገል የለበትም፤ ይልቁንም በማኅበረሰቦቻችን መሀል ይበልጥ ሚዛናዊ እና ዲሞክራሲያዊ የሥልጣን ግንኙነቶችን ለማበረታታት ጥቅም ላይ መዋል አለበት። በተደጋጋፊነት፣ በመተጋገዝ እና በመከባበር ላይ ተመሥርተው በጋራ የሚያበለጽጉ የዕውቀት፣ የተግባር እና የመፍትሔ ልውውጦችን የሚያመነጩ ሥነ ትምህርቶች ያስፈልጉናል።

እርስበርሳችን የምንማማረው በልዩነታችን ነው፤ የተማርነው ነገር ትርጉም የሚያገኘውም በጋራችን ዐውድ ውስጥ ነው። በጋራ ቦታ ውስጥ ያሉ ልዩነቶችን የሚከታተለውን "ሥነ ትምህርታዊ ልይይት" የተጋነነ ግላዊነት ካለው እና ተማሪዎችን ከተገለጸው ግላዊ-ግላዊነት የተላበሰ ትምህርት መለየት አስፈላጊ ነው፣ ይህም ተማሪዎችን ከዐውድ ነጥሎ፣ ከሕዝባዊ እና ከጋራ ሥፍራዎች እና ግንኙነቶች ከሚያለያየው በሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI) የታገዘ ትምህርት መለየት ያፈልጋል። ልዩነቶቻችን ተቃይጠው የተሻለ የጋራ መግባባት ሊያመጡ ይገባል።

ሥነ ትምህርት ምንጊዜም የሚካሄደው በታዳጊ፣ ተፈጥሯዊ ቅይጥነት ባለው እና ሁልጊዜም በግንባታ ላይ ባለ የሥፍራ እና ጊዜ ውስጥ ነው። የአንድ መጽሐፍ ሁለት አንዳ'ይነት ቅጂዎች ሊኖሩ ቢችሉም፤ መጽሐፉን ማንበቢያ ሁለት አንዳ'ይነት መንገዶች ግን አይኖሩም። ሁለት አንዳ'ይነት የትምህርት ዕቅዶች ወይም የሥርዓተ ትምህርት አሐዶች ሊኖሩ ቢችሉም፤ ሁለት አንዳ'ይነት የማስተማሪያ መንገዶች ግን አይኖሩም። ይህ ሐሳብ "በዓለም አቀፍ የትምህርት ኢንዱስትሪ" ውስጥ እየገነኑ ስላሉ አንዳንድ የትምህርት ቴክኖሎጂ አዝማሚያዎች ጥንቃቄ እንዲደረግ ያሳስባል። በሰው ሠራሽ አስተውሎት የሚጠቀሙ እና ለማስተማር፣ ለመማር ወይም ለምዘና ዝግጁ የሆኑ መንገዶችን ለማቅረብ ተስፋ በሚሰጡት አውቶሜትድ ሥርዓቶች መንሠራፋት ውስጥ የሰውን ልጅ ተጽዕኖ እና ሚዛን ማስጠበቂያ እንፈልጋለን። ጥቅም ላይ ሲውሉም የእንደዚህ ዓይነት ቴክኒኮች ውሱንነቶች፣ በግልጽ መታየት አለባቸው፤ ልክ ከሌሎች በተለየ መንገድ ትምህርትን "የሚያከናውኑትን" የማግለል አዝማሚያ ያላቸውን ነባር የሥልጣን አወቃቀሮች እና ችግር ያለባቸውን ግምቶች የማጠናከር አደጋዎችም መዘንጋት እንደሌለባቸው። ኃይሎቻችን በትዕግስት ሊያስተምሯቸው እና ሊማሯቸው በሚገቡ፣ እና የቴክኖሎጂ አቋራጭ መንገዶች በሌሏቸው የመተሳሰብ፣ የሥነ ምግባር፣ የአጋርነት፣ የአብሮ ግንባታ እና የፍትሕ ደፋር አካሄዶች ላይ ማተኮር አለባቸው። እነዚህ በሰው ልጆች በተሻለ ሁኔታ የተመቻቹ ጥልቅ ሰብዓዊ ድርጊቶች ናቸው።

## የተማሩትን ከፋፋይነት አለመማርን መማር

የትብብር እና የአጋርነት ሥነ ትምህርቶች ስብጥርን ለማዝለቅ፣ ከመቀበል እና ከመስጠት ያለፈ ነገር ይጠይቃሉ። ነባር አድልዎ፣ ጭፍን ጥላቻ እና ከፋፋይነትን መርምሮ መተውን ይጠይቃሉ። በእርግጥ፣ ዕውቀት ለማስተላለፍ የታሸገ "የተጠናቀቀ ምርት" አይደለም። ሥነ ትምህርት የዕውቀትን ሥርጭት ከማስፋፋት ይልቅ እንዴት በታሪክ እንደተመሠረተ እና በውይይታዊ መንገድ እንደተገነባ አጥርቶ ሊያሳይ ይችላል።

*የባሕል ሀብቶች ከዕውቀት ጋር ያሉን ግንኙነቶች ቁልፍ አካላት ናቸው።*

የባሕል ሀብቶች ከዕውቀት ጋር ያሉን ግንኙነቶች ቁልፍ አካላት ናቸው። የትምህርት ፖሊሲ የሥርዓተ ጾታ፣ የዘር፣ የጎሳ፣ የሃይማኖት፣ የመኖሪያ፣ የዜግነት፣ የሰነድ ሁኔታ፣ የአካል ጉዳት፣ የጾታ ማንነት ወይም የትውልድ መደብ ኢፍትሐዊነትን ለመፍታት ያለመ እየሆነ መጥቷል። ነገር ግን፣ በትምህርት እና በጋራ ዕውቀት ውስጥ ያሉ የጋራ ትውስታዎችን፣ ምኞቶችን፣ ባሕላዊ ወጎችን እና አገር በቀል ዕውቀቶችን ዝም ለማሰኘት እና ለማግለል ድርጊቶች የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው። ሥር የያዘ ገናን ዕውቀትን በጥልቀት መመርመርን መማር የአጋርነት ሥነ ትምህርት ማዕከላዊ ጉዳይ ነው። የተማሩትን አለመማርን መማር አለብን።

መሰባሰብ፣ የማይታወቁ የእርስበርስ ዕውነታዎችን መመርመር፣ እና ሥር የያዘን ዕውቀት በጥልቀት መመርመር ከባድ፣ ዐልፎ ተርፎም አደገኛ ሊሆን ይችላል። ሁሉም የትምህርት አካባቢዎች ተማሪዎች እንዲሞክሩ፣ እንዲደፍሩ፣ እንዲወድቁ እና እንዲፈጥሩ የሚበረታቱባቸው የደህንነት፣ ሲልም መሸሸጊያ ሥፍራዎች መሆን አለባቸው። ሥነ ትምህርት ምናብ እና የፈጠራ አስተሳሰብን ማንቃት እና የአእምሮ ነጻነትን ማበረታታት አለበት፤ ይህም የመሳሳት እና ከስሕተት የመማር መብትን ይጨምራል። እንዲህ ያለውን፣ አንዳንድ ጊዜ የሚዝረከረክ የትምህርት ሁኔታ የሚፈቅዱ እና የሚያስችሉ ከባቢዎች፣ የአረዳድ እና የአመለካከት ልዩነቶችን በዕውነተኛ ግንዛቤን፣ በርህራሄን፣ በሥነ ምግባር ማዕቀፎች እና በአድናቆት ለማስተናገድ ወሳኝ ናቸው። የትምህርት ባለሙያዎች ተማሪዎች ከአዳዲስ ሐሳቦች እና ከአስቸጋሪ ዕውቀቶች ጋር ሲታገሉ ለትችት መጋለጥን የሚደፍሩባቸው እና ከፍርሃት ነጻ የሚሆኑባቸውን ከባቢዎች ለመፍጠር መሥራት አለባቸው።

## የኢፍትሐዊነትን ቁስሎች መፈወስን መማር

ማወቅ ከስሜት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። የሰው ልጅ የማሰብ ችሎታ ከንቃተ ህሊና እና ስሜት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ይህንን ትስስር ከግንዛቤ ማስገባት፣ እጅግ በጣም ሰፊ የትምህርት ዕድል መስከ ይከፍታል። ማንኛውንም ነጠላ፣ ንጥል-ባሕላዊ ዕይታን መቃወም እና ለሌሎች የማወቅ እና ስሜት መንገዶች፣ ለተለያዩ የአኗኗር ዘይቤዎችን፣ ለተለያዩ የዕውቀት ንድፈ ሐሳቦች ዋጋ መስጠት እንችላለን። ሥነ ትምህርትን ከቅኝ አገዛዝ ማላቀቅ የሚቻለው በሥነ ዕውቀት ግምቶች እና አተያዮች መሀል በሚኖሩ ገንቢ፣ አግድሞሻዊ ግንኙነቶች አማካይነት ነው።

ትምህርት ለሚከስ ፍትሕ እና ለአጋርነት የሚኖረውንም አስፈላጊነት ከወዲሁ እንገምታለን። አጋርነት ለጥብቅ ቁርኝት ላለው ሕብረተሰብ ግንባታ ምንጊዜም አስፈላጊ ነው፤ ቅከርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በመደበኛ እና መደበኛነቱ ባነሰ ትምህርት ውስጥ ወሳኝ ሥነ ትምህርታዊ ዓላማ ሆኗል። የአጋርነት ሥነ ትምህርት ስለጋራ ንቃት እና ተግባር አስፈላጊነት ግንዛቤን በመገንባት ጨቋኝ አገዛዞችን ለማለፍ ረድተዋል። የትምህርት ሥራ የፈውስ ዕድሎችን ለመፍጠር በመተዛዘን፣ በመተሳሰብ እና በርህራሄ አማካይነት እየተስፋፋ የሚሄድ አጋርነት ላይ ሊያተኩር ይችላል። ርኅራኄ፣ ለሌሎች የመድረስ እና ስሜታቸውን የመጋራት እንደመሆኑ፣ ከሥነ ምግባር ጋር ተዳምሮ ለፍትሕ ወሳኝነት አለው። ያለፉ ኢፍትሐዊነቶችን ለመፈወስ መማር፣ የትብብር እና አጋርነት ሥነ ትምህርቶች ወሳኝ አካል መሆን አለበት።

### ትርጉም ያለው ምዘናን ማጠናከር

ምዘና በጣም መሠረታዊ በሆነው ደረጃው፣ ተማሪዎች በትምህርታቸው የሚያጋጥሟቸውን መሻሻሎች እና ተግዳሮቶች በተመለከተ ስልታዊ ተጨባጭ ምልከታ የማድረግ ተፈጥሯዊ ሂደት ነው። በሥርዓት ተደራጅቶ፣ ደረጃውን ጠብቆ፣ ተማሪዎችን ለመከፋፈል እና ለመከታተል ጥቅም ላይ ሲውል ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። ሁሉም የምዘና ውሳኔዎች በተደራጁ ግምቶች ላይ የተመሠረቱ እንደመሆናቸው፣ ግምቶቹ ከሚከተሏቸው ሥርዓተ ትምህርት እና ሥነ ትምህርት ግምቶች ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው።

ከትብብር እና ከአጋርነት ሥነ ትምህርት አንጻር ሲታሰብ፣ የትምህርት ባለሙያዎች ራሳቸውን ለመለካት የሚጠቅሙ እና የማይጠቅሙትን ትምህርታዊ ግቦች በግልፅ መለየት አለባቸው። አብዛኛው ጠቃሚ ትምህርት ሊለካ ወይም ሊቆጠር አይችልም፤ አንድ ነገር በቁጥር አይገለጽም ማለት ግን ትርጉም ያለው ዕድገት በፍፁም ሊታይ አይችልም ማለት አይደለም። ለምሳሌ የተማሪዎች ቡድን በድርድር፣ በግጭት አፈታት እና በሙከራ ሂደቶች ውስጥ ሲያስሱ እና በእነዚህ ሂደቶች ውስጥም የተለያዩ አመለካከቶችን የማዳመጥ፣ ገንቢ ትችቶችን የመስጠት እና የመቀበል አቅማቸውን ሲያሳድጉ፣ እንዲሁም አንዳቸው ለሌላው አስተዋጽኦ ሰፊ ዕድሎችን ሲሰጡ የትብብር ግብ በተጨባጭ ሊስተዋል ይችላል።

በርካታ የምዘና ንድፈ ሐሳቦች አሉ፤ በሚቀጥሉት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ በአከራካሪነታቸው ይቀጥላሉ። የትምህርት ባለሙያዎች እና ፖሊሲ አውጪዎች እያንዳንዱ ፈተና፣ ምዘና እና ሚዛን ሥነ ትምህርታዊ አሻራ እንደሚተው ማስታወስ አለባቸው። የትምህርት ቤቶችን እና የመምህራንን ሥነ ትምህርታዊ ምርጫዎች ስለሚገድቡ፣ ውድድርን ስለሚያበረታቱ እና የትብብር እና የአብሮ ግንባታ ዕድሎችን ስለሚቀንሱ፤ በለጋ ተማሪዎች ላይ አስቸጋሪነታቸው እየጨመረ የሚሄዱ የፈተና ሥርዓቶችን ጫና መቃወም ግድ ነው። በእርግጥ አንዳንድ የውድድር መልኮች ተማሪዎች በግልም ሆነ በጋራ ከፍተኛ የልህቀት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ሊያበረታቱ ይችላሉ። ነገር ግን፣ መምህራን ከሩቅ እና ከማይታወቁ ማነጻጸሪያዎች ጋር ለሚዛመዱ ውጫዊ ግፊቶች ምላሽ ከመስጠት ይልቅ፣ የውድድር እንቅስቃሴዎችን ለየት ያሉ ሥነ ትምህርታዊ ግቦችን ለማሳካት መቼ መዋል እንደሚችሉ የመወሰን ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል።

ልኬት እና ምዘና የትምህርትን ተፅእኖ ለመረዳት ጠቃሚዎች ቢሆኑም፤ አመላካቾቻቸው ግን ተገቢ፣ ትርጉም ያላቸው እና በጥንቃቄ የታሰበባቸው መሆን አለባቸው። ብዙውን ጊዜ 'የጥላ ትምህርት' እየተባለ የሚጠራው ግል-ተኮር ትምህርት በዓለም አቀፍ ደረጃ መስፋፋት፣ ውስን በሆኑ የትምህርት ውጤት መለኪያዎች ላይ ማተኮር (ብዙውን ጊዜ የአጭር ጊዜ የማስታወስ ችሎታ እና ዝቅተኛ የግንዛቤ ችሎታን በማጉላት) ተማሪዎችን በግል እና በሕብረት የበለፀጉ ዓላማዎችን እንዲያሳኩ ለማዘጋጀት አስፈላጊ የሆነውን ሥርዓተ ትምህርት እንዴት እንደሚቀንስ ዋና ማሳያ ነው። መጪውን ጊዜ ስንመለከት፣ በትምህርት ውስጥ እያደገ የመጣው ውድድር የሚያመጣቸውን አሉታዊ ተፅእኖዎች፣ እና ከባድ ፈተናዎች ያስከተሉት ለገለጻ የሚሰጠውን ጠባብ ትኩረት መቀልበስ እንደሚያስፈልግ ግልጽ ነው።

# በእያንዳንዱ ዕድሜ እና ደረጃ ላይ ያሉ ሥነ ትምህርታዊ ጉዞዎች

አሳታፊ እና የትብብር ሥነ ትምህርቶች በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች እንዲሁም በሁሉም መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የትምህርት አውዶች ጠቃሚ ናቸው። ምንም እንኳን የትብብር እና የሥነ ትምህርታዊ አብሮ ግንባታ ዕድሎች እንደየሰው ልጅ አካላዊ እና አእምሯዊ የዕድገት ደረጃዎች የሚለያዩ ቢሆንም፤ እነዚህ ትምህርቶች በየትኛውም የሕይወት እርከን ላይ ሊገኙ ይችላሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የትምህርት እርከኖች ብዙውን ጊዜ የለጋ ልጅነት፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ትምህርት ተብለው ይከፋፈላሉ። ምንም እንኳን ብዟይነት የሰው ልጅ የማሰብ ችሎታዎች ቢኖሩም፣ እና በሰዎች ፍላጎቶች እና የመማር መንገዶች መሀል ብዙ ልዩነቶች ቢኖሩም፤ ደግሞም ሰዎች በቀጥታ ባይዳብሩም፣ ትምህርትን ለመደገፍ ለዕድገት ተስማሚ የሆኑ መንገዶች አሉ፤ በተማሪዎች መካከል ልዩነቶችን ለማክበር እና ትምህርትን ሰዋዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አዋጭ

መንገዶች አሉ። ትምህርት በተለያዩ ደረጃዎች ይቀጥላል የሚለው የተለመደ አስተሳሰብ ለሁሉም ተደራሽ መሆን ያለበትን በዓላማ የተሞላ ጉዞን ያመለክታል። የዚህ ምዕራፍ ቀሪው ክፍል ዋና ትኩረቱን አሳታፊ እና የትብብር ሥነ ትምህርቶች ተግባራዊ የሚቻልበት መንገድ ላይ አድርጎ፤ በየእርከኑ እና በየሕይወት ኡደት ደረጃው የሚያጋጥሙትን ሥነ ትምህርታዊ ተግዳሮቶች እና ዕድሎች ጠለቅ ብሎ ይመለከታል።

## የለጋ ልጅነት መሠረቶችን መደገፍ

ሕፃናት ዓለምን በሚያድሱ ዓይኖች የማየት ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል። በሕፃን አቅም ነገሮችን እንዳዲስ ማየት የሚችሉት ጥቂቶች ናቸው። ሕፃናት ለሌሎች ሰዎች ተመክሮዎች የሚሰጡት ትኩረት እና ለማይታወቀውና ዕድሎችን ላረገዘው ዓለም የሚያሳዩት ጉጉት በሁሉም ዕድሜ ላሉ ሰዎች ምሳሌ ይሆናል። የአዳዲስ ጅማሮዎች አቅም ላለው ለዚህ ወቅት የምናሳየው ቁርጠኝነት የለጋ ሕፃናት ትምህርት እና በእርግጥም የሁሉም የትምህርት አውዶች መገለጫ መሆን አለበት።

ጥራት ያለው የለጋ ሕፃናት ትምህርት በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። በሰው ልጅ ሕይወት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ የአካል፣ የግንዛቤ፣ የማኅበራዊ እና የስሜታዊ ዕድገቶች የሚከናወኑበት ከፍተኛ መጠን ያለው የአንጎል ተቀራጭነት የሚታይበት እና የዕድገት ጊዜ ነው። ጠንካራ የትምህርት ምርምር ውጤት እንደሚያመለክተው፣ የለጋ ሕፃናት ትምህርት አስፈላጊነት የሚመነጨው ለሁሉም የወደፊት ትምህርት እና ስኬት ቁልፍ መሠረት ከመሆኑ ነው።

በትብብር እና እርስበርስ በመደጋገፍ ላይ የተቃኘ ሥነ ትምህርታዊ አቅጣጫ በአብዛኛው የለጋ ሕፃናት ትምህርት ከግንዛቤ ገብቷል። በዚህ ደረጃ የሰዎች ጥብቅ ትስስሮች፣ ኀሣሳ እና ጨዋታ ጉልሕ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። የዕድገት ቀዳሚ ሁኔታዎች ከጊዜ በኋላ ከሚዳብሩት ችሎታዎች እና ዝንባሌዎች ጋር የግድ ተመሳሳይ ላይሆኑ እንደሚችሉ ማስታወስ ያፈልጋል። አንዳንድ ምርጥ ሳይንሳዊ ጥያቄዎች በቀላል ተማርኮ፣ ለምሳሌ በነፍሳት ከመማረክ፣ ሊመነጩ ይችላሉ። ምናባዊ የሚና ጨዋታ ለተራቀቀ ዕውቀት እና ክህሎት ትልቅ መሠረት ሊሆን ይችላል። የለጋ ሕፃናት ትምህርት ባለሙያዎች እንደሚነግሩን፣ የማይረባ ጨዋታ የሚመስለው ድርጊት ብዙውን ጊዜ በጣም ከባድ ራስን እና ዓለምን የመረዳት ሥራ ሆኖ ይገኛል።

አሁን በፕላኔቷ ላይ እየተጋረጡ ያሉት የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ተግዳሮቶች የለጋ ሕፃናት ትምህርት ላይ ጉልሕ ተጽዕኖዎች አሏቸው። ምንም እንኳን በብዙ ቦታዎች ግለሰብ ተኮር ሕፃናትን ያማከሉ የትምህርት አሰጣጦች እየገነኑ ቢመጡም፣ እነዚህ አካሄዶች ሕፃናት እንደማንኛውም ሰው ከሰው በላይ የሆነው ዓለም አካል መሆናቸውን በሚያንጸባርቅ መልኩ መከለስ አለባቸው። የለጋ ሕፃናት ትምህርት ልጆች ከቦታ እና ከሌሎች ሕያዋን ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት በማዳበር ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ሕፃናት በወደፊት ዓለማት ውስጥ በጥሩ ሁኔታ እንዲኖሩ በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍ፣ አመዛዛኝነት፣ ጠያቂነት እና አዳዲስ ዕድሎችን መፍጠር ላይ ያተኮሩ የለጋ ሕፃናት ሥነ ትምህርቶችን መደገፍ አለብን።

በዚህ ደረጃ በቤት እና በትምህርት ቤት መካከል ያለው ግንኙነት በጣም ጠንካራ ነው። ቤተሰቦች ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፤ ስለዚህ የልጆችን መበልጸግ እና በአካላዊ፣ ማኅበረ-ስሜታዊ እና በግንዛቤ ማደግ እንዲያግዙ ራሳቸውም ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። የሰው ልጅ ትምህርት ዕውን የሚሆነው ከአካባቢው ጋር በሚኖረው ቀጣይነት ባለው ግንኙነት መሆኑን እናውቃለን። ተስማሚ የትምህርት አከባቢዎች ለለጋ ሕፃናት እና ትንንሽ ልጆች በአገራቸው ቋንቋ (ወይም ቋንቋዎች) በቂ ማነቃቂያ ይሰጣሉ። የጋራ መጽሐፍ ንባብ እና በዕለት ተዕለት መስተጋብር ውስጥ የተመረጡ ቃላትን መጠቀም የትምህርት መሠረታዊ አካል የሆኑትን የማንበብ እና መጻፍ ክህሎቶችን ለማዳበር ይረዳል። ልጆችን ከቴሌቪዥኖች፣ ታብሌቶች ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ጋር ማቆራኘት ለሚያስፈልጓቸው የላቁ መስተጋብራዊ ማኅበራዊ ተመክሮዎች የሚቀርብ ደካማ መተኪያ ነው። መንግሥታት እና የንግድ ድርጅቶች የወላጅ ፈቃድ ፖሊሲዎችን ማጠናከር አለባቸው። ለወላጆች እና ቤተሰቦች ድጋፍ ያለው እና የለጋ ሕፃናት ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ የላቀ የሚሆነው፣ የሕፃናት መዋያ ማዕከላት፣ አቢያተ መጻሕፍት፣ ሙዚየሞች፣ የማኅበረሰብ ማዕከላት እና መናፈሻዎች ጥሩ የገንዘብ ድጋፍ ሲደረግላቸው እና እንደ ወሳኝ የሕዝብ አገልግሎቶች ሲቆጠሩ ነው። “ልጅን የሚያሳድገው መንደር ነው” የሚለው አባባል እንደተርታ የተቆጠረው ከመጠን በላይ ጥቅም ላይ በመዋሉ ቢሆንም፤ ከፊል ምክንያቱ፣ ዋናው ሐሳቡ ከብዙዎች ጋር በጣም ስለሚስማማ ነው፦ የለጋ ሕፃናት ትምህርት አብረን የምናሳካው ነገር ነው።

ከፋቱ፣ በብዙ ማኅበረሰቦች ውስጥ የለጋ ሕፃናት ትምህርት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ያህል የሕዝብ ኃላፊነት ተደርጎ አይወሰድም። በቂ ወይም ብቁ የለጋ ሕፃናት ማዕከሎች የሉም። በዚህ ደረጃ ያሉ መምህራን ሥራቸው አካላዊ እንክብካቤ መስጠት ብቻ ተደርጎ ስለሚወሰድ ክፍያቸው ዝቅተኛ ነው። በዚህም የተነሣ በጣም ጉልህ የሆኑ አለመመጣጠኖች የያጋጥሙት በለጋ ሕፃንነት እርከን ነው፤ ምክንያቱም ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ እና ከፍተኛ ሀብት ያላቸው ቤተሰቦች በዚህ ዕድሜ ያሉ ልጆቻቸው ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ተመክሮ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፤ ይሄ ደግሞ በቂ የገንዘብ ድጋፍ በሌላቸው፣ ዝቅተኛ ክፍያ ስለሚከፈላቸው በደንብ የማይዘጋጁ መምህራን ባሉባቸው የመንግሥት ማዕከላት የሚማሩ ሕፃናት የማያገኙት ተመክሮ ነው። መንግሥታት ሁሉም ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ የሕፃናት ትምህርት፣ አካላዊ እና አእምሯዊ ዕድገት ለማረጋገጥ ጥራት ላለው የለጋ ሕፃናት ትምህርት በቂ እና ዘላቂ መንግሥታዊ የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን ማረጋገጥ አለባቸው።

ሕብረተሰቦቻችንን የሚከፋፍሉትን ሥር የሰደዱ አለመመጣጠኖች እና ጭፍን ጥላቻዎች የምንማራቸው ከለጋነት ጀምሮ፣ ብዙ ጊዜ ከቀጥታ መመሪያ ይልቅ በምልከታ ነው። ለምሳሌ፣ በለጋ ሕፃናት ትምህርት የወንዶች መምህራን ምጣኔ በአማካይ ከ2 በመቶ ያነሰ ሆኖ ቢቀጥል፤ ወንዶች ልጆች ሲያድጉ የለጋ ሕፃናት እና የተጋላጮች ተንከባካቢ ለመሆን መመኘት እንደማይገባቸው በተዘዋዋሪ ይማራሉ። የቤት እና ከአያት ቅድመ አያት የተወረሱ ቋንቋዎች በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ውስጥ መሳጭ ሆነው ካላገኟቸው፤ ልጆች ከቤተሰብ አባላት ጋር የሚኖራቸውን ውድ መተሳሰሪያ እና በቦታ እና በጊዜ ውስጥ ከቅርሶቻቸው ጋር የሚያገናኟቸውን የማወቅያ እና የመግባቢያ ባሕላዊ መንገዶች ሊያጡ ይችላሉ። ትምህርት ቤቶች በግድ በማዋሐጃ እና በመጨቆኛ መሳሪያነት ባገለገሉባቸው በብዙ ማኅበረሰቦች፣ ጨቋኝ ተቋማትን ለማቃናት እና ለመዝጋት በጣም አስፈላጊ ለውጦች ተካሂደዋል። የወደፊት የለጋ ሕፃናት ትምህርቶች ባሕላዊ ማግለል እና ጭፍን ጥላቻን እንዳያስቀጥሉ ለማድረግ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። የለጋ ሕፃናት ሥነ ትምህርቶች ግለሰባዊ እና የጋራ ባሕላዊ ማንነቶችን ማረጋገጥ እና ማጠናከር፣ እንዲሁም ስብጥርን በማድነቅ ላይ የተመሠረተ በይነ-ባሕላዊ ውይይትን ማበረታታት አለባቸው።

## ትብብራዊ ትምህርት ለሁሉም ሕፃናት

ከ1990 እስከ 2020 ባለው ጊዜ ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት ረገድ መጠነ ሰፊ መስፋፋት ቢኖርም፣ በሁሉም የትምህርት ዘርፍ ጥራትን ለማጠናከር እና አሳታፊ እና የትብብር ሥነ ትምህርቶችን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ መሥራት አለበት።

ከፋቱ፣ በጣም ብዙ ትምህርት ቤቶች እና ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ ሕፃናት ወደ ከፍተኛ ክፍል ሲሸጋገሩ እና የመጫወት፣ የመመርመር፣ የመተባበር እና የመገናኘት ዕድሎቻቸው ስለሚያንሱ፣ የለጋ የልጅነት ተፈጥሯዊ የማወቅ ጉጉት እና የመጠየቅ ዝንባሌዎቻቸው እየቀነሱ ይሄዳሉ። ስለሁሉም ጥበባት እና ሳይንሶች ውስጥ ከተገኙ አዳዲስ ግንዛቤዎች እና ክህሎቶች በመነሣት በግለሰብ ደረጃ የሚደረጉ ልምምዶች ዋጋ ሊካድ አይችልም። ነገር ግን በአንደኛ ደረጃ ለተናጥል ተግባር የሚውል በጣም ብዙ ጊዜ የአብሮ ግንባታ፣ የትብብር እና የችግር መፍታት ቁልፍ ዕድሎችን ይገድባል ሊባል ይችላል።

ያም ሆኖ፣ በትምህርት ቤቶች እና በመደበኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ እና ከእነሱም ውጭ በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ የትብብር እና የሕብረት ሥነ ትምህርታዊ ተነሣሽነቶች እየጨመሩ ነው። በአንዳንድ ቀጣናዎች፣ የማኅበረሰብ ትምህርት ቤቶች አዳዲስ የትምህርት ዕድሎችን እና አካባቢያዊ ችግር ለመፍታት ማኅበረሰቦች ከባሕል ሀብቶቻቸው አመንጭተው የፈጠሯቸው ምላሾች ሆነው ይገኛሉ። በሌሎች ሁኔታዎች፣ አንዳንድ ጊዜ “መደበኛ ያልሆኑ” ተብለው የሚታወቁት፣ ከትምህርት ቤቶች ጋር በአጋርነት የሚከናወኑት ትምህርታዊ መርሐ ግብሮች፣ ከአገር ሽማግሌዎች፣ የማኅበረሰብ መሪዎች እና ዕውቀት ጠባቂዎች ጋር በመሥራት ለትብብር ትምህርት እና ለባሕላዊ ግንዛቤ የሚያግዙ ዕድሎችን ያጠናክራሉ።

## የታዳጊዎችን እና የወጣቶችን አቅም ማጎልበት

ወጣቶች ዛሬ በዓለም ዙሪያ የተለያዩ ዕውነታዎች ያጋጥሟቸዋል። እነዚህም የመማር መብቶቻቸውን የማግኘት፣ ከጥቃት የመጠበቅ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ያለዕድሜ ጋብቻ ሥጋቶቻቸውን እና በቤተሰብ ኑሮ ላይ የሚደርሱ ጫናዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣትን ያጠቃልላል። ሌሎች ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ የመጡት ማኅበራዊ መነጠል፣ የአእምሮ ጤና ችግሮች እና የማንነት እና የዓላማ ቀውሶች ያጋጥሟቸዋል። ባለፉት ጥቂት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ ትምህርት ጤናማ ማኅበራዊ መስተጋብርን፣ የአቻ ግንኙነቶችን እና በአሁን እና ወደፊት በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ የባለ ዓላማነት ስሜትን በማጎልበት በዚህ የሕይወት እርከን የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ለማቃለል በተለያዩ ደረጃዎች ረድቷል። በሌሎች አጋጣሚዎች ግን፣ ትምህርት አካዳሚያዊ ጫናዎችን እና ማኅበራዊ መነጠልን በማብዛት ተግዳሮቶቹን አባብሷል።

የወጣትነት ጊዜ ከለጋ የልጅነት ጊዜ ጋር የሚነጻጸረው በጥቂት ዓመታት ወይም ወራት ውስጥ በሚከሰቱበት ከፍተኛ አእምሯዊ እና አካላዊ ለውጦች ብቻ ነው። ወጣቶች ጉልሕ አእምሯዊ እመርታዎች ቢያሳዩም፤ የአዋቂነትን ሙሉ ኃላፊነት ለመረከብ ወይም ለወደፊቱ ለመዘጋጀት ዝግጁ መሆናቸውን የሚወስኑት ባሕላዊ ግምቶች እና ፍልስፍናዎች ሊለያዩ ይችላሉ። ትምህርት ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ለመሥራት የሚያስችል ዕድል ሊሰጥ ይችላል - ትርጉም ባላቸው መንገዶች በዓለም ጉዳዮች የሚሳተፉባቸውን በቂ ዕድሎች እየሰጠ ይፈትናቸዋል።

ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ፍላጎታቸውን የሚያጠሩት፣ ተሰጥኦዎቻቸውን የሚከተሉት እና ጥሪያቸውን የሚሹበትን ሙያ የሚለዩት በዚህ የሕይወት እርከን ነው። በንድፈ ሐሳብ እና በተግባር መካከል፣ ማለቂያ የሌለው በሚመስለው ዝግጅት እና ትርጉም ባለው ተመክሮ መካከል ያለውን ልዩነት ማጥበብ እና ጠንካራ የዓላማ ግንዛቤ መፍጠር ለዚህ እርከን ወሳኝ የሥነ ትምህርት ግቦች ናቸው። ብዙውን ጊዜ በጠንካራ የፍትሕ ስሜታቸው የሚታወቁት ወጣቶች፣ የአዋቂዎችን ግብዝነት ጠንቅቀው ያውቃሉ። ከዚህ አንጻር፣ ወጣቶችን በተፈጥሯቸው አስቸጋሪ፣ ዐመፀኞች ወይም ለማኅበራዊ ጥቅም አደገኛ ናቸው ብለው የሚፈርጁ ጎዶሎ ትረካዎች ጎጂ እና በተለይ በዚህ ወሳኝ፣ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ፈታኝ በሆነው የሽግግር ዕድሜ ሊኖር የሚገባውን የበይነ-ትውልዳዊ ትብብር እና የድጋፍ ዕድሎች ይገድባሉ። ከዕድል አንጻር ሲታይ፣ የወጣቶችን አስደናቂ እምቅ አቅም በበቂ ሁኔታ ማውጣት እየቻሉ ያሉት ጥቂት ውድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መርሐ ግብሮች ብቻ መሆናቸው ግልጽ ነው።

> *ከጊዜ ወደ ጊዜ በወጣቶች የሚመሩ ንቅናቄዎች ድርጅቶች ችግሮቹን በተለዩ መንገዶች ማየት ጀምረዋል።*

ነገር ግን፣ በመካሄድ ላይ ያለ ነገን መልሶ የማጤን ተስፋ ሰጪ ሥራም አለ። ከጊዜ ወደ ጊዜ በወጣቶች የሚመሩ ንቅናቄዎች ድርጅቶች ችግሮቹን በተለዩ መንገዶች ማየት ጀምረዋል። “ዓርብን ለወደፊት”፣ “የፀሐይ መውጣት ንቅናቄ” እና ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ተመሳሳይ ዓለማቀፍ ጥረቶች ለተለየ ዓይነት ወደፊት የሚደረጉ ልምምዶች ናቸው። በበርካታ የላቲን አሜሪካ እና የደቡብ እስያ ሀገራት - ከተማን ያማከለውን ሞዴል ከማስቀጠል ይልቅ - የተገለሉ የገጠር ወጣቶችን እንደ መነሻ የሚወስዱ የትምህርት ሥርዓቶች እና ሥነ ትምህርቶች ተከለው፣ ወጣቶች እና ታዳጊዎች በአገር በቀል እና በጥንታዊ ልማዶቻቸው የሚኮሩበትን መንፈስ እየፈጠሩ ነው። እነዚህ እና ሌሎች በርካታ ምሳሌዎች ትምህርት ወጣቶችን በመደገፍ የበለጠ ሰፊ የበለፀገ እና ፍትሐዊ የወደፊት ዕድሎችን እንዲፈጥሩ የማስቻል አቅም እንዳለው ማሳያዎች ናቸው።

# የከፍተኛ ትምህርትን ተልእኮ ማደስ

ዕውቀትን ከማምረት እና ከማሰራጨት ጎን ለጎን፣ ትምህርት የዩኒቨርስቲ ዋና ተልእኮ አካል ቢሆንም፤ በብዙ ቦታዎች ግን ከቅርብ ዐሥርት ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ ትምህርት በሚደራጅበት፣ ዕውቅና በሚያገኝበት እና የገንዘብ ድጋፍ በሚያገኝበት መንገድ ምክንያት ይህ ተልእኮ ቸል ተብሏል። በአንዳንድ ቦታዎች፣ ፕሮፌሰሮች የሚገመገሙት በግለሰብ ውጤታቸው ላይ ብቻ ነው፤ ይህም ምርት ተብሎ የሚታሰብላቸውን ውጤት በማስተማር፣ በማማከር፣ በአቅም ግንባታ እና ሊያገለግሉት ከሚገባው ማኅበረሰብ ጋር ሊኖሩ የሚገቡ የትብብር ግንኙነቶችን በማጎልበት በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከሚለካው ጥራት፣ ተገቢነት እና ዋጋ አስበልጦ የማየት ምልክት ነው።

ሥነ ትምህርት በብዙ ዩኒቨርስቲዎች ዘንድ ወደ ጀርባ ተገፍቷል። የወደፊት ዩኒቨርስቲዎች ይህንኑ መንገድ ተከትለው፣ የማስተማር ተግባራትን ወደ ሌሎች ተቋማት ወይም በተራቀቁ የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂዎች ወደተሟሉ ልዩ ማዕከላት ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ወደፊት የበይነ-ትውልዳዊ ትምህርት ተልእኮ ዋና ሆኖ፣ ሁልጊዜም ከዕውቀት እና ምርምር ጋር የሚተሳሰርበት የዩኒቨርስቲ መታደስ ይመጣል ብሎ መገመትም ይቻላል። የቴክኒክ እና የሙያ ተቋማት አንዳንድ ጊዜ የዚህን ፔንዱለም ሌላኛውን ገጽ ይጋፈጣሉ - ማስተማር ብዙውን ጊዜ በሥልጠና እና በቴክኒክ ብቻ የተገደበ ነው፤ ስለዚህ ጥልቅ ማኅበራዊ፣ ሥነ ምግባራዊ እና ፅንሰ ሐሳባዊ ጥያቄዎች ከአድማሳቸው ውጭ ይተዋሉ። ሆኖም ለግል እና ለጋራ የወደፊት እጣ ፈንታዎቻችን በጣም ወሳኝ የሆኑ የማምረት አቅሞችን ማዳበር እና መተግበር ጥልቅ ግንዛቤን፣ ተወዳዳሪ ክህሎቶችን እና አስተዋይ አመለካከቶችን ለማዳበር እንደዳበረ የሥነ ትምህርት መስክ መታየት አለበት።

የከፍተኛ ትምህርን ትምህርታዊ ተልእኮ ለማደስ ከአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጋር ጠንካራ ትስስር መፍጠር እና ከተለምዷዊው የገለጻ እና ከሚወክለው የዕውቀት ማስተላለፍ ሞዴል ያለፉ ሥነ ትምህርታዊ ስልቶችን መተግበር ያስፈልጋል። የተማሪዎች የትብብር ሥራ፣ የምርምር ፕሮጀክቶች ልማት፣ ችግር መፍታት፣ ግለሰባዊ ጥናት፣ የሴሚናር ውይይት፣ የመስክ ጥናት፣ ጽሑፍ፣ የድርጊት ጥናት፣ የማኅበረሰብ ፕሮጀክቶች - እነዚህ እና ሌሎች በርካታ ሥነ ትምህርታዊ ቅርጾች ከፍተኛ ትምህርትን ዘልቀው መግባት አለባቸው። ሥነ ትምህርትን መልሶ ወደ ፊት ለማጣት ለፕሮፌሰሮች የማስተማር ሥራ የበለጠ ዋጋ መስጠት እና ሥነ ትምህርታዊ ሥልጠናቸውን እና ዕድገታቸውን መደገፍ ያስፈልጋል።

እንደ መከባበር፣ መተሳሰብ፣ እኩልነት እና አጋርነት ያሉ እሴቶች ወደፊት የዩኒቨርስቲዎች፣ የኮሌጆች እና የቴክኒክ ተቋማት ተልእኮዎች አንኳር ጉዳዮች መሆን አለባቸው። ከፍተኛ ትምህርት ሥነ ምግባርን ማበረታታት እና ተማሪዎች ስለ የዜግነት እና አካባቢያዊ ኃላፊነቶቻቸው የበለጠ ግንዛቤ ያላቸው የተሻሉ እና የበቁ ዜጎች እንዲሆኑ መደገፍ አለባቸው። ከፍተኛ ትምህርት ማኅበረ-ባሕላዊ አግባብነት ያለው መሆን አለበት። የባሕል ስብጥርን ማድነቅ፣ ሰብአዊ መብቶችን ለማስጠበቅ ቁርጠኛ መሆን፣ እና ዘረኝነትን፣ ጾታዊ አድልዎን፣ መደባዊ አድልዎን፣ ጎሰኝነትን እና ሁሉንም ዓይነት አድልዎ መቃወም ቁልፍ የትምህርት ዓላማዎች መሆን አለባቸው። እንደዚህ ያሉ እሴቶችን እና መርሆዎችን የሚያራምድ ከፍተኛ ትምህርት ከገለጻ አዳራሾች እና ቨርቹዋል ማስተማርያ መድረኮች ወሰን አልፏል። ግለሰቦች ከነበሩበት የተሻሉ እንዲሆኑ፣ ጠንካራ የእሴት ሥርዓቶችን ወደፊት እንዲያራምዱ እና ከባቢያቸውን እንዲቀይሩ ስለሚያስችል፣ በይዘቱ በየጊዜው እያደገ ነው።

# የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች

ይህ ምዕራፍ በአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ውስጥ ሥነ ትምህርት ተማሪዎች ዓለምን ለመለወጥ በትብብር የሚሠሩባቸውን አቅሞች በሚገነቡ የትብብር እና የአጋርነት መርሆዎች ዙሪያ መደራጀት እንዳለበት ሐሳብ አቅርቧል። 2050ን አሻግረን ስንመለከት፣ ይህንን ምክረ ሐሳብ ወደፊት ለማራመድ የሚያስፈልጉትን ውይይቶች እና ድርጊቶች ለመምራት አራት መርሆች አሉ፡-

- **እርስበርስ መተሳሰር እና መደጋገፍ የሥነ ትምህርት መለያዎች መሆን አለባቸው።** በመምህራን፣ በተማሪዎች እና በዕውቀት መካከል ያሉት ግንኙነቶች በሰፊው ዓለም ውስጥ ይገኛሉ። ሁሉም ተማሪዎች ከዓለም ጋር የተያያዙ ናቸው፤ ሁሉም ትምህርት የሚከናወነው ደግሞ በዓለም ውስጥ እና ከዓለም ጋር ነው። ተማሪዎች የሌሎች ሰዎች ድርጊቶች እንዴት ተጽዕኖ እንዳላቸው እና የራሳቸውም ድርጊቶች በሌሎች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ሊማሩ ይገባል፤ በዚህም ምክንያት መማሪያ ክፍሎች እና ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ከእነሱ ከተለዩ ሌሎች ሰዎች ጋር እንዲገናኙ ማድረግ አለባቸው።
- **ትብብር እና ሕብረትን በተለያዩ እርከኖች እና ዕድሜዎች በተገቢው መንገድ ማስተማር እና መተግበር ይገባል።** ትብብር እና ሕብረት የትምህርት ማኅበረሰቦችን መገለጫ ባሕርያት ከሆኑ፣ ትምህርት ግለሰቦች ራሳቸውን እና ዓለምን ለመለወጥ በጋራ ለመሥራት ያላቸውን አቅም ይገነባል። ይህ በጎልማሶች ትምህርትም ሆነ በለጋ ሕፃናት ትምህርት ይሠራል።
- **አጋርነት፣ ርህራሄ፣ ሥነ ምግባር እና መተሳሰብ በመማማርያ መንገዶቻችን ውስጥ ሥር ሊሰድዱ ይገባል።** የሰው ልጅን የባሕል ሀብቶች ስብጥር በሙሉ ወደ ትምህርት ተቀብለን፤ ጥረታችንን ስብጥርን እና ብዝኃነትን ከመመዘን ወደ መደገፍ እና ማዝለቅ ማስፋት አለብን። ማስተማር የተማሩትን ማዳላት፣ ጭፍን ጥላቻ እና መለያየትን አለመማር ላይ ማተኮር አለበት። ርህራሄ - ለሌሎች መድረስ እና ስሜታቸውን የመጋራት ችሎታ - የአጋርነት ሥነ ትምህርቶችን ለመገንባት አስፈላጊ ነው።
- **ምዘና ከነዚህ ዓላማዎች ጋር ሊጣጣም እና ለተማሪ ዕድገት እና ለትምህርት ትርጉም ሊኖረው ይገባል።** ፈተናዎች፣ ሙከራዎች እና ሌሎች የምዘና መሳሪያዎች ከትምህርታዊ ግቦች እና ዓላማዎች ጋር መስማማት አለባቸው። አብዛኛው ጠቃሚ ትምህርት በቀላሉ ሊለካ ወይም ሊቆጠር አይችልም። የተማሪዎችን መማር የሚያበረታቱ በአስተማሪ የሚመሩ መሠረታዊ ምዘናዎች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል። ፉክክርን የሚያበረታታ፣ ፈታኝነቱ የከበደ ደረጃ ያለውን ምዘና አስፈላጊነት መቀነስ አለብን።

በ2050 የትብብር እና የአጋርነት ሥነ ትምህርቶችን ለሁሉም ሰው ተደራሽ ለማድረግ በአካባቢ፣ በአገር አቀፍ፣ በክፍለ ዓለም እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁላችንም በጋራ መሥራት አለብን።

# ምዕራፍ 4

# ሥርዓተ ትምህርት እና እያደገ ያለው የጋራ ዕውቀት

*ግልጽ የሆነው ችግር ሰዎች ትምህርት በትክክል ምን እንደሆነ አለማወቃቸው ነው። በስቶክ ልውውጥ ገበያ ላይ ያለውን የመሬት ወይም የአክሲዮን ዋጋ በምንመዝንበት መንገድ የትምህርትን ዋጋ እንመዝናለን። ተማሪው የተሻለ ገቢ እንዲያገኝ የሚያስችለውን ትምህርት ብቻ መስጠት እንፈልጋለን። የተማሩ ሰዎችን ባሕርይ ስለማሻሻል ምንም ያህል አናስብም። ልጃገረዶቹ ገቢ ማግኘት የለባቸውም እንላለን፤ ታዲያ ለምን ይማራሉ? እንደዚህ ዓይነት ሐሳቦች እስከቀጠሉ ድረስ የትምህርትን ትክክለኛ ዋጋ የማወቅ ተስፋ የለንም።*

ማህትማ ጋንዲ፣ 'True National Education', 1907.

**በአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል፣ ሥርዓተ ትምህርቶች በጋራ ዕውቀት ሀብት ላይ ተመሥርተው በማደግ፤ ተማሪዎች የመመርመር እና የመተግበር አቅማቸውን በማጎልበት ዕውቀትን እንዲያገኙ እና እንዲያፈሩ የሚያግዝ ሥነ ምህዳራዊ፣ ባሕላዊ እና በይነ-ዲሲፕሊናዊ ትምህርትን ማካተት አለባቸው።**

በትምህርት እና በሚያዳብረው ዕውቀት፣ አቅም እና እሴት መካከል አዲስ ግንኙነት መፈጠር አለበት። ይህም ተማሪዎች ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ እና ዘላቂ ዓለም እንዲገነቡ የሚያስችላቸውን አቅም እና ዕውቀት በመፈተሽ የሚጀምር እና እነዚያን አቅሞች እንዲያዳብሩ ወደሚረዷቸው የሥርዓተ ትምህርት መንገዶች የሚመለስ ነው። አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን በጋራ ለመሥራት በተቻለ መጠን ከተለመደው የትምህርት ዓይነቶች ፍርግርግ ውጭ ስለ ሥርዓተ ትምህርት ማሰብ አለብን። የሥርዓተ ትምህርት ጥያቄዎች ብቃትን በመገንባት እና ሁልጊዜ በትምህርት ውስጥ በሚገኙት ሁለት ወሳኝ ሂደቶች ማዕቀፍ መዘጋጀት አለባቸው፦ ዕውቀትን እንደ የሰው ልጅ የጋራ ቅርስ አካል ማሳካት እና አዲስ ዕውቀት እና አዲስ ዓለምን በጋራ መፍጠር።

ስለ ምን እና እንዴት ማስተማር እና መማር እንደሚቻል የሚያሳዩ አዝማሚያዎች እና ንድፈ ሐሳቦች በዝተዋል። የመማሪያ ንድፎች ልጅ-ተኮር ወይም የትምህርት ዓይነት-ተኮር፣ ተማሪ-ተኮር ወይም አስተማሪ- ተኮር ሆኖ ሊቀረጽ ይችላል። ዕውቀት እንደ አካዳሚያዊ ወይም ተግባራዊ፣ ሳይንሳዊ ወይም ሰዋዊ፣ አጠቃላይ ወይም ልዩ ተብሎ ሊመደብ ይችላል። እያንዳንዱ አቀራረብ የሚሰጠው ነገር ቢኖረውም፣ ዕውቀት ከዓለም ጋር ያለውን መስተጋብር ውስብስብነት ለማንጸባረቅ አዳዲስ አቋሞች እና አተያዮች ያስፈልጋሉ። የትምህርት ባለሙያዎች የዕውቀትን አገኛኘት ሲያጤኑ በአንድ ጊዜ ሁለት ጥያቄዎችን መጠየቅ አለባቸው፦ ምን ሊማሩ ይገባል እና ከተማሩትስ የቱን አለመማር ይገባል? ይህ በተለይ፣ ዋናው የልማት እና የኢኮኖሚ ዕድገት አቋም ከሥነ ምህዳር ቀውስ አንጻር እንደገና መጤን ባለበት በዚህ ወሳኝ ወቅት ላይ በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነው።

*ምን ሊማሩ ይገባል እና ከተማሩትስ የቱን አለመማር ይገባል?*

ይህ ምዕራፍ እነዚህን ጥያቄዎች የቃኘው ስለ የጋራ ዕውቀት አጭር ውይይት በማድረግ፣ የጋራ ዕውቀት የሰው ልጅ ሁሉ ውርስ ሆኖ እንደገና እንዲታሰብበት እና በማድረግ፣ የተለያዩ የማወቂያ እና የመገንዘቢያ መንገዶችን አካቶ እንዲሰፋ በመሞገት ነው። እዚህ ለዕውቀት ትኩረት የተሰጠው ይዘት የበላይ መሆን አለበት ለማለት አይደለም። ዕውቀት ሁልጊዜም በአፈጣጠሩ፣ በአተገባበሩ እና በአፈታተሹ እያደገ ነው። ይህ ምዕራፍ የሰው ልጅ የሚያጋጥሙትን ውስብስብ ጥያቄዎች እና ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚያስፈልጉትን ተጨማሪ ዕውቀቶች ለመፍጠር እና ለመተግበር የሚያስችሉ ሰፋፊ አቅሞችን ለመገንባት የጋራ ጥረት እንዲደረግ ግልጽ ጥሪ ያቀርባል።

ትምህርት የሚታወቀውን ይዘት እና ማወቂያ መንገዱን በተቀላጠፈ ሁኔታ ማቀፍ ይችላል። በይዘት መካን ከትግበራ፣ ከክህሎቶች ወይም ከችሎታዎች ዕድገት ጋር መወዳደር የለበትም። ይልቁንም፣ መሠረታዊ ዕውቀትና ክህሎቶች እርስበርስ ሊጣመሩ እና ሊደጋገፉ ይችላሉ። ለተወሰኑ ዐሥርት ዓመታት፣ የሥርዓተ ትምህርት ሙግቶች በይዘት ዕውቀት እና በብቃት መካከል ሲወዛገቡ ኖረዋል። በፕሮጀክት-ምሥርት እና በችግር-ምሥርት አካሄዶች የተገኙትን ለምሳሌ ስለ ወቅታዊ ችግሮች ጥልቅ ውይይት የማድረግ እና ሥርዓተ ትምህርትን ለተማሪዎች ተገቢነት እንዲኖረው የማድረግ ውጤቶችን ሳይተዉ ጠንካራ የዕውቀት አቀራረብን የሚደግፍ አዳዲስ አዳጊ አካሄዶችን ለማዋቀር ጊዜው አሁን ነው።

ምዕራፉ በጋራ ዕውቀት እና በሥርዓተ ትምህርት መካከል ያለውን መስተጋብር በመመልከት፣ እንደ ማንበብና መጻፍ፣ ማስላት፣ ሳይንሳዊ ምርምር፣ ሥነ ጥበብ እና ዜግነት ባሉ ብቃቶች ዙሪያ ያለውን የዕውቀት ውስጣዊ ትስስር መረዳት እንደሚያስፈልግ ይሞግታል። የጋራ ዕውቀት ተደራሽነትን ማሳደግ እና ለአየር ንብረት ለውጥ ትምህርት፣ ለሳይንሳዊ ምርምር እና ለሰብአዊ መብቶች ቅድሚያ መስጠትን ጨምሮ፣ ከሥርዓተ ትምህርት ቀራጮች እኩል ለመምህራን እና ለትምህርት ባለሙያዎችም ፍላጎት ባለው የ2050 የውይይት እና የተግባር መመሪያ መርሆች ይጠናቀቃል።

# የጋራ ዕውቀት ተሳትፎ

ሥርዓተ ትምህርት ዕውቀትን የሁሉም የሆነ ታላቅ የሰው ልጅ ስኬት አድርጎ ማየት አለበት። በተመሳሳይም ሥርዓተ ትምህርት የጋራ ዕውቀት ከፍትሕ አንጻር እርማት የሚያስፈልጋቸው ጉልሕ ማግለያዎች እና ለይቶ ምደባዎች መያዙን ከግምት ማስገባት አለበት። ዕውቀት ስለማይሟላ፣ የትምህርት ባለሙያዎች ተማሪዎችን ለተጨማሪ ዕውቀት አብሮ ፈጠራ መጋበዝ እና እንዲሳተፉ ማስቻል አለባቸው። በብዙ የትምህርት መስኮች፣ የዕውቀት ሽግግር ሁሉንም የሰው ልጆች እና የምንጋራውን የወል ደህንነታችንን ከማበልጸግ ይልቅ፣ መሰናክሎችን ከመትከል እና አለመመጣጠንን ከማባዛት ጋር የተያያዘ ነው። ሆን ተብሎ እና ታስቦበት ከዕውቀት ጋር ለሚደረግ ትስስር ቅድሚያ የሚሰጥ ትምህርት በዕውቀት፣ በግንዛቤ እና በጥገና ላይ የተመሠረተ ፍትሕን ለመገንባት ይረዳል።

የዕውቀት ተዋረድን በመቃወም፤ የሰው ልጅ የተለያዩ የሥነ ዕውቀት አተያዮች ሙሉ በሙሉ በማካተት ብቻ የሚመጡትን የፈጠራ፣ የድንበር ተሻጋሪነት እና የሙከረት ዕድሎችን ማዳበር አለብን። የውርስ ጭፍን ጥላቻ፣ የዘፈቀደ ተዋረዶች እና የብዝበዛ አስተሳሰቦች መገፋት አለባቸው። ትምህርት እያንዳንዱ ትውልድ የየራሱን ዓለም መልሶ የመፍጠር አስተዋጽኦ የሚያበረክትበትን በጋራ ዕውቀት ላይ የመገንባት ችሎታን ሊያሳድግ ይችላል። ሥርዓተ ትምህርት ከዕውቀት ጋር የመስተጋበር እና በዕውቀት ሥራም የመሳተፍ አቅማችንን ማዳበር እና ማጥራት አለበት። ለምሳሌ ማንበብና መጻፍ፣ ሥሌት እና ሳይንሳዊ ምርምር ሰዎች ዓለማቸውን ተረድተው እና አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ወሳኝ በመሆናቸው፤ በሁሉም ቦታ ሊስፋፉ እና ጥልቀት ሊኖራቸው ይገባል።

ክፍት እና የጋራ ሥርዓተ ትምህርቶችን የመቅረጽ አንዱ አካሉ የዲሲፕሊን እና የትምህርት ዓይነት ድንበሮችን እንደ ቋሚ ወይም አስፈላጊ ገደቦች የሚገነቡትን ጫናዎች መቋቋም ነው። ይልቁንም ስለ ዓለም ውስብስብነት እና ስለ ዕውቀት ሥርዓቶች ታሪካዊ ጥራት ለማሰብ አቅሞቻችንን መጠቀም ይሻላል። ይህንን የብዝሃነት እና የተሻጋሪነት አመለካከት ወደ ሥርዓተ ትምህርት ማምጣት በአዲስ እና ውጤታማ አቅጣጫዎች ላይ ጠንካራ የዕውቀት መሠረቶችን እንድንገነባ ያግዘናል።

በእነዚህ ሁሉ አስፈላጊ የሥራ ዘርፎች ሥርዓተ ትምህርት መቼም ቢሆን "በተሟላ ዕውቀት" የተደራጀ እንደማይሆን፣ ይልቁንም የተለያዩ ትውልዶችን በሚያስተሳስር፣ የባሕል ቅርሶችን በሚያስተላልፍ፣ ለግምገማና ለማሻሻያ ቦታ ባለው ዕውቀት እንደሚቀረጽ ሊታወስ ይገባል። ይህ ግንዛቤ ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች ከታሪካዊ ማዕቀፍ አንጻር እና ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአውዳቸው ተገንዝበው አዲስ ትርጉም እንደሚሰጡት በይነ-ትውልዳዊ ውይይት አንድ አካል ወደማስተማር ሊመራን ይገባል።

## የሥርዓተ ትምህርት ቅድሚያዎች ለትምህርት ነገዎች

ትምህርትን አጥብበን ከማየት ይልቅ በታላላቅ ተግባሮቹ በንቃትወደ መሳተፍ መሸጋገር አለብን። የሥርዓተ ትምህርት ዘዴዎች የዕውቀቱን ዘርፍ ከችግር ፈቺ ችሎታዎች፣ ኢኖቬሽን እና ፈጠራዎች ጋር ማገናኘት፣ እንዲሁም የማኅበራዊ እና የስሜታዊ ትምህርትን እና ስለራስ የመማርን ዕድገት ማካተት አለባቸው። እዚህ የቀረቡት በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የሚኖሩ የተሳትፎ ዓይነቶች ዓላማቸው አንድ ማድረግ እና ነጻ ማውጣት ነው። ከዚህ በታች ያሉት ሥርዓተ ትምህርት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ነጋችንን በጋራ መልሶ ለማጤን የሚያፈልጉንን አካታችነትን፣ የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን፣ ኢ-ፍትሐዊነትን የማፈራረስን ተግባር  እና አለመመጣጠንን በመቃወም የሚደረገውን ሰፊ ትግል ለመደገፍ የታቀዱ ናቸው።

## ሥርዓተ ትምህርት ለተጎዳች ፕላኔት

ውጥረት እየተባባሰ በሚሄድባት ፕላኔት ላይ እንዴት አብረን እንኖራለን? ትምህርት ተማሪዎችን የአየር ንብረት ለውጥን እንዲለማመዱ፣ እንዲቀንሱ እና ወደነበረበት እንዲመልሱ በማዘጋጀት ለአየር ንብረት ለውጥ እና ለአካባቢ ውድመት ምላሽ መስጠት አለበት። የሰውን ልጅ የፕላኔቷ አካል አድርጎ የመመልከትን አዲስ መንገድ ለመትከል፣ ሥርዓተ ትምህርቶችን እንደገና ማሰብ እና እንደገና ማጤን አለብን። በሁሉም ሥፍራዎች ተማሪዎች ለአካባቢ ዘላቂነት የመሥራትን አጣዳፊነት በተግባር ሊገነዘቡ ይገባል - በፕላኔቶች ድንበሮች ውስጥ በመኖር እና የወደፊት ትውልዶችን ወይም የሁላችንም አካል የሆኑትን የተፈጥሮ ሥነ ምህዳሮችን ለአደጋ ባለማጋለጥ። በሰዎች እንቅስቃሴ በተጎዳች ፕላኔት ላይ በአክብሮት እና በኃላፊነት የመኖር ጥበብ በሁሉም የትምህርት አይነቶች ውስጥ ሊገባ ይችላል። ከአሁን በኋላ የሰው ልጅ ልዩ ነው ብለን ማወጅ ወይም ዓለምን ከ"ውጭ" እንዳለች በትምህርት እንደምትተዋወቃት ውጫዊ ነገር ማየት አንችልም። ይልቁንም ተዛምዷዊ እና በጋራ የሚሰራጭ እርምጃን ማነሣሳት አለብን። ይህ ማለት ከተፈጥሯዊው ዓለም ጋር እንደምንኖር እና እንደምንማር ዕውቅና መስጠት ማለት ነው።

በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ስለ ሕያው ዓለም የምንወያይበትን መንገድ መለወጥ ከዓለም ጋር ያለንን ግንኙነት ለማመጣጠን የሚያግዝ አንድ አስፈላጊ ስልት ነው። ነገር ግን ተማሪዎች የተፈጥሮ ጠባቂዎች እንዲሆኑ ብቻ የሚያስተምሩ ሥርዓተ ትምህርቶች በቂ አይደሉም። እነዚህም አካሄዶች በሰዎች እና በአካባቢያቸው መካከል ክፍፍል መኖሩን ይቀበላሉ።

ለአየር ንብረት ለውጥ ትምህርት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ውጤታማ እና አግባብነት ያለው የአየር ንብረት ለውጥ ትምህርት ለሥርዓተ ጾታ ምላሽ የሚሰጥ፣ በሁሉም ጊዜ እና ሥፍራ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እርስበርስ የተሳሰሩ መሆናቸውን የሚቀበል፣ እና ጥልቅ አስተሳሰብን እና ንቁ የሲቪክ ተሳትፎን የሚያበረታታ ነው። በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የምርት እና የፍጆታ ደረጃ ዘላቂነት እንደሌለው አምኖ፣ የበለፀጉ ሀገራት ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ በማበርከት ረገድ ሚና ያልተመጣጠነ መሆኑን እና እንዲሁም በአብዛኛው የችግሩን አስከፊነት የሚሸከሙት ደሃ አገሮች መሆናቸውን ይገነዘባል። በተጨማሪም፣ ስፍር ቁጥር በሌላቸው አገር በቀል ማኅበረሰቦች ውስጥ በሰብአዊው እና በልዕለ ሰብአዊው ዓለም መሀል ያለውን ሥሙም ግንኙነት ያበላሹ የቅኝ አገዛዝ እና የኢንዱስትሪ ውርሶች መኖራቸውንም ይገነዘባል። የአየር ንብረት ለውጥ ትምህርት ተማሪዎች ፍትሐዊ እና ዘላቂ አማራጮችን እንዲያስቡ እና በአካባቢያቸው ማኅበረሰቦች እና በአጋርነት ከዚያም ዐልፈው እርምጃ እንዲወስዱ ማስቻል አለበት።

*ሥርዓተ ትምህርት ከሕያው፣ የተጎዳች ፕላኔት ጋር እንዴት እንደተገናኘን እንደገና እንድንማር ሊያስችለን ይገባል።*

ሥርዓተ ትምህርት ከሕያው፣ የተጎዳች ፕላኔት ጋር እንዴት እንደተገናኘን እንደገና እንድንማር እና ከፍተኛ የብዝኃ ሕይወት መጥፋት፣ የጠቅላላ ሥነ ምህዳሮች መውደም እና የማይቀለበስ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲመጣ ያደረገውን የተማርነውን የሰው ልጅ እብሪት እንድንጥል ሊያስችለን ይገባል። ከተፈጥሯዊው ዓለም ጋር ጥልቅ ግንኙነትን በማዳበር እና ባዮስፌርን እንደ የትምህርት ሥፍራ በመቀበል ሥርዓተ ትምህርቶችን እንደ "ተፈጥሮን መመለሻ" ልንቆጥራቸው እንችላለን። ለምሳሌ በብዙ ወጣት-መር እና በማኅበረሰብ-መር እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንደሚከናወኑት ያሉ ከፕላኔቷ ጋር ለመኖር አስፈላጊ በሆኑ የዕውቀት ልምምዶች ላይ የሚያተኩሩ በይነ-ትውልዳዊ ንግግሮችን በማካተት ሥርዓተ ትምህርትን እንደገና መቃኘት እንችላለን።

አንስታዊ አተያዮች እና ቀደምት ሕዝቦች ድምጾች ይህን ወሳኝ ወቅት ለማሰስ ብዙ አስተዋጽኦ አላቸው። አገር በቀል የዕውቀት ሥርዓቶች ተማሪዎች የተፈጥሮ ማኅበረሰብ አካል እንደሆኑ እንዲገነዘቡ ንቃተ ህሊናቸውን ያሳድጋሉ፤ እንዲሁም የሰው ልጅ ከፕላኔቷ ጋር ተስማምቶ ለሺሕዎች ዓመታት እንዲኖር ካስቻሉት እሴቶች፣ ልምምዶች እና መንፈሳዊ ንቃተ ህሊና መማርም ይችላሉ። እያንዳንዱ ሕያው ዘላቂ በሆነ ሥነ ምህዳር ውስጥ የሚጫወተው ሚና አለው፤ ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ የመኖር

አቅም - ለጋራ ህልውና እና ደህንነት ከሚያስፈልገው በላይ ወይም ያነሰ አለመውሰድ - በትምህርት ሊገኝ ይችላል። አንስታዊ አተያዮች የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለው አብዛኛው የጎጂነት እና የብዝበዛ ግንኙነት መሠረት ያደረጋቸውን ተቃርኗዊ መነሻዎች ተቃውመው ይከራከራሉ። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በሚሄደው ፍጆታ እና ምድርን በበላይነት የመቆጣጠር ፍላጎቶች ላይ የተመሠረቱ ኢኮኖሚያዊ ሞዴሎች በግድየለሽነት የተሞላ ልብ ወለዳዊ ትርክትን ያስቀጥላሉ። ጥሩ የማኅበራዊ ደህንነት እና የሥነ ምህዳር ዘላቂነት ሚዛንን ለማሳካት ተምረን ልንኖርባቸው የሚገቡ የኢኮኖሚ አፈጻጸም ደረጃዎች አሉ።

*ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ የመኖር አቅም - ለጋራ ህልውና እና ደህንነት ከሚያስፈልገው በላይ ወይም ያነሰ አለመውሰድ - በትምህርት ሊገኝ ይችላል።*

ማኅበራዊ ፍትሕ ከሥነ ምህዳር ፍትሕ አይነጣጠልም። እርስበርሳችን መተሳሰብ ካልተማርን፣ ሕያዋን ፕላኔት መንከባከብን ልንማር አንችልም። እንክብካቤ ከፍቅር ወይም ከአመለካከት ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን፣ ማዕከላዊ ግንዛቤያዊ ገጽታም አለው። ሥርዓተ ትምህርቱ ለፕላኔቷ ሳይንሳዊ እና ቴክኒካዊ ዘዴዎች እንዴት እንደሚፈጠሩ፣ ምድር እና ሁለንታ እንዴት እንደተሰነዱ፣ እንደሚታዩ እና እንደሚታወቁ እና የዕውቀት ልምዶች በዚህ በተጎዳች ፕላኔት ላይ በሚኖርባቸው ልምምዶች ውስጥ እንዴት እንደተሳሰሩ የሚያሳዩ ጥልቅ ዕውቀቶችን ማካተት አለበት። ስለ የመረጃ መሳሪያዎች እና ስለ የግለሰብ እና የጋራ ፕሮጀክቶች ጥንካሬ እና ውሱንነት የሚደረግ ውይይት በፕላኔታችን ላይ የሚከሰት ውስብስብ ሕይወትን ለመከላከል የጋራ ግንዛቤን እና ንቅናቄን የሚያበረታቱ አግባብነት ያላቸው ሥርዓተ ትምህርቶችን ለማዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

የእንክብካቤ ሥነ ምግባር ራሳችንን እርስበርስ እንደተቆራኙ፣ በአንድ ጊዜ አቅም እና ተጋላጭ እንደሆኑ ሰዎች እንድናይ ያደርገናል። ሌሎች እና ዓለም ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደምናሳድር እና እነርሱም እንዴት እንደሚነኩን እንድናሰላስል ያስገድደናል። በተለምዷዊው የቤት ውስጥ እና የውጭ እንክብካቤ አሰጣጥ የሚታዩትን ጾታ ተኮር ሚዛንየለሽነቶች ለመዋጋት፣ ሥርዓተ ትምህርቱ የሥርዓተ ጾታ አገላለጽ ላይ ያልተመሠረተ ለሁሉም የሚሠራ የእንክብካቤ ሥነ-ምግባርን ማዳበሩ አስፈላጊ ነው። ልጆችን የማሳደግ፣ የታመሙትንና አረጋውያንን የመንከባከብ፣ ቤትን የመንከባከብ እና ለወሳኝ የሕብረተሰቡ አካል ለሆነው ቤተሰብ አካላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ፍላጎቶች ምላሽ የመስጠት ሥነ ተዋልዷዊ ዕውቀትም እንዲሁ የሰው ልጅ የጋራ ዕውቀት ከመሆኑም በላይ እና የተጎዳች እና ለአደጋ የተጋለጠች ፕላኔታችንን ለመንከባከብ እስከምንሄድባቸው መንገዶች ድረስ እንደሚዘልቅም ግልጽ ነው። መተሳሰብ፣ መንከባከብ፣ እንክብካቤ መስጠት እና እንክብካቤ መቀበል ተደጋጋፊ ነገዎቻችንን መልሰን በጋራ እንድናጤን በሚያስችለን ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ መካተት አለባቸው።

## ማወቅን እና ስሜትን ማቀናጀት

*ለመተሳሰብ፣ ለመተባበር፣ ጭፍን ጥላቻን እና ወገንተኝነትን ለመቅረፍ እና ግጭትን ለመፈተሽ በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ውስጥ ጠቃሚ ናቸው።*

ሥርዓተ ትምህርት ተማሪዎችን - ልጅ ይሁኑ ዐዋቂ - ወደ ትምህርታዊ ቦታዎች የመማር ጉጉትን እና ጥማትን እንደሚያመጡ ሙሉ ሰዎች ሊቆጥራቸው ይገባል። እንዲሁም ስሜቶችን፣ ፍርሃቶችን፣ ስጋቶችን፣ ልበ ሙሉነትን እና ፍቅርንም ያመጣሉ። ሰዎችን እንደ ሙሉ ሰው ቆጥረው የሚያስተምሩ ሥርዓተ ትምህርቶች ከዓለም ጋር ያላቸውን ማኅበራዊ እና ስሜታዊ ግንኙነቶቻቸውን በመደገፍ፣ ይህንኑም ለማሳደግ ከሌሎች ጋር በተሻለ ሁኔታ እንዲተባበሩ ያስችሏቸዋል።

ኒውሮሳይንስ እንደሚያሳየው፣ ማወቅ እና ስሜት በንጥል ግለሰብ ሳይሆን፣ በቀጥታ ከሌሎች ጋር ባለ ግንኙነት ውስጥ የሚካሄዱ የአንድ ዓይነት አእምሯዊ ሂደቶች አካላት ናቸው። በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች ማኅበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርትን ወደ ዋናው የትምህርት ልምምድ ለማምጣት፣ በተለይ ባለፉት ዐሥርት ዓመታት እጅግ በጣም አስገራሚ የትምህርት ሥራ ተከናውኗል። በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ

ያሉ ምርጥ የማኅበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች ማኅበራዊ፣ ስሜታዊ፣ አእምሯዊ እና ሥነ ምግባራዊ የተማሪዎች ማንነትን ያጠቃልላሉ። የግለሰቦችን የዕድገት አቅጣጫዎች ከሰፊው የማኅበራዊ ትስስር አንድምታቸው ጋር ያያይዛሉ። ለመተሳሰብ፣ ለመተባበር፣ ጭፍን ጥላቻን እና ወገንተኝነትን ለመቅረፍ እና ግጭትን ለመፈተሽ በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ውስጥ፣ በተለይም ከረጅም ጊዜ ክፍፍል ጋር በሚታገሉት ውስጥ ጠቃሚ ናቸው።

ማኅበራዊ እና ስሜታዊ የመማር ልምምዶች ቅይጥ በመሆናቸው፣ ተገቢ አውዳዊ አሠራር ያስፈልጋቸዋል። ዐውቆ የተነደፉ የመማማሪያ አጋጣሚዎች፣ ከመምህራን ጋር መተሳሰር፣ አወንታዊ የአቻ ተመክሮዎች፣ በይነ ትውልዳዊ መግባባት እና የማኅበረሰብ ተሳትፎ ያስፈልጋቸዋል። አስተዋይነት፣ ርህራሄ እና ጥልቅ ጠያቂነት ሁሉም ጠንካራ ማኅበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርትን ይደግፋሉ። ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት በመምህራን ላይ ተጨማሪ ሥራ እንደሚፈጥር እና ይህንን ለማከናወን ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ መታወቅ አለበት። ወደ 2050 ስናማትር፣ በማኅበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርት ላይ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶችን ችላ ማለት አንችልም - ምክንያቱም ትምህርቱ የወደፊት ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ለሚያስፈልገው የሰው ልጅ ፈጠራ፣ ግረገብ፣ ፍርድ እና ድርጊት መሠረታዊ ነው።

ተማሪዎችን እንደ ሙሉ ሰው መቀበል በሁሉም የሕይወት ደረጃዎች ውስጥ ለሚኖሯቸው አካላዊ ፍላጎቶች እና ችሎታዎች ዕውቅና ይሰጣል። ጤናማ የወደፊት ጊዜዎች ሁሉንም የአካል ችሎታ ዓይነቶች፣ ጾታዎች እና ዳራዎች ያካተቱ መሠረታዊ የመንቀሳቀስ ክህሎቶችን የሚያበረታታ ጥራት ያለው የአካል ማጎልመሻ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። ጥራት ያለው የአካል ማጎልመሻ ትምህርት በራስ መተማመንን እና ልበ ሙሉነትን፣ ቅንጅትን እና ቁጥጥርን፣ የቡድን ሥራን፣ ለአካላዊ አካባቢ ፍላጎቶች ምላሽ መስጠትን እና የቃላዊ እና የቃል አልባ ተግባቦትን ሊያሻሽል ይችላል። የአካል ማጎልመሻ ትምህርት የተሻለ የአካል ብቃት ላላቸው ብቻ የሚሰጥ ተደርጎ መታየት የለበትም፤ በውድድር እና ንጽጽር ላይ ከልክ በላይ ትኩረት ማድረግም ሰፋ ያለ ተሳትፎን ይከለክላል። እያንዳንዱ ተማሪ ጤናማ እና ንቁ የአኗኗር ዘይቤን ማጣጣም ይችላል በሚል፣ እና በጋራ እንቅስቃሴ ርህራሄ እና አክብሮት የተሞላባቸው ግንኙነቶችን ማዳበር እስከ ሕይወት ዘመን ፍጻሜ እየተገባቡ መዝለቅን ለመማር አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል በሚል እሴት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።

እንደዚሁ የሰው ልጅ ወሲባዊ ትምህርት ከዕድሜ ጋር የሚያስማማው እና በባሕል የሚቃኘው ሁሉን አቀፍ ትምህርታዊ አቀራረብን መውሰድ የማኅበራዊ እና ስሜታዊ ዕውቀትን አስፈላጊነት ይገነዘባል፤ የመከባበር እና የመፈቃቀድ ውይይቶችን ያበረታታል፤ በአካላዊ ብስለት ወቅት ስለሚካሄዱ አካላዊ እና ስሜታዊ ሂደቶችን ግንዛቤን ያዳብራል፤ እንዲሁም በመከባበር እና በእኩልነት ላይ የተመሠረቱ ግንኙነቶችን ያበረታታል። በበርካታ የዓለም ክፍሎች ያሉ ልጃገረዶች በአካላዊም ሆነ በጾታዊ ጉዳት ምክንያት የሚገለሉበት - በተለይ ኮረዶች በብዙ ሁኔታዎች የሚያጋጥማቸው እና ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው እንዳይቀጥሉ የሚከለክላቸው ዕውነታ - መጻዒ ጊዜ ሊታሰብ አይችልም። የእናቶች እና ሕፃናት ጤና፣ ሞት እና ደህንነት ከአጠቃላይ ወሲባዊ ትምህርት ጋር በቅርበት የተሳሰሩ ናቸው። ከሰፊ የጤና እና ደህንነት ዓይነቶች ጎን ለጎን፣ በእኩልነት፣ በመከባበር እና በራስ መተማመን እሴቶች ላይ የተመሠረተ ትምህርት ሁሉም ሕብረተሰቦች ወደሚኖራቸው የፍትሐዊ እና ሚዛናዊ ሰብአዊ ግንኙነቶች የላቀ አቅም ይተረጎማል።

## መሠረታዊ ትምህርትን ማስፋፋት እና ልሳነ ብዙ ነገዎችን መፍጠር

የቋንቋ አቅማችን እና ከቋንቋ ጋር ያለን ግንኙነት ለሰው ልጅ ማንነት፣ ዕውቀት እና ለዓለም ሕልውናችን ቁልፍ ነገር ነው፤ ምክንያቱም እንድንግባባበት እና ሌሎች አዲስ የግንዛቤ ከፍታ ላይ ለመድረስ የተማሩትን እንድናውቅ አስችሎናል። ቋንቋ ለጋራ ዕውቀት መኖር መሠረታዊ ነው። ባለፉት ዐሥርት ዓመታት ትምህርት እያንዳንዱን ትውልድ ከበፊቱ ትውልድ የበለጠ ማንበብና መጻፍ እንዲችል አስችሎታል። ተሳትፎን እና አካታችነትን ለማስፋት ግን የነገው መሠረተ ትምህርት ከማንበብና ከመጻፍ ዐልፎ፤ እንደቃላዊ ተግባቦት፣ ጽሑፋዊ ተግባቦት፣ እና የተረከ ነገራ ጥበብን እንደሚያካትተው አዳጊው ሚዲያ ባሉ መልኮቹ ሁሉ የሰዎችን የመረዳትና የመግለጽ አቅሞች ማጠናከር አለበት።

በእርግጠኝነት፣ የሰው ልጆች ተመክሮዎቻቸውን የመዘገቡባቸው እና ለአዳዲስ ትውልዶች ያስተላለፉባቸው መንገዶች ጽሕፈት እና ንግግር ብቻ አይደሉም፤ እና ምስሎች እና አካላዊ ዕውቀቶችም ይበልጥ ወሳኝ በሆኑ መንገዶች ወደ ሥርዓተ ትምህርቱ መግባት አለባቸው። ነገር ግን የቃል እና የጽሑፍ ዕውቀቶች በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የማይካድ ሚና ተጫውተዋል፤ በተለይም ጽሕፈት የሰው ልጅ የዕውቀት ቴክኖሎጂ ሆኖ፣ የተቀረጹ ጽሑፎች እንዲሠራጩ እና ከቦታ ቦታ እንዲጓዙ አስችሏቸዋል፤ ይህም በተለያዩ ባሕሎች ውስጥ የሰው ልጅ ተመክሮዎች የሚከማቹበት እና የሚደራጁባቸውን ዕድሎች አስፍቷል። ይህ ዕውቀት በመጪዎቹ ትውልዶችም ዘንድ መጥፋት የለበትም።

መሠረታዊ ትምህርት ከወደፊት የትምህርት እና የማኅበራዊ ተሳትፎ ዕድሎች ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ሆኖም ማብሪያ-ማጥፊያ ባለመሆኑ፤ በቋንቋ የመግባባት እና የመረዳት ችሎታችን ዕድሜ ልካችንን ሊጠናከር ይችላል። የወደፊት መሠረተ ትምህርት በጥልቀት፣ በስፋት እና በኂሳዊ ዓይን የማንበብ፤ በንግግር እና በጽሑፍ በግልፅ እና በብቃት የመግባባት፤ እንዲሁም በጥንቃቄ፣ በመተሳሰብ እና በማስተዋል የማዳመጥ ችሎታዎችን ሊያዳብር ይችላል። ለምሳሌ የተማሪዎችን ራስን ችሎ የማንበብ እና የተወሳሰቡ ጽሑፎችን በሁሉም የትምህርት ዘርፎች የማንበብ ችሎታዎች እና ዝንባሌዎች ማሳደግ ለጋራ ዕውቀት የበለጠ ሚዛናዊ ተደራሽነት የሚያገኙባቸው ሰፊ የወደፊት ዕድሎችን ይከፍታል። መሠረተ ትምህርት ከመማሪያ ክፍሎች እና ከትምህርት ቤቶች ዐልፎ ሕብረተሰብ አቀፍ ቃል ኪዳን ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ በአንዳንድ የሕንድ የሚዲያ አውታሮች በቅርቡ የተደረገው ለንግግር የተመሳሳይ ቋንቋ የጽሑፍ አቻ ማቅረብን ወደ መደበኛ አሠራርነት የማምጣት ጥረት፣ ለማድረግ የንባብ ክህሎትን በሰፊው እንደሚያጠናክር ታይቷል፤ በተለይ በትምህርት ቤት መሠረታዊ የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታን በተማሩ፣ ነገር ግን ተጨማሪ ልምምድ እና በራስ መተማመንን ማዳበር በሚያስፈልጋቸው ዘንድ።

> *የቋንቋ ስብጥር የሰው ልጅ የጋራ ዕውቀት ቁልፍ ባሕርይ ነው።*

ሥርዓተ ትምህርቶች የውጭ ቋንቋዎችን፣ አገር በቀል ቋንቋዎችን፣ የምልክት ቋንቋዎች እና ሌሎችንም በማስተማር ከብሔራዊ ልሳነ ዋሕድነት ወደ ልሳነ ብዙነት እየተሻገሩ ነው። ይህም ዘላቂነት ሊኖረው እና ሊስፋፋ የሚገባው ለውጥ ነው። እንዲሁም ሕፃናት፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች ተማሪዎች በቤት ውስጥ እና በአያት ቅድመ አያት ቋንቋቸው ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የትምህርት አማራጮችን ማግኘታቸው አስፈላጊ ነው። ይህም ለማስተማር እና ለመማር ውጤታማነት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፤ ነገር ግን ለመሠረታዊ መከባበር እና በመላው ዓለም ያሉ የትምህርት ሥርዓቶች ስብጥርን ከማክበር እና ከማዝለቅ ጋር እንዲጣጣሙ አቅጣጫ ለማስያዝም ወሳኝ ነው። በብዙ አውዶች፣ የተማሪዎችን ባሕላዊ ማንነቶች ለመደገፍ እና በሕብረተሰብ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለመፍቀድ ልሳነ ክልኤ እና ልሳነ ብዙ የትምህርት ፖሊሲዎች አስፈላጊ ናቸው። ይህ ለአነስተኛ ቁጥር ያለው ተናጋሪ ላላቸው አገር በቀል ቋንቋዎች ድጋፍ መደረግ እንዳለበት እና ተማሪዎች የገናን ወይም የብዙኃንን ቋንቋ ብቃት እንዲኖራቸው እንዲያገኙ መሠረት መጣል እንደሚገባም ያመለክታል።

ልሳነ ብዙነት ሁላችንንም በተለያዩ የቋንቋ ሥርዓቶች መካከል ንቁ ተርጓሚዎች እንድንሆን እና በተሠሩ የፍች ቅጦች ውስጥ የበለጠ ራስገዝነት እና ጥልቅ አስተዋይነት እንድናዳብር ያስገድደናል። ቋንቋ ከተግባቦት ዘዴ በላይ ነው፤ ቋንቋዎች የዓለማት አተያዮችን እና ልዩ የአረዳድ መንገዶችን ይሸከማሉ። የቋንቋ ስብጥር የሰው ልጅ የጋራ ዕውቀት ቁልፍ ባሕርይ ነው፤ ትምህርትም ይህንን ለማዝለቅ ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

## የሥሌት ዕውቀትን ማበልጸግ

ሰዎች የሒሳብ ዕውቀታቸውን እና ክህሎቶቻቸውን በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ እንዲተገብሩ ስለሚጠየቁ የሥሌት ዕውቀት በወደፊት ትምህርት አስፈላጊነቱ ቀላል አይደለም። የሥሌት ዕውቀት ቅጥንብሮችን የመመልከት፣ ስብስቦችን የመመደብ እና የማደራጀት፣ የመቁጠር እና የመለካት፣ መጠኖችን የማወዳደር እና በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት የመለየት ሰብአዊ ችሎታዎች ፍሬ ነው። እንደ የዐሥርዮሽ ሥርዓት እና የሁለትዮሽ ሥርዓት ያሉ የቁጥር ሥርዓቶች ለዘመናዊ ተግባቦቶች፣ ግብይቶች፣ ቅመራዎች እና ሥሌቶች መሠረት ናቸው። የሥሌት ዕውቀት የመደመር፣ የመቀነስ፣ የማባዛት እና የማካፈል መሠረታዊ አሠራሮችን ጠንቅቆ ከማወቅ በተጨማሪ፣ በተለያዩ አውዶች እና ፕሮብሌሞች ላይ መተግበራቸውን ይጠይቃል።

ከሥፍር የለሽ ምሳሌዎቹ መሀል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፦ የፋይናንስ ጤናን ማስጠበቅ እና ዕቅድ፣ የጤና ስጋቶች እና የበሽታ ክስተቶች፣ የግብርና ምርቶች እና ግብአቶች፣ የብክለት ደረጃዎች እና የአካባቢ ጥራት፣ የአገር ውስጥ ኢንተርፕራይዞች እና የማኅበረሰብ ባንክ፣ ወዘተ። እንደየአገባቡ ስንረዳው፣ የሥሌት ዕውቀት በጊዜ ሂደት የሚደረጉ ለውጦችን የመረዳት፣ የወደፊቱን የመተንበይ እና የማቀድ፣ ዝምድናዎችን የመረዳት እና አዝማሚያዎችን ትርጉም ወዳላቸው አተያዮች የመለወጥ አቅሞቻችንን ገልጦ ያሳያል።

የሥሌት ዕውቀት የሁሉም ሕዝቦች ሀብት እንደመሆኑ፤ ባሕልን ከግንዛቤ ያስገባ የሥሌት ሥርዓተ ትምህርት ለመደበኛ ትምህርት ትርጉም ያለው ማኅበራዊ እና ስሜታዊ ድልድዮችን መገንባት ይችላል። ለምሳሌ፣ የአርክቲክ ኖርዌይ ቀደምት ነዋሪዎች ባሕላዊ የጉንጉን አሠራር ከተማሪዎች ጋር ልዩ ልዩ የሆነ የኢንቲጀር ቅጦችን ከመረዳት፣ እንደ ማባዛትና የአልጀብራ ተለዋዋጮች ወዳሉ ውስብስብ ሥሌቶች ለመሸጋገር ጥቅም ላይ ውሏል። በተመሳሳይ፣ በካናዳ የሚገኙ የትምህርት ቤት ቦርዶች የሀገረሰብ ከያንያንን እና መምህራንን እንደ ዶቃ ሥራ፣ የቅርጫት አሠራር እና ሞካሲን አሠራር ያሉትን ባሕላዊ ጥበቦች አልጀብራዊ፣ ወደረኛ፣ እና መካናዊ አመክንዮን ጨምሮ ከተለያዩ ከሒሳብ ፅንሰ ሐሳቦች ጋር አዛምደው እንዲያስተምሩላቸው አድርገዋል። የሒሳብ ዕውቀትን ከተማሪዎች የባሕል ዕውቀት ጋር ማገናኘት በቤት ውስጥ እና በትምህርት ቤት መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ የሚያስፈልጉትን ማኅበረ-ስሜታዊ ባሕርያት ለመጠቀም ይረዳል። እንዲሁም ሒሳብ "ምዕራባዊ" ነው የሚለውን የተሳሳተ አስተሳሰብ ይሞግታል፣ እና እንደ ኢኑይት ሒሳብ እና ማኦሪ ሒሳብ የመሳሰሉት ባሕላዊ የሒሳብ ሥርዓቶች ከረጅም ዘመናት በፊት ጀምሮ በስፋት የመኖራቸውን ነገር ያታውሰናል።

## ሥነ ሰብአትን መጠቀም

ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች የሚያዩባቸውን የተለያዩ ዘዴዎች እንዲማሩ ለመርዳት የማኅበረሰብ እና ባሕል ዕውቀት እና ጥናት አስፈላጊ ናቸው። የሰው ልጅ ትውፊት፣ በተለያዩ መልኮቹ፣ ለዓለም የጋራ ዕውቀት ክምችት በማዋጣት፣ በጋራ ዓለም ግንባታ የተለያዩ ወሳኝ ገጽታዎች ላይ ብዙ እሴቶች አበርክቷል። በተመሳሳይም፣ የምናውቀው ከፊል እና የተዛባ መሆኑን መገንዘብ አለብን። ሰው መሆን ምን ማለት እንደሆነ እንደገና መበየን እርስበርሳችን፣ ከሕያው ፕላኔት እና ከቴክኖሎጂ ጋር ያለንን ግንኙነት ማመጣጠን ይጠይቃል። ሥነ ሰብአት (ሂውማኒቲስ) መስተካከል አለበት፣ እና ሥርዓት ያለው የጥናት መስክ እንደመሆኑ፣ በተራው እንድንስተካከል ይረዳናል።

ለምሳሌ፣ የታሪክ ትምህርት በአግባቡ ከተሰጠ፣ አድልዎ እና ልዩ ጥቅምን ጨምሮ ስለማኅበራዊ ለውጥ እና ማኅበራዊ ሥርዓቶች ላይ በዋጋ ሊተመን የማይችል አተያይ ሊያዳብር ይችላል። ነገሮች ከሆኑት ሌላ ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር ታሪካዊ ቢሆኖችን መረዳት፣ የወደፊት ዕድሎችን ለመገመት ጠቃሚ ነው። ነገር ግን፣ ይህንን እምቅ አቅም ለማውጣት፣ ታሪክ በዘመን ቅደም ተከተሎች ከመመሰጥ በዘለለ፣ በማስረጃነት ምን እንደሚካተት እና በመጀመሪያ ደረጃ ሰዋዊ እና ኢሰዋዊ ተመክሮዎችን እንዴት መረዳት እንዳለብን ወደ ማወያየት ማምራት አለበት።

ትምህርትን ከሥነ ሰብአት ጋር ማገናኘት እና መልሶ ማገናኘት የሚያስችሉ አዳዲስ መንገዶችን መፈለግ ለዲሞክራሲ የወደፊት ሁኔታም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ሥነ ጽሑፍ እና ሥነ ጥበባት ከዓላማ፣ ኂሳዊ ጠያቂነትን፣ ርህራሄን፣ ሥነ ምግባርን እና ምናብን ከማድነቅ ጋር ሊያገናኙን ይችላሉ። እነዚህ ሁሉ ሰብአዊ አቀራረቦች የተማሪዎችን "የወደፊት ዕውቀትና ክህሎት" - በሚያዩት እና በሚያደርጉት ነገር ውስጥ መጪው ጊዜ የሚጫወተውን ሚና የመረዳት ችሎታቸውን - ለማጠናከር ወሳኝ ናቸው። "በወደፊት የተማሩ" መሆን የወደፊቱን በብቃት እና በውጤታማነት ለመጠቀም አቅም ማግኘት፣ እና ለሚፈጠሩ ለውጦች በተሻለ ሁኔታ ለማዘጋጀት፣ ለማገገም እና ለመፈልሰፍ መቻል ማለት ነው። ይህም ከመደበኛ ትምህርት ውስጥም ሆነ ውጭ፣ ባሉ ሕዝባዊ ቦታዎች ሥነ ሰብአትን በማጠናከር ይደገፋል። ከወል ሰብአዊነታችን፣ ከምንጋራት ፕላኔት እና ከጋራ የፍትሕ ፍላጎታችን ተነሥተን ትምህርትን ከሥነ ሰብአት ጋር መልሶ በጋራ ማገናኘታችን ወሳኝ ተግባር ነው።

## ሳይንሳዊ ምርምር እና ግንዛቤ

ግዑዙን ሁለንታ የመረዳት ፍላጎት የሰውን የመጠየቅ እና የመማር አቅም ያንጸባርቃል። የሳይንሳዊ ምርምር ባሕርይ - መመልከት፣ መጠየቅ፣ መተንበይ፣ መፈተሽ፣ ንድፈ ሐሳብ መቀመር፣ መፈተን እና ግንዛቤን ማጥራት - ከሰብአዊው ተፈጥሮ የመነጨ ነው። የዘመናዊ ሳይንስ ሥሮቹ በእያንዳንዱ ባሕል እና ማኅበረሰብ ውስጥ ከተመዘገበው ጥንታዊ ታሪክ ይመዘዛሉ። ፍሬዎቹም፣ ከመድኃኒት እስከ ቴክኖሎጂ ድረስ፣ በሁሉም ሥጋዊና ቁሳዊ ሕይወታችን ውስጥ ይገኛሉ። ጠንካራ ሰብአዊ እሴቶች ባሉት እና መላውን ሰው በሚያቅፍ ሰፊ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ፣ ለሳይንሳዊ ዕውቀት እና ምርምር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

> *ሥርዓተ ትምህርቶች ውስብስብ እና ንብርብር የሆነውን ዕውነት ለይቶ የማወቅ እና በሀቀኝነት የመመርመር ቁርጠኝነትን ማዳበር አለባቸው።*

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሳይንስ መሠረታዊ ጥቅምን ያስገኘ ጉልሕ የሆነ የዕውቀት ልምምድ ነው፡- ይኸውም ዕውነት በጋራ ጥረት የተገኙ ሂደቶች እና ስምምነቶች ውጤት መሆኑ ነው። ሆኖም፣ አንዳንድ ጊዜ፣ ለምሳሌ በሳይንሳዊ ግኝቶች ወይም ሙከረቶቹ ውጤቶች፣ ከሥነ ምግባራዊ ጥያቄዎች በላይ ወደሆነ ልዩ መስከነት ይዳብራል። ይህም ሳይንስ ለተወሰኑ ምዕተ ዓመታት ያገኘውን እምነት የሚሸረሽሩ ክርክሮች እና ጥያቄዎችን አፍርቷል። ሥርዓተ ትምህርቶች የሳይንስ ዘዴዎችን፣ ግኝቶችን እና ሥነ ምግባሮችን እርስበርስ የተሳሰሩ አድርገው መቁጠር አለባቸው።

የጽንፈኛ አንጻራዊነት መስፋፋት እና የተዛቡ ዕውነቶች በተለያዩ ሚዲያዎች በስፋት መሰራጨታቸው ጠንካራ እና ነባራዊውን ሁኔታ የሚያንጸባርቅ የሳይንስ ትምህርት ማስፈለጉን ያመለክታል። እንደ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ እና የዓለም ሙቀት መጨመር ባሉ ዋና ዋና ቀውሶች ወቅት ተባብሶ የነበረው የተሳሳቱ መረጃዎች እና የውሸት ዜናዎች ስርጭት ለሳይንሳዊ ትምህርት ወሳኝነት ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጠው አድርጓል። ሳይንሳዊ ዕውቀትን መካድ እና 'ዕውነታዎች'ን አዛብቶ ማቅረብ ወደ የገሃድ ዓለም መዘዞችን፣ የደባ ክትትል ሥጋትን፣ አለመተማመንን፣ ፍርሃትን እና ጥላቻን አስከትሏል። ሥርዓተ ትምህርቶች ሳይንሳዊ ዕውነትን ለመጠበቅ እና የማስተዋል አቅምን ለማዳበር፣ እንዲሁም ውስብስብ እና ንብርብር የሆነውን ዕውነት ለይቶ የማወቅ እና በሀቀኝነት የመመርመር ቁርጠኝነትን ማዳበር አለባቸው።

ዓለም አቀፋዊ የጋራ ዕውቀት ሁሉም ሰው ለሰው ልጅ ደህንነት አበርክቶ ያለውን ትክክለኛ ዕውቀት የማግኘት መብት እንዲኖረው ይጠይቃል። ይህ መርህ በተለይ በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊ የሚሆነው፣ መልእክቶች እና ፅንሰ ሐሳቦች አእምሮን በማዳበር ረገድ ትልቅ ተፅእኖ ስላላቸው ነው። ለምሳሌ፣ በአንዳንድ ቀጣናዎች ወይም ትላልቅ የማዕድን እና የዘይት ኢንዱስትሪዎች ባሉባቸው አገሮች፣ በኦፊሴላዊ የሳይንስ ሥርዓተ ትምህርቶቻቸው ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ማውጣት አካባቢ ላይ የሚያስከትላቸውን ተጽዕኖዎች አጉልተው እንዳያሳዩ መንግሥታት ላይ ከፍተኛ ጫና ይደረጋል። በተቻለ መጠን ትምህርታዊ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲህ ዓይነቱን የተዛባ መረጃ አሰጣጥ መዋጋት ያስፈልጋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይም መብታቸውን በተነፈጉ እና በተገለሉ ሕዝቦች ዘንድ የሳይንስ ትምህርትን ለማስፋፋት አዳዲስ ጥረቶች ያስፈልጋሉ። በዛሬው ዓለም ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ መጠን ያለው መረጃ ይሰራጫል። የሳይንስ ትምህርት፣ ዘዴ፣ ጥብቅነት፣ ተጨባጭነት እና ሥነ ምግባር ሁሉም ወሳኝ እና አጣዳፊ የሥርዓተ ትምህርት ጉዳዮች ናቸው።

## ለዲጂታሉ ዓለም የሚያስፈልጉ ክህሎቶች

የተያያዙ ቴክኖሎጂዎች በየጊዜው እየተስፋፉ ባሉ የሕይወት፣ የመማር እና የሥራ መስኮች ላይ መሳተፍን ያበረታታሉ። ሁለንተናዊ የቴክኖሎጂ ተደራሽነትን ከመደገፍ ባለፈ፣ የትምህርት ሥርዓቶች ተማሪዎች ቴክኖሎጂን ትርጉም ባለው መልኩ ለመጠቀም የሚያስፈልጓቸውን ዲጂታል ክህሎቶች እና ብቃቶች ለማዳበር እየጣሩ መሆኑ ግልጽ ነው። እነዚህ ክህሎቶች ምንም 'አገር በቀልነት' ወይም 'ተፈጥሯዊነት' የላቸውም። ከተለያዩ ኢ-መደበኛ እና ራስ-መር የትምህርት ቅርጾች ጎን ለጎን፣ ሆን ተብሎ በሚደረግ ትምህርታዊ ጥረት በጊዜ ሂደት የተገነቡ እና እየጠሩ የመጡ ናቸው።

*ሥርዓተ ትምህርቶች መምህራን እና ተማሪዎች በቴክኖሎጂ ጉዳይ ላይ አብረው እንዲሠሩ መደገፍ እና ቴክኖሎጂም እንዴት እና ለምን ዓላማዎች ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ለመወሰን ማገዝ አለባቸው።*

የዲጂታል ትምህርት በተለምዶ የተግባር ክህሎት እና ቴክኒካዊ የአጠቃቀም ዕውቀትን የሚመለከት ቢሆንም፤ ስለ ዲጂታል ማኅበረሰብ ፖለቲካ እና ስለዲጂታል ኢኮኖሚ ግንዛቤዎችን እና አዝማሚያዎችን የያዘ 'ሂሳዊ ዲጂታል ትምህርት'ን ማካተት አለበት። ይህ ትምህርት የተማሪዎችን የዲጂታል ቴክኖሎጂን ፖለቲካዊ ገፅታዎች የሚተነትኑበት እና በእነርሱም የተወሰኑ ውጤቶችን ለማሳካት የሚጠቀሙባቸው ችሎታዎች ላይ ያተኩራል። ተማሪዎች የዲጂታል ቦታዎች ተዋናዮችን ዓላማ ማወቅ እና እንደ ግለሰብ እና እንደ ቡድን አባላትነታቸው የትልልቅ ዲጂታል ሥነ ምህዳሮች አካል የሆኑባቸውን መንገዶች መረዳትአለባቸው። ዛሬ፣ እነዚህ እርስበርስ የተያያዙ ቴክኖሎጂዎች በጭራሽ ተጠቅመውባቸው ወይም ዐይተዋቸው በማያውቁ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

ስለ ቴክኖሎጂ ትምህርትም የግድ በራሱ በቴክኖሎጂ ላይ የተንጠለጠለ ነው። ቴክኖሎጂን ለመረዳት እና ለበጎ ነገር ለመጠቀም የሚያስፈልጉት ችሎታዎች እና ሂሳዊ አመለካከቶች በአዳዲስ የቴክኖሎጂ ዕድገት ፍጥነት፣ በማያቋርጥ ፍሰት የሚለዋወጡ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ ትምህርት አዳዲስ የቴክኖሎጂ ዕድገቶችን እየተከተለ የሚሄድ የአንድ አቅጣጫ ጎዳና ነው ማለት አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ፣ ትምህርት በቴክኖሎጂ ፈጠራ እና በማኅበረሰቦች ዲጂታል ለውጥ ውስጥ የራሱን ሚና መጫወት አለበት። ሥርዓተ ትምህርቶች መምህራን እና ተማሪዎች በቴክኖሎጂ ጉዳይ ላይ አብረው እንዲሠሩ መደገፍ እና ቴክኖሎጂም እንዴት እና ለምን ዓላማዎች ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ለመወሰን ማገዝ አለባቸው።

## በሥነ ጥበባት ትምህርት ምናብን፣ ፍርድ እና ዕድልን መገንባት

የሥነ ጥበባት ትምህርት - ሙዚቃ፣ ድራማ፣ ዳንስ፣ ዲዛይን፣ የዕይታ ጥበባት፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ግጥም እና ሌሎችም - የተማሪዎችን በውስብስብ ክህሎቶች የመካን አቅም በእጅጉ ሊያሰፋ እና በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ያሉ ማኅበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርቶችን ሊደግፍ ይችላል። በመተሳሰብም ሆነ ኢ-ቃላዊ ፍንጮችን በማንበብ የሌሎችን ተመክሮ እንደራስ የማየት ሰብዓዊ ችሎታዎቻችን ሊያሳድግ ይችላል።

ጥበባት አንዳንድ ጊዜ ተሰውረው የሚገኙ ዕውነቶችን እንዲታዩ ከማድረጋቸውም በላይ፣ በርካታ የዓለምን አተያዮችን እና አተረጓጎሞችን ለማክበር ተጨባጭ መንገዶች ይሰጡናል። ብዙ ሥነ ጥበባዊ ቅርጾች በስውር እና አሻሚ በሆኑ የሕይወት ጉዳዮች ዙሪያ ያጠነጥናሉ፤ ተማሪዎችም ትንሽ ልዩነት ትልቅ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ሊገነዘቡባቸው ይችላሉ። ሥነ ጥበባዊ ተመክሮ ብዙውን ጊዜ ለማይታወቀው እጅ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል፤ ተማሪዎች ሁሉም ነገር እንደየሁኔታው እና እንደየአጋጣሚው እንደሚለዋወጥ ሊማሩ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ ሥነ ጥበባቱ በውስጥ እና በውጫቸው የማወቅ፣ የመሆን እና የመግባባት አድማሶቻችንን እንድናሰፋ በማገዝ፤ መነገር፣ መታየት እና መሰማት ያለበትን እንድንናገር፣ እንድናሳይ እና እንዲሰማን ያስተምሩናል።

በሥነ ጥበባት አማካኝነት የፈጠራ አገላለጾችን የሚጋብዙ ሥርዓተ ትምህርቶች ነገን የመቅረጽ ትልቅ እምቅ አቅም አላቸው። የሥነ ጥበብ ሥራ ዓለምን ለመረዳት፣ በባሕላዊ ምዘና ውስጥ ለመሳተፍ እና ፖለቲካዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያችሉ አዳዲስ ቋንቋዎችን እና ዘዴዎችን ይሰጣል። ሥርዓተ ትምህርት ባሕላዊ ቅርሶችን እና የጋራ ማንነታችንን ጠንካራ ምልክቶች፣ ዕውቀቶች እና ማጣቀሻዎች በአመክንዮ ማድነቅን እና መፈተሽን ሊያበረታታ ይችላል።

## ለሰብአዊ መብቶች፣ ለንቁ ዜግነት እና ለዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ማስተማር

የሰብአዊ መብት ትምህርት በሙሉ አቅሙ ሲተገበር፣ ለሁሉም ሰው ዕውቅና እና ብልጽግና ቁርጠኝነት ካለው ግብረገባዊ ዓለም ጋር የሚያግባባ የጋራ ቋንቋ እና ወደዚያም የሚያስገባ ዕድል የሚሰጥ ለዋጭ ጥረት መሆን ይችላል። የሰብአዊ መብት ትምህርት የተማሪዎችን የአድራጊነት አቅም ሊደግፍ ይችላል። አለመመጣጠንን የመተንተን እና ወሳኝ ንቃተ ህሊናን የማሳደግ ክህሎቶችን ማዳበር አሳታፊ ጥረትን መደገፍያ መንገድ ነው፤ በዚህ ረገድ የሰብአዊ መብት ትምህርት የዜግነት ትምህርትን በጥብቅ ይደግፋል።

የሰብአዊ መብት ትምህርት የብሔራዊ የትምህርት ሥርዓቶችን አጠቃላይ ውጤታማነት ያሻሽላል፤ እነሱ ደግሞ በተራቸው ዘላቂ እና ፍትሐዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ዕድገትን ይደግፋሉ። ስለመሠረታዊ መብቶች፣ እንዲሁም ስለ ለሁሉም ሰዎች ክብርና ነጻነት በማስተማር ትምህርት የራሱ የእኩልነት ተስፋው የሚፈጸምበት ቦታ መሆን አለበት። የሰብአዊ መብት እና የዜግነት ትምህርት ከሰላም ትምህርት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ የሰዎች የእርስበርስ ግንኙነት ዋና መንገድ ሁከት ነው፤ ሴቶች እና ሕፃናትን ጨምሮ ሁሉም የሕዝብ ቡድኖች መድልዎ፣ የቃል እና የአካል ጥቃት ስለሚደርስባቸው፣ የመኖር እና የማደግ ዕድሎቻቸው በእጅጉ ተገድበዋል። ከመብት ማስጠበቂያ ሕጎች እና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመሆን፣ የሰብአዊ መብት ትምህርት አለመግባባቶች በድርድር እና በዲፕሎማሲ የሚፈቱባቸውን ሰላማዊ ማኅበረሰቦች ለመገንባት ያግዛል።

ትምህርት ሰዎች በጋራ ማዕቀፍ ውስጥ ሥራዎቻቸውን በጋራ እንዲገመግሙ እና እንዲተነትኑ በማስተማር የዜግነት፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ተግባራት ዘላቂ አቅም ይገነባል። ሥርዓተ ትምህርቶች ጥምረቶችን በመገንባት እና ከትላልቅ የንቅናቄ እና የአጋርነት ታሪኮች እና አቅጣጫዎች ጋር ትስስር መፍጠር ላይ ሲያተኩሩ፣ ተዛምዷዊ እና የወል የድርጊት አቅም ጠንካራ ድጋፍ ያገኛል። ትምህርት በሕዝባዊ ቦታ የሚከናወኑትን የረዥም ጊዜ ማሰብን፣ መወያየት እና መመካከርን ማበረታታት ላይ ካተኮረ ስልታዊ እና የለውጥ እርምጃዎችን ይደግፋል። የሰብአዊ መብት ትምህርትም ስለ ሰው መሆን ምንነት የሚነሡ ክርክሮችን እና መወላወሎችን ማበረታታት እና በፕላኔታችን ላይ የተለያዩ የሕይወት ዓይነቶችን ጠብቆ ስለማቆየት የሚነሡ ሥነ ምግባራዊ ጥያቄዎችን መዳሰስ አለበት።

በተጨማሪም፣ ለኒሳዊ እና ፈጠራዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ እና ተሚጋችነት የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን እና ችሎታዎችን ማስጨበጥ፤ ኢፍትሐዊነትን እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን መከታተል፤ እንዲሁም በጾታ፣ በዘር፣ በአገሬ ተወላጅ ማንነት፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት፣ በጾታ ዝንባሌ ወይም በዜግነት ሁኔታ ምክንያት በቡድኖች ላይ ማግለል የሚያደርሱትን የሥልጣን አወቃቀሮችና ግንኙነቶችን መጠየቅ፣ መግለጥ እና መጋፈጥን ዒላማው ያደረገ መሆን አለበት። ስለዚህ በትምህርት ሥርዓቶች እና በማኅበራዊ ንቅናቄዎች መካከል የሚደረግ ውይይት መሠረታዊ ነው።

ሥርዓተ ትምህርቶች የሥርዓተ ጾታ አለመመጣጠንን በመፍታት ረገድም ትልቅ ሚና አለው። የተስፋፉት የአባዊነት - ለወንዶች አብላጫውን ማኅበራዊ መብቶች እና ሥልጣን የሚሰጥ ርዕዮተ ዓለማዊ ሥርዓት - ተጽዕኖዎች ለሕፃናት እና ወጣቶች በሕብረተሰብ እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚተላለፉ መልእክቶች እና የአስተሳሰብ ዘይቤዎች ላይ ጫና ማሳደሩን ቀጥሏል። ጨቋኝ የሥርዓተ ጾታ ሚናዎች እና የሥርዓተ ጾታ መድልዎ በሕብረተሰብ ውስጥ ላለ ለማንኛውም ሰው ጎጂ ናቸው። የእኩልነት መሠረታዊ መርሆች ትምህርት ገና በልጅነት መሰጠት አለበት። ወንዶች ልጆች የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ደጋፊ እንዲሆኑ እና እና ከእህቶቻቸው ወይም ከሴት እኩዮቻቸው የበለጠ ስውር ጥቅሞችን ሊሰጧቸው የሚችሉ ያልተመጣጠኑ የቤት ውስጥ ወይም ማኅበረሰባዊ ሥርዓቶችን እንዳያስቀጥሉ በተቻለ መጠን በለጋነታቸው መማር አለባቸው። ሴት ልጆች እና እህቶች አብዛኞቹን የቤት ውስጥ ኃላፊነቶች እና የቤት ውስጥ ሥራዎች እንዲወጡ መጠበቅ፣ በትምህርት ቤት ተሳትፎ

ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው፤ እንዲሁም ዋጋ እና ጥቅም የሚኖራቸው ለሌሎች ታዛዥ ሲሆኑ ነው የሚል ስውር መልእክት ያስተላልፋል። የሥርዓተ ጾታ እኩልነት መርሆዎች ሕፃናት በሚገናኙበት እና በሚማሩበት አካባቢዎች፣ ማለትም በቤት፣ በክፍል፣ በትምህርት ቤት ቅጥ ግቢ እና በማኅበረሰብ ውስጥ ወጥነት ሊኖራቸው ይገባል። እኩልነትን ማሳደግ የሁሉንም ሰው ድጋፍ የሚሻ የጋራ ጥረት ነው።

በተመሣሣይ ሁኔታ፣ ሥርዓተ ትምህርት ዘረኝነትን በማንሣት እንደ ቀዳሚ ሕዝቦች፣ የአፍሪካ መሠረት ያላቸው ማኅበረሰቦች እና አነስተኛ ቁጥርና የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ኅሳዎች ያሉ በማኅበረሰቦቻችን ውስጥ አብረው የሚኖሩ የተለያዩ የባሕል እና የቋንቋ ዳራ ያላቸው ቡድኖች የሚገለጹባቸውን የተዛቡ እና አድሎአዊ ምስሎች እና ትርክቶች መታገል አለበት።

# የከፍተኛ ትምህርት የአስቻይነት ሚና

አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ትምህርትን ከጋራ ዕውቀት የሚመነጭባቸውን ብቻ ሳይሆን፤ ተጨማሪ ዕድገትን እና የበለጠ አካታችነቱን የሚደግፍባቸውን መንገዶች እንደገና ማጤንን ይጠይቃል። ይህም የጋራ ዕውቀትን ለማጠናከር ቁልፍ ሚና ካለው፣ ከከፍተኛ ትምህርት የበለጠ ግልጽ የሚሆንበት ቦታ የለም። ያለንበት ጊዜ ከፍተኛ ትምህርት በረዥም ዘመን ታሪኩ ከፍተኛ እርግጠኛነት ማጣት ውስጥ ከገባባቸው ጊዜያት አንዱ ነው። ዩኒቨርስቲዎች አብዛኛው የዓለም የዕውቀት እና ምርምር እምቅ አቅም መመረቻ ሥፍራዎች ናቸው። ክፍት ሳይንስ እና ክፍት ተደራሽነት ከወደፊት የተመራማሪዎች እና የባለሙያዎች ትውልዶች ትምህርት ጎን ለጎን ምርምር፣ ፈጠራ እና ምርመራን ለማሳደግ ግዴታ የገቡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ዝግጁ ኢጋርነት ያገኛሉ።

## የዩኒቨርስቲ ምርምር ለክፍት የጋራ ዕውቀት

ዕውቀቶች ሊለሙ እንደሚችሉ እና ለሁሉም የጋራ ደህንነት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ንብረቶች መታወቅ አለባቸው። አሁን ያለው ዕውቀቶችን ሥረ ወጥ የማድረግ እና በየክፍላተ ዓለሙ የሚታየው ያልተመጣጠነ ስርጭት መፈተሽ አለበት። የዩኒቨርስቲ ምርምር በዘመናችን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ደንቦች የታጠሩ ዕውቀቶችን ከመፍጠር ይልቅ አዳዲስ አማራጮችን ማስቀደም አለበት። ይህ የሚጀምረው በርካታ የዕውቀት ዓይነቶች ለመኖራቸው ዕውቅና በመስጠት እና የተለያዩ ቋንቋዎችን በብዛት በመጠቀም ነው። በዚህ መንገድ ዩኒቨርስቲዎች የጋራ ዕውቀትን ማስፋፋት እና አካታችነቱን እና ሥብጥሩን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

> *ከፍተኛ ትምህርት ለነጻ እና ክፍት የዕውቀት እና የሳይንስ ተደራሽነት ጠንካራ ጠበቃ መሆን አለበት።*

የዩኒቨርስቲዎች መካከል የሚደረግ ትብብር እና የዓለም አቀፋዊነት ጥረቶች የምንጋራውን ዓለም አቀፍ የወል ብልጽግናችንን ለማስፋት ትልቅ ተስፋ ያላቸው የክፍትነት ምሳሌዎች ናቸው። በሚቀጥሉት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ቅበላ ቀጣይነት ያለው ዕድገት እንደሚኖረው ሁሉም ትንበያዎች ያመለክታሉ። ብዙ ዩንቨርስቲዎች ሕዝባዊ መማማሪያ ቦታዎችን በመፍጠር፣ በአስተዳደራቸው ምላሽ ሰጭነትን እና ይፋዊ ተጠያቂነት በማሳየት እና የሕዝብን ጥቅሞች በማሳደግ የትምህርትን ሕዝባዊነት የመደገፍ የተከበረ ባሕል አላቸው። ነገር ግን ዩኒቨርስቲዎች፣ በተለይ ከቅርብ ዐሥርት ዓመታት ወዲህ፣ በወጪ እንቅፋቶች እና በአእምሯዊ ንብረት ይገባኛል ጥያቄዎች ምክንያት ብዙ አግላይነቶች የሚመረቱባቸው ቦታዎችም ናቸው። ከዚህ በተቃራኒ ብዙ ጥረቶች ቢደረጉም፣ የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓቶች የማግለያ እና የመነጠያ ሥፍራዎች ሆነው ቀርተዋል። ይሄ በአስቸኳይ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል።

ከፍተኛ ትምህርት በአካዳሚያዊ የትምህርት ዕድል፣ የመማሪያ ቁሳቁስ፣ በሶፍትዌር እና በዲጂታል ግንኙነት እና በመሳሰሉት ረገድ፣ ለነጻ እና ክፍት የዕውቀት እና የሳይንስ ተደራሽነት ጠንካራ ጠበቃ መሆን አለበት። "ክፍት" የሚለው ቃል መገኘትን

እና ቀላሉ ተደራሽ መሆንን የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን፤ ግለሰቦች መረጃን እና ዕውቀትን ሊያሻሽሉ እና በሚፈልጉት መንገድ መጠቀሚያ ሊያደርጉት እንደሚችሉም እንደሚጠቅስ ማስተዋል ያስፈልጋል።

## የቴክኒክ እና ሙያ ከፍተኛ ትምህርት እና የጋራ ዕውቀት

የማኅበረሰብ ኮሌጆች እና ፖሊ ቴክኒኮችን ጨምሮ፣ የድኅረ ሁለተኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት እንደ ማሰልጠኛ ተቋማት ብቻ ሳይሆን እንደ የተግባራዊ ጥናትና ምርምር ስፍራዎችም መታየት አለባቸው። በግላዊ እና የጋራ ሕይወታችን ውስጥ ለአምራችነት ችሎታዎች አስፈላጊነት፣ ለትምህርት ማኅበረሰቦች ውጤታማ አሠራር፣ ትርጉም ያለው ሥራ ለሚያስገኙ በርካታ መንገዶች እና በተለያዩ ዘርፎች እና ማኅበረሰቦች መካከል ላለው የመቀናጀት፣ የሽርክና እና የትብብር ትልቅ አቅም ጉልሕ ቦታ መስጠት አለባቸው። ከማኅበረሰብ ጋር በቅርበት የተሳሰሩት የበርካታ የሙያ ተቋማት አካባቢያዊ ባሕርይ የዳበሩ አካባቢያዊ የመማር ባሕሎችን ለማዳበር ዕድል ይሰጣሉ። የአካባቢ ማኅበረሰቦች ከጋራ ዕውቀቶች ጋር የተለየ ግንኙነት አላቸው፤ የቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት ደግሞ በተለዩ፣ አውዳዊ አግባብነት ባላቸው መንገዶች ዕውቀቶቹ ስለሚተገበሩበት ሁኔታ ግንዛቤዎችን ለማዳበር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

## ከፍተኛ ትምህርት የተለያዩ የዕውቀት አቀራረቦችን ለመደገፍ

በከፍተኛ ትምህርት እና በበይነ-ባሕላዊ እና ሥነ ዕውቀታዊ ስብጥር መካከል ያለው ግንኙነት ብዙ ጊዜ አሻሚ ነው። በአንድ በኩል፣ ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ከአዲስ የዓለም አተያዮች እና ሐሳቦች በማስተዋወቁ ይኮራል። ነገር ግን በተመሳሳይ፣ ከፍተኛ ትምህርት የተወሰኑ የዕውቀት አመራረት ዓይነቶችን የሚያደራጅበትን፣ የሚመዘንበትን እና የሚያጸድቅባቸውን የተለዩ መንገዶችን አዘጋጅቷል።

የተፈጥሮ ሳይንስ ዘዴዎች እና የማኅበራዊ ምርምር ፅንሰ ሐሳቦች እንደ "ጥብቅነት"፣ "አስተማማኝነት" እና "ትክክለኛነት" ከባሕል ተጽዕኖ ነጻ አይደሉም። የምሁራዊ ሕትመት ማኅበራዊ ሂደቶች፣ የጥራት ማረጋገጫ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ለበይነ-ባሕላዊ እና ሥነ ዕውቀታዊ ስብጥር አክብሮት የለውም። አገር በቀል ዕውቀቶች እና የዕውቀት ማመንጨት እና መጋራት ዘዴዎቻቸውም በአጠቃላይ እንደ የምርምር መልኮች ሳይሆን፣ እንደ ግብአት ይቆጠራሉ።

በማወቂያ እና በመሥሪያ መንገዶች ረገድ ብዙነት እየተስፋፋ ሲመጣ፣ ከባሕል እና ተመክሮ ሀብቶች የሚመነጩ የዕውቀት ሥነ ምህዳሮች የበለጠ ዋጋ ሊሰጣቸው ይገባል። በሁሉም የዓለም ክፍሎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ማኅበረሰቦች መካከል ያሉት አጋርነቶች በትክክል ለጋራ ጥቅም የቆሙ መሆን አለባቸው። የማወቂያ እና የመሥሪያ መንገዶችን የጥንካሬ እና የዘላቂነት ምንጭ አድርጎ ማድነቅ በራሱ፣ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ኢሚዛናዊነቶች ለመቀነስ ይረዳል።

በከፍተኛ ትምህርት ዐውድ ውስጥ ያሉ ተቋማዊ ልይይቶችን በአግባቡ በማክበር ስብጥርን መደገፍ ይቻላል። የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነት በሚፈለገው ልክ ከቀጠለ በርካታ ልዩ ልዩ ተቋማትን እንፈልጋለን። የጋራ ዕውቀት ክፍት መሆን፣ በተቻለ መጠን ለብዙ ሰዎች ተደራሽ የሚሆንባቸውን እንዳስፈላጊነቱ የሚለዋወጡ የከፍተኛ ትምህርት መዋቅሮችን ይፈልጋል።

# የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች

ይህ ምዕራፍ በአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ውስጥ ሥርዓተ ትምህርቶች የተማሪዎችን የመመዘን እና የመተግበር አቅም እያዳበሩ፣ ዕውቀትን እንዲያገኙ እና እንዲያፈሩ ለሚረዷቸው ሥነ ምህዳራዊ፣ ባሕላዊ እና በይነ-ዲሲፕሊናዊ ትምህርቶች አጽንኦት እንዲሰጡ ምክረ ሐሳብ አቅርቧል። ወደ 2050 ስናማትር፣ ይህንን ምክረ ሐሳብ ወደፊት ለማራመድ የሚያስፈልገውን ውይይት እና ድርጊት ለመምራት የሚረዱ አራት መርሆች አሉ።

- **ሥርዓተ ትምህርቶች የተማሪዎችን የጋራ ዕውቀት የማግኘት እና ለእሱም ለማበርከት ያላቸውን ችሎታ ማሳደግ አለባቸው።** በዘመናት የተከማቹ የሰው ልጅ የጋራ የዕውቀት ሀብቶች የሥርዓት ትምህርት የጀርባ አጥንት መሆን አለባቸው። የጋራ ዕውቀቶች ይወሰዱ እና ይጨመርባቸው ዘንድ በሰፊው ተደራሽ መሆን አለባቸው። ተማሪዎች (በሁሉም ዕድሜ ያሉ) የዕውቀትን መነሻ ግምቶች እና ዓላማዎች በመፈተሽ በፈጠራ እና በኂሳዊ መንገድ በዕውቀት ሥራ እንዲሳተፉ ማስተማር አለብን። ትምህርት ሰዎች በጋራ ዕውቀት ውስጥ ያሉ ግድፈቶችን እና ማግለሎችን እንዲያርሙ እና ዕውቀቱም በዓለም ያሉ የማወቂያ እና የመኖሪያ መንገዶችን ስብጥር የሚያንጸባርቅ ዘላቂ፣ ክፍት ሀብት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።
- **የሥነ ምህዳር ቀውሱ የሰው ልጅ በዓለም ላይ ያለውን ቦታ የሚቀይሩ ሥርዓተ ትምህርቶችን ይፈልጋል።** ውጤታማ እና ተገቢ የአየር ንብረት ለውጥ ትምህርት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። በሥርዓት ትምህርቱ ሙሉ በሰዎች ድርጊት በተጎዳች ፕላኔት ላይ በአክብሮት እና በኃላፊነት የመኖር ጥበብን ማስተማር አለብን።
- **የተዛቡ መረጃዎችን መስፋፋት በሳይንሳዊ፣ ዲጂታል እና ሰብአዊነት ባላቸው መሠረታዊ ትምህርቶች መዋጋት ያስፈልጋል።** ሥርዓት ትምህርቶች ሳይንሳዊ ፍተሻን፣ እና በጠንካራ ምርምር እና በውሸት ፈጠራዎች መካከል ያለውን ልዩነት የመለየት ችሎታን ማጉላት አለባቸው። ተማሪዎች ቴክኖሎጂን ትርጉም ባለው መልኩ እንዲጠቀሙ የሚያስችሏቸውን ዲጂታል ክህሎቶች ማልማት አለብን። ሥርዓት ትምህርቶች ተማሪዎች እንዴት እና ለምን ዓላማዎች እንደሚጠቀሙበት የመወሰን ሚና ኖሯቸው በሳይንስና በቴክኖሎጂ “የሚሠሩበትን” ችሎታ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
- **ሰብአዊ መብቶች እና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ሰዎችን እና ዓለምን የሚቀይሩ ቁልፍ የትምህርት አላባዎች መሆን አለባቸው።** የተማሪዎችን የማድረ አቅም ለሚደግፍ፣ እና ለሁሉም ሰው ዕውቅና እና ዕድገት ወደሚቆም የትምህርት ዓለም ለሚያስገባ የሰብአዊ መብት ትምህርት ቅድሚያ መስጠት አለብን። የሥርዓተ ጾታ እኩልነት በሁሉም ሥርዓተ ትምህርቶች ትኩረት ሊሰጠው እና ጨቋኝ የሥርዓተ ጾታ አመለካከቶች ደግሞ ሊወገዱ ይገባል። ተማሪዎች ሁሉንም ዓይነት ዘረኝነት እና አድልዎ እንዴት በቀጥታ መጋፈጥ እንደሚችሉ መማር አለባቸው።

እነዚህ አራት የመመሪያ መርሆች አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ወደ ትምህርታዊ ልምምድ ለመተርጎም በማነሣሣት ሊያገለግሉ ይችላሉ።

# ምዕራፍ 5

# የመምህራን ለዋጭ ሥራ

*መምህሩ ጥበባዊውን ዕውቀት የሚያገኝበት የተለየ ዕድል ሁልጊዜ አይኖረውም። እሱም እንደተማሪዎቹ፣ መሆን የሚገባውን በመሆን ሂደት ላይ ነው።*

ዌይ-ሚንግ ቱ፣ *Humanity and Self-Cultivation, 1996.*

**በትምህርት አዲስ ማኅበራዊ ውል ውስጥ መምህራን ዋነኛ ማጠንጠኛ መሆን አለባቸው፤ ሙያቸውም ትምህርታዊ እና ማኅበራዊ ለውጦችን ለማምጣት የሚያስችሉ አዳዲስ ዕውቀቶችን እንደሚቀሰቅስ የትብብር ጥረት እንደገና መጤን አለበት።**

መምህራን በትምህርት አዲስ ማኅበራዊ ውል ግንባታ ረገድ ልዩ ሚና ይጫወታሉ። መምህርነት በሕዝባዊ እና በግል ውጥረቶች መሀል የሚሠራ መልከ ብዙ፣ ውስብስብ እና ፈታኝ ሙያ ነው። መምህራን የወደፊቱን ከሚወርሱትና ከሚገነቡት ወጣት ትውልዶች ጋር በመነጋገር የጋራ ዕውቀት ማሰባሰብን በትብብር ይሠራሉ። መምህርነት የቡድን ሥራ ቢሆንም፣ በተመሳሳይ ግን የእያንዳንዱን ተማሪ ልዩ ፍላጎቶችና አቅሞችም ያስተናግዳል። እነዚህ ጥንቅሮችና ተቃርኖዎች የመምህራን ሊተካ የማይችል ሥራ መለያ ባሕርያት ናቸው።

ማስተማር ርህራሄን፣ ብቃትን፣ ዕውቀትን እና የሥነ ምግባር ውሳኔን ይጠይቃል። ጥበበኛ እና የተማሩ ሰዎች በመላው ዓለም ባሉ ባሕሎች ውስጥ ዕውቅና ይሰጣቸዋል፤ በዚህ ትውፊት መሠረትም፣ “መምህር” በትምህርት ቤት አውድ ውስጥ እንደ ልዩ ተዋናይ ጎልቶ ይታያል። መምህራን የለውጥ ዕድሎችን የያዙ ቁልፍ ሰዎች ናቸው። እነሱ ደግሞ በተራቸው፣ በጋራ ሥነ ትምህርታዊ ገጠመኞቻቸው ለተማሪዎቻቸው የመሳተፍ፣ የመተባበር እና የመማር አቅም ዕውቅና መስጠት አለባቸው። ይህንን ሰፊ እና ውስብስብ ሥራ ለማከናወን መምህራን በቂ ነጻነት እና ድጋፍ ያላቸው፣ የበለጸጉ የማስተማር የትብብር ማኅበረሰቦች ያስፈልጋቸዋል። የመምህራንን ራስን በራስ የማስተዳደር፣ ዕድገታቸውን እና ትብብራቸውን መደገፍ ለወደፊት የትምህርት ዕድል አስፈላጊ የሆነው የሕዝባዊ አጋርነት መገለጫ ነው።

ይህ ምዕራፍ የሚጀምረው የማስተማርን ወደፊት በቡድን ሥራ እና ለልዩልዩ ዓይነት ተማሪዎች ሁለገብ የትምህርት ሥራን በሚያጠናክሩ ልዩ ባለሙያዎች እንደሚበለጽግ፣ እንደሚዳብር እና እንደሚተገበር ‘የትብብር ሙያ’ መልሶ በመቅረጽ ነው። መምህራን እንደ አስተዋይ ተግባሪዎች እና የዕውቀት አምራቾች ዕውቅና ሲያገኙ የትምህርት ከባቢን፣ ፖሊሲዎችን፣ ምርምሮችን እና ተግባሮችን ለመለወጥ በሚያስፈልጉት አዳጊ የዕውቀት አካላት ውስጥ በሙያቸውም ሆነ ከሙያቸው ባሻገር አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

በመቀጠልም ምዕራፉ አዲሱ የትምህርት ማኅበራዊ ውል በጠቅላላው በመምህራን የዕድገት ዘመን ውስጥ - ከምልምልነት፣ ወደ ጀማሪነት፣ ከዚያም ብቃቱ እስከተረጋገጠለት ባለሙያነት - በተለያዩ ጊዜያት እና ሥፍራዎች በተናጥል እና ከሌሎች ጋር በመሆን በሚደረገው የዳበረ ቀጣይነት ያለው ጉዞ ላይ የሚኖሩትን አንድምታዎች ይመለከታል።

ትምህርት ቤቶች፣ ማኅበረሰቦች፣ ቤተሰቦች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የፖለቲካ አካላት በመምህራን ዙሪያ በአንድነት እንዲሰለፉ፣ የሥራቸውን ወሳኝነት እንዲገነዘቡ እና ለስኬታማነታቸው ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጥሩ ምዕራፉ ጥሪውን ያቀርባል። በተለይ በመምህራን፣ በት/ቤት መሪዎች እና መንግሥታት ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ፣ የ2050ን የውይይት እና የድርጊት መምሪያ መርሆች አቅርቦ ያጠቃልላል። መርሆቹ የሚከተሉትን ዋና ዋና ዓላማዎች ያካትታሉ፡- የመምህራንን ትብብር መደገፍ፤ ለዕውቀት ማመንጨት ቅድሚያ መስጠት፤ እንዲሁም ስለትምህርት በሚደረግ ሕዝባዊ ክርክር ውስጥ የመምህራን ራስገዝነት እና ተሳትፎ መደገፍ።

# ማስተማርን እንደ የትብብር ሙያ መልሶ መቅረጽ

በተለያዩ ጊዜያት እና ቦታዎች፣ መምህራን የተለያዩ ማኅበራዊ ሚናዎች እና ተግባራት አሏቸው። ስለመምህራን ሚናዎች የሚነሡት ሐሳቦች በየባሕሉ ይለያያሉ፤ ለምሳሌ የሕዝብ አገልጋዮች እና የሕዝብ ምሁራን፣ ባለሙያዎች እና አርቲስቶች፣ የማኅበረሰብ መሪዎች እና ለውጥ ፈጣሪዎች፣ የግብረገብ አስጠባቂዎች እና የወደፊቱ የመተማመን ወኪሎች ሊሆኑ ይችላሉ። ብዙዎቹ የሰው ልጅ ታላላቅ ታሪካዊ ሰዎች በመምህርነት ተገልጸዋል፤ ከመንፈሳዊ መሪዎች እና ሳይንቲስቶች እስከ ጥንታዊ ፈላስፋዎች እና የሒሳብ ሊቃውንት፣ ሁሉም በዙሪያቸው ያሉትን እያስተማሩ የሰውን ልጅ የውርስ ዕውቀት ወደ አዲስ ከፍታ አሳድገውታል።

ከታሪክ አኳያ፣ መምህራን በዐሥራ ዘጠነኛው እና በሃያኛው ክፍለ ዘመን የትምህርት ማኅበራዊ ውል ግንባታ ውስጥ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። ከሕብረተሰቡ ጋር ባላቸው ግንኙነት እና በትምህርት ቤት አደረጃጀት ውስጥ ባላቸው ሥፍራ በትምህርት ለሁሉም እና አይተዌ ትምህርት ምሥረታ ዋነኛ ተዋናዮች ነበሩ። መጀመሪያ ላይ፣ መምህራን የመጀመሪያዎቹ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መምህራን እና ጀማሪዎች በመሆን ብዙ ጊዜ የፋና ወጊነት ሚና ተጫውተዋል። የ'ልከኛ ትምህርት ቤቶች' የመጀመሪያ ንድፍ ከእነሱ የሚጠበቀውን ያሳይ ነበር፦ መደበኛውን የትምህርት ቤት መዋቅር፣ ሥርዓተ ትምህርትን፣ ሥነ ትምህርትን እና የዕለት ከዕለት ሥራን ወደ አንድ ማምጣት። ደረጃ ማበጀት እና አርአያነትን መትከል ዓላማቸው ለሌሎች ትምህርት ቤቶች ዋቢ ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ ደንቦችን እና ሥርዓቶችን ማዘጋጀት ነበር። ያለፈው ክፍለ ዘመን ሥራ ከአሜሪካ እስከ ቻይና፣ ከብራዚል እስከ ሕንድ ድረስ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመምህራን ትምህርት ተቋማትን ለማጠናከር በተደረገው ጥረት በግልጽ ይታያል።

የትምህርት ቤት ሥራ ሲያድግ፣ ግለሰብ መምህራን በሥራቸው፣ በሚናዎቻቸው እና በብቃታቸው ዋነኛ የትምህርት ወኪሎች ሆነዋል። እንደዚሁም፣ የትምህርት ፍላጎት መጨመር ሁሉን በአንድ የሚያስተምረው የ"አንድ ክፍል" ሞዴል ተማሪዎችን በዕድሜ ምድቦች ወደ የተለያዩ ክፍሎች ወደሚመድበው "የእንቁላል ሣጥን" ሞዴል ሲያድግ ታይቷል። ነገር ግን፣ ይህ የተስፋፋው "የእንቁላል ክሬት" የትምህርት ቤት ሞዴል መምህራን የትምህርት ዕቅዶች እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶቻቸውን በተናጠል ለማዘጋጀት እንደተገደዱ መቅረታቸውን እና እርስበርስ የሚተባበሩበት ሁኔታ አለመፈጠሩን አላጤነም። ይህ ሞዴል በመምህራን ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ የሚሄዱ፣ ዘላቂ ያልሆኑ ጫናዎችን ይፈጥራል።

> *የመምህራን የግል ተሰጥኦዎች እና ችሎታዎች በትብብር እና በመደጋገፍ መጠናከር አለባቸው።*

የመምህራን የግል ተሰጥኦዎች እና ችሎታዎች በትብብር እና በመደጋገፍ መጠናከር አለባቸው። መምህራን ሊጋራ የወደፊት ሕይወታችን ሲባል፣ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን እንደገና በማዋቀር ረገድ ያላቸውን ማዕከላዊ ሚና መቀጠል አለባቸው። ይህን የማድረግ አቅሞቻቸው ትብብር እና ሕብረት በአሠራር ዘይቤዎቻቸው ውስጥ በተሳሰሩበት ደረጃ በቀጥታ ይወሰናል።

## መምህራን በአካታች የትምህርት ከባቢዎች

ተማሪዎችን ለመደገፍ፣ መምህራን የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ፍላጎት ለመደገፍ በት/ቤታቸው ውስጥ ከሚገኙ መምህራን እና ሌሎች ልዩ ባለሙያዎች ጋር በትብብር መሥራት አለባቸው። ትምህርት የአስተማሪ የብቻ ሥራ ነው የሚለው አስተሳሰብ በአንድ ግለሰብ የማይሟሉ ፍላጎቶችን ከመጫኑ በላይ፣ ብዙዎች ከሙያው እንዲወጡ ሊያደርግ ይችላል። በተመሳሳይም፣ የተማሪዎች አካላዊ፣ ማኅበራዊ እና ስሜታዊ ፍላጎቶች ለመማር ችሎታቸው ወሳኝ ናቸው። ተማሪዎች ከሌሎች አስፈላጊ ድጋፎች ጋር የመምህራንን ውጤታማነት በሚያሳድግ ሥርዓት ሊደገፉ ይገባል። እነዚህም ለጤና እና የአመጋገብ፣ የማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ የአእምሮ ጤና እና የልዩ የትምህርት ፍላጎቶች ድጋፍን ሊያካትቱ ይችላሉ። በተለይም የልጆቻቸውን ትምህርት ለመደገፍ ከቤተሰቦች የሚመጡ ውጤታማ ተሳትፎን ያካትታሉ።

መምህራን በቡድን የሚሠሩባቸው ተስፋ ሰጭ እርምጃዎች እየታዩ ነው። ለምሳሌ፣ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በቋንቋ ጥበባት ውስጥ ሁሉም ሰው ግንዛቤዎቻቸውን፣ ሐሳቦቻቸውን እና ምልከታዎቻቸውን መጋራታቸውን ለማረጋገጥ፤ ከክፍል መምህራን፣ ከመሠረተ ትምህርት ባለሙያዎች እና ከልዩ ትምህርት መምህራን ጋር የጋራ የዕቅድ ቡድኖችን ይፈጥራሉ። በእንደዚህ ዓይነት የአብሮ ማስተማር አጋርነቶች ውስጥ፣ መምህራን የተማሪዎችን የተለዩ ፍላጎቶች ለማሟላት በአንድነት ከመሥራታቸውም በላይ፣ የክፍሉን የጋራ አካሄድም ያጎለብታሉ። በሌሎች ምሳሌዎች፣ የሕዝብ አገልግሎቶች እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች የተማሪዎችን አጠቃላይ ትምህርት፣ ጤና እና ደህንነታቸውን በሚደግፉ መንገዶች ከክፍል ውጭ ከተማሪዎች እና ቤተሰቦች ጋር ለመገናኘት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ዘርፎች ከትምህርት ቤቶች ጋር አብረው ይሠራሉ። ለእያንዳንዱ ተማሪ ከሜንተሮች፣ ከአማካሪዎች፣ ከልዩ ባለሙያዎች እና ከአብሮ መምህራን ጀምሮ የሚያስፈልገውን የተሟላ ድጋፍ ለመስጠት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ተስፋ ሰጪ አካሄዶች አሉ።

ከእንደዚህ ዓይነት የትብብር ዕድሎች አንጻር፣ መምህራን ብዙ ቦታዎችን እና መገኘትን ያቀፉ አዳዲስ የትምህርት መልክዓ ምድሮችን በመገንባት ረገድ የሚጫወቱትን ጠቃሚ ሚና በተሻለ ሁኔታ መረዳት ይቻላል። እነዚህ አዳዲስ ከባቢዎች በአጋጣሚ የተገኙ ሳይሆኑ፤ በየአካባቢው ሥርዓት ባለው መንገድ እና ታስቦበት የተሠራ ሥራ ውጤቶች ናቸው። የአካባቢ መሪዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ባለሥልጣናት፣ ማኅበረሰቦች እና ቤተሰቦች ሁሉ የሚጫወቷቸው ወሳኝ ሚናዎች አሏቸው። ማኅበራዊ ሠራተኞች፣ ጋይዳንስ ካውንስለሮች፣ የልዩ ትምህርት መምህራን፣ የቤተ መጻሕፍት ባለሙያዎች እና የመሠረተ ትምህርት ስፔሻሊስቶች ተማሪዎች ወደ የመማሪያ አካባቢዎች የሚያመጡትን እና መምህራኑ የሚያቀናጁትን ልዩ እንቅስቃሴ የበለጠ ማጠናከር ይችላሉ።

በትምህርት ቤቶች ዙሪያ ያሉ የትምህርት አካባቢዎች የመማሪያ ቦታዎችን መረብ ያቀፉ መሆን አለባቸው። በትምህርት ቤቶች ውስጥ ወይም ባሻገር በሚሰጡ የክፍል ውስጥ ትምህርት እና የክፍል ውጭ ትምህርቶች መሀል ያሉ ክፍፍሎች ቢደበዝዙ ወይም ቢጠፉ ይመረጣል። መምህራን እነዚህን መረቦች የሚያዘልቁ ትሥሥሮችን በመንደፍ እና በመገንባት ረገድ ቁልፍ ሚና ቢጫወቱም፤ ነገር ግን ይህንን ውጤታማ ለማድረግ፣ በልማዳዊ ደንባቸው፣ በማንነታቸው እና በመለያዎቻቸው ላይ ለውጥ መደረግ አለበት። በዚህ እንደ አዲስ የትምህርት ሥነ-ምህዳሮች እና የመማሪያ ቦታዎች አውታረ መረቦች አደራጅነት ማኅበራዊ እና ተቋማዊ ሚናቸው፣ መምህራን እና የባልደረቦች ቡድናቸው የትምህርት ወደፊት በመቅረጽ ረገድ ወሳኝ ተዋናዮች ሆነው ይወጣሉ።

> *ማስተማር የአንድ ግለሰብ በተዘጋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪን በተግባራት ወይም በትምህርቶች አማካይነት የመምራት ጉዳይ አይደለም።*

ማስተማር የአንድ ግለሰብ በተዘጋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪን በተግባራት ወይም በትምህርቶች አማካይነት የመምራት ጉዳይ አይደለም። ይልቁንም፣ ማስተማርን በትምህርት ቤት ውስጥ ከዳር እስከ ዳር እና ከሌሎች የትምህር ባለሙያዎች ጋር በጋራ የሚከናወን ሥራ እንደሆነ ማሰብ አለብን። ከመማሪያ ክፍሎች ይልቅ ትምህርት ቤቶችን በመማሪያ አደረጃጀትነት ለመቀበል የሚደረገው ሽግግር ሁልጊዜ ቀላል አይሆንም። በእርግጥም የትምህርት ቤት አሠራር ጥብቅነት በመምህርነት ሙያ ውስጥ የሚኖሩ የትብብር ሂደቶችን አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል። የትብብር ሐሳብ የግለሰቦችን ግዴታዎች ወይም አስፈላጊነት አይቀንስም። በምትኩ፣ በትምህርት ቤት ሥፍራዎች ሁሉ በጋራ የመሥራት እና በትምህርት ቤቶች አስተዳደር እና አቅጣጫ ላይ የተሻሻሉ የግል ሚናዎችን የመወጣት አዳዲስ ኃላፊነቶችን ይዞ ይመጣል። ትብብርን በግድ ለመተግበር የሚደረጉ ሙከራዎች ግን፣ ፍሬ ቢሶች እና ውጤታማነትን የሚያደናቅፉ ናቸው። ትብብርን በተፈጥሯዊ መንገድ ለማሳደግ በሥርዓተ ትምህርት እና በሥነ ትምህርት አደረጃጀት ላይ ለውጦች መፈጠር አለባቸው። ሁሉም ትምህርት መምህራን በክፍል ውስጥ ገለጻ በሚያደርጉበት መንገድ ቢደራጅ፣ ትብብር ምንም ፋይዳ አይኖረውም። ነገር ግን መማር በችግሮች እና በፕሮጀክቶች ላይ በመመሥረት፣ በልዩ ልዩ ቦታዎች እና ጊዜዎች ውስጥ የሚከናወን ተደርጎ ቢደራጅ፣ ትብብር ወሳኝ ይሆናል።

## ሥርዓተ ትምህርት እና ሥነ ትምህርትን ማቀድ እና መደንገግ

ሥርዓተ ትምህርቶች ተነድፈው የሚደነገጉ ብቻ ሳይሆኑ፤ ተደንግገው የሚተገበሩ ናቸውው። ክፍት እና የጋራ ዕውቀትን መሠረት በማድረግ አዳዲስ የሥርዓተ ትምህርት ዓይነቶችን መቅረጽ እና ማውጣት በመምህራን ሥራ ላይ በእጅጉ የተመካ ነው። የዲጂታል ቴክኖሎጂ ዕድሎች የሞሉበትን ዓለም ቢሰጠንም፣ ፈጠራዎች ስኬታማ የመሆን ዕድላቸው ከፍተኛ የሚሆነው በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የተማሪዎችን ልዩ ፍላጎቶች እና ባሕርያት እንዲያሟሉ ተደርገው ሲዘጋጁ ነው። ትክክለኛ እና ተገቢነቱን ለማረጋገጥ ሲባል ትምህርትን ግል ተኮር ለማድረግ፣ መምህራን ወሳኝ ሚና ነው። ለማላመድ፣ ለመገንባት፣ ለመንደፍ እና ለተማሪዎቻቸው የተሻሉ የመማር ዕድሎችን ለመፍጠር ሥፍራ፣ በቂ ዝግጅት፣ የማስተማሪያ ግብዓቶች እና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። የወደፊት ሥርዓተ ትምህርቶች ከቴክኖሎጂ የሚገኘውን ጨምሮ፣ በጠንካራ ድጋፎች የተሟላ እና

ከአቻዎቻቸው ጋር በበለጸገ ትብብር እና እንደ የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮች እና ሳይንቲስቶች ካሉ የርእሰ ጉዳይ ባለሙያዎች ጋር በተፈጠረ አጋርነት አማካይነት ለመምህራን ሰፊ ራስገዝነት መስጠት አለባቸው።

በአሳታፊ እና በትብብራዊ አቀራረቦች ላይ የተመሠረቱ ሥነ ትምህርቶች የሚዳብሩት በክፍል ውስጥ ትብብራዊ ትምህርት ብቻ ሳይሆን፣ በመማሪያ ክፍሎች እና በባልደረባዊ የመማማሪያ ማኅበረሰቦች መካከል በሚኖር ትብብራዊ ትምህርት ነው። መምህራን የሚያጋጥሟቸው አንዳንድ ውስብስብ ፈተናዎች ሊፈቱ የሚችሉት በግለሰብ ደረጃ ሳይሆን፤ በትምህርት ቤቶች ትሥሥሮች፣ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በሚኖሩ አጋርነቶች ወይም በልዩ የትምህርት አደረጃጀቶች በሚደገፉ የሙያ ማኅበረሰቦች ነው። ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የመማሪያ ተመክሮዎች መንደፍ ሲያስፈልግ መምህራን ከሌሎች እንደ የጥናት ቡድኖች፣ የመምህራን ምክር ቤቶች፣ የሥነ ትምህርት ቡድኖች፣ የአቻ ምክክር፣ ሥልጠናዎች፣ ምልከታዎች እና የጣቢያ ጉብኝቶች እና ከመሳሰሉት ጋር መተባበር የሚችሉባቸው እጅግ በጣም ብዙ መንገዶች አሉ።

ሙያዊ የማስተማር ዕውቀት በንድፈ ሐሳብ እና በተግባር መካከል ባለው ውይይት ላይ የሚገነባ እና እያደገ በሚመጣው የተመክሮዎች ክምችት ላይ በግል እና በወል በሚደረግ ማውጠንጠን የሚዳብር ነው። የትኞቹም ሁለት ሥነ ትምህርታዊ ሁኔታዎች ፈጽሞ አንድ ዓይነት አይደሉም፤ ይህም የመምህራንን ተዛምዷዊ ሥራ በጣም በተራቀቁ ማሽኖች እንኳን የማይተካ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ ነው። ሥነ ትምህርት እያንዳንዱ ተማሪ የሰው ልጅ ከዕውቀት ጋር ያለው ግንኙነት አካል እንዲሆን፤ በማስተዋል፣ በፈጠራ እና በርህራሄ ዓለምን እንዲቀርብ ይፈቅዳል። መምህራን በሌሉበት ሥርዓተ ትምህርት እና ሥነ ትምህርትን እንደገና ማጤን የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም።

*መምህራን በሌሉበት ሥርዓተ ትምህርት እና ሥነ ትምህርትን እንደገና ማጤን የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም።*

## መምህራን እና ትምህርታዊ ምርምር

መምህራን አስተያየቶቻቸውን እንዲያንጸባርቁባቸው ከሚያስፈልጉ ወሳኝ ገጽታዎች አንዱ ከዕውቀት ጋር ያላቸው ግንኙነት ነው። ለአንዳንዶች በጣም አስፈላጊው ነገር የትምህርት ዓይነቶችን በግሩም ብቃት ማስተማር ነው። ለሌሎች፣ አስተምህሯዊ እና ትምህርታዊ ዕውቀት ይቀድማል። ሦስተኛው ዓይነት ዕውቀት ሙያዊ የማስተማር ዕውቀት ነው። በማንኛውም ሙያ ውስጥ፣ ባለሙያዎች ብዙውን ጊዜ ከስልታዊ ሙከረት፣ የተመክሮ ምዘና እና ልምምድ በመነሣት ሙያዊ ዕውቀትን የማመንጨት እና የማኸዘብ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።

መምህራን ሥራቸው ላይ እንደሚያንጸባርቁ ባለሙያዎች የሚታወቁበትን ሙያ ለመቅረጽ በተግባር ላይ የተመሠረተ ዕውቀት ወሳኝ ነው። በግል ደረጃ፣ ሙያዊ የማስተማር ዕውቀት በግንዛቤያዊ፣ ተግባራዊ እና ተዛምዷዊ አውታሮች አሉት። ትብብራዊ የማስተማር ሥራ በባሕርይው የማውጠንጠን እና በእኩዮች መካከል የመጋራትን አውታሮች ያቀናጃል። በሂደትም፣ ይህ ምርምር መምህራን የደራሲነቱን ድርሻ ወደሚወስዱበት ወደ ጽሑፍ ሊተረጎም ይችላል። አንድ ሙያ ቅርሶቹን፣ ተመክሮዎቹን እና አሠራሮቹን መመዝገብ ብቻ አይበቃውም፤ ለምርመራ እና ለፈጠራ አዳዲስ መስኮችን መለየት፣ የምርምር ጥያቄዎችን መበየን እና እነሱን መከተልም ያስፈልገዋል። መምህራን በአውጠንጣኝ ሙያተኞችነታቸው እና በዕውቀት አምራቾችነታቸው ዕውቅና ሲያገኙ በገዛ ሙያቸው ውስጥም ሆነ ከዚያ ባሻገር፣ የትምህርት አካባቢዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ምርምርን እና ተግባርን ለመለወጥ በሚያስፈልጉት በማደግ ላይ ባሉ የዕውቀት አካላት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

# ከሕይወት ጋር የተቆራኘው የመምህር ዕድገት ጉዞ

በአሁኑ ጊዜ መምህራን ሚናቸውን እንዲወጡ ለማዘጋጀት የሚረዱ በርካታ ሥርዓቶች እና ተቋማት በዓለም ላይ አሉ። የምስክር ወረቀት ወይም ልምድ ምንም ይሁን ምን፣ ዕውቅና ሊሰጠው የሚገባው ነገር፣ መምህራን በሙያዊ ማንነታቸው፣ አቅማቸው ወይም በሙያዊ ዕድገታቸው "የተጠናቀቁ" ወይም "የተሟሉ" አይደሉም። የመምህራን ዕድገት የዳበሩ እና ተለዋዋጭ የመማር ሂደቶች እና የሕይወት ዘመን እና ከሕይወት ጋር የተቆራኙ ተመክሮዎች ተከታታይነት ውጤት ነው።

የመምህራን ግላዊ እና ባሕላዊ ገጽታዎችም ዕውቅና እና ዋጋ ሊሰጣቸው ይገባል። መምህር መሆን የራስን ተመክሮዎች ማስፋትን እና ከዕውቀት እና የሐሳቦች ዓለም ጋር መተሳሰርን ይጠይቃል። ለንባብ ስሜት የሌላቸው መምህራን በተማሪዎች ዘንድ ማንበብን ሊያበረታቱ አይችሉም። በተመሳሳይም፣ ለሳይንስ ጉጉት እና ፍላጎት ሳይኖር ውጤታማ በሆነ መንገድ ሳይንስን ማስተማርም አይቻልም። ተማሪዎች ከመምህራን ቃል የሚማሩትን ያህል ከሕይወት ተምሳሌትነታቸውም ብዙ ይማራሉ።

የእያንዳንዱ መምህር "የሕይወት ቤተ መጻሕፍት" ለሥራቸው መሠረታዊ ነው። በዚህ የመማር እና የባሕል ማበልጸግ ደስታ ውስጥ ነው መምህራን ከሕይወት ጋር የተቆራኘ የትምህርት ወኪሎች የሆኑት፤ እና በዚህም ከሌሎች እና ከሕያው ፕላኔት ጋር ለሚኖር አዳዲስ አብሮነት እና አጋርነት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

## የመምህራን ምልመላ

ለአንዳንዶች አስተማሪ የመሆን ጉዞ የሚጀምረው ገና በራሳቸው የተማሪነት ዘመን ነው። ሌሎች ደግሞ በዕድሜ ቆየት ብለው ነው ዕድሎቹን የሚያዩዋቸው፤ ምናልባትም በተለያዩ ምክንያቶች ከሌላ የሙያ ጎዳናዎች አቅጣጫ ቀይረው። ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ የታየው ሰፊ የትምህርት መስፋፋት፣ የምልመላ ሁኔታውን ከዚያ በፊት ከነበረው ፍላጎት በላይ በርካታ ተመልማዮችን እየሰፋ ወደመጣው መስክ ስቧል። ይህም አወንታዊ ፋይዳዎች ነበሩት፤ ለምሳሌ በአንዳንድ ቦታዎች በሙያው የሴቶችን ድርሻ አሳድጓል፤ በሌሎች ሁኔታዎች አሉታዊ ተፅእኖዎች ነበሩት፤ ለምሳሌ የሙያ ዝግጅት ያላቸው መምህራን ድርሻ መቀነስ፣ የደመወዝ እና ማኅበራዊ ደረጃን መቀነስ፣ እና የድጋፍ ሥርዓቶችን ከአቅማቸው በላይ መለጠጥ ይገኙበታል።

በብዙ ቦታዎች፣ መምህራን የሚፈለግባቸው እየጨመረ በመምጣቱ፣ ጎበዝ እጩዎችን በመመልመል ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ የመጡት ጫናዎች፣ ስጋቶች እና የማስተማር ችግሮች ለማስተማር ከሚፈልጉ ሰዎች ፍላጎት እና ዝንባሌ በላይ በመሆናቸው፤ ወደ ሙያው በሚገቡት ላይ ከፍተኛ ማሽቆልቆል አስከትሏል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ፍላጎቱ እየጨመረ መምጣቱን ቀጥሏል፦ የዘላቂ ልማት ግብ 4ን ለማሳካት በ2030 ወደ 70 ሚሊዮን የሚጠጉ አዳዲስ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ መምህራንን መቅጠር ያስፈልጋል። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት ሁኔታው በመባባሱ፤ እና ከሙያው በሚወጡት መምህራን የተነሣ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ለመሙላት ብዙ ተጨማሪ መምህራን ያስፈልጋሉ። ጉልሕ ለውጦች ካልተደረጉ፣ ለእጥረቱ ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉትን ተነሣሽነት ያላቸውን ብዙ መምህራን ለመሳብ አስቸጋሪ ይሆናል። ይህ ለፖሊሲ አውጭዎች እና ለአጠቃላዩ ሕብረተሰብ አጣዳፊ ጉዳይ ይሆናል።

ይህ ሁኔታ በተለይ በአገሮች እና በቀጣናዎች መካከል እኩል አይደለም። ትልቁ የመምህራን እጥረት ያለው ዕድሜው ለትምህርት የደረሰ ሕዝብ ብዛት በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ባለበት ከሰሃራ በታች ባለው የአፍሪካ ክፍለ ዓለም ነው። አዳዲስ ምልምል መምህራንን የማስተማር አቅምን ለማሳደግ አስቸኳይ እርምጃ ያስፈልጋል። በጣም ከፍተኛ ተሰጥኦ እያለ፣ የአቅርቦት ጎን መሰናክሎች ብዙ ጊዜ ማን የምስክር ወረቀት እና የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት እንደሚችል ይገድባሉ፣ በተለይ በእነዚያ ውሱን የከፍተኛ ትምህርት ዕድሎች ባሉባቸው አገሮች። በአካባቢ ማኅበረሰቦች የዳበረ የትብብር አቅም ላይ ተመሥርቶ፣ የአካባቢ አቅምን ለማጠናከር ፈጠራ የታከለባቸው የመምህራን ቅጥር እና ልማት ዘዴዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል።

ብቁ የሆኑ መምህራን እጥረት በክፍለ አገር ደረጃም፣ አብዛኛውን ጊዜ በአለመመጣጠን ምክንያት ሊያጋጥም ይችላል። ከወረርሽኙ በፊት፣ በደንብ የሠለጠኑ እና ልምድ ያካበቱ መምህራን በከተማ እና በገጠር አካባቢዎች እና ከተለያዩ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ክፍሎች የመጡ ሕፃናትን በሚያገለግሉ ትምህርት ቤቶች መካከል ልዩነቱ በማያሻማ መልኩ በአለመመጣጠን

ተሠራጭተው ነበር። ባልተጠበቀ ሁኔታ፣ ጥሩ እና ልምድ ያላቸው መምህራን የሚያስፈልጓቸው አካባቢዎች ብዙውን ጊዜ በጀማሪ፣ በበጎ ፈቃደኛ ወይም በቂ ብቃት በሌላቸው፣ ያውም ከሥራ የመልቀቅ ምጣኔያቸው ከፍተኛ በሆነ መምህራን አገልግሎት ይሰጣሉ። አዳዲስ ትውልዶችን ወደ ሙያው ለመሳብ ከሚወጡ ፖሊሲዎች ጎን ለጎን፣ በጣም ብቁዎቹን መምህራን ለማቆየት አስቸኳይ እርምጃዎች ያስፈልጋሉ።

*በጣም ብቁዎቹን መምህራን ለማቆየት አስቸኳይ እርምጃዎች ያስፈልጋሉ።*

በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከአገሬው ቀደምት ሕዝቦች፣ ከቀዬው ተወላጆች እና ከዳያስፖራ የተውጣጡ መምህራንን መቅጠር እና መደገፍ - በአንዳንድ ሁኔታዎች የራሳቸውን ተማሪዎች ባሕላዊ ቅርሶች በተሻለ ሁኔታ ለማንጸባረቅ - ስብጥርን ለማክበር እና የተማሪን መማር ለማሳደግ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በእርግጥም ከእነዚህ ቡድኖች የተውጣጡ ባለሙያዎች ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ የወደፊት ትምህርት በመፍጠር ረገድ ግዙፍ ጠቀሜታ ያላቸውን የማኅበረሰብን ፍላጎቶች፣ ምኞቶች እና ባሕላዊ ቅጦች መረዳት የሚያስችሏቸው የሕይወት ተመክሮዎች እና የሚያስቀጥሏቸው ማኅበረሰባዊ ግንኙነቶችም አሏቸው።

## የመምህራን ትምህርት

የመምህራን ትምህርት በትምህርት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ጋር ለማጣጣም እና በተሻለ መንገድ የወደ ፊት ተግዳሮቶች እና ተስፋዎችን ወዳገናዘበ አቅጣጫ ለመምራት እንደገና መታሰብ አለበት። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች፣ በተለይም ከሰሃራ በታች አፍሪካ፣ የመምህራን ደካማ ብቃት አስቸኳይ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ግድ ይላል። ይህ ለውጥ ለሁሉም የሚሠራ አንድ ዓይነት ሞዴል የለም። ከመምህራን ትምህርት ጋር የተገናኙ የተለያዩ ተዋናዮች - ለምሳሌ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ተመራማሪዎች፣ የመምህራን ማኅበራት፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ ወዘተ - ትብብር ለመማሪያ እና ለፈጠራ አዳዲስ ከባቢዎችን የመፍጠር ዕድሎችን ይሰጣል።

የመምህራን ትምህርት የዲጂታል ባሕል በዕውቀት አመራረት እና አሰረጫጨት ረገድ ያለውን ጠቀሜታ እና በሰው ሕይወት እና በፕላኔታችን ላይ እያመጣ ያለውን ለውጥ ችላ ብሎ ማለፍ አይችልም። ቴክኖሎጂን እንደ ሁሉን ፈዋሽ መድኃኒት ሳይቆጥሩ፣ ዲጂታል ሚዲያዎች እንደተቀናጀ እና የሩቅ ሙያዊ ልማትን ማሳኪያ መንገድ ብቻ ሳይሆን፣ ከሁሉም በላይ፣ በምርምር ርእስ ጉዳይነት መካተት አለባቸው። በተጨማሪም፣ በዲጂታል ሚዲያ እና መድረኮች ዕድሎች፣ ሥነ ትምህርታዊ አንድምታዎች፣ ሥነ ዕውቀታዊ እና ሥነ ምግባራዊ ዕድሎች፣ እንዲሁም ጉድለቶች እና ድክመቶቻቸው ላይ ምርምር ማድረግ ያስፈልጋል።

ውጤታማ የመምህራን ትምህርት ለመምህራን ከሥራ መልቀቅ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ጉዳዮችን መፍታት አለበት። ሙያውን መደገፍ በቂ ብቃት ያላቸውን እጩዎች ከመመልመል በላይ ይፈልጋል፤ የቡድኖች ትብብር በአስፈላጊው ዕውቀትና ክህሎት፣ ግብአት እና መሠረተ ልማት በመታገዝ ሙያዊ ስኬት እንዲያስገኝ የመምህራንን ሚና በአዲስ መልክ ማዋቀርን ይጠይቃል። ለምሳሌ፣ ወረርሽኙ በተከሰተበት ወቅት፣ በአብዛኛው ዓለም፣ የርቀት ትምህርትን በብቃት ለመደገፍ የሚያስችሉ በቂ የቴክኖሎጂ መድረኮች እና ሙያ ማሻሻያዎች ስላልነበሩ መምህራን ውጥረት እና መሰላቸት አጋጥሟቸዋል፤ አንዳንዶቹም በዚህ ምክንያት ሙያውን ትተውታል።

## ጀማሪ መምህራን

በየትኛውም ሙያ ውስጥ፣ ለአዳዲስ ትውልዶች ከሚደረግ አቀባበል እና አማኀብሮት የበለጠ አስፈላጊ ነገር የለም። የማስተዋወቂያ መርሐ ግብሮች ጀማሪ መምህራንን በወሳኝ የመጀመሪያ ዓመታት በትብብር የትምህርት ማቀድ መዋቅሮች እና የበለጠ ልምድ ባላቸው የሥራ ባልደረቦች በሚደረጉ ምክክራዊ መርሖቶች አማካይነት መደገፍ አለባቸው። ይህ በዝግጅት እና በሙያዊ ልምምድ መሀል ያለው የሽግግር ደረጃ በመምህርነት ሙያዊ ሕይወት ውስጥ በጣም ወሳኝ ቢሆንም፤ ብዙውን ጊዜ በፖሊሲ አውጭዎችም ሆነ በራ በሙያው ችላ ይባላል፤ በዚህም ምክንያት ከፍተኛው የመመናመን ምጣኔ ይታይበታል።

የመምህርነት ሙያ፣ ልክ እንደሌሎች፣ ከዕውቀት መሠረት ጋር የተያያዘ ነው። የማስተማር ሙያዊ ዕውቀት የመጀመሪያ መምህራን ዝግጅት ተቋማትን፣ ትምህርት ቤቶችን እና ልምድ ያካበቱ መምህራንን የሚያካትት ቅንጅትን እና አማኀብሮትን ይጠይቃል። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ትምህርት ውስጥ ያሉትን ተለዋዋጭ ሁኔታዎች፣ አውዶች፣ የመማሪያ አካባቢዎች እንዲሁም የተማሪዎችን ስብጥር ከግምት ውስጥ ካገባን ይህ ግንኙነት የበለጠ አስፈላጊ ይሆናል። አዳዲስ ፈተናዎች የመምህራን ትውልዶች ትብብር ያስፈልጋቸዋል። መምህራን እንደሚተማመኑ ባልደረቦች እርስበርስ ከሚደጋገፉበት ችሎታ በላይ የወደፊቶቹን ተግዳሮቶች ለመወጣት የሚረዳ ምንም ነገር የለም።

መምህራን ከተማሪዎች ጋር በተግባራዊ-ምርምር፣ በችግር መፍታት እና የፕሮጀክት ሥራ ላይ ሲሳተፉ ወይም አዳዲስ ቴክኒኮችን ሲሞክሩ የዕውቀት ፈጠራን ይመራሉ። እነዚህ ሂደቶች የትውውቅ መርሐ ግብሮች እና ጀማሪ መምህራንን ወደ ሙያው የማስረጽ እና ከትብብራዊው ከሥራ ባልደረቦች ማኅበረሰብ ጋር የማቀናጀት ተግባራት መሠረት ሊሆኑ ይገባል።

## ተከታታይ ሙያዊ ዕድገት

መምህራን የሙያዊ ዕድገት፣ የትምህርት፣ እና ከተለያዩ የብሄር፣ የባሕል እና የቋንቋ ልዩነት ካላቸው የሕዝብ ቡድኖች ጋር ለመሥራት፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማካተት እና በበቂ ሁኔታ ለመደገፍ እና ትምህርትን ግል ተኮር ለማድረግ የሚያስችሏቸው የድጋፍ ዕድሎች ያስፈልጓቸዋል። በታሪክ የተገለሉ እና የተነጠሉ ቡድኖች ተማሪዎች በበቂ ሁኔታ መደገፋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ይህ በተለይ የክፍል ውስጥ ስብጥር በአየር ንብረት ለውጥ፣ በማኅበራዊ እና በፖለቲካዊ ብጥብጥ እና በጦር መሣሪያ በታገዙ ግጭቶች ሳቢያ በሚደርሱ - በሚቀጥሉት ዓመታት ይባባሳሉ ተብሎ በሚጠበቁ - ስደቶች እና የአገር ውስጥ መፈናቀሎች ምክንያት በከፍተኛ ሁኔታ ሊለወጥ በሚችልባቸው ቀጣናዎች ዕውነት እየሆነ ነው።

ሙያዊ ዕድገት ከመምህራን ትምህርት እና ክትትል ከሚደረግበት የመስክ ልምምድ ጀምሮ፣ በማስተዋወቅ፣ ተመክሮ በማካፈል እና በሥራ ላይ መደበኛ የሙያ ማሻሻያ የሚቀጥለው ተከታታይ ሂደት አካል መሆን አለበት። ውጤታማ የሙያ ዕድገት በመምህራን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኮረ እና ከእነሱም ጋር የተቀናጀ፣ በቀላሉም ከሙያዊው ልምምድ ጋር ከሚቀናጅ ትርጉም ካለው ቀጣይ ሙያዊ ዕድገት ጋር መያያዝ አለበት።

ውጤታማ የሙያ ማጎልበቻ መርሃ ግብሮች ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች ምን መማር አለባቸው፣ መምህራንስ እንደዚህ ያለውን ትምህርት ለመደገፍ እና ዕድገታቸውን ለመገምገም ምን ማድረግ ይችላሉ የሚለው ላይ ያተኩራሉ። በጣም ውጤታማ የሆኑት መርሐ ግብሮች በአንጻራዊነት ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ፤ ቢያንስ በከፊል ትምህርት ቤት ላይ የተመሠረቱ እና ተመክሮን የተመረኮዙ፤ እንዲሁም የተማሩትን ተግባራዊ ለማድረግ እና ትምህርታዊ እና ፅንሰ ሐሳባዊ ዕውቀትን ለማዳበር ተደጋጋሚ ዕድሎችን የሚሰጡ ናቸው።

# ትምህርትን ለመቀየር ሕዝባዊ አጋርነት

መምህራን ለአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችሉ፣ የመምህራንን አመራረጥ፣ ዝግጅት እና የሙያ ዕድገት አቅጣጫዎች በሚቆጣጠሩ ፖሊሲዎች እና በራሱ በሙያው አደረጃጀት ውስጥ አስፈላጊ ለውጦች መደረግ አለባቸው። ትብብር መምህራንን እንደዋዛ ከባድ ኃላፊነት የሚያሸክም ብቻ መሆን የለበትም፤ ይልቁንም መምህራን ከተለያዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት በተለይም ከቤተሰቦች እና ከማኅበረሰቦች፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ከተለያዩ ማኅበራዊ ተቋማት ጋር አብረው እንዲሠሩ ድጋፍና የገንዘብ ምንጭ ሊያስገኝላቸው ይገባል።

## የመምህራን የሥራ ሁኔታዎች

ምንም እንኳን ጥራት ያለው ማስተማር የተማሪን ስኬት የሚወስን ብቸኛውና በጣም አስፈላጊው የትምህርት ቤት ውስጥ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን የሚያሳዩ ጥናቶች ቢኖሩም፤ መምህራን ብዙም ዕውቅና የማይሰጣቸው፣ ምስጋና የማይቸራቸው፣ ዝቅተኛ ተከፋይ እና በቂ ድጋፍ የማያገኙ እንደሆኑ ቀርተዋል። በመላው ዓለም፣ ያለ በቂ የመንግሥት ኢንቨስትመንት እና የመንግሥት ፍላጎት ከመምህራን የሙያ መዋቅር፣ አስተዳደሩ፣ ከመምህራን ተነሣሽነት እና ከሥራ እርካታ ጋር የተያያዙ ችግሮችን መፍታት አስቸጋሪ ሆኗል። በማያዛልቁ ወይም ብቁ ባልሆኑ መምህራን ላይ ከመጠን በላይ መተማመን ሙያውን እና ሕዝባዊ ትምህርትን ሊሸረሽር ይችላል።

ምቹ ያልሆነ የሥራ ሁኔታ እና ዝቅተኛ ክፍያ እጩ መምህራንን ሊያሸሽ ይችላል። እነዚህ ውጥረቶች እና ፍላጎቶች ሲተነተኑ ጉዳዩን የመምህራን የጾታ ሁኔታ የተጫነው መሆኑ ሊታይ ይገባል፤ ምክንያቱም በአንዳንድ አገሮች ለመምህራን ክፍያ መቀነስ ወይም ለደመወዝ ተመጣጣኝነት ክፍተቶች መስፋት የሴቶች መምህራን መብዛት ሰበብ ተደርጎ እየተወሰደ ነው። በገንዘብ ማካካሻ ብቻ ሳይሆን፤ የክፍል መጠኖችን በመቀነስ፣ የትምህርት ቤት ደህንነትን በማሻሻል፣ ሙያዊ ዕውቅና እና ሕጋዊነትን በማጠናከር፣ ተቋማዊ ድጋፍን በማሳደግ እና የትብብር ባሕሎችን በማጎልበት የመምህራንን ሥራ ሁኔታዎችን ማሻሻል ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ፣ የመምህራንን ሙያ እንደገና መነደፍ አለበት። ዕድገቱ በብቃት፣ በሙያ ማሻሻያ እና በትምህርት ቤት መርሐ ግብሮች ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፤ እንዲሁም ለጀማሪ መምህራን መርሑት፣ ከጋራ መምህራን ጋር አብሮ ማቀድ፣ የትምህርት መስኮችን ወይም ዑደቶችን መምራት፣ እንደ አስጠኚዎች ወይም አማካሪዎች ያሉ የድጋፍ አገልግሎቶችን ማደራጀት፣ የምርምርና ሙያ ማጎልበቻ ሳባቲካልን እና ሌሎችንም ማካተት አለበት። ጫናዎቹ እየበረቱ ባለበት ሁኔታ፣ መምህራን በቢሮክራሲያዊ እና ሥነ ትምህርታዊ ፍላጎቶች መካከል የተሻለ ሚዛናዊ ግንኙነት እንዲኖር፤ እንዲሁም ለምሳሌ፣ መምህራን በማኅበረሰባቸው ውስጥ በጥልቀት በሚሳተፉባቸው አውዶች በማስተማር ውስጥ ያለው የማይታይ ሥራ ከግምት ውስጥ እንዲገባ ይጠይቃሉ።

ቅድሚያ አዲስ ትምህርታዊ ጉዳዮች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመምህራንን የሥራ ሁኔታ፣ ደንቦች እና የሥራ ጫናዎች ጥልቅ እና ሥርዓት ጾታ ተኮር ክለሳ ያስፈልጋል። ከዚህም በላይ የመምህራንን ራስገዝነት በሚቀንሱ የፍላጎቶች እና ተጠያቂነት ቴክኖሎጂዎች አማካይነት አዳዲስ የቁጥጥር ዓይነቶች መምጣታቸውን መቀበል አስፈላጊ ነው። የሰፋፊ ፈተናዎች፣ የመምህራን ግምገማ፣ የት/ቤት ቁጥጥር፣ የማስተማር ደረጃዎች መጨመር፣ ብዙውን ጊዜ በቂ ድጋፍ እንኳን በሌለበት በመምህራን ላይ ከሚደርሱ ከባድ ጫናዎች ጥቂቶቹ ምሳሌዎች ናቸው።

አንዳንድ የትምህርት ሥርዓቶች የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂዎችን እንደ ውስጣዊ አስተዳደርን፣ ቅልጥፍናን እና ተጠያቂነትን ማጎልበቻ መንገድ አድርገው ተቀብለውታል። በትምህርት ሂደቶች ታዋቂነት እና ታይነት ረገድ የተገኙ ውጤቶች ቢኖሩም፤ የማሽን መማርያ ቴክኖሎጂዎች ዕድገት የትምህርት ሂደቶችን ወደ “ውሂብ ስብስቦችነት” የመበጣጠስ እና ወደ አመራር-ተኮርነት፣ ክትትል እና መምህራንን ሙያ ወደ ማሳጣት አዝማሚያዎች መጣደፍን ያፋጥናል። በተለይም ለፖለቲካዊ ክትትል ሊጠቀሙበት በሚችሉ አገሮች ተማሪዎችን እና መምህራንን ለመከታተል የፊት ለይቶ ማወቂያ ሶፍትዌሮችን እና

አይሰው ሠራሽ አስተውሎትን መጠቀም፣ የትምህርት ግብ መሠረታዊ ነጻነቶች እና ሰብአዊ መብቶች ማራመድ እንደሆነ ከሚደነግገው የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 26 ጋር ይቃረናል።

የመምህራን ሥራ ትልቅ ኃላፊነትን ከማካተቱም በተጨማሪ፣ ለሕብረተሰብ እና ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ለወደፊቱ ተጠያቂነት አለባቸው። ለዚህም፣ ግልጽነት እና እምነት በተሞላበት አካባቢ ውስጥ ለመሥራት ደህንነት ሊሰማቸው እና አዳዲስ የአስተሳሰብ መንገዶችን እና የዓለምን ወገንነት ለማበረታታት ነጻነት ሊሰማቸው ይገባል፤ ይህ ግን ከመደገፍ ይልቅ፣ በሚያዳክመው ከልክ ያለፈ አመራር-ተኮርነት እና ኮርፖሬቲዝም ላይ ተመሥርተው ከመጡት አንዳንድ የቅርብ ጊዜ የተጠያቂነት ዓይነቶች ጋር ይቃረናል።

# ዩኒቨርስቲዎች ከመምህራን ጋር ያላቸው ቀጣይነት ያለው ግንኙነት

በከፍተኛ ትምህርት እና በመምህርነት ሙያ መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለ፤ አዳዲስ ተቋማዊ አወቃቀሮችም ይህንን ግንኙነት ማሳየት አለባቸው። የወደፊቱን በጋራ የማጤን ሐሳብ በትምህርት ቤቶች፣ በመምህራን እና በዩኒቨርስቲዎች መካከል በመነሻው የመምህራን ትምህርት እና ቀጣይነት ባለው ሙያዊ ዕድገት ውስጥ ለሚታይ ትብብር እና ሕብረት ወደሚኖር ቁርጠኝነት መተርጎም አለበት። ከፍተኛ ትምህርት የቀጣይ ትውልድ መምህራንን አስተሳሰብ እና ሥነ ትምህርቶችን መፈተሽ እና መቅረጽ የሚችል ነው። ስለዚህም፣ መምህራን ዩኒቨርስቲዎች ራሳቸውን እንዲለውጡ፣ ሕዝባዊ ተልእኳቸውን እንዲያድሱ እና በሰፊ የትምህርት ሥነ ምህዳር ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ ማገዝ ይችላሉ።

ከአጠቃላይ ትሥሥሮቻቸው መካከል፣ ዩኒቨርስቲዎች ለመምህራን ትምህርት ያላቸው ተጨባጭ ቁርጠኝነት ከፍ ሊል ይገባዋል። ከታሪክ አኳያ ይህ በአንደኛ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በዩኒቨርስቲዎች መካከል ከነበሩ ዋነኛ ትሥሥሮች አንዱ ነው። ሆኖም፣ በአብዛኛዎቹ ቦታዎች፣ በመምህራን ትምህርት መርሐ ግብሮች እና ስትራቴጂዎች ላይ መሠረታዊ ለውጦች ያስፈልጋሉ።

ከእነዚህ ቁርጠኝነቶች መሀል በጣም ወሳኙ፣ በተለይም የመምህራን የመነሻ ዝግጅት ላይ፣ የመምህራን ትምህርት መርሐ ግብሮች ሲገነቡ እና ሲተገበሩ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ አቀራረብ ማስፈለጉ ነው። ዩኒቨርስቲዎችም ሆኑ ትምህርት ቤቶች የመምህራንን የመነሻ ዝግጅት በራሳቸው ማድረግ አይችሉም። አንዳንድ መርሐ ግብሮች የመንግሥት ባለሥልጣናትን፣ የመምህራን ማኅበራትን እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ኢኒሼቲቮችን ጨምሮ በርካታ የትምህርት ተዋናዮች፣ ትርጉም ላለው የትብብር ሥራ የሚሰባሰቡባቸውን አዳዲስ ሥፍራዎችን እና ሁኔታዎችን በመገንባት ላይ በማተኮር ይህንን ክፍተት ያጠብባሉ። ሌሎች መርሐ ግብሮች ምርምር ተኮር የትምህርት እና የተግባር አካሄድን በመያዝ በት/ቤቶች ውስጥ በጥልቀት ሥር ሰደዋል። እነዚህም በትምህርት ፋክልቲዎች ብቻ ሳይገደቡ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ዩኒቨርስቲዎች ካነሳሱት እና ከሚያዳብሩት የጋራ ዕውቀት ጋር ሊያገናኙት ይችላሉ። በብዙ ቦታዎች ያሉ ዩኒቨርስቲዎች “የሳይንስና ኢንዱስትሪ ፓርኮች” እንደጀመሩ ሁሉ፣ በተመሳሳይ፣ የጋራ ትምህርትን ለመንደፍ እና ለመምህራን ዝግጅት ሥራ ሁሉንም ዓይነት ባለድርሻዎች የሚያገናኙ ትምህርት ላይ ያተኮሩ ቦታዎች ያስፈልጉናል።

*ዩኒቨርስቲዎችም ሆኑ ትምህርት ቤቶች የመምህራንን የመነሻ ዝግጅት በራሳቸው ማድረግ አይችሉም።*

ሌላው ተዛማጅ ቁርጠኝነት የመምህራን ሙያዊ የትውውቅ መርሐ ግብሮችን ማጠናከርን ያካትታል። ከእነዚህ ውስጥ ምርጡ ለባልደረባ ምክክር ቅድሚያ የሚሰጡት እና በሙያዊ ዕድገት እና በሙያዊ ልምምድ መካከል በቂ ሽግግርን በማመቻቸት የወጣት መምህራንን አማኀብሮት ያረጋግጣሉ፤ ይህ ሁሉ በዩኒቨርስቲዎች እና በመምህራን ኮሌጆች መሀል ጠንካራ ትብብር ይጠይቃል። በመምህራን እና በዩኒቨርስቲዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ቀጣይ ማድረግ ለት/ቤቶች እና ለትምህርታዊ ለውጥ ሂደቶች መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። መርሐ ግብሮች እና ፋክልቲዎች ከመምህራን ጋር በሙያው ውስጥ

እስካሉ ድረስ መቀራረብ አለባቸው፤ ይህም መምህራን ከሥራዎቻቸው የሚያገኟቸውን ዕውቀቶች ወደ ኮሌጆቻቸው እና ዩኒቨርስቲዎቻቸው የሚመልሱበትን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነትን ያበረታታል።

በመጨረሻም፣ የከፍተኛ ትምህርት የማስተማር ሥነ ትምህርታዊ ዕድገትም ለውጥ ያስፈልገዋል። የዩኒቨርስቲ እና የኮሌጅ መምህራን እና ፕሮፌሰሮች በትብብራዊ ዕቅድ፣ በማስተማር እና የተማሪዎችን መማር በመደገፍ ረገድ ቁርጠኛ ከመሆን ብዙ ያተርፋሉ። የአጋርነት እና የትብብር ሥነ ትምህርቶች በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ ያላቸው ወሳኝነት ከሕፃናት እና ታዳጊዎች ያነሰ አይደለም - እንዲያውም፣ ዩኒቨርስቲዎች ለማምረት በሚያልሟቸው አዳዲስ ባለሙያዎች፣ መሪዎች እና ተመራማሪዎች ዘንድ ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው።

## መምህራን በትምህርት ውሳኔ አሰጣጥ እና በሕዝባዊ ዐውድ ውስጥ

በአሁኑ ጊዜ ትምህርታዊ ጉዳዮች ለውይይት እና ለክርክር የሚቀርቡበት ሕዝባዊ አውድ አስፈላጊነት የሚካድ አይደለም። የመወያየት ወይም የመመካከር ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ወላጆች፣ ማኅበረሰቦች፣ የመንግሥት እና የግል ድርጅቶች፣ ማኅበራት እና የወጣቶች ንቅናቄዎች፣ እንዲሁም መምህራን እና ድርጅቶቻቸው የሚሳተፉባቸውን የውሳኔ አሰጣጥ ዘዴዎችን የመገንባት ጉዳይ ነው።

የመምህርነት ሙያ በሙያዊ ሥፍራው ቦታ ውስጥ አያልቅም፤ ሙያው በሕዝባዊ ቦታ፣ በማኅበራዊ ሕይወት እና በጋራ ጥቅም ግንባታ ውስጥ ይቀጥላል። ከዚህ አንጻር፣ በተለይ መምህራን በመንግሥት ፖሊሲዎች ብያኔ ላይ መሳተፋቸው በጣም አስፈላጊ ነው። በበርካታ አውዶች ግን ይህ አይሠራም፤ መምህራን የውሳኔ ሰጪነት አቅም በመነፈጋቸው ቦታ አያገኙም፤ በትምህርት ፖሊሲዎች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች እና ክርክሮች እንዲሳተፉ አይጋበዙም።

መምህር መሆን ማለት በሙያው ውስጥ ቦታ ማግኘት እና በዋና ዋና የትምህርት ጉዳዮች እና በመንግሥታዊ ፖሊሲዎች ግንባታ ላይ በይፋ ቦታ መያዝ ማለት ነው። ይህ ተሳትፎ ዋነኛ ዓላማው ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ሳይሆን፤ ድምፃቸውን እና ዕውቀታቸውን ወደ ሰፊ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ዐውድ ለማሻገር ነው።

የወደፊቱን ጊዜ አሻግረን ስንመለከት፣ የመምህራን ሥራ በክፍል ውስጥ ብቻ ሳይገደብ፤ ወደ ጠቅላላው የትምህርት ቤት አደረጃጀት እና ተግባር መዘርጋት እንዳለበት ማመላከት ተገቢ ነው። ትምህርት ቤቶች መምህራን በሁሉም ተማሪዎች መማር ላይ ያተኮረ ርዕይን የሚቀርጹባቸው እና የሚጋሩባቸው፤ እንዲሁም ለሁሉም ሠራተኞች ቀጣይነት ያለው የመማር ዕድሎች ያሉባቸው የመማሪያ ድርጅቶች እንዲሆኑ ለማስቻል ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። መምህራን በምርምር፣ በፈጠራ እና በአሰሳ ባሕል ውስጥ ለሚደረጉ የመተባበር እና በጋራ የመማር ጥረቶች ፈር ቀዳጅ ሊሆኑ፤ እንዲሁም መማርን ለማደራጀት እና ለመጋራት የተቀናጁ ሥርዓቶችን ሊያሳድጉ ይችላሉ።

# የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች

ይህ ምዕራፍ በአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ውስጥ ማስተማር መምህራን በሥራቸው እንደ ዕውቀት አመንጪዎች እና በትምህርት እና በማኅበራዊ ለውጥ ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ባለሙያዎች ዕውቅና እንደሚያገኙበት የትብብር ጥረት ሙያውን ጠብቆ እንዲሰፋ ምክረ ሐሳብ አቅርቧል። ወደ 2050 ስናማትር፣ ይህንን ምክረ ሐሳብ ወደፊት ለማራመድ የሚያስፈልገውን ውይይት እና ድርጊት ለመምራት የሚረዱ አራት መርሆች አሉ፦

- **ትብብር እና የቡድን ሥራ የመምህራን ሥራ መለያ መሆን አለበት።** መምህራን እንደ የትምህርት አካባቢዎች፣ ግንኙነቶች፣ ቦታዎች እና ጊዜያት ዋና ሰብሳቢዎች ሆነው በጋራ እንዲሠሩ መደገፍ አለብን። ጥራት ያለው ማስተማር የሚዘጋጀው በቡድን እና የተማሪዎች አካላዊ፣ ማኅበራዊ እና ስሜታዊ ፍላጎቶች መሟላታቸውን በሚያረጋግጡ አካባቢዎች ነው።
- **ዕውቀትን፣ ጽብረቃን እና ምርምርን ማፍራት ለማስተማር ወሳኝ መሆን አለበት።** መምህራን አዳዲስ የምርምር እና የፈጠራ መስኮችን እንደሚለዩ፣ የምርምር ጥያቄዎችን እንደሚበይኑ እና አዳዲስ ሥነ ትምህርታዊ ልምምዶችን እንደሚያመነጩ አእምሯዊ ተሳትፎ ያላቸው ተማሪዎች መደገፍ እና መታወቅ አለባቸው።
- **የመምህራን ራስገዝነት እና ነጻነት መደገፍ አለበት።** የመምህራን ጠንካራ ሙያዊ ማንነት ሊበረታታ ይገባል። ይህም መምህራን የተማሪን ትምህርት በመንደፍ እና በመምራት ረገድ ያላቸውን ውሳኔ እና ዕውቀታቸውን በብቃት መጠቀም መቻላቸውን የሚያረጋግጥ አግባብ ያለው ትውውቅ እና ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ማሻሻያን ያካትታል።
- **መምህራን ስለትምህርት የወደፊት ዕጣ ፈንታ በሚደረግ ሕዝባዊ ክርክር እና ውይይት ላይ መሳተፍ አለባቸው።** ትምህርትን እንደገና በጋራ ለመቅረጽ በማኅበራዊ ውይይቶች እና አሳታፊ የውሳኔ አሰጣጥ ዘዴዎች ውስጥ መምህራን መኖራቸውን ማረጋገጥ አለብን።

አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ስንቀርጽ፣ ከመምህራን የለውጥ ሥራ ጋር የተያያዙትን እነዚህን አራት የመመሪያ መርሆች ከግንዛቤ ማስገባት አለብን። ስለ ማስተማር እና ስለ መምህራን የሚደረግ የጋራ ውይይት የትምህርት መታደስ መሠረታዊ አላባ ነው።

# ምዕራፍ 6

# ትምህርት ቤቶችን መጠበቅ እና መለወጥ

*ቤት ማን እና ምን መሆን እንዳለብኝ ሌላ ሰው ከቀረጸው ምስል ጋር እንድስማማ የተገደድኩበት ቦታ ነበር። ትምህርት ቤት ያንን ማንነት ረስቼ እና በሐሳቦች ራሴን እንደገና መፍጠር የምችልበት ቦታ ነበር ... የመማሪያው ክፍል፣ ከነውስንነቶቹ፣ የአማራጮች ቦታ ሆኖም ይቆያል። በዚያ የአማራጮች መስክ፣ ለነጻነት ሲባል ለመድከም፣ ስለራሳችንንና ስለጓዶቻችን ለመጠየቅ፣ በክፍት አእምሮና ልብ የዕውቀት ድንበሮችን ዐልፈን ለማሰብ እንችል ዘንድ እውነታን ለመጋፈጥ የሚያበቃን ዕድል አለን።*

ቤል ሁክስ፣ *Teaching to transgress: Education as the practice of freedom,* 1994.

**ትምህርት ቤቶች አካታችነትን፣ ፍትሐዊነት እና የግል እና የጋራ ደህንነትን ስለሚደግፉ ጥብቅ የትምህርት ቦታዎች መሆን አለባቸው - እንዲሁም ዓለም ወደ ፍትሐዊ፣ ተመጣጣኝ እና ዘላቂ ወደፊቶች የምታደርገውን ለውጥ በተሻለ ሁኔታ ማበረታታት እንዲችሉ ተደርገው ዳግም መቀረጽ አለባቸው።**

የትብብር እና የአጋርነት ሥነ ትምህርቶችን ለማስቻል እና ከጋራ ዕውቀት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር፣ እነዚህን ግቦች ለማሳካት የተመደቡ ጊዜዎች እና ቦታዎች መኖር በጣም ወሳኝ ነው። ትምህርት ቤቶች፣ በሙሉ አቅማቸው እና ተስፋዎቻቸው፣ ከነጉድለቶች እና ውሱንነቶቻቸው፣ አሁንም በጣም አስፈላጊ ከሆኑ የትምህርት አውዶች መሀል ናቸው። ትምህርት ቤቶች ሕብረተሰብ ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ ሰብአዊ እንቅስቃሴ በመቁጠር ለትምህርት ያለውን ቁርጠኝነት ይወክላሉ። ነገር ግን፣ ትምህርት ቤቶች የተነደፉበት መንገድ ገለልተኛ ስላልሆነ፤ ስለ መማር፣ ስለስኬት፣ ስለውጤታማነት እና ግንኙነት የተያዙ ግምቶችን ያንጸባርቃሉ።

በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተገነቡት አካባቢያዊ እና የጊዜ ደንቦች ምን እንደሚቻል፣ ምን እንደሚከለከል፣ እነማን እንደተፈቀደላቸው እና እነማን እንደተገለሉ ጥርት አድርገው ያሳያሉ። መምህራን፣ የትምህርታዊ መስተጋብሮች ዋና አስተባባሪዎች እንደመሆናቸው መጠን፣ በእነዚህ ድርጅታዊ ቢጋሮች እና በሚያስችሏቸው የተራክቦ እና የመማር ዓይነቶች ላይ በመሥራት ብዙ ጊዜ ማሳለፍ አለባቸው። የትምህርት ቤት ከባቢ ለትብብር፣ ለምርምር እና ለሙከረት ምቹ ይሆናል? ከባድ ፈራጅ ይሆናል ወይስ በሙከራ እና በስሕተት እየተማሩ ማውጠንጠንን ያበረታታል? በክፍል ደረጃ ወይም በዕድሜ አቻነት ብቻ ሳይሆን፣ በሁሉም ዕድሜዎች እና የሕይወት ደረጃዎች ውስጥ የተለያዩ መስተጋብሮችም ያመቻቻል? ከእነዚህ መስተጋብሮችስ ምን ዓይነት መካሪዎች፣ ጓደኝነቶች እና አስተሳሰቦች ይገነባሉ? የትምህርት ቤት ከባቢ ከምንም ነገር በላይ በግለሰብ ስኬት ላይ ያተኩራል ወይንስ የግለሰብ እና የአቻ ዕድገትን እንደ እርስበርስ መደጋገፍ ይቆጥራል?

ይህ ምዕራፍ የሚጀምረው ትምህርት ቤቶች በሁሉም ባሕልና ወግ ውስጥ ወሳኝ ሚና ያላቸው ወሳኝ ማኅበራዊ ተቋማት ሆነው መፈጠራቸውን በአጭሩ በመዳሰስ ነው። የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ጊዜዎችን እና ቦታዎችን የሚወክሉ ብቻ ሳይሆኑ፤ ብዙዎቹ የግለሰቦችን፣ የቤተሰቦችን እና የማኅበረሰቦችን ደህንነትን የሚደግፉ የተለያዩ ማኅበራዊ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በአንድነት በማቅረባቸው ራሳቸው የሕብረተሰብ ማዕከላት ሆነዋል። ቢሆንም ትምህርት ቤቶች የስኬት ውሱንነት አለባቸው፤ ይህም በከፊል ከመማሪያ ቦታ እና ጊዜ አወቃቀሮች ጠባብነት የመጣ ነው። በመቀጠልም፣ ምዕራፉ ሊኖሩ ስለሚችሉ ለውጦች ያብራራል። የመማርን መጠነ ርእይ ከመማሪያ ክፍል በላይ ማስፋፋት፤ ጥልቅ ተሳትፎን ለማመቻቸት የመማሪያ ጊዜዎችን እና አወቃቀሮችን እንደገና ማጤን፤ እንዲሁም በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚፈጠረውን ነገር ለመደገፍ የዲጂታል ቴክኖሎጂን አቅም ማውጠንጠን አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል በትምህርት ቤት የለውጥ ሂደት ሲተገበር ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች ናቸው።

ትምህርት ከቀውሶች፣ እና ከአይታወቄ እና ከአይገመቴዎች ጋር መላመድ የሚችሉ የጋራ የወደፊት ጊዜዎችን ለመገንባት እንዲረዳን ከተፈለገ፣ ጠንካራ ትምህርት ቤቶች ወሳኝነት አላቸው።

ምዕራፉ ለተማሪዎች፣ ለትምህርት ባለሙያዎች እና ለመምህራን፣ ለመንግሥት እና ለሲቪል ማኅበረሰብ አጋሮች ጠቃሚ በሆኑ የ2050 የውይይት እና የተግባር መምሪያ መርሆች ይጠናቀቃል፤ መርሆቹም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦ ትምህርት ቤቶችን እንደ የትብብር ሥፍራ መጠበቅ እና እንደገና መንደፍ፤ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በአዎንታዊ መልኩ መጠቀም፤ እና የዘላቂነት እና የሰብአዊ መብቶች ተምሳሌት መሆን።

# የትምህርት ቤቶች የማይተካ ሚና

ትምህርት ቤት ባይኖር ኖሮ፣ ልንፈለስፈው እንገደድ ነበር። ትምህርት ቤቶች የትላልቅ የትምህርት ሥነ ምህዳሮች ማዕከላዊ አካል ናቸው። ሕያውነታቸው ሕብረተሰብ አንድ የጋራ ጥቅም ለሆነው ትምህርት ያሳየው ቁርጠኝነት መግለጫ ነው። ትምህርት ቤቶች ሕፃናት እና ወጣቶች በጋራ ዕውቀት ውስጥ እንዲሳተፉ ልዩ ከባቢዎችን ይሰጧቸዋል። ሥጋቶችን የሚደፍሩባቸው፣ ፈተናዎችን የሚጋፈጡባቸው እና ዕድሎችን የሚሞክሩባቸው ቦታዎች ናቸው። ት/ቤቶች የጋራ የወደፊት ሕይወታችንን ዘላቂ የሚያደርጉ ተመክሮዎች፣ ችሎታዎች፣ ዕውቀቶች፣ ሥነ ምግባር እና እሴቶች ሁሉም ሰው ማግኘቱን ያረጋግጣሉ። ወደ 2050 ስናማትር፣ ት/ቤቶች በይነ-ትውልዳዊ፣ በይነ-ባሕላዊ እና በብዝኃዊ መስተጋብሮች አማካይነት የመተሳሰብ እና የመደጋገፍ ሥነ ምግባርን ማበልጸግ አለባቸው።

*ትምህርት ቤት ባይኖር ኖሮ፣ ልንፈለስፈው እንገደድ ነበር።*

መሠረታዊ ትምህርታዊ ሥራ በብዙ ጊዜያት እና ቦታዎች ይከናወናል፤ የሕዝብ የትምህርት ጊዜ እና ቦታ ግን ልዩ ናቸው። የትምህርት ቤት ሥፍራ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ያበረታታል። ትምህርት እና መማር ሰዋዊ ተራክቦዎችን፣ ውይይት እና ልውውጥ ያነሣሳል፤ ስለዚህ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ለማሳደግ በዓላማ መገንባት አለባቸው። ትምህርት ቤቶች በተለያየ ዕድሜ እና የሕይወት ደረጃ ያሉ ሰዎችን በአንድነት የሚያሰባስቡ፣ እርስበርስ እንዲማማሩ እና ከሌሎች ጋር እንዲማሩ የሚያደርጉ የጋራ ኑሮ ዓይነቶች ናቸው። የርቀት ትምህርት አቅርቦቶች የትምህርት ቤቶችን ሥራ ሊደግፉ ቢችሉም፤ ተዛምዷዊ ጠባያቸውን ግን ሙሉ በሙሉ መተካት አይችሉም።

እንደ ኮቪድ-19 ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ እና የምዕራብ አፍሪካው የኢቦላ አገር አቀፍ ወረርሽኝ፣ ደም አፋሳሽ ግጭቶች፣ እና የአየር ንብረት ድንገተኛ አደጋዎች ያሉ አስተጓጓዮች እየጨመሩ መምጣት፣ የትምህርት ቤቶችን ልዩ ሚና ይበልጥ አጉልተው አሳይተዋል። እነዚህ አጋጣሚዎች ትምህርት ቤቶች በመማርያነት ብቻ ሳይሆን፣ በማኅበራዊ ደህንነት ማዕከሎችነት ጭምር ያላቸውን ጠቀሜታ አስታውሰውናል። ትምህርት ቤቶች በጣም ድሃ እና በጣም ተጋላጭ ለሆኑት ጥበቃ ለማድረግ እና ዕድል ለመስጠት ታስቦ ከተዘጋጁ ጥቂት ተቋማት ውስጥ አንዱ ነው። ትምህርት ቤቶች እንደ የማኅበረሰብ ሕይወት ማዕከልነታቸው፣ ራስን ለመቻል እና በአካባቢ ማኅበረሰቦች ውስጥ እና ከተፈጥሯዊው ዓለም ጋር ዘላቂ ግንኙነቶችን ለማዳበር ጠንካራ ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ በ2020 እና 2021 ድንገተኛ እና ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ሰፊ የትምህርት ቤት መዘጋት ሲያጋጥም፣ በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናት እና ታዳጊዎች ከትምህርት ቤቶቻቸው፣ ከክፍል ጓደኞቻቸው እና ከመምህሮቻቸው እንዳይገናኙ ተገደዋል። ይህም በተከታታይ በአካል ሳይማሩ መቅረት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናት እና ታዳጊዎች በማኅበራዊ፣ ዕውቀታዊ እና አእምሯዊ ደህንነት ላይ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የሚሰማቸውን ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል።

የተማሪዎቻቸው ዕድሜ ምንም ያህል ይሁን፣ ትምህርት ቤቶች የማወቅ ጉጉትን እና ፍላጎትን ማዳበር አለባቸው። ተማሪዎች በቤት ውስጥ ወይም በአቅራቢያቸው ባሉ ማኅበረሰቦች ውስጥ ዕለት ከዕለት ለማያጋጥሟቸው ሐሳቦች እና ተመክሮዎች መጋለጥ አለባቸው። የታሰበባቸው ሥነ ትምህርታዊ አጋጣሚዎች ትምህርት ቤቶችን የማይተኩ ያደርጓቸዋል። ከሌሎች የትምህርት ሥፍራዎች መካከል፣ ልዩዎቹ የሆኑት ትምህርት ቤቶች የመማር እና የማስተማር ቦታዎች ናቸው። የሰው ልጆች ይማራሉ፤ ደግሞም የማስተማር እና የመማር ችሎታ አላቸው። ይህ ውብ አሠራር በቦታ እና በጊዜ፣ በትውልዶች እና በዕውቀት መንገዶች ሳይገደብ ከጋራ ዕውቀት ጋር እና እርስበርስ ያገናኘናል። መምህራን የሌሏቸው ትምህርት ቤቶች የሉም። መምህራን ዕውቀትን ለሁሉም ተደራሽ የማድረግ፣ የጋራ ዓላማዎችን እና አቅሞችን የመገንባት እና አርነት የሚያወጡ ምሑራዊ ኀሣሳዎችን በማበረታታት የሥነ ትምህርት ተልእኮዎችን ያዳብራሉ። እንደዚሁም፣ መምህራን ሥራቸውን ለማጠናከር እና ለመደገፍ በትምህርት ቤት ሥፍራ እና ጊዜያት ጤናማ አሠራር ላይ ይመሠረታሉ።

## የጋራ ታሪካዊ ግዴታዎች

የዕውቀት ልምምዶቻቸውን በምልከታ፣ በኩረጃ ወይም በተረት ነገራ ሊማሯቸው የማይችሏቸው የውስብስብነት ደረጃ በደረሱ በአብዛኛዎቹ ባሕሎች ውስጥ ዕውቀትን፣ ክህሎትን፣ እሴቶችን እና መረዳትን ለማዳበር የተሰጡ ሥፍራዎች እና ጊዜያት አሉ። በብዙ አጋጣሚዎች ጥንታዊው ትምህርት ቤት የተጀመረው ከጽሑፍ ዕድገት ጋር ነው። የሚገርመው የእንግሊዝኛው ቃል “ስኩል” የመጣው ከግሪኩ “ስኮሌ” ሲሆን፤ ትርጉሙም ነጻ ወይም የመዝናኛ ጊዜ ነው። ደግሞም ምንም እንኳን የግሪኩ ተቋም ለአውሮፓ የትምህርት ዕድገት ዋነኛ ተምሳሌት ቢሆንም፤ ብዙ ባሕሎች የትምህርት ተቋማትን አዳብረዋል፤ ከእነዚህም ውስጥ የሺቫ፣ መድራሳ እና ካልሜካክ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። ትምህርት ቤቶች ባለፉት ሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ እያደጉ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲሰራጩ፣ ትውልዶች በዓለም ውስጥ እንዴት እንደሚኖሩ፣ ዓለማትን እንዴት እንደሚሠሩ እና እነሱንም እንዴት እንደሚንከባከቧቸው የሚነጋገሩባቸውን በይነ-ትውልዳዊ ውይይቶች የሚያደራጅ፣ የማዕከላዊ የሕዝብ መሠረተ ልማት አውታርነትን ሚና ወስደዋል። ትምህርት ቤቶች ባሕላዊ ቅርሶችን ለመተዋወቅ፣ እንደገና ለመፍጠር እና ለማስፋፋት ያስችሉናል።

ትምህርት ቤቶች ሆን ተብሎ ከጋራ ዕውቀት ጋር መገናኘትን ለማደራጀት ቁልፍ ከሆኑ ሥፍራ እና ጊዜዎች አንዱ ሆነዋል። ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ከበለጸጉ የማመዛዘን፣ የጥናት፣ የምርምር እና የመጠየቅ ባሕሎች በማስተዋወቅ ሥነ ዕውቀታዊ ልምምዶችን የማዳበር ኃይል ነበራቸው። የትምህርት ቤት ተግባራት እና ልምምዶች አንዳንድ ደንቦችን እና ከዕውቀት ጋር ያለን ግንኙነት ለማስተዋወቅ ያገለግላሉ። በታሪክ ቅቡልነት ያላቸው ናቸው የተባሉ ዕውነቶችን (የእምነት ሥርዓቱ ዕውነት ነው በሚል እርግጠኝነት) ለማስተላለፍ የበለጠ አጽንኦት ተሰጥቶ ቆይቷል። ነገር ግን፣ ባለፉት በርካታ ዐሥርት ዓመታት ውስጥ የተደረጉት ወሳኝ ለውጦች በብዙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙትን ቀጥተኛ ትምህርት ከላይ ወደታች የመስጠት ዘዴዎች ተቃውመዋል። ይበልጥ አሳታፊ በሆኑ የትምህርት ቤት ልምምዶች እና የትምህርት ቤት ባሕሎች፣ ስለቅቡል ዕውነቶችን ተቀበሉ አካሄዶች አፈጣጠር እና መዘዞቻቸው ግንዛቤን ለማሳደግ ጥረት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል። በአሁኑ ወቅት ለሚያጋጥሙን አጣብቂኞች እና ተግዳሮቶች በት/ቤቶች ውስጥ ልዩ ልዩ ዕውቀታዊ ልምምዶች እንዲዳብሩ በማድረግ እና በሥነ ዕውቀቶች እና በዕውቀት ሥነ ምህዳሮች መካከል ገንቢ የሆነ ሰፊ ትስስር በመፍጠር ውጤታማ መፍትሄ ማግኘት ይቻላል።

በዚህ ከዕውቀት ማስተላለፊያ ሥፍራነት የላቀ ተሳትፎ እና አሰሳ ወደሚደረግባቸው ሥፍራዎችነት ት/ቤቶች በሚያደርጉት ሽግግር ሁሉ፣ በትምህርት ቤት መማር አስፈላጊ እንደሆነ ይቆያል። ነገር ግን፣ ግትርነትን አስወግዶ ለዓለም ተግዳሮቶች ምላሽ መስጠት፣ የሰውን ተመክሮ ከማደኸየት ይልቅ ማበልጸግን ያለሙ፣ ምን ዓይነት የዕውቀት መንገዶች በመማማሪያ ጊዜያት እና ሥፍራዎች ሊተከሉ እንደሚችሉ መረዳትን ይጠይቃል። የበይነ ትውልዶች ትምህርትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለማሳለጥ የሚያስችሉ የትምህርት ቤት ሥፍራዎች እና ጊዜዎችን ለመፍጠር ብዙ ተጨማሪ ሥራዎች ይቀራሉ።

# የትምህርት ቤቶች አስፈላጊ ለውጥ

ትምህርት ቤቶች ሁሉም ሰዎች የመለወጥ፣ የመቀየር፣ እና የደህንነት ምኞታቸውን የሚቀርጹባቸው እና ዕውን የሚያደርጉባቸው ቦታዎች መሆን አለባቸው። ከሁሉም በላይ፣ ትምህርት ቤቶች በተናጥልም ሆነ በጋራ፣ ያልተጠበቁ ዕድሎችን ዕውን ማድረግ ሊያስችሉን ይገባል። በብዙ የዓለም ክፍሎች፣ የትምህርት ቤት ተደራሽነት መጨመር፣ ንቃተ ህሊናን የሚያሳድጉባቸውን፣ አዳዲስ ክህሎቶችን እና ግንዛቤዎችን የሚያዳብሩባቸውን እና አዳዲስ የመማር እና የማደግ አቅጣጫዎችን አሻግረው የሚያዩባቸውን ለዋጭ ዕድሎችን ለግለሰቦች እና ለመላው ማኅበረሰቦች ሰጥቷል። ብዙ ጊዜ ግን፣ የዛሬዎቹ ት/ቤቶች ሊተዉ የሚገቡ አለመመጣጠኖችን ለመትከል እና ልዩነቶችን ለማስፋት ያገለግላሉ።

ጥልቅ ለውጥ ለማምጣት የወደፊቱ ትምህርት ቤት ማደራጃ መርሆዎች አካታችነትን እና ትብብርን ያማከሉ መሆን አለባቸው። ልህቀት፣ ስኬት፣ ጥራት፣ ልኬት እና ዕድገት ከአግላይ ይልቅ በአካታቾቹ መንገዶች ተቃንተው ሊጣጣሙ የሚችሉ ጠቃሚ ግዴታዎች ናቸው።

እነዚህ አዳዲስ የትምህርት ቤቶች ከባቢዎች አንዳንድ ተማሪዎች ከኢንተርኔት ጋር ተገናኝተውም ይሁን ሳይገናኙ ብቻቸውን እንደሚያጠኑበት፣ ሌሎች ደግሞ ሥራቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እና መምህራን እንደሚያቀርቡበት ትልቅ ቤተ መጻሕፍት ማሰብ እንችላለን። ሌሎች ደግሞ ከቤተ መጽሐፍት ውጭ፣ ምናልባትም ሩቅ ቦታዎች ሆነው፣ ከትምህርት ቤት ውጭ ካሉ ሰዎች እና ከዓለማት ጋር ይገናኛሉ። ቤተ መጻሕፍቱ የሁኔታዎችን እና የመቼቶችን ሰፊ ስብጥር ይደግፋል። ከተለመደው የትምህርት ቤት እና የመማርያ ክፍል መዋቅር የተለየ አዲስ አካባቢም ነው። ይህ ቤተ መጻሕፍት በምሳሌያዊነቱም እና በጥሬውም ሊወሰድ ይችላል። የትምህርት ጊዜያት እና ቦታዎች ተማሪዎችን ከጋራ ዕውቀት ጋር እንደሚያገናኙ በሮች ማገልገል እንዳለባቸው ያስታውሰናል።

*ትምህርት ቤቶች በተናጥልም ሆነ በጋራ፣ ያልተጠበቁ ዕድሎችን ዕውን ማድረግ ሊያስችሉን ይገባል።*

## ትምህርት ቤቶች በትብብር፣ በመተሳሰብ እና በለውጥ መድረኮችነት

ት/ቤቶች አካታች እና ትብብራዊ የመማሪያ አካባቢዎች ሲሆኑ፣ ተማሪዎችን ከነልዩነታቸው እና ከነሥብጥራቸው የሚቀበሉ፣ ከጥቃት እና ጉልበተኝነት ነጻ የሆኑ ደህንነታቸው የተጠበቀ ቦታዎች መሆን አለባቸው። በጋራ እና በትብብር መማር አንዳይነትነትን አያመለክትም። ውጤታማ ትብብራዊ ትምህርት የተማሪዎችን እና የመምህራንን ልዩነቶች (የአቅም፣ የችሎታ፣ የግንዛቤ፣ የፍላጎት እና የአጠቃላይ ችሎታ) ጥቅም ላይ ያውላል። ከአንድ አተያይ አንጻር፣ መማር የግለሰብ ጉዞ ነው፣ የእያንዳንዳችን ጉዞ። ትብብራዊ ትምህርት የተማሪዎችን ግለሰባዊነት የማይጎዳ፣ አካታች እና ፍትሐዊ መሆን አለበት። ነገር ግን ከሌላ እኩል ተቀባይነት ካለው አተያይ አንጻር፣ መማር የጋራ ጉዞ ነው፣ ከሌሎች ጋር በሚኖሩ ግንኙነቶች ውስጥ ቅርጽ የሚይዝ።

የትምህርት ግለሰባዊ እና የጋራ ተግባራት እርስበርስ ጉልበት የሚሰጣጡ እና የሚጠናከሩ በመሆናቸው፤ ራስን ማስተማር እንደ አንድ የትልቁ ምስል አካልነቱ አስፈላጊ ነው። ለሌላ ሰው መማር ባንችልም፣ ሁላችንም አብረን ግን የበለጠ መማር እንችላለን። እኛ የምናውቀው ሌሎች በሚያውቁት ላይ የተመካ ነው፣ ሌሎች የሚያውቁትም በእኛ ዕውቀት ላይ። ትምህርት የሚከወነው በግንኙነቶቻችን እና በመደጋገፎቻችን ውስጥ ነው። ውጤታማ የጋራ ትምህርት በዓለም ዙሪያ ባሉ ብዙ አርአያነት ባላቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ እየተከወነ ነው። ነገር ግን፣ በሁሉም ቦታ ያሉ ትምህርት ቤቶች በእነዚህ ግንኙነቶች እና መደጋገፎች ዙሪያ ሊቃኙ ይገባል።

ትምህርት ቤቶች እና መምህራን ተማሪዎችን የሚደግፉ ወሳኝ ሥራዎች ይሠራሉ። ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን በአዎንታዊ መልኩ የለወጠ(ች)ውን መምህር ወይም የትምህርት ቤት ተመክሮ ሊጠቁሙ ይችላሉ። በዚያው ልክ፣ ትምህርት ቤቶች ብዙ ጊዜ ያገልላሉ፣ ይነጥላሉ፣ እንዲሁም ልዩነቶችን ያራባሉ። ከዓለም ተማሪዎች መካከል ግማሽ ያህሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት በመሠረታዊ ብቃቶች አነስተኛውን የብቃት መመዘኛ ሳያሟሉ ነው - ይህም ተቀባይነት የሌለው፣ እና ትምህርት ቤቶች በተማሪዎቻቸው እና በማኅበረሰባቸው ላይ ያስከተሉት ውድቀት ማሳያ ውጤት ነው። ከዓለም ዙሪያ የተገኙ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ምሳሌዎች እንደሚያሳዩን፣ ተላማጅ እና ለዋጭ የሆነው የትምህርት ቤቶች ተግባራዊ ለውጥ አስቻይ ሁኔታ ሊፈጠርለት የሚገባ እና ሙሉ በሙሉ ዕውን ሊደረግ የሚችል ነው።

ትምህርት ቤት ከሌሎች ትምህርታዊ ቦታዎች ጋር ጥብቅ ቅንጅት ሲኖረው ብቻ ነው ተጠቃሚ የሚሆነው። የትምህርት ቤቶች ዲዛይን (በተገነባው ዲዛይን፣ ሥርዓተ ትምህርቶች፣ የክፍል አደረጃጀት እና የመማር ተግባራት የሚገለጠው) መለወጥ እንዳለበት በየትምህርት ወደፊቶች ኢኒሼቲቭ የትምህርት በተሳተፉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች መካከል ግልጽ የሆነ ስምምነት አለ። በ2050 የትምህርት ራዕይ መነሻነት የተሠራው የሥነ ጥበብ ሥራ ከጠረጴዛዎች ድርድር እና ከዴስኮች ሰልፍ መውጣትን ይተነብያል። ከትምህርት ኢኖቬተሮች ጋር የተደረጉ በርካታ ውይይቶች ትምህርት በበርካታ ጊዜያት እና ሥፍራዎች የሚከወንባቸውን መንገዶች፣ ለምሳሌ በመማርያ ክፍሎች እና በውጭው ዓለም መሀል ያሉ ግድግዳዎችን እንደማሳሳት እና ትምህርትን እንደ ጉዞ መልሶ የማሰብ መንገዶችን በአግባቡ ከለየን በኋላ ትምህርት ቤቶችን ከመሠረቱ መለወጥ እንደሚቻል ዳስሰዋል። በድምሩ፣ ት/ቤቶች ለወደፊት ትውልዶች የበለጠ አካታች፣ የበለጠ ጋባዥ፣ የበለጠ አሳታፊ እና ተገቢ በመሆን የተለዩ ሆነው ሊታዩ እና ሊሰሙ ይገባል።

ተማሪዎች በዘላቂነት መኖርን እና የተማሯቸውን መልእክቶች ወደ ቤታቸው እና ማኅበረሰባቸው ማድረስን የሚማሩባቸው ቦታዎች መሆን አለባቸው። “አረንጓዴ” ትምህርት ቤቶችን ዕውን የማድረግ እና ትምህርትን ወደ ካርበን-ዜሮ ደረጃ ለማምጣት ትልቅ አቅም አለ። ተማሪዎች ዓለማችን በአንገብጋቢ ደረጃ የምትፈልገውን አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚረዳቸውን ዕውቀትና ክህሎት በማዳበር፣ በዚህ ሥራ ግንባር ቀደም መሆን ይችላሉ።

ትምህርት ቤቶች እንዲያሳኩ የምንፈልግባቸውን ለማሳካት፣ ባለፉት ሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የታሪካቸውን ሰፊ ክፍል ይዘው ከኖሩት ግትር፣ አንድ ወጥ የአደረጃጀት ሞዴሎች መላቀቅ አለባቸው። መታደስ ወሳኝ ነው። ዛሬ የምናውቃቸውን የተለመዱ የትምህርት ቤት ሞዴሎች ያስተዋወቁት የዐሥራ ዘጠነኛው እና የሃያኛው ክፍለ ዘመን አስደናቂ ጥረቶች ለወደፊቱ የግንዛቤ ምንጮች ናቸው። ባለፉት አንድ መቶ አምሳ ዓመታት ውስጥ አርክቴክቶች፣ የማኅበረሰብ ጤና ባለሙያዎች፣ ፈላስፋዎች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ ማኅበረሰቦች እና ቤተሰቦች የትምህርት ዕድሎችን ለማስፋት ከሰው ልጅ ረጅም ታሪክ የተቀዱ ትምህርታዊ ግንዛቤዎችን መሠረት አድርገዋል። ይህም በጊዜ ሂደት፣ ለጅምላ የሕዝብ ትምህርት ቁሳዊ መልክ - ለምሳሌ በትምህርት ቤት ሕንፃዎች እና በመማሪያ ክፍሎች አማካይነት - ልዩ ማኅበራዊ ተቋማት ቅርጽ ሰጥቷል። የበለጠ ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ በሆነ የጋራ የወደፊት ዕድል መሠረት የተቃኙ እንዲሆኑ የሚያስችል ቁሳዊ ቅርጽ ለአዳዲስ ት/ቤቶች ለመስጠት፣ ይኸው ተመሳሳይ ዕይታ፣ ቁርጠኝነት እና ትብብር ዛሬም ያስፈልጋል።

## ከክፍል እስከ የተማሪዎች ማኅበረሰቦች

በዓለም ዙሪያ ክፍሎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ የመማር ማስተማር ዋነኛ ትምህርታዊ ቦታዎች ሆነዋል። አዳዲስ የአካታችነት እና የትብብር ቦታዎች ሲታሰቡ፤ “ክፍል” ብዙ ጊዜ ሊተው ይችል ይሆናል። ነገር ግን የቁርጠኛ እና የተሠባጠረ የተማሪዎች ማኅበረሰብ አባል መሆንም ያለውን ጥቅም መዘንጋት የለበትም።

የመደበኛ ትምህርት ቤት ሞዴሎች ተማሪዎችን በዕድሜ፣ በውጤት፣ በችሎታ፣ ወይም በጾታ መመደብ ላይ ከፍተኛ ጉልበት አውለዋል። በአንጻሩ፣ መምህራን በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚፈጠሩትን የተማሪዎችን ቡድኖች ለማዳበር፣ ለመሞከር እና ለማላመድ የሚያስችል ነጻነት ሊሰጣቸው ይገባል። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ትናንሽ የተማሪ ቡድኖች የተሻሉ ሊሆኑ ይችላሉ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ትላልቅ ቡድኖች ተሽለው ይገኛሉ። ነገር ግን የተማሪዎች ማኅበረሰብ አካል የመሆን ዋጋ መጠናከር ያለበት የትምህርት ቤቱ ገጽታ ነው። ተማሪዎች በወደፊት ትምህርት ቤቶች በተለመዱ የመማሪያ ክፍሎች ብቻ የተገደቡ ሳይሆኑ፣ ይልቁንም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር፣ የጋራ ትምህርት የሚያመጣውን ደስታ እና እንባ ጨምሮ፣ ዘላቂ ግንኙነት እንደሚያስፈልጋቸው ሆነው ይቀጥላሉ።

> *ተማሪዎች በወደፊት ትምህርት ቤቶች በተለመዱ የመማሪያ ክፍሎች ብቻ የተገደቡ ሳይሆኑ፣ ይልቁንም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር፣ ዘላቂ ግንኙነት እንደሚያስፈልጋቸው ሆነው ይቀጥላሉ።*

በመማር ዙሪያ ከክፍል የሚጠበቁ ነገሮችም እንዲሁ እንደገና መታሰብ ያስፈልጋቸዋል። በዓለም ዙሪያ ባሉ ብዙ ቦታዎች ሕፃናት እና ወጣቶች ቀኑን ሙሉ ክፍል ውስጥ ተቀምጠው ብዙ መረጃዎችን በፍዝ ተቀባይነት ይሰበስባሉ። ይህ ደንብ በትምህርት ቤት ኪነ ሕንፃ፣ የመገልገያ ዕቃዎች ዲዛይን፣ እና በክፍል ውስጥ ባሉ ነገሮች እና ቁሶች ውስጥ ተቀርጿል። የተማሪ ዝምተኝነት እና ታዛዥነት ከትኩረት እና ውጤታማነት ጋር እንደአቻ ተቆጥሯል። ብዙ ጊዜ፣ በማስተማር ዘዴ የተካኑ መሆን ሥነ ሥርዓትን ከማስከበር እና ‘አላስፈላጊ’ ጫጫታ ወይም እንቅስቃሴን ከማስወገድ ጋር እኩል ተደርጎ ይታያል። ያለመንቀሳቀስ እንደ መማር መስፈርት ሲቆጠር፣ ትምህርት ቤቱ እና መማሪያ ክፍሎቹ አሰልቺ እና የማያስደስቱ ቦታዎች ይሆናሉ። ጥልቅ፣ ጥብቅና መሳጭ ትኩረት እጅግ የላቀ ትምህርታዊ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል። ሆኖም አሁን ያሉን የመማሪያ ክፍል እና የትምህርት ቤት አደረጃጀቶች ይህንን በትክክለኛው መንገድ ያመቻቹ እንደሆነ መጠየቅ አለብን።

የትምህርት ቤትን ማኅበራዊ ቦታ መጠበቅ ካለብን፣ በአራት ግድግዳዎች ውስጥ መታጠር አያስፈልግም። በሰፊ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊ እና አካባቢያዊ ሀብቶች በመጠቀም ክፍት እና ተለዋዋጭ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል። ትምህርትን ሁሉንም በጅምላ በሚያዩ ክፍሎች ውስጥ መገደብ መማርን ይገድባል፤ ትምህርት ቤቶች ሊፈጥሩ የሚገባቸውን አጋጣሚዎች እና ዕድሎችም ያጠባል።

## የተለያዩ ሥነ ትምህርቶችን የሚደግፉ አወቃቀሮች

የክፍል ትምህርቶች እና የጊዜ ሰሌዳዎች ማሻሻያ ያስፈልጋቸዋል። የክፍል ትምህርት የተማሪዎችን ስብስብ በጋራ ተግባር ላይ እንዲያተኩር በማድረግ ጠቃሚ ሚና ከመጫወቱም ሌላ፣ ትምህርታዊ ግንኙነቶችን መል ለማያዝ እና በይነ-ትውልዳዊ ውይይቶችን ወደፊት ለማራመድ ጠቃሚ ዘዴ ነው። ነገር ግን የመደበኛ የክፍል ትምህርት ንድፎች ከፍተኛ ገደቦች አሏቸው፤ በተለይም በየቀኑ ወይም በየሳምንቱ በሚደጋገም ቋሚ ክፍለ ጊዜ ብቻ ሲገለጹ።

የክፍል ትምህርቱ ለተለያዩ የጥናት እና የመማር ሥልቶች እና ዘዴዎች ዋጋ ለሚሰጡ ሥነ ትምህርቶች ቦታ መልቀቅ አለበት። በይነ-ትውልዳዊ እና በይነ-ባሕላዊ ልውውጦችን ጥቅም ላይ ለሚያውሉ እና በመምህራን ከፍተኛ ችሎታዎች እና ዕውቀቶች ለሚመሠረቱ የተለያዩ የጥናት እና የመማር ሥልቶች እና ዘዴዎች ዋጋ በመስጠት ሰዎችን ለጋራ ጥረት የሚያስተባብሩ ሌሎች ብዙ መንገዶች አሉ። ለምሳሌ ችግር-ምሥርት እና ፕሮጀክት-ምሥርት ትምህርታዊ አካሄዶች ከተለመዱት የክፍል ትምህርት አሰጣጦች የበለጠ አሳታፊ እና ትብብራዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ጥያቄ-ምሥርት እና የተግባር ምርምር ሥነ ትምህርቶች ተማሪዎች በአንድ ጊዜ ዕውቀትን እንዲወስዱ፣ እንዲተገብሩ እና እንዲያመነጩ ሊያሳትፏቸው ይችላሉ። ማኅበረሰብ አሳታፊ ሥነ ትምህርቶች እና አገልግሎት ተኮር ትምህርት በትሑት የመማር ሁኔታ ውስጥ ሲካሄዱ፣ ለትምህርት ጠንካራ ፋይዳ ሊጨምሩለት ይችላሉ። እንደዚህ ያሉ ሥነ ትምህርቶች የተማሪዎችን በጋራ የመሥራት ችሎታዎች እንዲያሳድጉ እና በአጋርነት መንፈስ በጋራ የመወያየት እና የመተግበር አቅማችንን ለማስፋት የትምህርት ቤቶች አደረጃጀት ጉልሕ በሆነ መልኩ ሊከለስ ይገባል።

## የዲጂታል ድጋፍ ለትምህርት ቤት

የዲጂታል የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች ተማሪዎች ተመሳሳይ ፍላጎቶች እና ጥያቄዎች ካላቸው ከሌሎች ጋር እንዲገናኙ ሲፈቅዱ፤ የመምህራንን እና የትምህርት ቤቶችን ሥራ ይደግፋሉ። ዲጂታል ግንኙነት ለመምህራን እና ተማሪዎች መረጃን፣ ጽሑፎችን እና የጥበብ ቅርፆችን ከመላው ዓለም የሚያገኙባቸውን ዕድሎች በእጅጉ ያሳድጋል። የዓለማችን ታላላቅ አቢያተ መጻሕፍት እና ሙዚየሞች ስብስቦች አሁን በማንኛውም ጊዜ በሁሉም ቦታዎች ሊገኙ ይችላሉ። ዲጂታል መሳሪያዎች ደግሞ ተማሪዎች የፈጠራ ሐሳቦቻቸውን ለዓለም የሚያሳዩባቸውን ቪዲዮዎችን እንዲሠሩ፣ ድብልቅ ሚዲያ ይዘቶችን እንዲያቀናብሩ እና ጌሞችን እና መተግበሪያዎችን ኮድ እንዲያደርጉ ያስችሏቸዋል።

ዲጂታል መሳሪያዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ በፈጠራ የታገዘ ማስተማር እና መማርን መደገፍ የሚያስችላቸው ፈር ቀዳጅ እምቅ አቅም አላቸው። ዲጂታል መሳሪያዎች በወላጆች፣ በመምህራን እና በተማሪዎች መሀል ውጤታማ ተግባቦትን ለማዳበር፣ እና ወላጆችም የልጆቻቸውን የትምህርት ቤት ትምህርት እንዲያግዙ ጠቃሚ መንገዶች ሆነዋል።

*ወረርሽኙ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርቹዋል ሥፍራዎች ሊተካ እንደማይችል አረጋግጧል።*

ወረርሽኙ ትምህርት ቤት ሙሉ በሙሉ በቨርቹዋል ሥፍራዎች ሊተካ እንደማይችል አረጋግጧል። ከፍተኛ የኢንተርኔት ግንኙነት ባላቸው እና አንጻራዊ ፍትሐዊ የመሳሪያ ተደራሽነት ባለባቸው አካባቢዎች እንኳን፣ በችግር ጊዜ የትምህርት ቤቶች ሕንፃዎች/ቅጥሮች በጠቅላላው ወይም በከፊል መዘጋት በትምህርት ቤቶች ውስጥ የጋራ አካላዊ እና ማኅበራዊ መገኘት ስላለው አስፈላጊነት አዲስ ብርሃን ፈንጥቋል። ቤት ድረስ የሚመጡ ቨርቹዋል የመማሪያ ክፍሎች አካላዊ ትምህርት ቤቶች ሊሰጡ ከሚችሉት ጥቅም ከፊሉን ነው የሚተኩት።

በተግዳሮት እና በመስተጓጎል ወቅት - ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ጊዜ እስከተከወነ ትምህርት ድረስ - የተደረጉት የፈጠራ እርምጃዎች እና ሙከራቶች የመምህራንን እና የተማሪዎችን ቁራጥነት፣ ቁርጠኝነት እና ብልኀነት አሳይተዋል። ለምሳሌ፣ ብዙ የትምህርት ቤት መዋቅሮች የግል ፍላጎቶች እና ማኅበራዊ ደህንነት ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ሲገነዘቡ፣ ፈተናዎች ለሌላ ጊዜ ተላልፈዋል፤ የሥርዓተ ትምህርት የይዘት ሽፋን መስፈርቶች በይደር ተትተዋል፤ የክፍል ውስጥ መስተጋብሮችም ዕውናዊ ትምህርት እና ደህንነት ላይ ያተኮሩ ነበር። በኮቪድ ወቅት፣ የመምህራን ሥራ፣ በተለይ በወላጆች ዘንድ፣ በይበልጥ ታወቀ። ከመምህራን የሚጠበቀው ከፍተኛ የባለሙያ ዕውቀት እና የሥነ ትምህርት ተሳትፎ በብዙዎች ዘንድ በአንድ ጊዜ ተከበረ፤ ተመረመረም። አንዳንድ ተማሪዎች በመስመር ላይ እና በርቀት ትምህርት ምቾት ተሰምቷቸው ነበር፤ አዎንታዊ ተመክሮዎቻቸውም ወደፊት ትምህርት ቤቶች የመላውን ሰው ማኅበራዊ፣ ስሜታዊ፣ ግንዛቤያዊ እና ግብረገባዊ ዕድገትን በሚደግፉ መንገዶች ተማሪ ያማከሉ መሆን እንዳለባቸው ያስታውሱናል።

የመማርን ማኅበራዊ ገጽታ ማሳደግ ግለሰቦች እርስበርስ እንዲተሳሰቡ፣ ሌሎች አመለካከቶችን እና ተመክሮዎች እንዲያከብሩ እና በአካባቢ እና በጋራ የተፈጥሮ ሀብታችን ጉዳይ ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ እንዲሳተፉ የሚያስችለውን የዜግነት ትምህርት ከጊዜ ወደ ጊዜ እርስበርስ መተሣሠሩ እየጠነከረ በመጣው ዓለም ውስጥ ማስቀጠል ማለት ነው። ዲጂታሉ ዘዴ ግን ብቻውን እነዚህን ግቦች ማሳካት አይችልም። በትምህርት ቤቶች እና ከእነሱም ባሻገር አሳታፊ እና የተቀናጀ የትምህርት አሰጣጥ አስፈላጊ ነው።

ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ካለፉ ውሱንነቶች ይልቅ ከወደፊት ዕድሎቻው ጋር በቅርበት የተሳሰሩባቸው ቦታዎች መሆን አለባቸው። የእኩል ዕድል መርህ ማኅበራዊ አመጣጥ ማኅበራዊ ዕጣ ፈንታ እንዳይሆን እና በግለሰቦችም ሆነ በማኅበረሰቦች ዘንድ መጪው ጊዜ ካለፈው የተሻለ እንዲሆን ለማስቻል፤ የኋላ ታሪካቸው ምንም ይሁን ምን፣ ተማሪዎች በሌሎች ሰዎች በሚጠበቅባቸው ነገር ከመታሰር ራሳቸውን እንዲያላቅቁ ለማስቻል ነው።

የአብዛኛው የማሽን ትምህርት ቁልፍ ችግር የወደፊቱን ጊዜ መፍጠር የሚችለው ያለፈውን በማየት ብቻ መሆኑ ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ በሰዎች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያለው ዓይነት የተሣሣተ አመለካከት፣ የጾታ አድልዎ እና ዘረኝነት በዲጂታል መድረኮች ውስጥም ሥር ሰዷል፤ ምክንያቱም ማሽኖች ዛሬ በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ተመሳሳይ አድሎአዊ ጉዳዮችን በያዙ የመረጃ ቋቶች አማካይነት “የሰለጠኑ” ናቸው። አብዛኛዎቹ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረቱ ግል-ተኮር የመማሪያ መርሐ ግብሮች በተሠሩባቸው ሥልተ ቀመሮች ይህ ዕውነት ነው። እንደዚህ ዓይነት የጥናት አካሄድ የሚከታተለው ተማሪ የሚታወቀው እና የሚገለጸው ካለፈው አፈጻጸሙ ጋር በተገናኘ ብቻ ነው፡- ባለፈው ጊዜ ምን ያህል ጥያቄዎች/ፕሮብሌሞች እንደተሣሣቱ፣ ድክመት የታየባቸው ቦታዎች። ይህ ለዳግም ፈጠራ፣ ለራስን ማወቅ እና ትምህርት ቤቶች ሊያዳብሩት ለሚገባ የዕድሎች ግንዛቤ ትንሽ ቦታ ነው የሚተወው።

መምህራን በቀድሞ ግላዊ ውድቀቶቻቸው ላይ ሳይሆን፣ በተሳትፎ እና በተካቶ ዕድሎቻቸው ላይ ባተኮሩ፣ የተለዩ ግምቶች ላይ በመመሥረት የግል-ተኮር ትምህርት ንድፍ አውጪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ዲጂታል ዘዴዎች ማስተማር እና መማርን በብዙ መልኩ ሊደግፉ ይችላሉ። ነገር ግን፣ ተማሪዎችን ከሰው ልጅ የጋራ የዕውቀት ውርስ ሀብትና ስብጥር ጋር እንዲገናኙ የሚያስችል፣ የዕውቀት ነጻነትን የሚደግፍ እና ፍትሐዊ እና ዘላቂ የወደፊቱን አብሮ መፍጠር የሚያስችል የቅንጅት ሥራን ዕውን የሚያደርጉት የእርስበርስ ግንኙነቶቻችን እና ጠንካራ ትሥሥሮቻችን (በመምህራን እና ተማሪዎች መካከል፣ ነገር ግን በተማሪዎች እና በመምህራን መካከል) ናቸው።

ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ዲጂታል ሥፍራዎች እና ከባቢዎች በቀላሉ ሊበላሹ እና ሊሣሣቱ እንደሚችሉ የሰው ፈጠራዎች እንዲቆጥሯቸው የምናስተምርባቸው ቦታዎችም ጭምር ናቸው። ኮዲንግ እና ሥነ ስሌታዊ አስተሳሰብ በብዙ የትምህርት ሥርዓቶች ውስጥ እንደ ዋና አርእስተ ጉዳይ ብቅ ብለዋል፤ ዲጂታል ሕንፃዎቻችን የሚገነቡበትን መንገድ አጥርተው ለማሳየት እና እንደገና ለማዋቀር የሚረዱንን ተግባራዊ እና ንድፈ ሐሳባዊ መሳሪያዎችን ለማቅረብ ያግዛሉ። ዲጂታል ሚዲያን፣ እንደ ትምህርታዊ ሚዲያም ቢሆን፣ መጠቀም ብቻ ተማሪዎች አዳዲስ ዲጂታል አማራጮችን ራቅ ብለው የሚያስቡበትን ወሳኝ ርቀት እምብዛም አይሰጡም። የሚያገናኙን እና ብዙውን አስተሳሰባችንን የሚመሩት ቴክኖሎጂ እና አውታረ መረቦቹ የተለያዩ አውዶች፣ ማበረታቻዎች፣ አቅጣጫዎች፣ አመክንዮዎች እና አሠራሮች አሏቸው። በእነዚህ ምክንያቶች የተነሣ፣ ትምህርት ዲጂታል መስተጋብሮችን እንደ የሥርዓተ ትምህርት ዓላማዎች ማስፈጸሚያ ብቻ ሳይሆን፤ ራሳቸውንም የምርመራ እና የጥናር

አርእስተ ጉዳይ ማየት አለበት። ስለ ዲጂታል መብቶች፣ ክትትል፣ ባለቤትነት፣ ግለ መብት፣ ሥልጣን፣ ቁጥጥር እና ደህንነት ላይ የሚደረጉ ውይይቶች የመደበኛ ትምህርት አካል መሆን አለባቸው። ብዙውን ጊዜ እንዲያውም አንድ ቀን በቨርቹዋል ዓለም ውስጥ እንደምንኖር ይነገራል፤ ግን በተወሰነ ደረጃ እና በአንዳንድ ቦታዎች፣ ይህ ቀድሞውኑ ዕውነት ሆኗል። በአንዳንድ አገሮች የአንድ አማካይ ሰው በቀን ከዐሥር ሰዓት በላይ በመስመር ላይ ማሳለፍ እና በዲጂታል ቴክኖሎጂ ውስጥ መዘፈቅ ያልተለመደ ነገር አይደለም። ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በእነዚህ ከባቢዎች ውስጥ እንዲበለጽጉ እና ለፈጠራ፣ ተግዳሮቶችን ለመፍታት እና ለዕድገታቸው እንዲጠቀሙባቸው ሊረዷቸው ይገባል። ትምህርት ቤቶች ሰዎች በጋራም ሆነ በተናጥል ቴክኖሎጂን የሚቆጣጠሩበትን ሥነ ምግባርን ማወጅ አለባቸው።

## የትብብር ባሕሎችን መገንባት

ትምህርት ቤቶች ወደ ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ ወደፊት የሚያደርሱትን ትብብርን፣ የጋራ አመራርን፣ የጋራ ትምህርትን እና ቀጣይነት ያለው ዕድገትን የማበረታታት የተሟላ ብቃት አላቸው። ነገር ግን፣ ይህንን እንደ የትምህርት ቤት ማዕከላዊ ዓላማ መቀበል መምህራን፣ አስተዳዳሪዎች እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች አዳዲስ ችሎታዎችን እንዲያዳብሩ ግድ ይላል። ቤት ተጠያቂነት ከመታዘዝ ወደ የጋራ ግብ ቀረጻ እና ምዘና ሂደት ማደግ አለበት። የትምህርት ቤት አስተዳደር በትዕዛዝ እና በቁጥጥር ፋንታ ሙያዊ ትብብርን፣ ራስገዝነትን፣ እና መተጋገዝን ማሳደግ ይገባዋል። በተማሪዎች መካከል ትብብርን የሚያበረታቱ ትምህርት ቤቶች፣ ይህንኑ በመምህሮቻቸው መካከል ማበረታታት አለባቸው። ይህ የመምህራን፣ የአስተዳዳሪዎች እና የሠራተኞችን ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ዕድገት በሚያበረታቱ የትምህርት ቤት ባሕሎች ይደገፋል። ማሰልጠን፣ ማማከር፣ የግል እና የቡድን ጥናት፣ ተግባር-ተኮር ምርምር እና ከሌሎች ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርስቲዎች ጋር የሚደረጉ የጥናትና ምርምር ትብብሮች ሁሉ ትምህርት ቤቱን እንደ መማሪያ ድርጅት መልሶ ለመፍጠር ይረዳል።

በመላው ዓለም፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ መምህራን እና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ትምህርት ቤቶች በእነዚህ አቅጣጫዎች አልፈዋል። ለምሳሌ፣ በተለያዩ አገር በቀል አውዶች፣ ትምህርት ቤቶች በይነ-ትውልዳዊ እና ጥንታዊ የውርስ ዕውቀቶች፣ ቋንቋ እና የምርምር ልምምዶች ላይ ተመሥርተው መማርን እና በይነ-ባሕላዊ እና ከሰው በላይ ከሆነው ዓለም ጋር የሚደረግ መስተጋብርን ማበረታታት እንዲችሉ ተደርገው በአዲስ መልክ ተነድፈዋል። በሌሎች ሁኔታዎች፣ ትምህርት ቤቶች ገንቢ የሆነ የማኅበረሰብ ተሳትፎ እና የፈጠራ የጋራ ጥረቶችን ባካተተ የምርምር መስመር ራሳቸውን እያደራጁ ነው። በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ውስጥ የተመዘገቡት ዕድገቶች በአዲስ መልክ በተዘጋጁ ልምምዶች፣ ትርጉም ባላቸው ኮርሶች እና በውጤታማ ሥልጠናዎች አማካይነት በንድፈ ሐሳብ እና በተግባር መካከል ያለውን ሰው ሠራሽ ልዩነት እያጠበቡ ነው።

ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ጋር እና በሀገሮች መካከል በዕውቀት ማጋራት ተግባር የሚተጉ እና ራሳቸውን እንደ የሕዝብ ቦታዎች እና የትብብር ከባቢዎች ለማደስ እና እንደገና ለማቋቋም የሚተጉ ከዓለም አቀፋዊ አጋርነት ጋር የሚጣጣሙ ትምህርት ቤቶች ያስፈልጉናል። ትምህርት ቤቶች ትምህርትን በአጠቃላይ እንደ አንድ የጋራ ጥቅም ለማጠናከር ወሳኝ ሚና አላቸው።

# ሽግግር ከትምህርት ቤት ወደ ከፍተኛ ትምህርት

በታሪክ ከትምህርት ፋክልቲዎች ውጭ፣ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ብዙም ትኩረት ሲሰጡ አልታዩም። ይሁን እንጂ በዩኒቨርስቲዎች እና ኮሌጆች ውስጥ የሚያጋጥሙ ከተማሪ ውጤት ጋር የተያያዙ አብዛኞቹ ችግሮች የከፍተኛ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት መፈታት እንዳለባቸው ከቅርብ ዐሥርት ዓመታት በላይ ግንዛቤ ተጨብጧል። ከሒሳብ እስከ ሳይንሶች፣ ከሥነ ጽሑፍ እስከ ፍልስፍና፣ በከፍተኛ ትምህርትና ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ትስስር ለማጠናከር የሚያስችሉ፣ ብዙ ጊዜም በታሪክ በወጉ ያልተወከሉ ቡድኖችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ያለሙ፣ አጠቃላይ ማቀራረቢያ እና የማበልጸጊያ መርሐ ግብሮች ሲዘጋጁ ኖረዋል። እንደዚሁም የዩኒቨርስቲ ተመራማሪዎች ስለትምህርት በሚደረጉ አጠቃላይ ክርክሮች ውስጥ ዝናቸው እየገነነ መጥቷል።

*የከፍተኛ ትምህርት የወደፊት የፖሊሲ አጀንዳዎች እና ተለምዷዊ ያልሆኑ ትምህርታዊ አቅጣጫዎችን እና መንገዶችን በተሻለ ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።*

የከፍተኛ ትምህርት ሚናዎችን በተመለከተ የሚደረግ ማንኛውም ውይይት፣ ከአንደኛ ደረጃ እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት፣ እንዲሁም ከጎልማሶች ትምህርት እና መደበኛ ካልሆነ ትምህርት ጋር ያለውን አይቀሬ ግንኙነት ሊዘለው አይችልም። በ2050 ተማሪዎች በከፍተኛ ትምህርት እና ከዚያም በላይ ባሉ ደረጃዎች ማበብ እንዲችሉ፣ የሁሉም የትምህርት ደረጃዎች እሴቶች እና አደረጃጀቶች መተሳሰር አለባቸው። የከፍተኛ ትምህርት የወደፊት የፖሊሲ አጀንዳዎች ሁሉንም የትምህርት ደረጃዎች ማቀፍ እና ተለምዷዊ ያልሆኑ ትምህርታዊ አቅጣጫዎችን እና መንገዶችን በተሻለ ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። የተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች እና የትምህርት ዓይነቶች እርስበርስ የተሳሰሩ መሆናቸውን መገንዘብ፣ ለወደፊት የከፍተኛ ትምህርት ዕድገት ዘርፍ-አቀፍ፣ የዕድሜ ልክ የትምህርት አቀራረብ አስፈላጊ መሆኑን ይናገራል።

በትምህርት ቤቶች እና በዩኒቨርስቲዎች መካከል ያሉ አጋርነቶች ትምህርትን እንደገና ለማጤን እና ለማጠናከር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የዩኒቨርስቲ አቢያተ መጻሕፍት እና የምርምር ተቋማት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን መደገፍ ይችላሉ። የፕሮፌሰሮች ዕውቀትና ክህሎት ለአካባቢው ትምህርት ቤቶች በቀላሉ የሚገኝ መሆን አለበት። እንደዚህ ዓይነት አጋርነቶች የትምህርት መዋቅሮችን ተቋማዊ አቅም በማጎልበት፣ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለማፍለቅ እና ለመተግበር ያስችላሉ። በተጨማሪም፣ ዩኒቨርስቲዎች ይበልጥ አስበውበት ሦስቱን የምርምር፣ የማስተማር እና የማስፋፋት ዋና ተግባሮቻቸውን አቀናጅተው፣ በዘመናችን በጣም ወሳኝ በሆኑ አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለሕዝባዊ ጥረቶች አገልግሎት የሚሰጡበት ዕድል ነው።

# የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች

ይህ ምዕራፍ በአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ውስጥ ትምህርት ቤቶች አካታችነትን፣ ፍትሐዊነትን እና የግል እና የጋራ ደህንነትን ስለሚደግፉ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገባ የትምህርት ቦታዎች እንዲሆኑ - እንዲሁም የዓለምን ወደ የበለጠ ፍትሐዊ፣ ተመጣጣኝ እና ዘላቂ ወደፊት መለወጥ እንደሚደግፉ ተደርገው እንደገና እንዲጤኑ ምክረ ሐሳብ አቅርቧል። ወደ 2050 ስናማትር፣ ይህንን ምክረ ሐሳብ ወደፊት ለማራመድ የሚያስፈልገውን ውይይት እና ድርጊት ለመምራት የሚረዱ አራት መርሆች አሉ፡-

- **ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ሌላ ቦታ ከማያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች ጋር እንደሚጋፈጡባቸው እና ዕድሎችም እንደሚያገኙባቸው ቦታዎች ሊጠበቁ ይገባል። ትምህርት ቤቶች ባይኖሩ ኖሮ፣ ልንፈለስፋቸው ግድ ይለን ነበር።** ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ሰዎችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ እርስበርስ እና አብረው እንዲማሩ ማድረግ መቻላቸውን ማረጋገጥ አለብን።
- **የጋራ አቅምን መገንባት ትምህርት ቤቶችን መልሶ የመንደፉን ጥረት መምራት አለበት።** የትምህርት ቤት ኪነ ሕንፃ፣ ሥፍራዎች፣ ጊዜያት/የጊዜ ሰሌዳዎች፣ እና የተማሪ አቦዳደኖች የግለሰቦችን አብሮ የመሥራት አቅምን ለመገንባት የተነደፉ መሆን አለባቸው። የትብብር ባሕሎች በትምህርት ቤቶች አስተዳደር እና አመራር እንዲሁም በትምህርት ቤቶች መካከል ባሉ ግንኙነቶች ውስጥ መስፋፋት አለባቸው።
- **ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ትምህርት ቤቶችን - ለመተካት ሳይሆን - ለመደገፍ ማለም አለባቸው። የተማሪዎችን ፈጠራ እና ተግባቦት ለማሳደግ ዲጂታል መሳሪያዎችን መጠቀም አለብን።** ሰው ሠራሽ አስተውሎት እና ዲጂታል ስልተ ቀመሮች ወደ ትምህርት ቤቶች ሲገቡ፣ አሁን ያሉትን የተዛቡ አመለካከቶች እና የማግለል ሥርዓቶች እንደማያራቡ ማረጋገጥ አለብን።
- **ትምህርት ቤቶች ሰብአዊ መብቶችን በማረጋገጥ እና የዘላቂነት እና የካርበን ነጻ አርአያ በመሆን ለምንመኘው ወደፊት ተምሳሌቶች መሆን አለባቸው።** የትምህርት ሴክተሩን አረንጓዴ ለማድረግ ተማሪዎች እምነት ሊጣልባቸውና በግንባር ቀደምትነት እንዲሠሩ ኃላፊነት ሊጣልባቸው ይገባል። ሁሉም የትምህርት ፖሊሲዎች ሰብአዊ መብቶችን በዘላቂነት እንደሚጠብቁ እና እንደሚያጎለብቱ ማረጋገጥ አለብን።

አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል በመቅረጽ ሂደት፣ በመላው ዓለም ያሉ ሁሉም ሰዎች ከሰው ልጅ ወሳኝ እና ጠንካራ የትምህርት ተቋማት አንዱ የሆነውን ትምህርት ቤት ደህንነት ከማስጠበቅ እና ከመለወጥ ጋር የተያያዙትን አራቱን የመመሪያ መርሆች እንደመነሻሻ መውሰድ መቻል አለባቸው።

# ምዕራፍ 7

# ትምህርት በልዩ ልዩ ጊዜያት እና ሥፍራዎች

*ሜዳዎቿን፣ ተራሮቿን፣ ሸለቆዎቿን፣ ወንዞቿን፣ ጎዳናዎቿን፣ አደባባዮቿን፣ ምንጮቿን፣ ቤቶቿን፣ ሕንፃዎቿን ይዘን፤ የጊዜ እና የዘይቤ አሻራችንን እያተምን፣ የዘመን ጣዕም እየተውን የምናልፍባት ከተማ ከማስተማር፣ መማር፣ ማሳወቅ፣ ማወቅ፣ መፍጠር፣ ማለም እና መመነብ ፍላጎታችን የተነሣ ትምህርታዊ ትሆናለች። ከተማዋ እኛን ናት፤ እኛም ከተማዋን ነን።*

*ፓውሎ ፍሬሬ፣ Politics and education,* 1993.

**በትምህርት በአዲስ ማኅበራዊ ውል ውስጥ በሕይወት ዘመን እና በተለያዩ ባሕላዊ እና ማኅበራዊ ቦታዎች ውስጥ በሚከናወኑ አበልጻጊ የትምህርት ዕድሎችን መጠቀም እና እነሱንም ማስፋፋት አለብን።**

ዛሬ ብዙ ሰዎች ትምህርት በዋነኝነት ሕፃናት እና ወጣቶችን ለዐዋቂነት ዕድሜ ሕይወታቸው ማዘጋጀት ላይ ያነጣጠረ ይመስላቸዋል። ብዙ ሕዝባዊ ውይይቶች "ትምህርት"ን ከተማሪ ቤተሰቦች እና ከሕብረተሰብ አንጻራዊ ርቀት ላይ ለሚንቀሳቀሱ ልዩ ተቋማት የሚሰጥ አቻ ስያሜ ያደርጉታል። ልዩ አውዶች ለጋራ ማስተማር እና መማር የተሰጡ ጊዜያትን እና ቦታዎችን ለመጠበቅ ጠቃሚ መሆናቸው ተረጋግጧል። በት/ቤቶች ውስጥ ያለው ትምህርት የራሱ ልዩ ባሕርያት ያሉት የሰው ልጅ ወሳኝ የሥፍራ-ጊዜ ተመክሮ ሆኗል። እኩልነትን እና የዕድልን ተደራሽነት ለማላቅ ለሕፃናት እና ወጣቶች ቅድሚያ መሰጠቱ አስፈላጊ ነው።

ያም ሆኖ፣ ስለ ትምህርት በመደበኛ ተቋማት ብቻ የሚቀርበው ውይይት በሕብረተሰቡ ውስጥ እና ከዳር እስከ ዳር ያሉትን የዳበሩ የትምህርት ዕድሎችን አያካትትም። በዚህ ሪፖርት ውስጥ የቀረበው የትምህርት ማኅበራዊ ውል መሥራች መርህ የዕድሜ ልክ ትምህርት መብት ለሁሉም የሚል ነው። ይህ መርህ መማር እንደማያበቃው ሁሉ ትምህርት በሁሉም ጊዜያት እና ቦታዎች የበለጠ መስፋፋትና መበልጸግ እንዳለበት ይገነዘባል። ይህ መርህ በሁሉም የሕብረተሰብ ደረጃዎች እና በጋራ ሕይወታችን ላይ ሰፊ አንድምታ አለው - በማኅበረሰቦቻችን፣ በከተሞቻችን፣ በመንደሮቻችን እና ትናንሽ ከተሞቻችን፣ በብሔራዊ መለያዎቻችን እና ባሕላዊ ሥርዓቶቻችን፣ እንዲሁም በቀጣናዊ እና በዓለም አቀፍ ማኅበረሰቦች ላይ ሁሉ። ሥራ፣ እንክብካቤ፣ መዝናኛ፣ ጥበባዊ ፈጠራዎች፣ ባሕላዊ ልምምዶች፣ ስፖርቶች፣ የሲቪክ እና የማኅበረሰብ ሕይወት፣ ማኅበራዊ እርምጃ፣ መሠረተ ልማት፣ የዲጂታል እና ሚዲያ ተሳትፎ - እነዚህ ሁሉ ከሌሎች ስፍር ቁጥር ከሌላቸው ነገሮች ጋር ተዳምረው ለጋራ ወደፊታችን ትምህርታዊ፣ ሥነ ትምህርታዊ እና ትርጉም ያላቸው የመማር ዕድሎች የመስጠት አቅም ያላቸው ናቸው። አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል በሁሉም ጊዜያት እና ቦታዎች ውስጥ ተለዋዋጭ የመማር ባሕሎች ያላቸውን አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ መገንዘብ አለበት።

ከዋነኛ ሥራዎቻችን አንዱ ትምህርት ስለሚካሄድበት ሥፍራ እና ጊዜ ያለንን አስተሳሰብ ማስፋት ሥራችን ነው። ይህ አዲስ አጣዳፊ ፈተና ከ50 ዓመታት በፊት የተነሳው የትምህርት ሥርዓቶችን መልሶ ለማሰብ በሚደረገው ጥረት የCité éducatif ('የመማር ከተማ') ራዕይን ባስቀመጠው በፋውሬ ኮሚሽን ሪፖርት ላይ ነው። በተለያዩ መንገዶች ወደ ሌሎች ቋንቋዎች የተተረጎመው (ለምሳሌ በእንግሊዘኛ "learning society" ['የመማር ማኅበረሰብ'] ተብሏል) "ከተማ"፣ በዚህ ዐውድ ሁሉንም ዕድሎች እና እምቅ አቅሞች፣ በተለይም እርስበርስ የተያያዙ በመሆናቸው፣ የሚያጠቃልል የቦታ ዘይቤ ነው። ትምህርትን ስለሚደግፉ ቦታዎች እና ማኅበራዊ ሥራዎች ብልጽግና እና ስብጥር፣ እንዲሁም ስለተሳታፊዎቻቸው አስፍተን ማሰብ አለብን በሚለው ሐሳብ ላይ የተመሠረተ ነው።

የዛሬዎቹ ሥር የያዙ አስተሳሰቦችም በጥቅሉ ትምህርትን በ5 ወይም 6 ዓመት ተጀምሮ፣ ከአንድ ዐሥር ዓመት በኋላ የሚጠናቀቅ አድርገው ይቆጥሩታል። ይህ የዓመታት ክልል ባለፉት ዓመታት እየሰፋ መጥቷል፤ ትምህርታዊ ጥረቶችን እስከ ቅድመ ልጅነት የማራዘም፤ ትኩረትንም አዲስ በተወለዱ እና ጨቅላ ሕፃናት ላይ ጭምር እና በዐዋቂዎችም እስከ ዕድሜ ልክ ድረስ የማድረግ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። በመጀመርያው ሁኔታ፣ የቅድመ ልጅነት ትምህርት፣ ምንም እንኳን አሁንም "ቅድመ-አንደኛ ደረጃ" የትምህርት ቤት ዝግጅት ተደርጎ ቢቀረጽም፤ በራሱ እንደ መሠረታዊ የትምህርት ጊዜ ይታያል። በሁለተኛው ሁኔታ፣ ብዙ ጊዜ "ሁለተኛ ዕድል" ከመስጠት ወይም በሥራ ቦታ አዲስ ክህሎት ከመጨበጥ እና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አንጻር፣ የጎልማሶች ትምህርት በአብዛኛዎቹ የዓለም አገሮች የትምህርት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ውስጥ ዋና ጉዳይ ቢሆንም፤ እስካሁንም ድረስ ግን ብዙውን ጊዜ የትምህርት ቤት ማራዘሚያ በሚል ማዕቀፍ ውስጥ ነው የሚገኘው።

ይህን ስንል፣ "በትምህርት ቤት ቅርጽ" ላይ የተመሠረቱ የትምህርት ሞዴሎች፣ ብዙውን ጊዜ በትንንሽ ልጆች እና በጎልማሶች ትምህርት ውስጥ ገንነው፣ የተለያዩ እና የተለዩ የትምህርት ዓይነቶች የሚኖሩበትን ዕድል ይቀንሳሉ ማለታችን ነው። እውነት ነው፣ ይህንን "የትምህርት ቤት ቅርጽ" ለተወሰኑ የዕድሜ እና የባሕርይ ቡድኖች ማስቀጠልን የመቃወም የረጅም ጊዜ ልማድ አለ፤ በዚህም ምክንያት እነዚህ ቡድኖች የተለዩ የትምህርት ሂደቶች እና ማዕቀፎች ሊኖሯቸው ግድ ሆኗል።

በቅድመ ልጅነት ትምህርት፣ ይህ ልማድ በደንብ ተተክሏል፤ ለሙከረት እና ደህንነት ዋጋ የሚሰጡ እና በስሜታዊ፣ ስሜተ ሕዋሳዊ እና ተዛምዷዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሚያደርጉ የተለያዩ የትምህርት ስትራቴጂዎችም ይተገበሩበታል። ብዙዎች እንዲያውም፣ ከቦታዎች እና ጊዜያት አዲስ አደረጃጀት አንጻር፣ የትምህርት ቤት ለውጥ ይበልጥ ክፍት እና ተለዋዋጭ ከሆኑት የቅድመ ልጅነት ትምህርት ሞዴሎች መነሣት እንዳለበት ያምናሉ።

የጎልማሶች ትምህርትን በተመለከተ፣ ይህ ልማድ ለብዙ ዐሥርተ ዓመታት መዝለቁን በግልጽ የሚያሳዩን፣ የጎልማሶች ትምህርትን "ከትምህርት ቤታዊ ልማድ ውጭ ለማድረግ"፣ ማለትም የጎልማሶችን ራስገዝነት፣ የሕይወት እና የሥራ ተመክሮዎቻቸውን እና ከመደበኛ ትምህርት ቤት ማዕቀፎች ውጭ የሚከናወን ትምህርትን በሚያከብሩ ቅርጾች እና ሂደቶች አማካይነት እንዲከናወን የሚጠይቁ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ፕሮፖዛሎች ናቸው። እነዚህ ሰብአዊነትን ከሚያነጥፉ፣ ከጭቆና ወይም ከቅኝ አገዛዝ ሥርዓቶች ጋር የሚዋጉ እና ጎልማሶችን ከትምህርት ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት አማካይነት ለማስቻል የሚጥሩ ነጻ አውጪ ትምህርታዊ ፕሮፖዛሎች ናቸው።

ነገር ግን፣ እንዲህ ዓይነት ተቃውሞዎች ቢኖሩም፣ "የትምህርት ቤት ፎርማት" እስከ ዕድሜ ልክ የመማር አዝማሚያዎችን በኩል ወደ የቅድመ ልጅነት ትምህርት እና የጎልማሶች ትምህርት መንሰራፋቱን መካድ አይቻልም። ስለ 2050 ትምህርት ለማሰብ የሁሉንም ቦታዎች፣ የሁሉም ጊዜያት እና የሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች አስፈላጊነት መረዳት አለብን። ሆኖም ይህ ማለት ዓለምን ወደ ግዙፍ የመማሪያ ክፍል እንለውጣለን ማለት አይደለም። ልናመጣው የሚገባው መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ዛሬ ያሉ ማኅበረሰቦች በባሕል፣ በሥራ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ እና በዲጂታል መንገድ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የትምህርት ዕድሎች እንዳሏቸው፣ እንደየራሳቸው መመዘን እና እንደ ጠቃሚ የትምህርት ዕድሎች መገንባት እንደሚገባቸው መረዳት ነው። በሚቀጥሉት 30 ዓመታት ውስጥ፣ ከትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውል ዋነኛ ገጽታዎች አንዱ ትምህርት ከሕይወት ጋር የተሣሠረበት ሁኔታ ወሳኝ መሆኑን መረዳት ይሆናል። ስለዚህ፣ ትምህርት ቤቶችን እንደ ልዩ የትምህርት ቦታ-ጊዜ እንዲጠበቁ ብንከላከልም፣ ዕይታችንን ወደ ሁሉም የሕይወት ቦታዎች እና ጊዜያት ማስፋት አለብን።

> *ትምህርት ቤቶችን እንደ ልዩ የትምህርት ቦታ-ጊዜ እንዲጠበቁ ብንከላከልም፣ ዕይታችንን ወደ ሁሉም የሕይወት ቦታዎች እና ጊዜያት ማስፋት አለብን።*

ይህ ምዕራፍ የሚጀምረው ስላሉት በርካታ የትምህርት ቦታዎች እና ዕድሎች በመወያየት፤ ይኸውም ጥረታችንን ሥፍራዎቹ እና ጊዜያቱ አካታችነትን እና ለአዳዲስ ፈተናዎች ምላሽ ሰጪነትን የሚደግፉ መሆናቸውን ወደ ማረጋገጥ መቃኘት እንዳለብን በመሟገት ይጀምራል። በመቀጠልም አገሮች የመማር መብትን ዕውን ለማድረግ የሚጫወቱትን ወሳኝ ሚና እንዲሁም ቴክኖሎጂ ትምህርት የጋራ ነጋችንን በሚያገለግል መልኩ መታደሱን እንደሚደግፉ ለማረጋገጥ የዲጂታል ቦታዎች አስተዳደር ያለውን አስፈላጊነት ይዳስሳል። የምድር ባዮስፌርም እንዲሁ በቀላሉ ሊታለፍ የማይገባው ወሳኝ የመማማሪያ ቦታ ነው። ምዕራፉ የሚጠናቀቀው በተለይ በመንግሥታት እና በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ ያተኮሩ የ2050 የውይይት እና የድርጊት መርሆች በማቅረብ ሲሆን፤ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፦ አካታች የጎልማሶች ትምህርትን አስፈላጊነት ማጉላት፤ አዳዲስ የመማሪያ ቦታዎችን መገመት፤ የገንዘብ ድጋፍን ማጠናከር፤ እና ትምህርት የማግኘት መብትን ማስፋት።

# የትምህርት ዕድሎችን ወደ አካታችነት እና ዘላቂነት መምራት

በተሻለ ሁኔታ ለመሥራት የትምህርት አስተዳደር የትምህርት ተቋማትን፣ የማኅበራዊ ተቋማትን እና ጊዜያዊ ግንኙነቶችን ሠፊ ተደራሽነት፣ ድንበር ጣሽነት እና የትም ተገኚነት ማወቅ እና ማድነቅ አለበት። ሆኖም እነዚህ ልዩ ልዩ ባለድርሻዎች ለአካታችነት እና ለዘላቂነት ቁርጠኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ የትምህርት ዕድሎች - መደበኛ ሆኑም አልሆኑ - ለሁሉም ተደራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ትብብር እና ቁርጠኝነትን ይጠይቃል።

ትምህርትን ለማስተዳደር የጋራ ሥራችንን በአካታች ንድፍ መርሆች የተመሠረተ የማካተት ሥነ ምግባር ሊመራው ይገባል። የመነሻ ነጥብ መሆን ያለባቸው ብዙ ጊዜ በጣም ከሚገለሉት መሀል ያሉ እና ሥጋት እና ተጋላጭነት ያለባቸው መቼቶች ናቸው። ግልጽ እና አካታች እሴቶች በሌሉበት የትምህርት ሥነ ምህዳሮች ጤናቢስ እና በሽተኛ ሊሆኑ ይችላሉ። የሥልጣን፣ የልዩ መብት፣ የብዝበዛ እና የጭቆና ጉዳዮች ወደ የትኞቹም የትምህርት ግንኙነቶች ሊዘልቁ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ የትምህርት ዲዛይኖች እና ተቋማት ውድቀትን እና ማግለልን ያመጣሉ፤ ብሄር ብሄረሰቦች፣ ቀደምት ሕዝቦች እና ሌሎች የተገለሉ ቡድኖች ከመደበኛ ትምህርት ከማቋረጣቸው በላይ መገፋት ሊደርስባቸውም ይቻላል። ስደተኞች እና አካል ጉዳተኞች ተለይተው ደካማ አገልግሎት ሊሰጣቸው ይችላል። ለትምህርት ሥርዓቶች የሚዘጋጅ ሰፋ ያለ አቀራረብ፣ እነዚህን ውድቀቶች ችላ ማለት በጣም አስቸጋሪ እንዲሆን በማድረግ፤ ሰንሰለታማ ትስስር ባላቸው ምላሾች እና በተቋማት፣ በባለድርሻዎች እና በቦታዎች መካከል በሚኖሩ አስተሣሣሪ ተፅእኖዎች ላይ ግልጽ ትኩረት ያደርጋል።

## የመንግሥታት እና የአገራት ሚና

ትምህርት መሠረታዊ የሰው ልጅ መብት መሆኑን እና ይህ መብት ለሁሉም ሕፃናት፣ ወጣቶች እና አዋቂዎች ዕውን እንዲሆን መንግሥታት እና ማኅበረሰቦች ልዩ ኃላፊነት እንዳለባቸው ዓለም አቀፍ መግባባት አለ። በዚህም መሠረት መንግሥታት እና አገራት በትምህርታዊ ሥነ ምህዳሩ ውስጥ ወሳኝ ሚና መጫወት አለባቸው፤ እንዲሁም ተጠያቂ የሚሆኑባቸው ጉልሕ ኃላፊነቶችም አሉባቸው።

በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 26 ላይ የተመሠረተው የትምህርት መብት በየአገሩ የሕግ አስገዳጅነት ባላቸው በርካታ ስምምነቶች አማካይነት በበለጠ ዳብሯል። ስምምነቶቹም የ1960ውን የትምህርት ጸረ አድሎአዊ ኮንቬንሽን (CADE) እና የ1966ቱን ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና የባሕል መብቶች ቃል ኪዳን (ICESCR) አንቀጽ 13 ያካትታሉ። በእዚህ ሰነዶች፣ ትምህርት ሁሉም ሰዎች በነጻ ማኅበረሰብ ውስጥ በብቃት እንዲሳተፉ ማስቻል እና በሁሉም ሀገራት መካከል መግባባትን፣ መቻቻልን እና ወዳጅነትን ማጎልበት እንዳለበት ሁሉም ተፈራራሚ ወገኖች ተስማምተዋል።

አሁን ባለው ዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ሁሉም ተፈራራሚ ወገኖች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ነጻ እና አስገዳጅ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትም፣ ከነልዩ መልኮቹ፣ በጥቅሉ ለሁሉም ክፍት እና ተደራሽ መሆን አለበት። ከፍተኛ ትምህርትም በግለሰብ አቅም ላይ ተመሥርቶ ለሁሉም እኩል ተደራሽ መሆን አለበት። መንግሥታት የትምህርት መብትን በተመለከተ ሦስት እጥፍ ግዴታዎች አሉባቸው፦ መፈጸም፣ ማክበር እና መጠበቅ። የአገሩ የመፈጸም ግዴታ የትምህርት መብትን የማመቻቸት እና የመስጠት ግዴታን ያጠቃልላል፤ የማክበር ግዴታ ደግሞ የትምህርት መብትን የሚጎዱ እርምጃዎችን መከላከልን ያካትታል። የመጨረሻውና እኩል ወሳኝነት ያለው ደግሞ፣ አገሩ ሦስተኛ ወገኖች በመማር መብት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገቡ የመጠበቅ እና የመከልከል ግዴታ አለበት።

የመማር መብት ከሌሎች ሰብአዊ መብቶች ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ከዚህ አንጻር፣ አገሮች የመብቶች ዋስትናዎች እንደመሆናቸው መጠን፣ ሁሉም ሕፃናትና ወጣቶች እንዲማሩ ለማስቻልና ለማመቻቸት የሚያስችሉ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፣ በይነ-ዘርፋዊ ጥረቶች የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። ይህ ማለት መሠረታዊ መብቶችን፣ ለምሳሌ የውኃ እና የንጽሕና አጠባበቅ፣ የጤናማ ምግብ እና አመጋገብ፣ የማኅበራዊ ጥበቃ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ ደህንነትን በሚያበረታታ

በተረጋጋ እና ጤናማ ቤተሰብ እና ማኅበረሰብ ውስጥ የመኖር እና ከሁሉም የጥቃት ዓይነቶች ነጻ ሆኖ የመኖር መብቶችን ማረጋገጥ ነው።

ከ2000ዎቹ መጀመሪያ አንሥቶ፣ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት መብት ልዩ ራፖርተሮች ትምህርት የሕብረተሰቡን የጋራ ጥቅሞች የሚያስጠብቅ የጋራ ሀብት ነው ብለው ይጠሩታል። የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤትም በ2005 እና 2015 በትምህርት መብት ላይ ባወጣቸው ውሳኔዎቹ ትምህርትን በጋራ ሀብትነት ዐውቆታል። በ2015 የወጣው Education 2030: Incheon Declaration and Framework for Action በዓለም የትምህርት መድረክ የተሳተፉ ከ160 በላይ ሀገራት ተወካዮች ተቀብለውታል። ይህ ሰነድ ትምህርት "መሠረታዊ ሰብአዊ መብት እና ለሌሎች መብቶች መረጋገጥ መሠረት" መሆኑን በድጋሚ አረጋግጧል። እንዲሁም "ትምህርት መንግሥት ባለግዴታ የሆነበት የጋራ ሀብት" መሆኑን ከማስተጋባቱም በላይ፣ መንግሥት ደረጃዎችን እና ደንቦችን በማውጣት እና በማስፈጸም ረገድ ያለውን አስፈላጊነትም ይመለከታል።

መንግሥታት የትምህርት ሥነ ምህዳሮች ትምህርትን እንደ የጋራ ሀብት መያዛቸውን በማረጋገጥ ረገድ ቁልፍ ሚና አላቸው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ ሁሉንም የሚያስተባብር ርብርብ ያስፈልገናል። ትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም ማደስ በሁሉም ቦታ ያሉ የሁሉም የትምህርት ባለሙያዎች፣ የሁሉም ትምህርት ቤቶች፣ የሁሉም የትምህርት መርሐ ግብሮች ኃላፊነት ነው። ደግሞም በብዙ የዓለም አጋጣሚዎች፣ በርካታ የመንግሥት እና የመንግሥት ያልሆኑ ተዋናዮች በአንድነት የሕዝብ ትምህርትን ሕዝባዊነት እንደሚያረጋግጡ መታወስ አለበት።

መንግሥታት የትምህርት ሥርዓቶች የዜጎቻቸውን እና ሌሎች በእነሱ ጥበቃ ሥር የሚኖሩትን ሰዎች ፍላጎቶች ለማሟላት በቂ እና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘታቸውን የማረጋገጥ ቁልፍ ኃላፊነት አለባቸው። የግል ሀብት ግብር ለመሰወር ወደ ውጭ አገር እንዳይሻገር ይልቁንም ለጋራ ሀብት አስተዋጽኦ እንዲኖረው በሚያስችሉ ፍትሐዊ የግብር ፖሊሲዎች አማካይነት በቂ የመንግሥት ፋይናንስ ማሰባሰብ አለባቸው። መንግሥታት የጋራ የትምህርት መብትን ዕውን ለማድረግ እነዚህን ሀብቶች በፍትሐዊነት እና በብቃት ጥቅም ላይ ማዋል አለባቸው።

መንግሥታት የትምህርት ሥርዓቶች በቂ እና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘታቸውን የማረጋገጥ ቁልፍ ኃላፊነት አለባቸው።

መንግሥታት በአንድ ሥነ ምህዳር ውስጥ ያሉ ሁሉም አቅራቢዎች ሰብአዊ መብቶችን ማክበራቸውን እና ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጥራት ያለው የመማር ተመክሮ ማቅረባቸውን በማረጋገጥ፣ የትምህርት አቅርቦትን የመቆጣጠር ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ።

በመጨረሻም፣ መንግሥታት ትምህርት የዜጎቻቸውን እና ድንበሮቻቸው ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ሰዎችን ፍላጎቶች፣ በተለይም በታሪክ የተገፉ ወይም የተገለሉትን ሰዎች ፍላጎቶች እንደሚያሟላ ማረጋገጥ አለባቸው። የትምህርት ሥርዓቶች መልካም አስተዳደር ዜጎችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በውሳኔ ሰጪነት እና በውይይት ላይ ማሳተፍን ይጠይቃል፤ እንዲሁም በየደረጃው ግልጽነት እና ተጠያቂነት አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል።

ቀደምት ሕዝቦችን በተመለከተ፣ ተጨማሪ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የቀደምት ሕዝቦች መብት መግለጫ፣ ቀደምት ሕዝቦች በመንግሥት የተረጋገጡ በሁሉም ደረጃዎች ያሉ ሁሉንም ዓይነት ትምህርቶች የማግኘት መብት ከማግኘታቸው በተጨማሪ፣ "በራሳቸው ቋንቋዎች፣ ከባሕላዊ የማስተማርና የመማር ዘዴዎቻቸው ጋር በሚስማማ መልኩ የትምህርት ሥርዓቶቻቸውንና ተቋሞቻቸውን የመመሥረት እና የመቆጣጠር መብት" እንዳላቸው ገልጿል።

በዓለም ላይ የግዳጅ ፍልሰት እየጨመረ በመምጣቱ - በተለይ የአየር ንብረት ለውጥ ጫና ባስከተለው የሰዎች መፈናቀል - የመንግሥትን ጥበቃ ለማይደረግላቸው ስደተኞች ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። በእንደዚህ ዓይነት፣ እየተባባሱ እንደሚመጡ በሚጠበቁ ሁኔታዎች ውስጥ የመማር መብትን ለማረጋገጥ ዓለም አቀፍ አካላት እና የዓለም አቀፍ ትብብሮች መስፋፋት አስፈላጊ ናቸው።

## ዲጂታል የመማሪያ ቦታዎችን ማስተዳደር

በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ፣ ቴክኖሎጂ የትምህርትን ሕዝባዊነት፣ አካታችነት እና የጋራ ዓላማዎችን ሊደግፍ ይችላል። ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች የተመሠረቱባቸው በርካታ አመክንዮዎች አሉ፤ አንዳንዶቹ ትልቅ ነጻ የማውጣት አቅም ያላቸው፣ ሌሎች ደግሞ ትልልቅ ተፅእኖዎች እና አደጋዎች ያሏቸው ናቸው። በዚህ ረገድ "ዲጂታል አብዮት" እንደ ግብርና ወይም የኢንዱስትሪ አብዮት ካሉ ቀደምት ታላላቅ የቴክኖሎጂ አብዮቶች የተለየ አይደለም። ዋና ዋናዎቹ የጋራ ጥቅሞች የዕድል አለመመጣጠንን እና መገለልን በአሳሳቢ ደረጃ ጨምረው መጥተዋል። ፈተናው እነዚህን ድብልቅ ውጤቶች የመፈተሽ እና የወደፊት ውጤቶቻቸውን የመምራት ነው።

ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ከትምህርት እና ከዕውቀት ጋር የተያያዙ እንደመሆናቸው፣ ስለ እነሱ የሚሰጡ ቁልፍ ውሳኔዎች በሕዝባዊ ዐውድ መሰጠታቸውን እና ትምህርትን እንደ የጋራ ሀብት እና ጥቅም በሚያየው መርህ መመራታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ይህም፣ የዲጂታል መሠረተ ልማት አውታሮችን ግላዊ ቁጥጥር መቃወም እና በየጊዜው የትምህርተ ሥነ ምህዳር አካልነቱ እየጨመረ የመጣውን የዲጂታል የጋራ ዕውቀት ፀረ-ዴሞክራሲያዊ እገታ እና መዘጋት መከላከል እንዳለብን ያመለክታል።

ዲጂታል መድረኮች ባለፉት ጥቂት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ ለዕውቀት፣ ለትምህርት እና ለምርምር አንዳንድ አስተዋጽኦዎችን ቢያበረክቱም፣ ከዚህ የተገኙት ማኅበራዊ ጥቅሞች ግን በአብዛኛው የቴክ ኢንዱስትሪው ትክክለኛ፣ ማስታወቂያ የተጫናቸው የንግድ ሞዴሎች የአጋጣሚ ውጤቶች ናቸው። ለምሳሌ ጉግል/አልፋቤት ወደ ሕዝባዊ ዲጂታል ሕይወታችን ለመስረጽ ተደራሽነቱን ለማስፋት ሲጥር፣ በዲጂታሉ ሕዝባዊ ዐውድ ውስጥ በጣም ወሳኝ ከሆኑ አገናኞች አንዱ ሆኗል። እንደ ጉግል ስኮላር እና ጉግል ክላስሩም ያሉ አንዳንድ ለትምህርት በጣም ጠቃሚ የሆኑ አገልግሎቶቹ ምንም ዓይነት የማስታወቂያ ገቢ አያስገኙም፤ እንዲያውም ጉግል ይደግፋቸው ዘንድ ፍላጎት እስካሳደሩበት ድረስ ብዙ ወጪ ያስወጡታል። ይህም ትምህርት ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥገኛ እየሆነባቸው የመጡት የዲጂታል መሠረተ ልማት አውታሮች በጣም አስጊ ሁኔታ ውስጥ እንደሆኑ ያሳያል።

እጅግ በጣም ብዙ ሌሎች የጉግል አገልግሎቶች፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ቆይተው በመጨረሻ መዘጋታቸውን ስናስብ፣ አሁን ባለው አሠራር አላስተማማኝነት መጨነቃችን ትክክል ነው። በ2020 እና 2021 የኮቪድ ወረርሽኝ በርካታ ዩኒቨርስቲዎች ሲዘጉ፣ በፕላኔታችን ላይ ባሉ አንዳንድ ሀብታም እና በጣም ጥሩ ዩኒቨርቲዎች ውስጥ ያሉ ምሁራን እንኳን መሣሪያዎቻቸውን ማግኘት የቻሉት እንደ ጉግል ስኮላር ስላሉ አገልግሎቶቹ ጥቅሞች ጉግል ውስጣዊ ውሳኔ በማድረጉ ምክንያት ነው። ከኖረባቸው ብዙ ዓመታት አንጻር፣ ጉግል ስኮላር ጥቂት ለውጦች ተደረገበት እንጂ፣ እዚህ ግባ የሚባል አዳዲስ ተግባርም አልታከለበትም፤ ይህም ከኩባንያው አጠቃላይ አጀንዳዎች መሀል ዝቅተኛ ቅድሚያ እንደሚሰጠው ያሳያል። ይህ እንደዚህ ያሉ በግል የሚተዳደሩ የመማሪያ መሠረተ ልማቶች ያሉባቸውን አስጊ ሁኔታዎች በማሳየት፣ እንደ ማስጠንቀቂያ ሆኖ ሊያገለግለን እና ለወደፊት ሕዝባዊ ትምህርታችን አስተማማኝ የሕዝብ ዲጂታል መሠረተ ልማት የሚበጁ የበለጠ ዘላቂነት ያላቸው ሞዴሎች ስለመኖራቸው እንድንጠይቅ ያደርገናል።

የዲጂታል መድረኮች ለሕዝብ ከወጭ ነጻ ሆነው መቆየት የሚችሉት፣ በአብዛኛው "አዲሱ ነዳጅ ዘይት" እስኪባል ድረስ እንደ ሸቀጥ ከፍተኛ አትራፊነት ያለውን የግል የተጠቃሚ ውሂብ በብዛት እና ስልታዊ በሆነ መንገድ አውጥቶ መጠቀም እስከተቻለ ድረስ ነው። መጀመሪያ ላይ ይህ ውሂብ የተሰበሰበበት ግልጽ ዓላማ የማስታወቂያ ሽያጭ ነበር። በኋላ፣ ከዲጂታል አገልግሎቶች ጀርባ ያሉት መድረኮች ከዚህ ግዙፍ እና በየጊዜው እየሰፋ ከሚሄደው የተጠቃሚ ውሂብ የሚገኘው ጥቅም የንግድ አገልግሎቶችን እና ምርቶችን በመገንባት እና በማሻሻል ላይ ብቻ የሚወሰን እንዳልሆነ፤ ይልቁንም በሰው ሠራሽ አስተውሎት እና በማሽን መማር አማካይነት ሐሳቦችን፣ አስተያየቶችን እና ምርጫዎችን ለመገንባት እንደሚጠቅም ደርሰውበታል።

ይህም ለገበያ ድርሻ በሚደረገው ትግል አሸናፊ ለመሆን በሚጓጉ፣ በዓለም ትላላቅ ኩባንያዎች መካከል በሰው ሠራሽ አስተውሎት የበላይ የመሆን ፉክክር ፈጥሯል። በዚህ ምክንያት የዛሬው ዲጂታል ኢኮኖሚ የሚመራው ውሂብ መሰብሰቢያ ሴንሰሮች፣ ስልተ ቀመሮች እና ኔትወርኮች ከዚሕ በፊት በድርጅታዊም ይሁን በግላዊ ዓይኖች ወደማይደረስባቸው ሥፍራዎች እና የሕይወት ኪሶች - ከኤሌክትሮኒክ መጽሐፍ አንባቢዎች፣ እስከ የኢንተርኔት መፈለጊያ እና የስማርት ሰዓት ተጠቃሚዎች

ድረስ - መስፋፋታቸውን በሚፈቅደው ውሂብ አውጭ ፍላጎት ነው። በየቦታው እና በቋሚነት ክትትል በሚደረግበት ጊዜ ውስጥ እየኖርን ነው የሚለው የብዙዎች ስሜት ሰፋፊ ፖለቲካዊ መዘዞችን ያስከትላል። ሐሳብን በነጻነት በመግለጽ እና በሰዎች በራስ አእምሮ የመመራት ስሜት ላይ አስፈሪ ተጽዕኖ አለው። በክትትል ውስጥ ነኝ የሚሉ ጭንቀቶች በፈጠራ ተግባር ላይ በዓይን የማይታዩ ራስን ሳንሱር የማድረግ የክትትል እንቅፋቶችን ይፈጥራሉ፤ ይህም ስሜታዊ ወይም አደገኛ መጽሐፍ ማንበብ አሁን የመስመር ላይ ድርጊቶቻችን ቀጥተኛ ውጤት እየሆነ የመጣው ዝና ላይ ከባድ ተጽዕኖ ይኖረው ይሆን ወይ ወደሚል ተጨማሪ ጭንቀት ያመራል።

ክትትል እና ውሂብ አውጭነት ወደ ትምህርታችን ሥነ ምህዳር ሲዘረጋ፣ ተመሳሳይ ተጽዕኖዎች እና ጭንቀቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። የክትትሉ እንደመደበኛ እየተቆጠረ መምጣት - በተለይም የትምህርት ሥርዓቶች ሕፃናትን ከልጅነታቸው ጀምሮ በዚያ የሚያለማምዱ ከሆነ - የሰው ልጅን ክብር ፅንሰ ሐሳብ ወደ መሸርሸር እና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ የተቀመጠውን የግላዊነት እና ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ ሰብአዊ መብትን በሰፊው ወደመጣስ ሥር ነቀል ማሽቆልቆል ይመራናል።

የተማሪ እና የመምህር ውሂብ ጥበቃ ስጋት በትምህርት ሥነ ምህዳር ውስጥ ዲጂታል መድረኮች ስላላቸው ቦታ በሚነሣባቸው በማንኛቸውም ውይይቶች ውስጥ መንጸባረቅ አለበት። በዲጂታል ቦታዎች ላይ ውሂብ ቀርጾ ማስቀረት፣ ማከማቸት እና ክትትል መማር ማስተማርን ለማሻሻል ይረዳል። ተማሪዎችን እና መምህራንን መጠቀሚያ እንዳይሆኑ ለመከላከል ትክክለኛ ደንቦች እና ሥነ ሥርዓቶች ያስፈልጋሉ። የግልጽነት ሥነ ምግባር የውሂብ ፖሊሲዎችን መምራት አለበት፤ ነባሪው መቼት ሁልጊዜም ግለሰቦች እንዳይጎዱ የውሁቡን ባለቤት ማንነት መደበቅ ነው።

የዲጂታል መድረኮች እና ሥልተ ቀመራዊ የዕውቀት መሰብሰቢያና ማሰራጫ ዘዴያቸው የትምህርት ሥነ ምህዳርን ጨምሮ በብዙ ጎራዎች ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱበት አንዱ ምክንያት በፍጥነት እያደገ ያለውን ዓለም አቀፍ ዕውቀት ስልታዊ በሆነ መንገድ ለማደራጀት እና ለመጠበቅ ተግዳሮት የተሰጠ ተግባራዊ ሕዝባዊ ምላሽ ካለመገኘቱ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ምክንያት፣ ባለሙያዎች እንኳን አሁን በዲጂታል መድረኮች አገናኝ አገልግሎቶች ላይ ለመተማመን በመገደዳቸው፣ ይህም ብቁ እና በመረጃ የተደገፈ አስተያየታቸውን የሚታተሙበትን መድረክ በሚመራው የዓቃቤ ውሂብ ሥልተ ቀመር ፍላጎት ታግቷል። በአሁኑ ጊዜ በብዙ ቦታዎች ለምናያቸው እንደ "ሐሰተኛ ዜና" ላሉ ችግሮች እና በሳይንስ እና በሕዝብ ተቋማት ላይ ላለው የእምነት ቀውስ ዘላቂ መፍትሄዎችን ለማፈላለግ በመረጃ የተደገፈ፣ በዕውነት እና በዕውቀት የሚመራ የጋራ ተሳትፎን እና የዕውቀት ጥበቃን ዲሞክራሲያዊ ማድረግን ይጠይቃል።

ዲጂታል ነውጡን ትምህርትን በጋራ ጥቅምነት ወደሚደግፍበት አቅጣጫ ለመምራት፣ የተሻለው ስትራቴጂ የዴሞክራሲያዊነት ሂደቱን በጠንካራ ሕዝባዊ ዐውድ ውስጥ ማረጋገጥ ነው።

እነዚህ ብዙ ምሳሌዎች የትምህርት ዲጂታል መሠረተ ልማቶችን ደካማነት አጉልተው ያሳያሉ። የተሻሉ የዲጂታል መሳሪያዎች መፈጠራቸው የሚቻል እና የግድ ቢሆንም፣ ዲጂታል ነውጡን ትምህርትን በጋራ ጥቅምነት ወደሚደግፍበት አቅጣጫ ለመምራት፣ የተሻለው ስትራቴጂ የዴሞክራሲያዊነት ሂደቱን በጠንካራ ሕዝባዊ ዐውድ ውስጥ ማረጋገጥ ነው። ብዙ ዲጂታል ማኅበረሰቦች እና ቀደምት የኢንተርኔት ቴክኖሎጂዎች የተገነቡት በነጻ የኮድ ምንጭ እና በትብብር ጥረቶች ነው። ትምህርትን እንደ ትርፋማ መድረክ ሳይሆን፣ በዘላቂ፣ ፍትሐዊ እና ሰላማዊ ወደፊቶች ላይ ኢንቨስት እንደሚደረግበት ሥፍራ መታየቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል በዘላቂነት፣ በፍትሐዊነት እና በአካታችነት የተቃኙ የትምህርት ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ቀጣይነት ያለው ዕድገት የመንግሥታትን እርምጃ፣ የሲቪል ማኅበረሰብን ድጋፍ እና ሰፊ የሕዝብ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል።

## ከሕያው ፕላኔት ጋር መማር

ሰውን ካማከሉ ሥፍራዎች እና ተቋማት ውጭ ትምህርት ሊካሄድባቸው ስለሚችሉ ሥፍራዎች ያለንን አስተሳሰብ ማስፋት አለብን፤ በዚህም ለምሳሌ መናፈሻዎች፣ የከተማ መንገዶች፣ የገጠር መንገዶች፣ የአትክልት ስፍራዎች፣ ዱሮች፣ እርሻዎች፣ ደኖች፣ በረሃዎች፣ ሀይቆች፣ ረግረጋማ ቦታዎች፣ ውቅያኖሶች እና ሌሎች የልእለ ሰብ ሕይወት ሥፍራዎች ሁሉ ሊካተቱ ይችላሉ።

የሰው ልጆች የሕያው ፕላኔት ምድር አካል ናቸው። ብዙ የቆዩ የአገር በቀል ባሕሎች ሰዎች እና ሰው ያልሆኑ ሕያዋን በጋራ ተጠቃሚ የሚያደርጓቸውን ግንኙነቶች ስለሚመሠርቱባቸው ሁኔታዎች እየደየአግባቡ የተስፋፋ ሰፊ አተያይ አላቸው። ባዮስፌር ወሳኝ የመማሪያ ቦታ ነው። ዛሬ በቀደምት ሕዝቦች የሚተዳደሩ መሬቶች በግምት 80% የሚሆነው የዓለም ብዝኃ ሕይወት መገኛ መሆናቸው ራሱ፣ አገር በቀል አተያዮች ለፕላኔቷ ስለሚጨነቅ ትምህርት ሁሉንም ሰው የሚያስተምሩት ብዙ ነገር እንዳላቸው በቂ ማሳያ ነው።

አገር በቀል መሬት-ምሥርት እና ውኃ-ምሥርት ዕውቀቶች እና አስተምህሮዎች፣ እንዲሁም በርካታ የአፍሪካ እና የእስያ ሥነ ሕዋዎች፣ ሰው ያልሆኑትን የራሳቸው መብቶች እንዳሏቸው ሕያዋን ብቻ ሳይሆን፣ የሰው ልጆች ከእነሱ ጋር ባላቸው ግንኙነት ሊማሩባቸው እንደሚችሉ ሊቃውንት እና መምህራን የሚገነዘቡበት መስተጋብር አላቸው። በአንዳንድ ትውፊቶች ውስጥ የልዕለ ሰብ ዓለም አባላት በዕድሜ የገፉ፣ ጥበበኞች እና ክብር የሚገባቸው እንደሆኑ ግንዛቤ አለ፤ ብዙ ሊያስተምሩን እንደሚችሉም ይታወቃል።

በምዕራባውያን የትምህርት ትውፊቶችም ውስጥ ከእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ አንዳንዶቹን የመፍታት ረጅም ታሪክ አለ። የቦታ ተኮር፣ አካባቢያዊ፣ የመስክ እና ተመክሯዊ የትምህርት መስኮች ተፈጥሮን እና አካባቢን በመማር ሂደቶች ውስጥ ተሳታፊ ሆነው እንዲገኙ ለማድረግ ሞክረዋል። ቢሆንም፣ እንዲህ ያለው ሥራ ብዙ ጊዜ አካባቢን የተማሪን መማር ለማገዝ አገልግሎት ላይ እንደሚውል አድርጎ ነው የሚቆጥረው። ተማሪዎች በእነዚህ አጋጣሚዎች የሚማሯቸው ጠቃሚ ነገሮች፣ በሌላ መንገድ የማያገኟቸው እንደሆኑ ብዙ ጊዜ ይነገራል። እንዲያውም በብዙ አጋጣሚዎች፣ የሰው እና ተፈጥሮ ግንኙነት በመጠቃቀም እና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ አይታሰብም። እንዲሁም፣ ሰው ያልሆኑ የህዋው አባላትን የራሳቸው አቅም እንዳላቸው፣ እንደ አስተማሪዎች አንረዳቸውም። በጣም የቅርብ ጊዜዎቹ የአካባቢ እና ቦታ ተኮር የትምህርት ዓይነቶች ከዚህ አቋም ራሳቸውን እየለዩ ነው። ከአካባቢ ጥበቃ እና መልሶ ማቋቋም የተወሰደው ትምህርትን እንደ “ተፈጥሮን መመለሻ” የመቁጠር ዘይቤ፣ በተለይም ትምህርትን በአዳዲስ መንገዶች ከመገንባት ሐሳብ ጋር በተያያዘ ተስፋ ሰጭ ነው።

በዓለም ላይ ባሉ በርካታ የዕውቀት ሥርዓቶች እና የሕዋ ምርምሮች መካከል በውይይት እየታዩ ያሉ አብዛኛዎቹ ሥነ ትምህርታዊ ሁነቶችም በተመሳሳይ፣ የትምህርት እና የሕያው ፕላኔት ግንኙነት የመነጣጠል ሳይሆን ከዓለም ጋር አብሮ በማደግ እና አብሮ በመለወጥ ዐይን የሚታይባቸው ዕድሎች ስለመኖራቸው ተስፋ እየሰጡ ነው። የሰው ልጆች ራሳቸውን እንደ ማኅበራዊ ሕያዋን ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ሥነ ምህዳራዊ ሕያዋን መረዳት አለባቸው። ተፈጥሮን “ተንከባካቢ” እና “ጠባቂዎች” አድርጎ የሚያሳዩን የአካባቢ ጥበቃ መርሆዎች፣ አሁንም በሰዎች እና በአካባቢያቸው መካከል ክፍፍል እንዳለ ይገምታሉ። ሥነ ምህዳራዊ ምናቦቻችን ሥፍራችን ሙሉ በሙሉ በሕያው ፕላኔት ውስጥ መሆኑን መቀበል አለባቸው።

የሰው ልጆች ያስከተሏቸው የሥነ ምህዳር ቀውሶች የጋራ ዓላማ ላይ ያተኮረ ትምህርት መሠረት ስለሆነው ተማሪ እንደገና ማሰብን ይጠይቃሉ። ትምህርት እርስበርሱ የተሣሠረ ዓለም ውስጥ ቀሎት እና ተመችቶት የሚመላሰውን ተምኔታዊ ሉላዊ ተማሪ - በሰው ልማት ላይ ብቻ በሚያተኩር ትምህርት ውስጥ በተለምዶ “የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ተማሪ” ተብሎ የሚጠራውን - ብቻ ዒላማ ማድረግ አይችልም። ትምህርት ፍትሐዊ እና ዘላቂ ነገን እንዲደግፍ ምድር አቀፍ ንቃተ ህሊናን ማበረታታት አለብን። ከሌሎች የምድር አባላት ጋር ዓለምን ለመሥራት ኃላፊነት የሚወስድ ተማሪ፣ የትምህርት ማጠንጠኛ መሆን አለበት። ይህ አተያይ በትምህርት ተግባር ላይ በሁሉም መስኮች ሊባል በሚችል ደረጃ፣ አንድምታ አለው። በተለይ የዓለም አቀፍ ዜግነት ትምህርት ከዚህ የምድር አቀፍ ንቃተ ህሊና ጋር በደንብ መጣጣም አለበት።

ከሕያው ፕላኔት ጋር ያለንን ግንኙነት እንደገና ማመጣጠን የመደጋገፍ ግንኙነታችንን እንደገና መማር እና የሰውን ቦታ እና አቅም እንደገና ማጤንን ይጠይቃል። ብዙ ባሕሎች የሰውን ልጅ ከተቀረው የፕላኔቷ አባል መለየት እንደማንችል ለምዕተ

ዓመታት ወይም ለሺሕ ዓመታት ያውቃሉ። ለምሳሌ፣ የኬቹዋ "ሱማክ ካውሳይ" ፅንሰ ሐሳብ ለተፈጥሮ መብቶችን የሚሰጥ እና ሥነ ምህዳራዊ ሚዛናዊ የአኗኗር ዘይቤን የሚገልጽ ነው። የእንጉኒ ባንቱው ፍልስፍና የኡቡንቱ ተዛምዷዊ መርሆዎች (እኔን የሆንኩት በእኛ ምክንያት ነው) የቡዲስቱን የካሩና (ርህራሄ) ሥነ ምግባር ያህል ብዙ ይነገረናል፤ እነዚህ የሰው ልጅ መሠረት ሊያደርጋቸው ከሚገቡ የዳበሩ የባሕል ሀብቶቹ ሁለት ምሳሌዎችን ብቻ ናቸው።

ሌሎች ማኅበረሰቦች አሁንም፣ አንዳንዴም በጣም በስቃይ፣ የጋራ ሰዋዊ እና ፕላኔታዊ ተደጋፊነታችንን ለመረዳት እየታገሉ ነው። በ2050 የምድር አካል ሆነን በስምምነት፣ በደህንነት እና በፍትሕ መርሆዎች እንዴት እንኖራለን? በዓለም አቀፍ ደረጃ እስካሁን ሁሉም መልሶች የሉንም። በሕይወት ምልዑነት ላይ የተመሠረተ ትምህርት፣ መፍትሄዎችን በጋራ ለመፈለግ አንዱ ቁልፍ መሳሪያችን መሆን አለበት።

# የትምህርትን "መቼ" ማስፋፋት

ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ ሰዎች ረጅም እና ጤናማ ሕይወት ሲኖሩ፣ ትምህርት ከሕይወት ጋር የተቆራኘበት መንገድም ይለወጣል። በወጣቶች እና በአረጋውያን ቁጥር መሀል፣ በሥራ ዕድሜ ላይ ባሉ ሰዎች ምጥጥን፣ እንዲሁም በሚሰጡ እንክብካቤዎች እና የእንክብካቤ ሥራ ዓይነቶች (በክፍያ እና ያለ ክፍያ)፣ በሰጪዎቹ እና በመስጫ ጊዜው ቅይይር ሲኖር የትምህርት ፍላጎቶች፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች እና ዘዴዎቹም ይለወጣሉ። እንደውም፣ እነዚህ ጉዳዮች ማኅበረሰቦቻችን ስለ እሴት ማፍራት ምንነት ያሏቸውን መሠረታዊ ግምቶች ጥርት አድርገው ያሳዩናል።

## የዕድሜ ልክ ትምህርት እና እንክብካቤ

ደህንነታችን እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገታችን ከመደበኛው ኢኮኖሚ ብቻ እንዳልመጣ በደንብ እየታወቀ ነው። የሚከፈልበት ሥራ አንዱ አካል ነው፤ ነገር ግን በቤተሰብ ውስጥ ለሰዎች እንክብካቤን በመስጠት የሚከናወነው ሥራ በእርግጠኝነት አስፈላጊነቱ ከዚህ ያነሰ አይደለም። ይህም ልጆችን እና አረጋውያንን የመንከባከብን፣ ምግብ የማምረት እና ማዘጋጀትን፣ መጠለያ የመገንባትን እና በብዙ የሥነ ምህዳር ጫና ባለባቸው አካባቢዎች ውኃ የመሰብሰብን ልፋት ይጨምራል። ቤተሰቦችን፣ ማኅበረሰቦችን፣ ጤናን፣ የምግብ ዋስትናን፣ የአካባቢን እና የሥነ ምህዳርን ጤናን ከመደገፍ አንጻር ሴቶች እና ልጃገረዶች ትልቁን ሸክም ይሸከማሉ፤ እና ለዚህ ግዙፍ እና ወሳኝ አስተዋጽኦዋቸው ግን የሚያገኙት ዕውቅና ወይም ድጋፍ አነስተኛ ነው።

በሚቀጥሉት 30 ዓመታት ውስጥ የሚኖሩ ውስብስብ መስተጋብሮች በእነዚህ ሁሉ የ"ማቅረብ" ተግባራት መሀል ያለውን ሚዛን እንደየክፍለ ዓለሙ እና እንደየአገሩ ሁኔታ በተለዩ መንገዶች እንደገና ይቀርጹታል። በአንዳንድ አካባቢዎች የጤናን እና/ወይም የጉልበትን እጥረት ማሻሻል አረጋውያን በሥራ ኃይልነት ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆዩ ዕድሎችን እና ፍላጎቶችን ሊፈጥር ይችላል። በሌሎች አጋጣሚዎች፣ የአረጋውያን እንክብካቤ ተግዳሮቶች ባለፉት ሦስት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ ሴቶች የሠራተኛውን ኃይል በመቀላቀላቸው የሕፃናት እንክብካቤ ካጋጠሙት ተግዳሮቶች ጋር ሊመሳሰሉ ይችላሉ። የትብብር ኑሮ እና ተራዛሚ የቤተሰብ ድጋፍ በብዙ የዓለም ክፍሎች ፋይዳቸው እየጎላ ከመጣ፣ አዳዲስ የቤተሰብ ቅርጾች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ይህ ሁሉ የሚነግረን፣ የሰዎች ዘላቂ እና ጠንካራ የመተሳሰብ ግንኙነቶችን የመገንባት እና የመቅረጽ አቅም በሁሉም ዕድሜ ላሉ ተማሪዎች ትምህርታዊ ጉዳይ መሆኑን ነው።

መንከባከብን መማር እና እንክብካቤን ከሕይወት ጋር የተቆራኘ የትምህርት ባሕርይ ማድረግ፣ እንደዋዛ "ቢኖረን ጥሩ ነው" የሚባል ባሕርይ አይደለም። ወደ 2050 እና ከዚያም ባሻገር ስናማትር፣ ይህን በተመለከተ አስቸጋሪ አመክንዮ ያጋጥመናል። ምግብን የማዘጋጀት እና አንዳንዴም የማብቀል የዕለት ተዕለት ሥራን የሚደግፍ ትምህርት፣ እና አካል እና ቤተሰብን መንከባከብ እና በሕይወት ማቆየትን የሚደግፍ ትምህርት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ይህ ስለ ትምህርት ከሕይወት ጋር የተቆራኘ ስለመሆኑን እና በተለያዩ ቦታዎች እና ጊዜያት ስለመካሄዱ ያለን ጠንካራ ግንዛቤ ወደሚያመራን ወደዚህ ሰፊ የመማር አተያይ ነው።

## የጎልማሶች መማር እና ትምህርት እንደ ነጻ አውጪ ፕሮጀክት

ከቅርብ ዐሥርት ዓመታት ወዲህ፣ የዕድሜ ልክ ትምህርት መርህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የትምህርት ፖሊሲዎችን በማዘጋጀት ረገድ ማዕከላዊ ጉዳይ ሆኗል። ለምሳሌ፣ የዘላቂ ልማት ግብ 4፣ "አካታች እና ፍትሐዊ ጥራት ያለው ትምህርት እንድናረጋግጥ እና ለሁሉም የዕድሜ ልክ የመማር ዕድሎችን እንድናበረታታ" ጥሪ አቅርቦልናል።

ለግለሰቦች በሚሰጠው አቅም እና በሰፊውም የዜጎች ተሳትፎ ላይ ባሳደረው ተጽዕኖ የሚገለጽ ጠንካራ ነጻ አውጪ የጎልማሶች የመማር እና የትምህርት ባሕል አለ። ይህ ባሕል ግን፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዕድሜ ልክ ትምህርት የሙያ እና ክህሎት ገጽታዎች ላይ ከመጠን በላይ እንዲያተኩር በመደረጉ ተዳክሟል። በመሠረቱ፣ የጎልማሶች በተለይም በሕይወታቸው ውስጥ፣ በልጅነታቸው ሙሉ የትምህርት ዕድል ያልነበራቸው ጎልማሶች በጣም አስፈላጊ "ሙብቶች" አንዱ የነበረው ትምህርት - ሰዎች ከወቅቱ ጋር እንዲራመዱ እና የመቀጠር አቅም ይዘው እንዲገኙ ስለሚገደዱ ለብዙዎች "ግዴታ" ሆኗል። ውጤቱም ክህሎት የመማር እና እንደገና ሌላ ክህሎት የመማርን ቋሚ አመክንዮ ሆኗል።

የጎልማሶች መማር እና ትምህርት ከአንድ ትውልድ በኋላ በጣም የተለዩ መምሰል አለባቸው። ኢኮኖሚዎቻችን እና ማኅበረሰቦቻችን ሲቀየሩ፣ የጎልማሶች ትምህርት ለሥራ ገበያ ዓላማ ሲባል የዕድሜ ልክ ትምህርትን ከማካሄድ ባለፈ መስፋፋት ይኖርበታል። የሙያ ለውጥ እና የክህሎት ለውጥ ዕድሎች ልዩ ልዩ፣ ተለዋዋጭ መንገዶችን ለመፍጠር አስፈላጊነት ትኩረት ከሚሰጡ፣ ከሁሉም የትምህርት ሥርዓቶች ሰፋፊ ማሻሻያዎች ጋር መተሳሰር አለባቸው። በሁሉም ዘርፍ እንዳለው ትምህርት፣ የጎልማሶች ትምህርት አፀፋዊ ወይም ተላማጅ (ከሥራ ገበያ፣ ከቴክኖሎጂ፣ ወይም ከአካባቢ ለውጥ አንጻር) ሳይሆን፤ የምር ለዋጭ ትምህርት እንዲሆን እንደገና ሊጤን ይገባል።

> *የጎልማሶች ትምህርት ለሥራ ገበያ ዓላማ ሲባል የዕድሜ ልክ ትምህርትን ከማካሄድ ባለፈ መስፋፋት ይኖርበታል።*

ወደ 2050 እና ከዚያ ባሻገር ወዳለው አድማስ ስናማትር፣ በጎልማሶች ትምህርት ላይ ጥልቅ ለውጦች እንደሚመጡ መገመት እንችላለን። አንዳንዶች በቅርቡ የሰው ልጅ የዕድሜ ጣራ በመደበኛነት ከ100 ዓመት ሊበልጥ እንደሚችል ይተነብያሉ። የሰው ልጅ ረጅም ዕድሜ የመኖርን ሥር ነቀል መራዘም ወደጎን ትተን፣ እስካሁንም ብዙዎች ረጅም ዕድሜ መኖራቸውን ብናይ፣ ትምህርት መቼ መከናወን አለበት የሚለውን እንደገና ማሰብ መቀጠል እንደሚገባ ያሳየናል። በአንዳንድ አካባቢዎች በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ፣ አራት ትውልዶች በአንድ ቦታ እና ጊዜ አብረው ይኖራሉ። ስለ ጉልምስና እና ስለ ብስለት የተያዙ ባሕላዊ እሳቤዎች ይፈተሻሉ። የተለመዱ የአኗኗር ዘይቤዎች እና ከሥራ እና ከመዝናኛ ጋር ያሉን ግንኙነቶች ይቀየራሉ። ቀድሞውኑም፣ በአንድ ግለሰብ የሥራ ዘመን ውስጥ ሥራዎች እና የሥራ ተፈጥሮ በከፍተኛ ሁኔታ ሊለወጡ እንደሚችሉ የታወቀ ነው። የሲቪክ እና የፖለቲካ ሕይወት በአንድ የሕይወት ዘመን ይለወጣሉ፤ ይህም ምናልባት ወደፊት እየጨመረ ሊሄድ ይችላል። በዚህ ሪፖርት ውስጥ ጥሪ የቀረበባቸው አዲሶቹ የሥነ ምህዳር ንቃተ ህሊናዎች እና ዳግም የተቃኘው ሰብአዊነት፣ ዕድሜ ሳይለይ፣ በሁሉም ዕድሜ ያሉ ተማሪዎች ሊያልፉባቸው የሚገቡ የአዳዲስ ትምህርታዊ ጉዳዮች ምሳሌዎች ናቸው። ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እየገፋ ሲሄድ፣ የትምህርት ፖሊሲዎች ትኩረታቸውን ወደ ሙሉ ሕይወት መቀየር እና ለጎልማሶችና ለአረጋውያን ልዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል።

የሕይወት ዘመን ትምህርት ምርጥ ባሕል አካል የሆነው ሁለተኛው አቅጣጫ ብዙ ጊዜ ከትምህርት ዕድሎች የሚገለሉ ተጋላጭ ቡድኖችን የማሳተፍ እና የማካተት ሐሳብን ይመለከታል። ተሳትፎ እና ማካተት ለኢመደበኛ መማር - ከመደበኛ የትምህርት ቤት ዐውዶች ውጭ ለተገኙ ዕውቀት እና ችሎታዎች - ትኩረት ከሚሰጠው ከጎልማሶች ትምህርት ነጻ አውጪ ርእዮች ጋር ይስማማሉ። የጎልማሶች ትምህርት ፖሊሲ ኢመደበኛ የዕድሜ ልክ ትምህርትን ለማካተት እና ማሳተፍ ቅድሚያ የመስጠት አካል አድርጎ ማወቅ አለበት።

በመጨረሻም፣ በጎልማሶች ትምህርት ላይ የተሰማሩ ሰዎች ዲጂታል መንገዶች በተሳትፎው ማመቻቸት እና ማስቻያነት ሚናቸው እየጨመረ መምጣቱን ከግምት ማስገባት አለባቸው። ወጣት ትውልዶች ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ለዲጂታል ዓለም

ተጋላጭነት ቢኖራቸውም፣ ጎልማሶቹም ትውልዶች ዕውቀትን ለማዳበር እና ለመገንባት እነዚህ መሳሪያዎች ያስፈልጓቸዋል። የጎልማሶች ትምህርት የዲጂታል ሚዲያን ሰፊ ተደራሽነት ማሳደግ እና የክፍት ተደራሽነት እና የክፍት ምንጭ እንቅስቃሴ አጀንዳዎችን በጥብቅ መደገፍ አለበት። ሳይንሳዊ ዕውቀትን ማጠናከር እና ሁሉንም መረጃ ማዛባቶች መዋጋት የማንኛውም የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ የአሁን እና የወደፊት ዋነኛ ነገሮች ናቸው።

የጎልማሶች መማር እና ትምህርት ዘርፈ ብዙ ሚናዎችን ይጫወታል። ሰዎች በተለያዩ ችግሮች ውስጥ መንገዳቸውን እንዲያገኙ ከማገዙ ሌላ፣ ችሎታዎቻቸው እና የማድረግ ብቃቶቻቸው እንዲጨምር ይረዳል። ሰዎች ለወደፊት ሕይወታቸው የበለጠ ኃላፊነት እንዲወስዱ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም፣ ጎልማሶች በአተያይ እና በሥልጣን ግንኙነቶች ላይ የሚከሰቱ ለውጦችን እንዲረዱ እና እንዲተቹ፣ እንዲሁም ፍትሐዊ እና ቀጣይነት ያለው ዓለምን ለመቅረጽ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ያግዛል። የወደፊቱ ቅኝት የጎልማሶች ትምህርትን፣ በማንኛውም ጊዜ እንደሚገኝ ትምህርት የመቁጠሩን ያህል፣ ከሕይወት ጋር የተቆራኘ ትምህርት አድርጎ ሊበይነውም ይገባል። ጎልማሶች ለሚኖሩበት ዓለም እና ለወደፊቱም ዓለም ተጠያቂዎች ናቸው። የወደፊቱ ኃላፊነት በቀላሉ ለቀጣዩ ትውልድ ሊተላለፍ አይችልም። የበይነ-ትውልዳዊ አጋርነት የጋራ ሥነ ምግባር ያስፈልጋል።

# የትምህርት መብትን ማስፋት

ከፊትለፊታችን ከተደቀኑት ከባድ ተግዳሮቶች አንጻር፣ በተለያዩ ጊዜያት እና ቦታዎች ትምህርትን በአግባቡ ለማስተዳደር ከላይ የተጠቀሱትን ምክረ ሐሳቦች ወደፊት ማራመድ በመምህራን፣ በመንግሥታት እና በሲቪል ማኅበረሰቡ ዘንድ አንገብጋቢ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። እዚህ የቀረበው የማይደረስበት ተምኔታዊ ሞዴል ሳይሆን፣ የሰው ዘርን ማትረፊያ ተጨባጭ ስትራቴጂ ነው። ትምህርት፣ የመማር መሠረታዊ አካል ወደ ሆነው እኛን ከጥልቅ የሕይወት ትርጉም እና ደስታ ጋር ወደማገናኘት ተግባሩ መጠራት አለበት።

ይህ ሪፖርት ትምህርትን በምልዐተ ሕይወት ውስጥ ማሰብ እንደሚያስፈልግ ያረጋግጣል። ምንም ያህል አስፈላጊ ቢሆንም፣ እንደ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርስቲዎች ባሉ ተቋማት የሚካሄድ ትምህርት እንደ ብቸኛ ቅርጽ መታየት የለበትም። የትምህርት ልህቀቱ የአቻ እና የበይነ-ትውልዳዊ እንዲሁም የበይነ-ባሕላዊ ትምህርትን ዋጋ የሚቀበል የጋራ ሂደት መሆኑ ነው። ይህ ማኅበራዊ አቅጣጫ እርስበርስ ለመተሳሰብ፣ ለማኅበረሰባችን እና ለፕላኔታችን ማሰብን ለመማር ጉልሕ ሥፍራ ይሰጣል። እነዚህ የጋራ ሂደቶች እና ማኅበራዊ አቅጣጫዎች በትምህርት ቤቶች እና በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ መኖር ቢኖርባቸውም፣ እዚያ ብቻ መገደብ ግን የለባቸውም።

ወደ 2050 ስናማትር፣ የትምህርት መብት መቼ እና የት መተግበር አለበት የሚለውን ሐሳብ በተለመዱት ግንዛቤዎች ያለመገደብ ወሳኝነት በጣም እየጨመረ ይመጣል። የመማር መብት ለሕፃናት እና ለወጣቶች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሰዎች በግልፅ መተግበር አለበት። በመማሪያ ክፍሎች እና በትምህርት ቤቶች ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ሥፍራዎች የሚካሄደውንም ትምህርት በበለጠ ግልጽነት ማካተት ይኖርበታል።

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ትምህርት ቤት በተዘጋበት ወቅት ሬዲዮ እና ቴሌቭዥን የተማሪዎችን የአካዳሚክ ትምህርት ለመደገፍ ጥቅም ላይ መዋላቸው፣ እነዚህ ሚዲያዎች ለትምህርት፣ ለባሕል እና ለጠቅላላ ዕውቀት ያላቸውን ጠቀሜታ ያስታውሰናል። በተለይም የትምህርት መርጃዎችን ከኢንተርኔት እና ስማርት መሳሪያዎችን ከማያገኙ ተማሪዎች አንጻር ሚናቸው የጎላ ነበር። የኮቪድ-19 ቀውስ የዲጂታል ትስስር እና የመስመር ላይ መድረኮችን ትልቅ ጠቀሜታ አሳይቷል። መሠረታዊ መብት የሆነውን መረጃን የማግኘት መብትን ከዐሥር ዓመት በፊት እንኳን ባልተገመቱ መንገዶች ከትምህርት መብት ጋር አያይዘን መልሰን እንድናስበው ጭምር አድርጎናል።

የመማር መብት መረጃ በማግኘት መብት እና በባሕል መብት ይደገፋል (እና በተራውም ይደግፋቸዋል)። የአመለካከትና የሐሳብ ነጻነትን በአግባቡ መጠበቅ የሚቻለው ሰዎች መረጃና ሐሳብ የማግኘት፣ የመቀበልና የማስተላለፍ አቅም ሲኖራቸው ነው። በሐሰተኛ እና አሳሳች ዜናዎች በተሞሉ ሚዲያዎች በተሞላው በዛሬው ዓለማችን፣ ትምህርት የሰዎችን ትክክለኛ መረጃ

*ትምህርት ማንነቶችን የሚቀርጹ እና ርዕዮተ ዓለሞችን የሚያሰፉ የባሕል ሀብቶችን ተደራሽ በማድረግ በባሕላዊ ሕይወት ውስጥ የመሳተፍ መብትን ይደግፋል።*

ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት በመደገፍ እና ሳያዘቡ በታማኝነት ለማስተላለፍ ያላቸውን ፍላጎት ዕውን እንዲያደርጉ ለማስቻል ወሳኝ ሚና አለው። ትምህርት ማንነቶችን የሚቀርጹ እና ርዕዮተ ዓለሞችን የሚያሰፉ የባሕል ሀብቶችን ተደራሽ በማድረግ በባሕላዊ ሕይወት ውስጥ የመሳተፍ መብትን ይደግፋል። እንዲሁም፣ ትምህርት ሰዎች ለባሕላዊ ሀብቶች አስተዋፅኦ የሚያደርጉባቸውን ችሎታዎች ሊደግፍ ይችላል። በባሕሎች መካከል የሚደረግ ግልጽ እና ጎንዮሻዊ ውይይት የባሕል ብዝሃነትን ለመደገፍ ወሳኝ ነው። ትምህርት የባሕል ብዝሃነትን ለማበረታታት ከሚያበረክታቸው በርካታ አስተዋጽኦዎች አንዱ የሆነውን ውይይትን በአርአያነት ማሳየት አለበት።

የመማር መብት ግንዛቤን ወደ የተለያዩ ጊዜያት እና ቦታዎች ማስፋፋት፣ ትምህርትን በእኛ፣ ለእኛ እንደተሠራ፣ እንደሚመራ እና እንደሚካሄድ የጋራ ጥረት ያጠናክራል። ትምህርት እንደ የጋራ ጥቅምነቱ -በጋራ የተሳካ እና የተመረጠ የጋራ ዕድገትነቱ - ከዕለት ተዕለት ሕይወታችን ጋር በቅርበት መተሳሰር አለበት። ልጆች እና አዋቂዎች በትምህርት ተመክሮ ውስጥ እንደ ባለድርሻዎች እንጂ እንደ ደንበኛ ወይም እንደ ተመልካች ሊያልፉ አይገባም። በሕይወታችን በተለያዩ ጊዜያት እና በተለያዩ የሕይወት ዘርፎች በትምህርት ውስጥ የተለያዩ ሚናዎችን እንጫወታለን፤ የትምህርት አካልም እንሆናለን። ሁሉም ሰዎች በየሕይወታቸው የሚያስቡትን፣ የሚያውቁትን፣ የሚሰማቸውን እና የሚያደርጉትን የሚያጠናክር እና ሁላችንም በጋራ የምናደርገውን የሚያጠናክር ትምህርት አካል የመሆን መብት አላቸው።

# የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች

ይህ ምዕራፍ በአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ውስጥ በዕድሜ ልክ እና በተለያዩ ባሕላዊ እና ማኅበራዊ ቦታዎች ውስጥ የሚካሄዱትን የትምህርት ዕድሎች ማካተት እና ማስፋፋት እንዳለብን ምክረ ሐሳብ አቅርቧል። ወደ 2050 ስናማትር፣ ይህንን ምክረ ሐሳብ ወደፊት ለማራመድ የሚያስፈልገውን ውይይት እና ድርጊት ለመምራት የሚያግዙ አራት መርሆዎች አሉ፦

- **ሰዎች በማንኛውም የሕይወት ዘመን ትርጉም ያላቸው፣ ጥራታቸው የተጠበቀ የትምህርት ዕድሎች ሊያገኙ ይገባል።** *መማር የዕድሜ ልክ፣ ሕይወት አቀፍ፣ ለኅልማሶች ትምህርት ቅድሚያ እና ዕውቅና የሚሰጥ መሆን አለበት። የአካታች ንድፍ መርሆችን ልንጠቀም እና ማንኛውንም ዕቅድም በጣም የተገለሉትን እና በጣም ደካማ የሆኑትን መቼቶች በማገልገል ላይ አተኩረን ልንጀምር ይገባል።*
- **ጤናማ ትምህርታዊ ሥነ ምህዳሮች ተፈጥሯዊ፣ የተገነቡ እና ቨርቹዋል የመማሪያ ቦታዎችን ያስተሣሥራሉ።** *ባዮስፈርን በተሻለ ሁኔታ እንደ የመማሪያ ሥፍራ ልንቀበለው ይገባል። ዲጂታል የመማሪያ ቦታዎች አሁን ከትምህርታዊ ሥነ ምህዳሮች ጋር የማይነጣጠሉ በመሆናቸው ሕዝባዊ፣ አካታች እና የጋራ የትምህርት ዓላማዎችን ለመደገፍ መጎልበት አለባቸው። ለተማሪ እና አስተማሪ ውሁቦች ጠንካራ ጥበቃ የሚያደርጉ፣ የክፍት ተደራሽነት እና የክፍት ምንጭ መድረኮች፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል።*
- **የመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ እና የትምህርት ቁጥጥር አቅም መጠናከር አለበት።** *መንግሥታት ፈጥኖ መላሽ፣ ፍትሐዊ እና ሰብአዊ መብቶችን ለሚያከብሩ የትምህርት አቅርቦቶች ደረጃዎችን እና ደንቦችን የሚያወጡበትን እና የሚስፈጽሙበትን አቅማቸውን መገንባት እና ማሳደግ አለብን።*
- **የመማር መብት መስፋት አለበት።** *የመማር መብትን የትምህርት ቤት ጉዳይ ብቻ ማድረጋችን ከእንግዲህ በቂ ውጤት አያስገኝልንም። በየትኛውም ቦታ ያለ ማንኛውም ሰው የዕድሜ ልክ ትምህርት የማግኘት መብት ሊኖረው ይገባል። የመረጃ መብትን እና የባሕልን መብት እንደ አስፈላጊ የትምህርት መብት አካላት መደገፍ አለብን። የመተሣሠር መብትም መካተት አለበት።*

አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ሲቀረጽ፣ እነዚህን አራት የመመሪያ መርሆች መከተል ይገባል። በአገር ውስጥ፣ በአገር አቀፍ፣ በክፍለ ዓለም እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ውይይት እና ድርጊቶቻችንን በእነዚህ መርሆች ዙሪያ መመሥረት እና ወደፊቶቻችንን መልሶ የማጤን ተግባርን በጋራ መደገፍ አለብን።

# ክፍል ሦስት

## አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ማፋጠን

የሰው ልጅን እና የሕያው ፕላኔትን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥሉትን በርካታ ተደራራቢ ቀውሶችን ለመወጣት፣ ሥር ነቀል የአካሄድ ለውጥ ያስፈልጋል። የወደፊቱን ለመለወጥ የሚረዳውን - ከማኅበራዊ፣ ሥነ ዕውቀታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ፍትሕ መርሆዎች የሚነሣውን - የትምህርት ማኅበራዊ አዲስ ውልን በአስቸኳይ መቅረጽ አለብን። አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ ማኅበረሰባዊ ጥረት እና የጋራ ጥቅም የሚያጠናክሩ እና ለጋራ ዕውቀት ጥበቃ የሚያደርጉ የታደሱ አካሄዶችን ያመለክታል። የተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አጋሮች ያለፉትን ያልተፈጸሙ ቃል ኪዳኖች ለማሟላት እና ለወደፊት የትምህርትን ለዋጭ እምቅ አቅም ለማውጣት በጋራ መሥራት እንዳለባቸው ይገነዘባል። ዩንቨርስቲዎች እና ሌሎች አጋሮች የትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም መታደስ እና አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን አብሮ ግንባታ ለመደገፍ በምርምር እና ኢኖቬሽን ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል።

በተመሳሳይም፣ ሁኔታ ወደ 2050 ስናማትር፣ የሚያስፈልገንን ዓለም አቀፍ ትብብር እና አጋርነት ዳግም በመቅረጽ ረገድ የቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ የትምህርት ልማት ድርጅቶችን ሚና እንደገና መልክ ማስያዝ አስፈላጊ ነው። በመጨረሻ ግን፣ ትምህርትን እንደ የጋራ ጥቅም ለማስተዳደር ቁልፍ ከሆኑት ከዓለም አቀፋዊ እና ቀጣናዊ ደረጃዎች ባሻገር፣ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ማነሣሣት በተለዩ ዐውዶች ውስጥ በዓለም ዙሪያ ባሉ በርካታ ልዩ ልዩ ቡድኖች መሀል፣ በሚደረግ ሰፊ ማኅበራዊ መሠረት ባለው ውይይት አማካይነት መቀጠል አለበት። ይህ ሪፖርት ይህን ውይይት የማስቀጠል ግብዣ ነው።

# ምዕራፍ 8

# የምርምር እና የፈጠራ ጥሪ

*በሁሉም ማኅበረሰባዊ መንገዶች ሂደት - ማለትም ሥነ ዘዴ እና ዘዴ - በጣም አስፈላጊ ነው። በብዙ ፕሮጀክቶች ሂደቱ ከውጤቱ የበለጠ አስፈላጊ ነው። ሂደቶች መከባበር፣ ሰዎችን ማስቻል፣ መፈወስ እና ማስተማር ይጠበቅባቸዋል። የራስን ዕድል በራስ ለመወሰን አንድ ትንሽ እርምጃ ወደፊት መምራት ይጠበቅባቸዋል።*

ሊንዳ ቱሂዋይ ስሚዝ፣ *Decolonizing Methodologies*, 1999.

**አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ለማፋጠን፣ ኮሚሽኑ በዕድሜ ልክ የመማር መብት ላይ የተመሠረተ እና ከመሠረታዊ ማኅበራት፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ ተቋማት፣ ዘርፎች እና ከብዟይነት ባሕሎች የተውጣጡ አስተዋጽኦዎችን የሚቀበል ዓለም አቀፍ ትብብራዊ የምርምር አጀንዳ ይፈልጋል።**

በቀደሙት ምዕራፎች ውስጥ የተገለጹትን ሐሳቦች ለማራመድ ለትምህርት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሰፊ በሆኑ ዐውዶች እና ሁኔታዎች ውስጥ የሚከወኑ ጥረቶችን፣ ሙከረቶችን፣ ምርመራዎችን እና ኢኖቬሽኖችን ይጠይቃል። ይህ ምዕራፍ እንደገና በምናጤናቸው ወደፊቶቻችን ሊኖር ስለሚገባው ትምህርት ትብብራዊ ምርምር እና ኢኖቬሽን እንዲደረግ ጥሪ ያቀርባል። እንደ ትምህርት እንደ ራሱ፣ ምርምር እና ኢኖቬሽን አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ለማፋጠን ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ የጋራ ሀብቶች እና ሂደቶች ናቸው።

ስለ ትምህርት የወደፊት ዕጣዎች የሚደረግ የምርምር አጀንዳ የሚጀምረው ተማሪዎች እና መምህራን ባሉበት ነው። በብዙ መንገዶች፣ የትምህርት ነገዎች አካላት፣ ቢያንስ በሆነ የመነሻ ቅርጽ፣ ቀድሞውንም በመካከላችን አሉ። የማንኛውም የትምህርት ሥርዓት መነሻው እነዚያን ጭላንጭሎች - በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተገለጹትን መርሆች የያዙትን አወንታዊ አጋጣሚዎች - መፈለግ ነው። ማኅበረሰቦች ሐሳቦቻቸውን ምን፣ እንዴት ባለ ልዩነት እንደሚሠሩ ጭምር ወደሚዘረዝር ተግባራዊ ስልት የሚተረጉሙበትን መንገድ ስለሚፈልጉ፣ የተጽዕኖዎቻቸው ጥናት እና ትንተና ዕውን ካደረጓቸው ሁኔታዎች ጋር ተዳምረው፣ በዚህ ሪፖርት ውስጥ ያሉትን ሐሳቦች መሠረት ሊያስይዙ ይችላሉ። ትምህርት ሰፋት ባላቸው የተለያዩ የምርምር ምንጮች፣ ዘዴዎች እና ተምሳሌቶች ላይ የመመሥረት ታሪክ አለው። እነዚህ መሳሪያዎች በየደረጃው፣ ከተግባሪ እና ከማኅበረሰብ ውይይት እስከ ዩኒቨርስቲዎች እና የምርምር አጋርነቶች፣ ዐልፎም የዩኔስኮን ጨምሮ እስከ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ መድረኮች ድረስ ሊጠናከሩ እና ሊስፋፉ ይገባል።

ይህ ምዕራፍ፣ ከሁሉም በላይ፣ ምርምር እና ኢኖቬሽን በአንድነት ለመማር - ለጽብረቃ፣ ለሙከረት እና በሕብረተሰብ ላይ በጋራ ተጽዕኖ ለማሳደር፣ እና ይህንንም በማድረግ፣ ወደፊቶቻችንን በጋራ ዳግም እንድናጤን ለሚያስችሉንባቸው መንገዶች አጽንኦት ይሰጣል። ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ ምርምር እና ኢኖቬሽን፣ ምናባችንን በማብቃት እና ነጋችን በትምህር ውስጥ በምናያቸው እና በምናደርጋቸው ነገሮች ላይ ስለሚጫወተው ሚና ግንዛቤያችንን በማሳደግ፣ አርቆ የማየት አቅሞቻችንን እና የወደፊቱን የትምህርት ክህሎቶቻችንን ማጠናከር አለባቸው። ሁሉም የትምህርት ምርምር አጀንዳዎቻችን በትብብር፣ በትሕትና እና በአርቆ አስተዋይነት ሥነ ምግባር ተሞልተዋል።

> *ምርምር እና ኢኖቬሽን፣ አርቆ የማየት አቅሞቻችንን እና የወደፊቱን የትምህርት ክህሎቶቻችንን ማጠናከር አለባቸው።*

ይህ ምዕራፍ በዚህ ሪፖርት ሐሳቦች ላይ ዕውቀትን እና ምርምርን ለማስፋፋት የሁሉንም የትምህርት ተሳታፊዎች አስተዋፅኦ ይጠይቃል። በተጨማሪም፣ ከእነዚህ ጭብጦች ጋር የተያያዙ የመማር ተግባራትን እና ግንዛቤዎችን እንዲደግፉ እና ሥርዓት እንዲያበጁ ለዩኒቨርስቲዎች፣ ለምርምር ተቋማት እና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ልዩ ጥሪዎች ቀርበዋል ። የአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን መርሆች ለማራመድ፣ መተግበር በሚያስችሉን መሳሪያዎች ራሳችንን በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስታጠቅ ያስፈልገናል። ምዕራፉ የሚጠናቀቀው ለሁሉም የትምህርት ተሳታፊዎች ፍላጎት ያላቸውን የ2050 የውይይት እና የድርጊት መርሆች በማቅረብ ሲሆን፤ ይህም የሚከተለውን ያካትታል፡- በተለያዩ አመለካከቶችን፣ ይዘቶችን እና ቦታዎችን ላይ የተመሠረቱ አካታች የምርምር አጀንዳ ጥሪ።

# ለትምህርት አዲስ የምርምር አጀንዳ

ይህ ሪፖርት ኮሚሽኑ የወደፊቱ ትምህርት አዲስ የምርምር አጀንዳ መምራት አለባቸው ያላቸውን ምልከታዎች፣ መርሆች እና ሐሳቦች አስተዋውቋል። ይህ የምርምር አጀንዳ በጋራ ነጋችን ውስጥ ወደሚካሄድ ወደፊት ተኮር፣ ፕላኔት አቀፍ የመማር ሂደት የተቃኘ እንደመሆኑ፤ ሰፊ እና ዘርፈ ብዙ ነው። ከተለያዩ የዕውቀት ዓይነቶች እና አመለካከቶች እና ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ ግንዛቤዎችን ከማግለል እና ከመቃረን ይልቅ በማሚያነት የሚቀበል ፅንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ነው።

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተመለከቱት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ወደ አንድ ወጥ የጋራ የምርምር አጀንዳ ለመምጣት እርስበርስ ይደጋገፋሉ። በምዕራፍ 1 ላይ እንደተገለጸው፣ ይህ የምርምር አጀንዳ በዋናነት የመማር መብት ላይ ሊያተኩር፤ ጥራት ያለው፣ ፍትሐዊ ትምህርት ለሁሉም እንዳይደርስ እንቅፋት የሚሆኑትን ሁሉንም ጉዳዮችን ሊመረምር ይገባል። ምርምር፣ በምዕራፍ 2 ላይ የተገለጹት የለውጥ ኃይሎች - ተለዋዋጭ የአየር ንብረት እና አካባቢያችን፣ የቴክኖሎጂ ለውጦች መፋጠን፣ የፖለቲካ አካል ስብራቶች መባባስ እና እርግጠኛ ያልሆኑ የሥራ እና የአኗኗር ሁኔታዎች - በሚቀጥሉት ወሳኝ ዓመታት ውስጥ ከትምህርት ጋር እንዴት እንደሚገናኙ መከታተል አለበት። ምርምር በዚህ ሪፖርት ክፍል ሁለት ላይ በተገለጹት የአሠራር መርሆች - በአጋርነት እና በትብብር ላይ የተመሠረቱ ሥነ ትምህርቶች፣ ሥርዓተ ትምህርቱ ከጋራ ዕውቀት ጋር ያለው ግንኙነት፣ የመምህራንን አቅም ማጎልበት፣ ትምህርት ቤቶችን እንደገና ማጤን፣ እና መማር ከሁሉም የሕይወት ጊዜያት እና ቦታዎች ጋር ያለው ትስስር - መሠረት የትምህርት ዕድሳትን ለማሰስ ከልኬት እና ከትችት ዐልፎ መሄድ አለበት። ከእንዲህ ዓይነቱ ሰፊ የምርምር አጀንዳ የሚመነጩት ትምህርት፣ ግንዛቤዎች እና ተመክሮዎች አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል በጋራ የመቅረጽ ሂደትን ማፋጠኛ ይሆናሉ።

## ከትምህርት ውስጥ የሚመነጭ ምርምር

ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እና ከዚያም ወዲያ ጥልቅ እና ጠቃሚ የትምህርት ምርምር ቅርስ ይገኛል፤ ይኸውም ልዩ ልዩ ሥራዎችን፤ ጉልሕ የአስተሳሰብ እና የድርጊት ዘዴዎችን ያበጁ የዘመን አዝማሚያዎች እና አመለካከቶችን ያቀፈ ነው። ትምህርታዊ ምርምር በትምህርት ቤቶች፣ በመማሪያ ክፍሎች እና ትምህርት በሚካሄድባቸው በርካታ ሥፍራዎች ያለውን ዕውነታ የበለጠ እንድንረዳ ያስችለናል። በግለሰቦች፣ በማኅበረሰቦች እና በአጠቃላይ በሕብረተሰብ ውስጥ እየታዩ ስላሉት ለውጦችም ግንዛቤዎችን ይሰጣል።

የባለሙያ ምርምር፣ የተግባር ምርምር፣ የታሪካዊ መዛግብታዊ ምርምር፣ ጉዳይ ተኮር ምርምር፣ ኢትኖግራፊ፣ ወዘተ በዘርፉ ውስጥ ባሉ ሰዎች ቢሰማሩባቸው ፍሬያማ እንደሚሆኑ ከተረጋገጠላቸው በርካታ የምርምር ዘዴዎች መካከል ይጠቀሳሉ። ትምህርት እንዲሁ፣ የውጫዊ ሙከረት እና ጥናት ተግባራዊ ማድረጊያ መስክ ብቻ ሳይሆን፣ ራሱም የምርመራ እና የትንታኔ መስክ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

ትምህርት ቤቶች ዕውቀት የሚመረትባቸው ቦታዎች እና መምህራን ደግሞ ዐዋቂዎች መሆናቸው መታመኑ፤ ዩኒቨርስቲዎች፣ ድርጅቶች እና ተመራማሪዎች በትምህርት ውስጥ ከተካተቱት ጋር ባላቸው መስተጋብር እና የትብብር ሁኔታ የሚወሰን እና በበለጸጉ ግንዛቤዎቻቸው፣ አስተያየቶቻቸውን እና ተመክሮዎቻቸው ላይ የሚመሠረት ነው። ዩኒቨርስቲዎች የዲሲፕሊን ዕውቀትን በማሳደግ ብቃታቸው እና በበይነ-ዲሲፕሊናዊነታቸው አማካይነት ትምህርታዊ ምርምርን በማሳደግ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። መምህራን ከተመክሮዎቻቸው የተነሣ፣ ምንጊዜም በየሙያቸው፣ ከዋነኞቹ የዕውቀት አመንጪዎች መሀል ናቸው፤ ስለዚህም ጥናቶቻቸውን እና አስተያየቶቻቸውን እንዲያሳትሙ ሊደገፉ ይገባል።

*ተማሪዎች ስለራሳቸው የትምህርት ተመክሮዎች፣ ምኞቶች፣ ስኬቶች እና ጽብረቃዎች ወሳኝ የዕውቀት እና የግንዛቤ ምንጮች ናቸው።*

ተማሪዎች ስለራሳቸው የትምህርት ተመክሮዎች፣ ምኞቶች፣ ስኬቶች እና ጽብረቃዎች ወሳኝ የዕውቀት እና የግንዛቤ ምንጮች ናቸው።

ዩኒቨርስቲዎች እና ተመራማሪዎች ሁልጊዜ ከትምህርት ቤቶች፣ መምህራን እና ተማሪዎች ጋር በመወያየት ድጋፋቸውን ሊሰጡ ይችላሉ። አሳታፊ ምዘና፣ ትብብራዊ ምርምር፣ ወጣት-መር ምርምር እና የባለሙያ ምርምር ከውስጥ እና ከውጪ ስለ ትምህርት በሚመራመሩት መሀል ላለው መማማር የበለጠ ሥርዓት ለማበጀት መሠረት ሊደረጉ ከሚችሉ በርካታ ሥነ ዘዴዎች መሀል ናቸው። የትምህርት ምርምር ለአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል አስፈላጊ የሆኑትን ለውጦች ለመቅረጽ እና ለመከታተል ቁልፍ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል።

## የመማር ሳይንሶችን ማነቃነቅ

ከቅርብ አሥርት ዓመታት ውስጥ ከትምህርት አንጻር በጣም ልዩ ከሆኑት የሳይንስ ዕድገቶች መሀል፣ በኒውሮሳይንስ የተገኘው እና አንጎል ከመማር ጋር ተያይዞ የተፈተሸበት ጥናት ይገኙበታል። እነዚህም በሁሉም የሰው ልጅ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ ስላለው ኒውሮፕላስቲክነት የተገኘውን ግንዛቤ፤ የአንጎልን እና የሰውን ኒውሮሎጂ መዋቅረ አካል፣ መዋቅር፣ የማስታወስ ችሎታን፣ የመረጃ አጠቃቀምን፣ ቋንቋ መማርን እና ውስብስብ አስተሳሰብን፤ እንዲሁም እንደ እንቅልፍ፣ የአካል እንቅስቃሴ፣ ስሜት፣ ውጥረት እና መድኃኒቶችን የመሳሰሉ አወንታዊ እና አሉታዊ ማነቃቂያዎች፣ በመማር ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ያካትታሉ። የትምህርት የመገንዘብ ሂደቶች ራሳቸው እንደ ንግግር፣ ማንበብ፣ መጻፍ፣ የቦታ ግንዛቤ እና የመሳሰሉትን ልዩ ችሎታዎች ያገነዝባሉ።

ምንም እንኳን ሳይንቲስቶች ስለዚህ መስክ በጥቅሉ፣ እና እንዴትስ በትምህርት ላይ ሊተገበር እንደሚችል ገና ዕውነተኛ ግንዛቤ የመጨበጥ ጅምር ላይ ቢሆኑም፤ ለመማር እና ለማስተማር ትልቅ ፋይዳ አለው፤ ግንዛቤዎችን በተቻለ መጠን ለአስተማሪዎች፣ ተመራማሪዎች እና ለተማሪዎች ለራሳቸው ተደራሽ መደረግ አለባቸው። ለምሳሌ፣ ሳይንቲስቶች ቁጥጥር በሚደረግባቸው የቤተ ሙከራ ዐውዶች ውስጥ በባሕሪዎች እና በአንጎል አሠራር መካከል ጠንካራ ቅጦችን እና ተዛምዶዎችን መመልከት ቢችሉም፤ እነዚህ ቅጦች ወደ ውስብስብ የማኅበራዊ ትምህርት ከባቢዎች እንዴት ሊተረጎሙ እንደሚችሉ ወይም በልዩ ልዩ ሕዝቦች፣ ሰዎች፣ ጊዜያት እና ቦታዎች ውስጥ እንዴት ሊለያዩ እንደሚችሉ ገና ግልፅ አይደለም።

የወደፊት የመማር ሳይንሶች ሰፊ የምርምር ጥያቄዎችን፣ መነሻ ግምቶችን፣ መላምቶችን እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን በተመጣጣኝ መልኩ መወከላቸውን ለማረጋገጥ፣ ሰፊ ስብጥር ካላቸው የጾታ፣ የባሕል፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራዎች፣ ቋንቋ፣ ዕድሜ እና የመሳሰሉትን የተውጣጡ ተመራማሪዎችን ማሳተፍ አለባቸው። ነርቫዊ ስብጥር፣ የመማር ልዩነቶች፣ የአካል ጉዳት ጥናቶች እና ልዩ ትምህርት በመማር ሳይንሶች ውስጥ ካሉ ጉልህ ዕድገቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

የመማር ሳይንሶች ግኝቶች ወሳኝ እና አስፈላጊ ቢሆኑም፣ ትምህርትን በሁለመናው አያካትቱም። ግንዛቤ የምንማርበት ብቸኛው መንገድ አይደለም፤ ማኅበራዊ ዕውቀት፣ አካላዊ ዕውቀት፣ ስሜታዊ ዕውቀት እና ሌሎችም በኒውሮሳይንስ አማካይነት ከምንረዳቸው ጋር ሊገናዘቡ ቢችሉም፣ በሳይንሱ ብቻ አይበየኑም።

በሥነ ትምህርት እና ሥርዓተ ትምህርት ላይ ባተኮሩት ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለጸው፣ የትምህርት ውስብስብነቱ የሚመነጨው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ገጽታዎችን ጨምሮ ከሁሉም የዓለም ገጽታዎች ጋር በማይነጣጠል መልኩ በመተሣሠሩ ነው። አእምሮን ከቁስ ማፋታት ትልቅ አደጋ አለው፤ ይህም ለሚማሩት ለብዙዎች ወደማይጠቅሙ የትምህርት ሐሳቦች ያመራል። በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተገለጹትን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች

ለማራመድ፣ የመማር ኒውሮሳይንሶች ግኝቶቻቸውን ከፍተኛ ጥራት ካለው ትምህርት የሚገኘውን አእምሯዊ እና ማኅበራዊ ጥቅሞች ለማምጣት በሚያችል መልኩ ከእነዚህ ልዩ ልዩ እና ውስብስብ የትምህርት ገጽታዎች ጋር ማገናዘባቸው እየጨመረ መሄድ ይኖርበታል።

## የትምህርት የምርምር አጋርነቶችን መለወጥ

የጥናት አጋርነቶች በይነ-ዲሲፕሊናዊ፣ በይነ-ዘርፋዊ እና ባሕል ተሻጋሪ ሆነው፤ አካዳሚያዊ፣ ሲቪል ማኅበረሰብ እና ትምህርታዊ ዐውዶችን ያቀፉ፣ እና የጋራ ተግባቦትን እና መማማርን የሚያጎለብቱ ከመሆናቸውም በላይ፣ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የቀረቡትን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እና ምክረ ሐሳቦች ለማራመድ ትልቅ አቅም አላቸው።

ሁሉም የምርምር አጋርነቶች ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ ባለመሆናቸው፤ ከፍተኛ ሀብት ወይም ተቋማዊ ሥልጣን ያላቸው አጋሮች፣ ታስቦበትም ባይሆን፣ በአጋርነት አካሄድ እና ውጤቶች ላይ ያልተገባ ተፅእኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ። በትምህርት እና በዙሪያው ያሉትን በአብዛኛው ስለ የሰው ልጆች ተፈጥሮ፣ ስለ ማኅበረሰብ እና ከሰው በላይ ስለሆነው ዓለም በያዝናቸው አስተሳሰቦቻችን ውስጥ የታቀፉትን መነሻ ግምቶች ለመፈተሽ ሥነ ዕውቀታዊ ትሕትና ያስፈልጋል። የአሠራር ቅኝታችን እንደ "ሰሜን/ደቡብ" ወይም "ምዕራባዊ/ምዕራባዊ ያልሆነ" ካሉ በማቃለል ላይ የተመሠረቱ የዕውቀት ግንኙነቶች ምደባዎች ተነጥሎ፣ ወደ ውስብስብ እና ተዛዲዊ የዕውቀት ምህዳሮች መቀየር አለበት።

ለአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል፣ እነዚህ የትምህርት ሥነ ምህዳሮች በልዩ ልዩ ተመክሮዎች እና የዕውቀት መንገዶች ሊበለጽጉ ይገባል እንጂ፤ በማግለል፣ በዕውቀት-አጠርነት ፍረጃ፣ እና በጠባብ ምሁራዊ ሥነ ዕውቀታዊ ግምቶች ምክንያት መራቆት የለባቸውም። ትምህርት ተዛምዷዊ ሂደት ነው - በተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ማኅበረሰቦች መካከል የሚከወን - እናም ስለዚህ ከተዋረድ ዕውቀት ይልቅ ተዛምዷዊ ዕውቀትን ነው መሻት ያለብን። ከዚህም በላይ ይህ ብሔራዊ እና ቀዬአዊ የምርምር አቅምን ሊያጎለብት እና ዕውቀትን እንደየዐውዶቹ፣ ባሕሎቹ እና ቋንቋዎቹ በልዩ ልዩ መንገድ የሚያፈሩ እና የሚወክሉ ሰዎችን አቅሞች ያካትታል።

በተጨማሪም የመሠረታዊ ማኅበረሰቦች እና የማኅበራዊ ንቅናቄዎች ድምፅ ጠቃሚ የዕውቀት እና የማስተዋል ምንጮች በመሆናቸው፤ ትምህርት ሊያዳምጣቸው፣ ሊመሠረትባቸው፣ እና አስተዋፅኦ ሊያበረክትላቸው ይገባል፤ ምክንያቱም እነርሱ ወደፊቶቻችንን ከሚቀርጹት ነውጦች እና ለውጦች መሀል ግንባር ቀደም ተሰላፊዎች ናቸው። የምድራችንን ጥፋት የሚቃወሙ እና ሁሉንም ዓይነት ጭፍን ጥላቻ እና አድልዎ የማይቀበሉ ንቅናቄዎች ወደፊታችንን በጋራ ከምናጤንባቸው በርካታ ምሳሌዎች መካከል ናቸው። እንዲህ ካሉት ማኅበረሰቦች እና ንቅናቄዎች ጋር የሚደረጉ ትብብሮች ሁልጊዜ መደበኛ ወይም ተቋማዊ ላይሆኑ ቢችሉም፤ ነገር ግን ስለ ትምህርት ሚና እና ከእንደዚህ ዓይነት ንቅናቄዎች ጋር ስላለው ግንኙነት ለመማር የጋራ ሥራ ወሳኝነታቸው ቀላል አይሆንም።

# ዕውቀትን፣ ውሂብን እና ማስረጃን ማስፋፋት

ለትምህርት ወደፊቶች አዲስ የምርምር አጀንዳን ማሰባሰብ ሰፊ መጠን ያለውን ዕውቀት፣ ውሂብ እና ማስረጃ በተለያዩ ቅርጾች - መጠናዊ እና ጥራታዊ፣ ደንጋጊ እና ገላጭ፣ ዲጂታል መሆን የሚችል እና ዐላፊ፣ ንድፈ ሐሳባዊ እና ተግባራዊ - በከፍተኛ መጠን ያመነጫል፣ ለእነሱም ያዋጣል።

አሁን ያሉ ሁኔታዎችን ለመረዳት እና ወደፊት ለትምህርት አዳዲስ ዕድሎችን ለመገመት ዕውቀትን ማስተላለፍ እና ማስፋፋት ያስፈልጋል። ከታሪክ አኳያ ግን፣ የተወሰኑ የዕውቀት ቅርጾች እና ምንጮች ዕውቅና ተሰጥቷቸው፣ ሌሎቹ ግን ተገፍተዋል። ዕውቀት - በጥቅሉ እና በተለይ በትምህርት ውስጥ ያለው ዕውቀት - ከሥልጣን ጋር በቅርበት ይገናኛል። በሰዎች እና በፕላኔቷ ላይ የሚሠለጥኑ ገናን የሥልጣን ሥልቶች በትምህርት በአዳዲስ የማካተት እና የተሳትፎ መንገዶችን ለማግኘት በሚያስችሉን ሥልጣንን ለሰዎች እና ከሰዎች ጋር በሚሉ ሥልቶች መተካት አለባቸው። በሚቀጥሉት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ የትምህርትን

ወደፊቶች ለማራመድ እንደሚያስፈልግ የምርምር አጀንዳ፣ በትምህርት ውስጥ የዕውቀት፣ የውሂብ እና የማስረጃ ተፈጥሮን ያለማቋረጥ መመርመር አለበት።

## ውስብስብ የዕውቀት ሥነ ምህዳሮችን ማጠናከር

ከአሁኑ ባሻገር፣ የሚመጡትን እጅግ የተሠባጠሩ ልዩ ልዩ የወደፊት ዕድሎች ለመተንበይ፣ ምርምር እና ኢኖቬሽን ልዩ ልዩ ሕዝቦች፣ ባሕሎች እና ወጎች ዓለምን የሚያነቡባቸውን እና የሚገነዘቡባቸውን ብዙ መንገዶችን መግፋት አይችሉም። በእርግጥ የዚህ ሪፖርት የሥነ ትምህርት፣ የዕውቀት፣ የተሳትፎ፣ የትብብር እና የአጋርነት መመሪያዎች በብዙ ባሕላዊ አተያዮች እና ርእዮተ ዓለሞች እይታዎች የበለፀጉ የዕውቀት ትውፊቶች አላቸው። ዕውቀትን ከቅኝ አገዛዝ ነጻ ማውጣት የተለያዩ የዕውቀት ምንጮች የአሁኖቹን እና የወደፊቶቹን ፍላጎቶች ለመሙላት ተገቢነት እና ተግባራዊነት እንዳላቸው በቂ ዕውቅና መስጠትን ይጠይቃል። አገር በቀል ሥነ ዕውቀቶችን ዓለምን ለመረዳት እና ለማወቅ እንደአዋጭ ዘዴዎች ሳይሆን፣ እንደ የጥናት ርእስ ጉዳይ ከመመልከት መራቅን ይጠይቃል።

ከልማት እስከ ኢኮኖሚክስ፣ እስከ ትምህርትም ድረስ በብዙ መስኮች፣ አንዳንድ የዕውቀት ዓይነቶች በሌሎች ላይ ልዩ መብት አላቸው። ብዙውን ጊዜ፣ የሰሜኑ ዓለም ዕውቀት ወደ ታዳጊ አውዶች የሚተላለፈው፣ በአካባቢው የመነጨ ዕውቀት የለም ወይም ጉድለት አለበት በሚል ግምት ነው። ሆኖም፣ እነዚህ ከውጭ የተጫኑ 'መፍትሄዎች' ብዙውን ጊዜ፣ ለእነዚህ ዐውዶች የዘላቂ ልማት አስተዋጽኦ ማድረግ ይሳናቸዋል፣ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን እና የአካባቢን የረጅም ጊዜ ደህንነት አደጋ ጥለው ጥቂቶችን ተጠቃሚ ያደርጋሉ።

ለብዙ የዕውቀት መንገዶች ዋጋ እና ዕውቅና መስጠት የከረረ ንጽጽራዊነትን እንደ መቀበል ወይም ለዕውነት መቆምን እንደ መተው ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። ይሄ ከእዚያ የራቀ ነው። አገር በቀል እና ብዙኃዊ የማወቅ መንገዶች ያሉበትን ዕውነታው በበቂ ሁኔታ ማንጸባረቅ ያልቻሉ የዕድገት ሞዴሎች እና ተግባራት መነሻ ያደረጓቸውን ግምቶች ይገዳደራሉ። ለምሳሌ፣ ትምህርትን ጨምሮ በብዙ የምዕራባውያን የአስተሳሰብ ባሕሎች የሁለት ክፍለት አካሄድ እየተለመደ መጥቷል፦ ንድፈ ሐሳብ እና ተግባር፣ ግለሰብ እና ቡድን፣ ሥነ ጥበብ እና ሳይንስ፣ ሰው እና ተፈጥሮ፣ ተራማጅ እና ወግ አጥባቂ፣ ማወቅ እና ስሜት፣ አእምሯዊ እና አካላዊ፣ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ፣ ዘመናዊ እና ባሕላዊ፣ ወዘተ። የብዙ ምዕራባውያን ያልሆኑ አተያዮች ወሳኙ አስተዋጽኦ የእነዚህን ዋልተኛ መዋቅሮች መነሻ በመፈተሽ፣ የአንድ እርስበርሱ የተሣሠረ ውስብስብ ዓለም ተያያዥ አካላት በመሆናቸው ስላሏቸው የጋራ ግንኙነቶቻቸው እና ስለፍሬያማ ውጥረትነታቸውም አዲስ ብርሃን መፈንጠቁ ነው።

> *አገር በቀል እና ብዙኃዊ የማወቅ መንገዶች የዕድገት ሞዴሎች እና ተግባራት መነሻ ያደረጓቸውን ግምቶች ይገዳደራሉ።*

በችግር ጊዜ፣ ለምሳሌ፣ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ብዙውን ጊዜ ሰፊ የተመክሮ፣ የዕውቀት እና የፈጠራ ክምችታቸውን በመጠቀም ጉዳቶችን ለመቀነስ እና ትምህርትን ከድንገተኛ አደጋዎች ጋር ለማስማማት ችለዋል። ስለ ዘላቂ የግብርና ብልኀቶች፣ ማኅበራዊ ተደጋጋፊነት እና ከተፈጥሯዊው ዓለም ጋር መኖር ስለሚቻልባቸው መንገዶች፣ ወዘተ የተከማቸው ትውልዶችን የተሻገረ ዕውቀት የሰው ልጅ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አሁን የሚፈልገው የተከማቸ ዕውቀት ምንጮች ናቸው። ሆኖም የዚህ ዓይነቱ ዕውቀት ሙሉ በሙሉ ዕውቅና ያልተሰጣቸው፣ በአስተምህሮም ውስጥ ያልገቡ እና በመደበኛ ትምህርት የተዘለሉም ነበሩ።

ስለ ትምህርት ወደፊቶች የሚደረግ ጥናት በዚህ ሪፖርት ውስጥ በተለዩት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ልዩ ልዩ የዕውቀት ዓይነቶች እና ምንጮችን ማደስን እና ማካተትን ይጠይቃል። ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለጸው፣ ይህ በፍትሐዊነት እና ተመጣጣኝነት ላይ በተመሠረተ የጋራ ዕውቀት ላይ ባለው ተለዋዋጭ ተሳትፎ ይወሰናል። ለትምህርት ወደፊቶች፣ ስኬታማ የዕውቀት ማምረት ተግባር የታሰበበት አካታችነት፣ ማኅበራዊ እና ባሕላዊ ስብጥር፣ በይነ-ዲሲፕሊናዊነት እና በይነ-ሙያዊነት ሊኖረው እና ተግባቦትን፣ ትብብርን፣ ባለቤትነትን እና መማማርን የመፍጠር አቅም ሊኖረው ይገባል።

## ስታቲስቲካዊ ውሂብ፣ አመላካቾች እና ትንተና

ስታቲስቲካዊ ውሂብ የአንድን አመላካች የቅጽበት ነጠላ ምስል የማቅረብ ኃይል አለው፤ ከሌሎች የውሂብ ነጥቦች ጋር ሲያያዝ ደግሞ፣ በጊዜ እና በቦታዎች ላይ ስላሉ ግንኙነቶች፣ ለውጦች እና ሁኔታዎች በዋጋ ሊተመኑ የማይችሉ ግንዛቤዎችን ሊሰጥ ይችላል። የሆኑ አመላካቾች በጊዜ ሂደት የሄዱባቸውን አቅጣጫዎች በማሳየት፣ እንደየተለዋዋጭ ሁኔታው፣ እንደየምርጫው፣ እንደየከስተቱ ወይም እንደየእርምጃው ወደፊት ሊሆኑ የሚችሉ ውጤቶችን መተንበይ ይችላሉ።

የዩኔስኮ ስታቲስቲክስ ኢንስቲትዩት (ዩአይኤስ) በርካታ ልዩ ልዩ የትምህርት አመላካቾችን በተመለከተ ወሳኝ ስታቲስቲክስን በማሰባሰብ እና በማኸዘብ ትልቅ ሚና ይጫወታል። የዩአይኤስ አካሄድ በአገር አቀፍ፣ በክፍለ ዓለም እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ስታቲስቲክስን የመሰብሰብ እና ማረጋገጫ የመስጠት አቅም ከሚገነባባቸው መንገዶች አንዱ ነው። በጾታ፣ በቦታ፣ በገቢ ደረጃ እና በሌሎች ባሕርያት ውሂብ መነጣጠያን መጨመር ስለ ፍትሐዊነት እና የእኩልነት ጉዳዮች ግንዛቤን ለመስጠት ይረዳል። የዩአይኤስ በተከታታይ ብያኔዎችን የማጥራት ሥራ፣ በዚያውም ትርጉም ላለው ትንተና ስታቲስቲካዊ ታማኝነትን የማረጋገጥ ሥራ፣ ጥራታቸውን እና ጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ወሳኝነት አለው። በጣም ወሳኝ ስለሆኑ የትምህርት አመላካቾች ጠቃሚ ውሂብ ለማቅረብ እና እነዚህ ውሂቦች ለሁሉም ሰው ተገኚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተከታታይ ሥራቸውን መደገፍ አስፈላጊ ነው።

በተመሳሳይ፣ በሚቀጥሉት ዐሥርት ዓመታት የሚመጡ የስታቲስቲካዊ እና መጠናዊ ውሂብ አቀራረቦች አቃላይነትን በጥብቅ ማስወገድ አለባቸው። ምደባ ለትንታኔ ጠቃሚ ቢሆንም፣ የማይለዋወጥ እና ቋሚ ሆኖ መታየት ግን የለበትም። ምድቦች ሁልጊዜ በቁጥር መመዘኛ ሊመዘኑ ከሚችሉት ይልቅ፣ በዕውነታው ዓለም የበለጠ ስውር፣ ውስብስብ እና ደብዛዛ ናቸው። ስታቲስቲክሳዊ ውሂብ የመሰብሰብ እና የማጣራት ሥራ፣ በተለይም በትልቅ ደረጃ ሲሠራ፣ ብዙ ጉልበት የሚጠይቅ እና ውድ ሊሆን ይችላል። የሚቻል ሆኖ ሲገኝ ትይዩ የውሂብ ስብስቦችን ለመጫን የሚጠይቀውን ከፍተኛ ፍላጎትና ወጪ ለማስቀረት የውሂብ አሰባሰብ ጥረቱ ያሉትን አገር አቀፍ የውሂብ ምንጮች ማጠናከር እና መደገፍ ይገባዋል።

እንደዚሁም፣ ከአካባቢው ትምህርታዊ ቅድሚያዎች እና ከዓለም አቀፍ ግቦች ጋር በሚዛመዱ መንገዶች ትርጉም ያላቸውን አመላካቾች ለመለየት በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ አካሄዶች የተለካ ነገር ሁሉ እንደማይጠቅም እና በትምህርት ውስጥ ጠቃሚ የሆነውን ሁሉም መቁጠር እንደማይቻል መገንዘብ አለባቸው። ስለዚህ ስታቲስቲክስን የሚሰበስቡ እና የሚጠቀሙ ሰዎች ትሑት አቀራረብ ትምህርታዊ ዓላማዎችን እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮችን ለማሳደግ ለሚያደረጉ ተጨማሪ ምርምሮች እና ኀሠሳዎች ግኝታቸውን እንደ መነሻ ለማየት ቁልፍ ነገር ነው። በዩኔስኮ ዲፓርትመንቶች፣ እና በሌሎች ድርጅቶች እና ተመራማሪዎች የሚከናወነው በጥንቃቄ የታሰበበት ሥራ በተቻለ መጠን ትንበያዎችን በማድረግ፣ ወዲያውም የመግለጽ ኃይላቸውን የሚያሳዩ እና የሚፈትኑ ታሪኮችን በመንገር የትምህርት ስታቲስቲክስን ወደ ሕይወት ማምጣት ይችላል።

## ግዙፍ ውሂብ እና የዕውቀት ተለዋዋጭ ባሕርይ

የቴክኖሎጂ ዕድገቶች ስለዕውቀት ምንነት እና እንዴት መፈጠር እንዳለበት አዳዲስ መነሻ ግምቶችን ፈጥረዋል። ወቅታዊ ቴክኖሎጂዎቻችን መረጃ እና የሚያመነጨው ዕውቀት እና ግንዛቤዎች፣ ግዙፍ (ከነጠላ ተመክሮዎች ሳይሆን ከብዙ የውሂብ ነጥቦች ላይ ስለሚቀዱ)፣ የሚበረበሩ (ተገኚ እና በቀላሉ የሚፈለጉ)፣ ተከማች (በማህደር ሊቀመጡ የሚችሉ)፣ ተስተላላፊ (ያለችግር ሊጋሩ የሚችሉ) እና ግለሰብ ተኮር (ለግል ፍጆታ የተመቻቹ) ሆነዋል። እነዚህ እያንዳንዳቸው ባሕርያት በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው፤ ምክንያቱም ዓላማዎቹን እና ሂደቶችን ጨምሮ ትምህርት ነክ ሐሳቦችን ያፈልቃሉ፣ ይቀርፃሉ፤ አንዳንድ ዕድሎችን ይከፍታሉ፣ ሌሎችን ደግሞ ይዘጋሉ።

የላቀ የዲጂታል መሳሪያዎች ተደራሽነት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አሁን ለተመራማሪዎች ሰፋ ያሉ የትምህርታዊ ውሂብ ስብስቦችን የማደራጀት፣ የማዋሐድ እና የማስኬድ ታይቶ የማይታወቅ ኃይል ሰጥቷቸዋል። የዲጂታል ዘዴዎች፣ መሳሪያዎች፣ የውሂብ አሰባሰብ እና አከመቻቸት፣ እና ሥልተ ቀመራዊ የውሂብ ማቀናበር ኃይል የትምህርት ዘዴዎች እና አቀራረቦችን ግንዛቤ፣ ልምምድ እና ውጤታማነት ለማሳደግ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ የማወቅ ከፍተኛ ጉጉት ፈጥሯል። ስታቲስቲካዊ

ውሂብ ማቀናበር እና ማደራጀት፣ ጂኦግራፊያዊ ካርታ ሥራ፣ የኔትወርክ ካርታ ሥራ፣ ንድፎችን መፈለግ እና ቁልፍ ቃል ፍለጋ ተመራማሪዎች ሊጠቀሙባቸው ከሚችሏቸው መሳሪያዎች መካከል ናቸው። ከጊዜ ወደ ጊዜ ዲጂታል መሆናቸው እየጨመረ በመጣው የትምህርት ሕይወታችን ገጽታዎች ውስጥ ለምርምር ታላቅ ዕድል አለ።

ዛሬ የ'ግዙፍ ውሂብ' ውዳሴዎች በየዩንቨርስቲው የገለጻ አዳራሾች፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤቶች ይዘመራሉ። ይህ ልማድ ሁለት ተጽዕኖዎች አሉት። የመጀመሪያው ብዙ ቁጥር ያላቸው የውሂብ ነጥቦች፣ ወይም በብዛት የተጠራቀሙ ፕሮፋይሎች፣ ንኡሳን ባሕርያት፣ የቁልፍ መጫኖች፣ የብሌን ክትትሎች ወይም የኤሌክትሮኒክስ ምልክቶች ከሌሉ ምንም ዓይነት ንድፍ ተለይቶ ሊታወቅ አይችልም የሚል ግምት ይዞ መነሣት ነው። እንደ አንድ የውሂብ ትንታኔ አመክንዮ ደግሞ፣ ያለ ንድፍ፣ ትርጉም አይኖርም። ሁለተኛው ተጽዕኖ ውሂብን የማየት ስውር ዝንባሌ ነው፤ በተለይም በዲጂታል ቴክኖሎጂ ውስጥ እንደ ዋናው የዕውቀት ዓይነት በጥሩ ሁኔታ የሚጫወተውን በቁጥር ሊገለጽ የሚችል ውሂብ። አሁን የውሂብ ሳይንስ እንደ ልዩ የቴክኒክ ዕውቀት መስክ መወለዱን ተመልክተናል፤ ደግሞም በብዙ ዘርፎች እንደሆነው፣ የውሂብ ሳይንስ በትምህርትም ውስጥ አሳማኝ የሆኑ ትረካዎችን እና ማብራሪያዎችን በመቅረጽ ረገድ ትልቅ ሚና አለው።

ተመራማሪዎች፣ እንደ የትኞቹም መሳሪያዎች፣ በዲጂታል የምርምር መሳሪያዎች አማካይነት ምን ሊገኝ እንደሚችል እና ምንስ እንደማይችል ማጥራት አለባቸው። በሚሠራው ምርምር ዓላማ ላይ በመመሥረት፣ ብዙ ውሂብ የግድ የተሻለ ወይም ትክክለኛ አይደለም። አቋማችን መሳሪያን ያማከለ ሳይሆን፣ ዓላማን ያማከለ የምርምር አጀንዳ እና ባሕል እንዲኖር ነው። ኮምፒውተሮች ሊደርሱባቸው የሚችሏቸው ግንዛቤዎች፣ የሰው ልጆች ከሚያገኟቸው ጋር ተመሳሳይ አይደሉም። አንዳንድ ጊዜ ሶፍትዌሮች አስገራሚ እና አብሪ ግኝቶችን ሊገልጡ ይችላሉ፤ ምክንያቱም መረጃን ሰዎች በአናሎግ ዘዴዎች ሊያብላሉ ከሚችሉበት መጠን እና ፍጥነት በላይ ውሂብን የማብላላት ችሎታ አላቸው። በሌላ ሁኔታ፣ የሰው አእምሮ ዐውዶችን፣ ትርጓሜዎችን፣ እሴቶችን እና አንድምታዎችን ለሰው ሠራሽ አስተውሎት እጅግ በሚረቅ መንገድ መረዳት ይችላል።

ተመራማሪዎች በትምህርት ውስጥ ያለው ግዙፍ ውሂብ እና የዲጂታል መሳሪያዎች ሰፊ እምቅ አቅም ላይ ስለሚመሠረቱ፤ ለግምታዊ ተጨባጭነት አቀራረብ ብለን በዲጂታል አናሊቲክ ሶፍትዌር ፍቅር ከመውደቅ ራሳችንን መጠበቅ አለብን። በተለይም የዲጂታል የምርምር ዘዴዎቻችንን አድልዎ እና ጉድለቶች በፍትሐዊነት እና ሚዛናዊነት መነፅር በማየት ከመርሐ ግብሩ አወጣጥ ጀርባ ያለውን ነገር በተከታታይ መገምገም አለብን። እነዚህ አዝማሚያዎች በዚሁ ከቀጠሉ፣ በ2050 አብዛኞቹ ዕውቀቶቻችን ወደ መጠናዊ፣ ለሥልተ ቀመር ተስማሚ፣ ሞለኪውላዊ፣ በቀላሉ ሊከማቹ የሚችሉ፣ በፍጥነት ሊጋሩ የሚችሉ በዲጂታል መሳሪያዎች በኩል ብቻ የሚገኙ ቅርጾች እንደሚሆኑ ትልቅ ስጋት አለ። በፍጥነት እያደገ እና እየተስፋፋ ያለው የሰው ሠራሽ አስተውሎት መስክ እነዚህን ባሕርያት ራሳቸውን እንዲችሉ፣ ራስገዝ እንዲሆኑ እና ከሰዎች አስተዳደር ነጻ እንዲወጡ ለማድረግ መፈለጉ ሊያሳስበን ይገባል። እንደዚህ ዓይነት ምኞቶች የሚፈጥሯቸው የሥነ ምግባር ሥጋቶች በሚቀጥሉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ ንቁ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል።

# የትምህርትን ወደፊቶች መፍጠር

በትምህርት ውስጥ ኢኖቬሽን/ፈጠራ የሙከረት፣ የመጋራት፣ የማስረጽ እና ሌሎችን የማነሣሳት ችሎታን ያንጸባርቃል። መምህር ከግለሰብ ተማሪ ወይም ከክፍል ጋር ከሚሠራበት፣ እስከ ትምህርት ቤት አቀፍ ወይም አገር አቀፍ አቀራረቦች ድረስ በማንኛውም ቦታ እና መለኪያ ሊከወን ይችላል። ኢኖቬሽን ብዙውን ጊዜ ከሌሎች መምህራን፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ ተመራማሪዎች እና ትምህርት ቤቶች ጋር በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ካሉ ተመክሮዎች እና ስኬቶች የሚገኝ የብዙ ትብብር እና መነሣሳት ፍሬ ነው።

## ፖሊሲ እና መርሐ ግብሮችን መቅረጽ፣ መዋስ እና ማላመድ

ልምምዶችን እና ፖሊሲዎችን በማጋራት የትምህርት ተመክሮዎችን እና ፈጠራዎችን ወደ አዲስ መቼቶች ማስረጽ ወሳኝ ይሆናል። በንጽጽር የመማር ግፊት አመለካከቶችን በማስፋት እና በአሜንታ የተቀበልናቸውን መለዮዎች እና ግምቶችን በመመርመር "የለመዱትን እንግዳ የማድረግ" ኃይል አለው። ማላመድ እና ውሰት በየራሳቸው የመማር እና የኢኖቬሽን ሂደቶች ተደርገው መታየት አለባቸው። በዚህ ሪፖርት ውስጥ በተለዩት ደንጋጊ መርሆች መሠረት፣ ዐውዳዊ ሁኔታዎችን፣ ተመክሮዎችን እና ነባር ዕውቀቶችን ከግምት ስናስገባ፣ ሁላችንም ከሌሎች ቦታዎች የሚገኙ ተመክሮዎችን ማድነቅ እና በእነርሱም አማካይነት መነሣሳት እንችላለን።

በትምህርት ሥርዓቶች ውስጥ ያሉ ተዋናዮችም ለፈጠራዊ አቀራረቦች እና ግንዛቤዎች ጠቃሚ ምንጮች ናቸው። ሙሉ በሙሉ ከመስኩ "ውጭ" የተጫኑ ኢኖቬሽኖች በግኝቶቻቸው እና በሚያቀርቧቸው የመፍትሄ ሐሳቦች ውሱን ወይም የተዛቡ ይሆናሉ። የትምህርት ዕውቀት በተለያዩ መንገዶች ተመርቶ፣ ትክክለኛነቱ ይረጋገጣል። ሁሉም ማዕከላዊ ተዋናዮቹም - መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ርእሳነ መምህራን፣ ትምህርት ቤቶች፣ ወዘተ - የምርምር እና የፈጠራ ሥራዎች ተሳታፊዎች ናቸው። የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ማሻሻያ፣ በተጠቃሚዎቹ አስተዋጽኦ ነው የሚበለጽገው፤ በተለይም በየጋራ ዕውቀት ውስጥ ወደ ጥልቅ ተሳትፎ ሲገቡ። መንግሥታት በዚህ ረገድ፣ መምህራን እና ትምህርት ቤቶች በሕዝብ ትምህርት ሥርዓቶች እና ሂደቶች ውይይት እና ክለሳ ላይ እንዲሳተፉ በቂ ድጋፍ የማድረግ ትልቅ ሚና አላቸው።

የመለኪያ ጉዳይ ብዙውን ጊዜ በምርምር እና ኢኖቬሽን ውስጥ ይነሣል። ተስፋ ሰጪ ተመክሮ ሊጠቅም እና ሊጋራ ይችላል። ሆኖም "ምርጥ ተመክሮዎች" ራሳቸው ብዙውን ጊዜ ወደ ውጤት ያደረሱትን ሂደቱን ወይም ሁኔታውን ከመዘርዘር ይልቅ በውጤቶቹ ላይ ያተኩራሉ። የትብብር መረቦችን እና የተማሪ ማኅበረሰቦችን - በመምህራን፣ ትምህርት ቤቶች፣ የዕውቀትና ክህሎት ስፔሻሊስቶች፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ ወዘተ ላይ - መጨመር በተለያዩ ዐውዶች የሥርዓተ ትምህርት፣ የመርሐ ግብር እና የፖሊሲ ግንዛቤዎችን ጊዜውን የጠበቀ ጥናት እና ትግበራን ለመደገፍ ይረዳል። የትህትና ሥነ ምግባር ማንኛውንም ትምህርታዊ ኢኖቬሽን ከተመሠረተበት ታሪክ እና ዐውድ ከሚነጥሉት ግምቶች ለመጠበቅ ይረዳል።

ዩንቨርስቲዎች፣ የምርምር ተቋማት እና አጋሮቻቸው ትምህርትን እንደ የጋራ ጥቅም ለማደስ እና ለትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውል አብሮ ግንባታ ለሚያግዝ ምርምርና ኢኖቬሽን ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ጥሪ ቀርቧል። ነገር ግን ራሳቸውም ቀድሞውኑ ትምህርት ውስጥ እየሠሩ፣ እያሰቡበት፣ ሐሳባቸውን እያቀረቡበት ካሉት - ከመምህራን፣ ተማሪዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ቤተሰቦች፣ ማኅበረሰቦች - ጋር ቢገናኙ እና ቢወያዩ የበለጠ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ። ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተጠቀሰው፣ ክፍት እና ተደራሽ የጋራ ዕውቀት ከማፍለቅ አንጻር የዩኒቨርስቲዎችን ሕዝባዊ ተልእኮ ማደስ እና ለራሳቸው እና ለሰው ልጅ ጥቅም ሲሉ ለዕውቀት ዕድገት የሚተጉ የአዳዲስ ተመራማሪዎች እና ባለሙያዎች ትውልድን በትምህርት መፍጠርን ይጠይቃል።

*ዩንቨርስቲዎች፣ የምርምር ተቋማት እና አጋሮቻቸው ትምህርትን እንደ የጋራ ጥቅም ለማደስ ለሚያግዝ ምርምርና ኢኖቬሽን ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ጥሪ ቀርቧል።*

ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም በትምህርት ወደ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ውስጥ ለምርምር እና ፈጠራ ዕድገት የሚያግዙበት ልዩ እና ጠንካራ ሚና አላቸው። ከዚህ ሪፖርት በኋላ፣ ዩኔስኮ እርስበርሳቸው የሚነጋገሩ፣ እና በየራሳቸው መንገድ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የቀረቡትን ሐሳቦች ዕውን የሚያደርጉ የተመክሮዎች ቢጋር እንዲያዘጋጅ ተጋብዟል። የዓለም ለውጥ ፍጥነት እና የአዳዲስ ዕውቀቶች መገኘት፣ የዚህን ሪፖርት ተለዋዋጭነት እና በየጊዜው እንደገና ሊጻፍ መቻል ይጠይቃል።

## ግምገማ፣ ሙከረት እና ደረጃ ማውጣት

ግምገማ እና ጽብረቃ በትምህርት መርሐ ግብሮች እና ፖሊሲዎች የሕይወት ዑደት ውስጥ አስፈላጊ ሂደቶች ናቸው። ግምገማዎች አንድን መርሐ ግብር ወይም የፖሊሲ ንድፍ ያነሣሱት ዓላማዎች በተግባር እየተፈጸሙ ያሉት መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል። የመርሐ ግብሩን እና የንድፉን ውጤቶች መረዳት እና መግለጽ ይችላሉ፤ ከሁሉም በላይ፣ የታቀዱትን እና ያለ ዕቅድ የተገኙትን ውጤቶች መመዝገብ አለባቸው። ለምሳሌ፣ አንድ መርሐ ግብር ወይም ፖሊሲ አጠቃላይ እኩልነትን አጉድሎ፣ ለአንዳንዶች ግልጽ ጥቅም እያስገኘ ከሆነ፣ ወይም የረጅም ጊዜ ጽናትን ትቶ፣ የአጭር ጊዜ አፈጻጸምን የሚያበረታታ ከሆነ፣ የዚህ ፕሮጀክት መነሻ ግምቶች በፍጥነት ሊጤኑ ይገባል።

በዚህ ሪፖርት የትብብር ሥነ ምግባር መሠረት፣ ግምገማ በትምህርት ሥርዓቶች ውስጥ ያሉትን - መምህራንን፣ ተማሪዎችን እና ትምህርት ቤቶችን - የአንድን ኢኖቬሽን ተግዳሮቶች፣ ድክመቶች ወይም ጥንካሬዎች የመለየት ብቻ ሳይሆን፤ ለለውጦቹ፣ መሻሻሎቹ ወይም ለመሠረዙ ትርጉም ያላቸው ዕድሎችን የማንጸባረቅ አቅማቸውንም መጠቀም ይኖርበታል። ከሁሉም በላይ፣ በፈጠራ ንድፍ፣ ግምገማ እና የውሳኔ ሐሳቦች መካከል ያለውን ትስስር የሚያረጋግጥ ግልጽ የትንታኔ ማዕቀፍ ያስፈልጋል።

ሙከራ፣ ሙከረት እና ዘፈቀዳዊ የቁጥጥር ሙከራዎች መነሻ ግምቶችን ለማረጋገጥ፣ ቴክኒኮችን ለማስተካከል፣ የተሳሳቱ ስሌቶችን ለማረም እና ለአጠቃላይ ድምዳሜ አብቂነት ወሰኑን ለመረዳት ይረዳሉ። ውስብስብ በሆኑ ሥርዓቶች ውስጥ ተለዋዋጮችን የመለየት ችሎታ ግን በጥንቃቄ ማሰብ እና የተራቀቀ ንድፍ ያስፈልገዋል። በወሳኝ መልኩ፣ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ለመቅረጽ የትብብር ሥነ ምግባርን ስናራምድ፣ በሰዎች ላይ ሙከረት የማናደርግበትን የሥነ ምግባር መርሆ ማስታወስ አለብን። ሁሉም ሰዎች - ተማሪዎች፣ አስተማሪዎች እና ቤተሰቦች - ስለ ራሳቸው ትምህርት እና ዕድገት በመማር ውስጥ ሙሉ ተሳታፊ ተደርገው መታየት አለባቸው። በትምህርታዊ ተመክሮዎች ውስጥ ምን ያህል ሰፊ ጣልቃገብነቶች ወይም ለውጦች እንዳሉ እየተሰሙ ያሉ ተጽዕኖዎችን ለመረዳት 'የተፈጥሯዊ' ሙከረቶችን ማድረግ በሚቀጥሉት ዓመታት በተለይም በአድማሱ ላይ ካሉ ጉልሕ ለውጦች እና ነውጦች አንጻር አዲስ ግንዛቤን ይሰጣል። የዚህ ዓይነት ትንታኔዎች የትምህርትን ለውጥ የመቋቋም ጽናት እና የለውጥ ምላሽ ሰጪነት የምንገነዘብበትን የአርቆ ማስተዋል ዕውቀት ሊሰጡን ይችላሉ።

ለማንጸባረቅ፣ ለማሻሻል ወይም ለመነሳሳት፣ ወይም ለበለጠ ጥያቄ፣ የትኩረት ወይም የድጋፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ቦታዎች ለማጉላት ጠቃሚ ንጽጽሮችን ማድረግ ይቻላል። ነገር ግን፣ በጣም ብዙ ጊዜ፣ ንጽጽሮች እና ደረጃዎች ለቅጣት፣ የገንዘብ ድጋፍን ለመከልከል ወይም የቤተሰብ ምዝገባን በጣም ለሚፈልገው አገልግሎት እንዳይመዘገብ ለማድረግ ይውላሉ። ንጽጽር ተመክሮን ሲደፈጥጥ፣ ምኞቶችን አንድ ወጥ ሲያደርግ እና የአውድ፣ የሀብቶች እና የታሪካዊ ሁኔታዎችን ስብጥር ችላ ሲል ብዙም አይጠቅምም።

በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የንጽጽር ደረጃዎችን የሚያገኙበትን መንገዶች እንደገና ማጤን አስፈላጊ ይሆናል። በቅን ልቦና፣ በሥነ ምግባር፣ እና ሥረወጥነትን ሳይጭኑ ማነጻጸር አስቸጋሪ ነው። በጣም የተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በተቃራኒ አውድ ውስጥ የሚሠሩ፣ የራሳቸው ልዩ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲወዳደሩ ሲገደዱ ንፅፅር ችግር ይፈጥራል። በሀብት እና በምርምር የተጠናከሩ የዩኒቨርሲቲዎች ልሂቃን ሞዴሎች፣ ብዙውን ጊዜ አካባቢያዊ አግባብነትን እና የአካባቢ ተማሪዎችን እና ማኅበረሰባቸውን ፍላጎቶች አስዘንግተው፣ ባልተመጣጠነ ሁኔታ የሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምኞት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

ነገር ግን ለደረጃ አሰጣጥ እና በፉክክር ለተመራ ተቋማዊ ሥረወጥነት ተጠያቂዎቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቻ አይደሉም። መንግሥታት እና የዓለም አቀፍ የፖሊሲ ማኅበረሰቡ የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓቶች ምርምር ተኮርነት የሚያስከትለውን ውጤት አርቆ ማየት ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው። ዓለም አቀፋዊው ብዙኃን ትምህርት ለሚከታተሉባቸው አብዛኛዎቹ ተቋማት የበለጠ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ተቋማት የተማሪዎቻቸውን ትምህርት፣ ሙያዊ የወደፊት ተስፋ እና ማኅበረሰባቸውን ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ እንደሚያገለግሉ፤ ተቋማት የሲቪል ንግግሮችን እና የፖለቲካ ክርክሮችን እንዴት እንደሚደግፉ፤ ተቋማት አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፍትሕን ምን ያህል እንደሚያሳድጉ - እነዚህ ብዙውን ጊዜ የሚታለፉ ነገር ግን ሁሉም ሊማሩባቸው የሚችሉ የንፅፅር ነጥቦች በጣም ጠቃሚ ናቸው። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለው ምዘና

የተወዳዳሪነት ደረጃ ከመስጠት ማለፍ አለበት፤ ይልቁንም በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዘንድ የማስተማር እና የምርምር አቅሞችን በማሻሻል ሕዝባዊ ተልእኳቸውን እንዲወጡ ለማድረግ መሞከር ይገባዋል።

# የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች

ወደ 2050 ስንመለከት፣ ለትምህርት ወደፊቶች ከሚያስፈልገው ምርምር እና ኢኖቬሽን ጋር የተያያዙ አራት ቁልፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች አሉ፦

- **ኮሚሽኑ ስለትምህርት ወደፊቶች አጠቃላይ፣ ዓለም አቀፋዊ፣ የጋራ የምርምር አጀንዳ እንዲቀረጽ ጥሪ ያቀርባል።** ይህ የምርምር መርሐ ግብር የሁሉንም ሰው የመማር መብት ያማከለ መሆን፤ ወደፊት የሚፈጠሩ ነውጦች እና ለውጦችን መመርመር እና በዚህ ሪፖርት ክፍል ሁለት ውስጥ ስለተቀመጡት መርሆዎች ግንዛቤን እና ተመክሮን ማሳደግ አለበት። በዚህ ሪፖርት መንፈስ ይህ የምርምር መርሃ ግብር ከወደፊት ዕውቀት እና ከወደፊት አስተሳሰብ አንጻር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እንደገና ማደራጀት አለበት።
- **የትምህርት ወደፊቶች ዕውቀት፣ ውሂብ እና ማስረጃዎች ልዩ ልዩ የዕውቀት ምንጮችን እና የማወቅ መንገዶችን ማካተት አለባቸው።** ከተለያየ አመለካከቶች የሚገኙ ግንዛቤዎች እርስበርስ ከመገፋፋት እና ከመተካካት ይልቅ፣ ስለ ስለ ትምህርት የጋራ ግንዛቤ መጨበጥ የሚያስችሉ አውታረ ብዙ ዕይታዎችን ያቀርቡልናል።
- **ትምህርታዊ ኢኖቬሽን በልዩ ልዩ ዐውዶች እና ቦታዎች ላይ በጣም ሰፊ ዕድሎችን የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት።** ንጽጽር እና ተመክሮዎች አንዱ አንዱን ለማነሣሣት ቢያስችሉም፣ በተለየ ዐውድ ውስጥ ለተለዩ ማኅበራዊ እና ታሪካዊ ዕውነታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት አለባቸው።
- **ስለ የትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውል የሚደረግ ምርምር ወደፊት ያራምዱት ዘንድ የተጋበዙትን ሁሉ በሚያካትት መልኩ እንደገና መደራጀት አለበት። በተለይ በመምህራን፣ በተማሪዎች እና በትምህርት ቤቶች ዘንድ ዘሩ ተዘርቷል።** የትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውልን አብሮ ግንባታ የሚያፋጥን የምርምር አጀንዳን በመቅረጽ የመሳተፍ እና የመደገፍ ልዩ ኃላፊነቶች በምርምር ተቋማት፣ መንግሥታት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ላይ ያርፋሉ።

# ምዕራፍ 9

# የዓለም አቀፍ አጋርነት እና የዓለም አቀፍ ትብብር ጥሪ

*አዲስ ማኅበራዊ ውል በማኅበረሰቦች ውስጥ ወጣቶች በክብር እንዲኖሩ ያስችላቸዋል፤ ሴቶች ከወንዶች ጋር ተመሳሳይ ተስፋዎች እና ዕድሎች እንዲኖሯቸው ያደርጋል፤ እንዲሁም የታመሙትን፣ አቅመ ደካሞችን እና ሁሉንም ዓይነት አነስተኛ ቁጥርና የእድገት ደረጃ ያላቸውን ማኅበረሰቦች ይጠብቃል... በአንድ ትውልድ ውስጥ በሁሉም ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ውስጥ ያሉ ሕፃናት በየደረጃው ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘት ይችላሉ። ይህ ይቻላል። ይህን ለማድረግ መወሰን ብቻ ነው ያለብን... ክፍተቶችን ለመዝጋት እና አዲሱን ማኅበራዊ ውል ተግባራዊ ለማድረግ ሥልጣን፣ ሀብትና ዕድሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ በስፋትና በፍትሐዊነት መዳረሳቸውን የሚያረጋግጥ፣ አዲስ ሉላዊ ስምምነት ያስፈልገናል።*

አንቶኒዮ ጉቴሬዝ፣ የተመድ ዋና ጸሐፊ፣ ኔልሰን ማንዴላ ሌክቸር፣ ጁላይ 18፣ 2020።

**አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ለማፋጠን፣ ትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም የሚደግፍ፣ በአካባቢ፣ በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ባሉ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ባለድርሻዎች መካከል ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ ሕብረትን ለሚያመጣ ዓለም አቀፍ ትብብር እንዲፈጠር ለአዲስ ቁርጠኝነት ጥሪ ያቀርባል።**

ትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም የመቁጠር መርህ ከዓለም አቀፍ ኃላፊነት ጋር በማይነጣጠል ሁኔታ የተያያዘ ነው። በ2020 እና 2021፣ በመንግሥታት፣ በሕዝብ እና በግል አካላት እና በሲቪል ማኅበረሰብ የተደገፈ፣ ለኮቪድ-19 ክትባቶችን ለማዘጋጀት በዓለም ዙሪያ ያሉ ሳይንሳዊ ማኅበረሰቦችን ታይቶ የማያውቅ ያስተባበረ ቅስቀሳ አይተናል። ሆኖም ይህ አስደናቂ ምሳሌ የሰው ልጅ የወደፊት ዕጣ ፈንታ አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ዓለም አቀፍ ሳይንሳዊ ትብብር ምን ሊያደርግ እንደሚችል የሚያሳይ ቢሆንም፣ የእነዚያኑ ክትባቶች አቅርቦት ፍትሐዊነት ማረጋገጥ በጣም ከባድ ዓለም አቀፍ ፈተና ሆኖ ንቅናቄውም ልሳኑ ተዘግቷል። ሁሉም ደኅና እስካልሆኑ ድረስ ማንም ሰው ደኅና እንደማይሆን በሰፊው ቢታወቅም፣ የክትባት ብሔርተኝነት ለዓለም አቀፉ የጋራ ጥቅም በጋራ ለመሥራት ያሉብንን ከባድ የአቅም ክፍተቶች አሳይቷል።

> *የክትባት ብሔርተኝነት በጋራ ለመሥራት ያሉብንን ከባድ የአቅም ክፍተቶች አሳይቷል።*

ትምህርት በዘመናችን የሚያጋጥሙንን ዋና ዋና ተግዳሮቶች ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑትን የሰው ልጅ ብልኅትን እና ለጋራ ተግባር ያለንን አቅም ያዳብራል። ስለዚህ ዛሬ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከየትኛውም ጊዜ በላይ የበለፀገ፣ ፍትሐዊ፣ ዘላቂ እና ሰላም የሰፈነበት ዓለም ለመገንባት፣ ሁሉም ሰዎች መነሻቸው፣ ባሕል እና ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን፣ በዕድሜ ዘመናቸው ጥራት ያለው ትምህርት ሊያገኙ ይገባል። የመደበኛ ትምህርት እና የመማር ተደራሽነት በፍትሐዊ የዕውቀት እና የመረጃ ተደራሽነት መሟላት አለበት፡- ሁሉም ሰው በሁሉም ቦታ ዲጂታል ተደራሽነት ያስፈልገዋል። የማንኛውም ሰው ጤና ከሁሉም ጤና ጋር የተቆራኘ እንደሆነው ሁሉ፣ የወደፊት ሕይወታችንም የሚወሰነው የሁሉንም ሕፃናት፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች ትምህርታዊ ፍላጎቶችን በማሟላት ላይ ነው፤ ይህም የጋራ የወደፊት ሕይወታችንን በመቅረጽ እና በመምራት ረገድ በጥንቃቄ እና በንቃት መሳተፍ ያስችላቸዋል።

ይህ ትምህርትን እንደ አንድ የጋራ ጥቅም መገንዘብ የትምህርትን ዓለም አቀፍ ትብብር እና በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የትምህርት የሚደረግ ሕዝባዊ የገንዘብ ድጋፍ ለማጠናከር መሠረት መሆን አለበት። የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በቅርቡ እንደሞገቱት ሁሉም ሕፃናት እና ወጣቶች ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ የበለጠ ፍትሐዊ እና ዘላቂ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት ለመፍጠር ወሳኝ ምሰሶ ነው። የመማር መብትን የማክበር፣ የመጠበቅ እና የማክበር ግዴታ በእያንዳንዱ አገር ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ላይም ጭምር የተጣለ ነው።

# ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ ለሆነ የዓለም ሥርዓት ምላሽ መስጠት

ዓለም አቀፍ የትምህርት ትብብር ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ በሆነው የዓለም ሥርዓት ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የዓለምን ማኅበረሰብ የሚያስተሳስሩት የጋራ ሁለንታዊ እሴቶች በእጅጉ እየተሸረሸሩ ባሉበት ሁኔታ ነው። እንደ የተባበሩት መንግሥታት ያሉ የጋራ ግቦችን ለማቋቋም እና ዓለም አቀፍ የጋራ ተግባራትን የማደራጀት ኃላፊነት ያለባቸው ዓለም አቀፍ መድረኮች ከባድ ትችት እና የፊስካል ችግር ይደርስባቸዋል።

*መንግሥታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች እና ሲቪል ማኅበረሰብ - በሃያኛው ክፍለ ዘመን የአገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶችን የማሳደግ ኃላፊነት ያለባቸው ድንበር አስፋፊዎች እና ደንብ ቀያሪዎች - ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበታተነ በመጣ የዓለም ሥርዓት ውስጥ ዘላቂ ጥምረት እና ጥምረት ለመፍጠር ይታገላሉ። የሥራ ስፋታቸው በድህረ ወረርሽኝ ባሉ ዓለማቀፍ ኢኮኖሚያዊ ዕውነታዎች ምክንያት የሚያገኙት የፋይናንስ ድጋፍ ስለሚቀንስ ይጎዳል። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግልፅ በሆነ መንገድ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን እና የመረጃ ፍሰትን የመቆጣጠር አቅማቸውን እያፈረጠሙ ያሉ*

ሊበራል ያልሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች በተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ማግለጫ ላይ ከተመዘገቡት እሴቶች እና በቅርብ ጊዜያት በግልጽ ከተቀመጡት የዘላቂ ልማት ግቦች ጋር በሚፃረሩ መንገዶች፣ በራሳቸው መንገድ ደንብ ቀያሪዎች እና አስተማሪዎች ሆነው እየመጡ ነው።

ያለፈው ግማሽ ምዕተ ዓመት የኢኮኖሚ ለውጦች ቢያንስ እንደ እነዚህ የፖለቲካ ለውጦች ጥልቅ ናቸው። የቴክኖሎጂ እና ሳይንሳዊ ዕድገቶች ከኢኮኖሚ ግሎባላይዜሽን ጋር ተደምረው ለብልጽግና መሻሻል፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለቤተሰብ ድህነት መቀነስ እና ለተሻለ የትምህርት ተደራሽነት አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ነገር ግን 'ዝርግ' እና የበለጠ ክፍት ዓለም በመፍጠራቸው ከእንግዲህ አይከበሩም። የኤኮኖሚ ዕድገት ሀብት ላላቸው ሰዎች ኃይለኛ መንደር ፈጥሯል። የቴክኖሎጂ ዕድገት ከአዳዲስ የኢኮኖሚ እና የመረጃ ሞኖፖሊ ዓይነቶች ጋር ተያይዞ የሊበራል ዲሞክራሲን መሠረት አደጋ ላይ ጥሎታል። በኢኮኖሚ ዕድገትና በዴሞክራሲ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር የረጅም ጊዜ ተስፋ ቢኖርም፣ በአገሮች ውስጥም ሆነ በመካከላቸው ያለው የጋራ ተግባር እና የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር አቅሞች ከቅርብ ዐሥርት ዓመታት ወዲህ በተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ባልተጠበቀ ሁኔታ ተገድበዋል።

በአሳዛኝ ሁኔታ በአየር ንብረት እርምጃዎች ላይ፣ እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ትብብር አስፈላጊ በሆነባቸው መስኮች (ፍልሰት፣ ሰላም፣ የመረጃ ገመና) የተደረገው አዝጋሚ መሻሻል፣ ከቅርብ ዐሥርት ዓመታት ወዲህ ስለዓለም አቀፍ የጋራ ሀብቶች እና ድሆችን ባልተመጣጠነ መንገድ እየጎዱ ያሉትን የጊዜውን ተግዳሮቶች ለመቋቋም ስለሚያስፈልጉት ዓለም አቀፍ የትብብር ዓይነቶች ውሱን መግባባት (ወይም የመስማማት አቅም) ነው ያለው።

የአሁኑ የተባበሩት መንግሥታት ማሻሻያዎች ለዚህ ባለብዙ ጎን ቀውስ ምላሽ ለመፍጠር ይሞክራሉ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሦስት አዳዲስ አቀራረቦች ቀርበዋል፦ የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን በዓለም አቀፍ አስተዳደር ውስጥ በአጋርነት ማካተት፣ ከላይ ወደ ታች የሚደረግ እንቅስቃሴ፤ ወደ ማዕከለ-ብዙነት መራመድ፤ እና አዲስ ቀጣናዊ ትብብር ዓይነቶች፣ በተለይም የደቡብ-ደቡብ እና የሦስት ማዕዘን ትብብር።

## ከእርዳታ ወደ አጋርነት

ዓለም አቀፍ የትምህርት ትብብር በአስኂ የዓለም ሥርዓት ውስጥ የሚሠራ ብቻ ሳይሆን ለዚያም ምላሽ የሚሰጥ መሆን አለበት። አዲስ ዓለም አቀፋዊ የትምህርት ስምምነትን ዕውን ለማድረግ የታደሱ የዓለም አቀፍ ትብብር ዘዴዎችን ይጠይቃል። ከዚሁ ጎን ለጎን፣ የትምህርት ተቋማት ራሳቸው ስለ ወቅታዊ ተግዳሮቶች እና በተለይም ስለ የወጣቶች የጋራ ተግባር አስፈላጊነት ሰፋ ያለ ግንዛቤ የሚኖርበትን መሠረት ለመጣል ይረዳሉ።

ታሪክ እንደሚያሳየን ዓለም አቀፉ የትምህርት ትብብር ንድፍ ከሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ጂኦፖለቲካዊ ጥቅሞች ፍላጎት ጎን ለጎን በቅኝ አገዛዝ ቅኝት የተቀረጸ ነው። ይህ ኪነ ሕንፃ ከሰሜን ወደ ደቡብ በሚደረጉ የፋይናንስ እና የሐሳቦች ፍሰት ይገለጻል። ዓለም አቀፍ የትምህርት ልማት እና የውጭ ዕርዳታ አሁንም ችግር አለባቸው። ትምህርት ከአጠቃላይ ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ (ኦዲኤ) የሚያገኘው በጣም ትንሽ ድርሻ ብቻ ሳይሆን፣ ለትምህርት የሚሰጠው ዕርዳታ መካከለኛ ገቢ ወዳላቸው አገሮች ያደላ ነው። ከሰሃራ በታች ላሉ የአፍሪካ አገሮች የሚሰጠው የትምህርት ዕርዳታ እየቀነሰ ነው - በ2050 የዓለም ከፍተኛውን የወጣቶች ድርሻ በምትይዘው፣ እና በምድር ላይ ካሉ ቀጥተኛ የአካባቢ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መካከል አንዳንዶቹን ትጋፈጣለች ተብላ ለምትጠበቀው አህጉር ዕርዳታው ቀንሶባታል።

ከዚህም በላይ፣ የትምህርት ኦፊሴላዊ የልማት ዕርዳታ በተለይም ትልልቅ ኢኮኖሚ ያላቸውን የቡድን ሰባት ለጋሽ ሀገራት ከፍተኛ ትምህርት፣ በተለይም ስኮላርሺፕን የመደገፍ አዝማሚያ አለው። ሁለንታዊ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተደራሽነት እና ጥራት ያለው የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ለማረጋገጥ የሚደረገው ድጋፍ በጣም አናሳ ነው። የልጅነት መሃይምነትን ለማጥፋት የጋራ እርምጃ አሳማኝ ዓለም አቀፍ ስትራቴጂ - በተባበሩት መንግሥታት ለመጀመሪያ ጊዜ በሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የጸደቀው ግብ - ገና አልተሳካም። የማይነቃነቅ የሕፃናት ቁጥር አሁንም ከትምህርት ገበታ ውጪ እንደሆኑ ናቸው፤ እና ብዙ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት እና ወጣቶች ትምህርታቸውን ቢከታተሉም፣ የሚማሩት ግን ጥቂት ነው። የስደተኞች እና ያለፈቃዳቸው የወጡ ፍልሰተኞች የትምህርት ፍላጎቶችም የገንዘብ እጥረት አለባቸው።

*የስደተኞች እና ያለፈቃዳቸው የወጡ ፍልሰተኞች የትምህርት ፍላጎቶችም የገንዘብ እጥረት አለባቸው።*

በትምህርት ዕርዳታ ሰጪዎች መካከል ቅንጅት አለመኖሩ አሁንም ፈታኝ ነው። ይህ በተለይ አብዛኛውን እርዳታ በሚቆጣጠሩት ከሰሜን በመጡ የሁለትዮሽ ድርጅቶች መካከል ዕውነት ነው። ከፓሪሱ የዕርዳታ ውጤታማነት ድንጋጌ ከሃያ ዓመታት ገደማ በኋላ፣ የትምህርት ለጋሾች አሁንም ከአገር ፍላጎቶች ጋር በማይጣጣሙ በተነጣጠሉ፣ ፕሮጀክት ተኮር ዘዴዎች የልማት ዕርዳታን ይሰጣሉ። ለትምህርታዊ ዕድገት የሚረዱ ባለብዙ-ጎን መንገዶች ብዙም ጥቅም ላይ አይውሉም፤ እንዲሁም ኢኖቬሽንን፣ የማስረጃ የተሻለ አጠቃቀምን እና ብሔራዊ አቅሞችን ማጠናከርን በሚደግፉ መንገዶች ሀብቶችን የማሰባሰብ እና የማጣጣም ዕድሎች ጠፍተዋል።

ሆኖም በትምህርት ትብብር ላይ መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ አዳዲስ እና ተስፋ ሰጪ ዕድገቶችም አሉ። ከቅርብ ዐሥርት ዓመታት ወዲህ የሲቪል ማኅበረሰብ በትምህርት ላይ በአካባቢያዊ፣ በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ተሳትፎ እያደገ መጥቷል፤ እና በመንግሥታት እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተዋናዮች መካከልም አዲስ አጋርነት ተፈጥሯል። የደቡብ-ደቡብ እና የሦስት ማዕዘን ቅርጾች የልማት ትብብር እየጨመረ ነው። ጠንካራ የቅርብ ጊዜ የተሟጋችነት ጥረቶች ትምህርትን በዓለም አቀፍ የፖለቲካ አጀንዳ ላይ ከፍ ለማድረግ ረድተዋል። ትምህርት በዓለም አቀፍ እና በክልላዊ የፖለቲካ አካላት አጀንዳ ላይ መገኘቱ እየጨመረ ነው።

ወደፊት፣ ሦስት ዓይነት ዓለም አቀፍ የሕዝብ ሀብቶች በተለይ የጋራ፣ የበለጠ ፍትሐዊ፣ የበለጠ ተገቢ እና የበለጠ ዘላቂ ትምህርታዊ የወደፊት እጣዎችን ለማሳካት አስፈላጊ ይሆናሉ። በመጀመሪያ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ መንግሥታት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውልን ለማሳካት ከሚረዱ አዳዲስ የጋራ ዓላማዎች፣ ደንቦች እና መመዘኛዎች ጋር እንዲጣጣሙ ለመርዳት በጋራ መሥራት አለበት። በሁለተኛ ደረጃ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የትምህርትን የሆነ የዕውቀት ክምችት፣ ጥናት፣ መረጃ እና ማስረጃ ለሁሉም ተደራሽነት እንዲረጋገጥ ኢንቨስት ማድረግ እና ማስተዋወቅ፣ እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የትምህር ባለሙያዎች የትምህርት ሥርዓቶችን ለማሻሻል ማስረጃዎችን ማመንጨት እና መጠቀም እንደሚችሉ ማረጋገጥ አለበት። በመጨረሻም፣ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ድጋፍ መስፋፋት እና ሁለንታዊ የመማር መብታቸው ከፍተኛ ስጋት ላይ የወደቀባቸውን ሕዝቦች ለመደገፍ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

# ለጋራ ዓላማዎች፣ ግዴታዎች፣ ደንቦች እና ደረጃዎች

የተባበሩት መንግሥታት እና ዩኔስኮ ከተፈጠሩበት፣ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ተቀባይነት ካገኘበት ከሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በትምህርት ውስጥ የሚደረግ ዓለም አቀፍ ትብብር ስለ ትምህርት ዓላማዎች እና ግቦች መግባባት በመፍጠር ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ዛሬ፣ ስለ የጋራ ትምህርታዊ ግቦች የመመካከር አስፈላጊነት ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ወሳኝ ነው።

በኢንዱስትሪ የበለጸገውን ዓለም ሐሳቦች እና ተቋማት እየደጋገሙ ከማባዛት ታሪካዊ ትኩረት ርቀን ዓለም አቀፍ ትብብርን ማደስ አለብን። ደቡብ-ደቡብ እና የሦስት ማዕዘን ቅርጾችን ማሳደግ አለብን። በተለይ በተለያዩ የትምህርት ባለድርሻዎች - የመምህራን ማኅበራት፣ የተማሪዎች ንቅናቄዎች፣ የወጣቶች ድርጅቶች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ፣ የግሉ ዘርፍ አቅራቢዎች እና አሰሪዎች፣ በጎ አድራጊዎች፣ መንግሥታት እና ዜጎች - መካከል የተሻሻለ ውይይት እና መግባባት ያስፈልጋል። በረጅም ጊዜ ወደፊቶች ላይ ያተኮረ ትብብር የሕፃናትን እና የወጣቶችን ድምፅ ማዕከል አለማድረግ አይችልም።

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ መራዘም ምክንያት ወደ ሚፈጠር የገንዘብ እጥረት ጊዜ ውስጥ ስንገባ፣ በጋራ ግቦች ዙሪያ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የመምረጥ ፍላጎት በፍጥነት እያደገ ይሄዳል፤ እና የተገቡ ዓለም አቀፍ እና የአገር ውስጥ የፋይናንስ ቃል ኪዳኖች እንደሚፈጸሙ ማረጋገጥም ግድ ይሆናል። የሁለትዮሽ እና የበጎ አድራጎት ፈንድ ለማግኘት ከመወዳደር ይልቅ በማስተባበር፣

እነዚህን ግቦች ለማሳካት የጋራ ድጋፍ እና የገንዘብ ማሰባሰብያ አጀንዳዎችን ለመደገፍ ዓለም አቀፍ ባለድርሻዎች መሰባሰብ አለባቸው።

የጋራ ግቦችን እና የተግባር ማዕቀፎችን በማውጣት የትምህርት ዘርፉ ከአየር ንብረት እና ከጤና ዘርፎች ጠቃሚ ትምህርቶችን መውሰድ ይችላል። ወደ ዓለም አቀፍ ትብብር የሚመጡ ሁሉም ተዋናዮች የየራሳቸውን የተወሰነ፣ በጊዜ ገደብ የተቀመጡ ግቦችን እና ቁርጠኝነትን እንዲያዘጋጁ ለማድረግ የበለጠ መሥራት እንችላለን። ዓለም አቀፍ ትብብር በድጎማ መርህ ላይ መደራጀት አለበት፣ ምክንያቱም ግቡ ይበልጥ የበለጠ ተጨባጭ እና የአገር ውስጥ ባለቤትነት ሲኖረው፣ ለጋራ ዘመቻ እና ተጠያቂነት ዒላማው የበለጠ አዋጭ ስለሚሆን፣ እና የዓላማው ልዩ 'ባለቤቶች' ለተግባራዊነቱ ዋስትና ይሆናሉ። ስለ ባለድርሻዎች ዕድገት በማስረጃ ላይ የተመሠረቱ ግምገማዎችን በማድረግ ለገቧቸው ግዴታዎች እና ግቦች ተጠያቂ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የበለጠ ጠንካራ ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ የክትትል ዘዴዎችን መፍጠር ይቻላል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ፣ የትምህርት ሴክተሩ እና የሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ አካላት በርእሰ ጉዳይ እና በንኡስ ዘርፍ ጉዳዮች ላይ ቅድሚያ የመስጠት ችግር ነበረባቸው፤ ይህም ወደ መግለጫ መአት፣ ወደተበታተኑ ትናንሽ ተግባራት እና ለረጅም ጊዜ የኖሩ እና የተከበሩ አንዳንድ ግቦቻችንን እንኳን ማሳካት ወዳለመቻል መርቷቸዋል። ዓለም አቀፍ ተቋማት ሁሉንም ነገር ለማድረግ መሞከር የለባቸውም። የእነሱ ተግባር የሌሎችን አቅም ማጠናከር ነው። ይህንን ለማድረግ ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ አቅምን በማሳደግ የጋራ መግባባት ላይ የተመሠረቱ ቃል ኪዳኖችን በማረጋገጥ ላይ ማተኮር አለባቸው። ዓለም አቀፋዊ ባለድርሻዎችም ውጤታማ የሚሆኑት የዕውቀት እና የማስረጃ አገናኞች በመሆን የተለያዩ ባለድርሻዎች በዕውቀት ማመንጨት እና አጠቃቀም ላይ መሳተፋቸውን ሲያረጋግጡ ነው። ለከፍተኛ የትምህርት ተግዳሮቶች፣ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች እና በድንገተኛ አውድ ውስጥ ያሉ እንደ የመጨረሻ አማራጭ የገንዘብ ድጋፍ ሰጪዎች በመሆን ጠቃሚ ሚና መጫወት ይችላሉ።

የጋራ የትምህርት የወደፊት ሁኔታዎችን በመቅረጽ ረገድ፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት ትኩረታችንን የረጅም ጊዜ ተግዳሮቶች ላይ እንድናተኩር በመቃኘት ልዩ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ብዙው ምርምር እና ክርክር ለተለወጠው የሥራ እና አውቶሜሽን ዓለም ምላሽ በመስጠት ረገድ ትምህርት የሚጫወተው ሚና ላይ ማተኮር አለበት። ከስደት እና ከአየር ንብረት ለውጥ የሚመጡ ድንበር ተሻጋሪ ውጫዊ ሁኔታዎችን እንዴት በተሻለ ሁኔታ መፍታት በሚቻልበት መንገድ፤ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ዲጂታይዝ የተደረጉ እና በባሕር ተሻጋሪ መንገድ የሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶችን ማስተዳደር በሚቻልበት መንገድ ላይ ማተኮት አለበት።

*ዓለም አቀፍ ተቋማት ትኩረታችንን የረጅም ጊዜ ተግዳሮቶች ላይ እንድናተኩር በመቃኘት ልዩ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።*

በሰፊ የተሳትፎ ሂደቶች እና የጋራ ውሳኔ አሰጣጥ አማካይነት የጋራ አጀንዳ በጋራ መገንባት አለበት። ካለፈው የተወረሱ የትምህርት እኩልነቶችን እና መገለሎችን ለማስተካከል የወደፊቱን ለማስተዳደር ባለው የረጅም ጊዜ ሐሳብ እና በአሁን ጊዜ እርምጃዎች አንገብጋቢነት መካከል ያለውን ውጥረት ማስታረቅ ይገባል።

# የዕውቀት ማመንጨት እና የማስረጃ አጠቃቀም ትብብር

ምርምር እና ማስረጃ በትምህርት ውስጥ አስፈላጊ ዓለም አቀፍ ሀብቶች ናቸው። በአንድነት፣ መንግሥታት እና አጋሮቻቸው የትምህርት ለውጥን ለማፋጠን ችግሮችን እንዲፈቱ እና ኢኖቬት እንዲያደርጉ ይረዳሉ። ለዓለም አቀፍ፣ ቀጣናዊ እና ሀገራዊ ቁርጠኝነት ዓለም አቀፍ ተጠያቂነትን ለማጠናከር መሠረታዊ ናቸው።

ከኢኮኖሚያዊ ትብብር እና ልማድ ድርጅት (ኦኢሲዲ) እስከ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ድረስ ያሉ ዋና ዋና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሥራች ላይ አካል የሌላቸው ውሂቦችን፣ የሊግ ሰንጠረዦችን እና ሌሎች የ'አስተዳደር በቁጥር' ላይ ያላግባብ ጥቅም ላይ ማዋላቸው ብዙ ትችቶች አስከትለዋል። እነዚህ ትችቶች ተገቢ ናቸው፤ ነገር ግን የትምህርት ሥርዓቶችን በፍትሐዊነት

ለማስተዳደር እና የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የጋራ ስታቲስቲካዊ ውሂብ ያስፈልገናል። በጤና እና በአየር ንብረት ሴክተሮች እና በቅርብ ጊዜ ተሻጋሪ የትምህርት ቅስቀሳዎች እንደታየው፣ ዕድገትን ለመከታተል እና ለመገምገም የሚደረጉ ጥረቶች የጋራ ግቦቻችንን ለማሳካት እና የተለያዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለበለጠ ዓለም አቀፍ ተጠያቂነት አስተዋጽኦ ያደርጋል።

እስካሁን ድረስ፣ ዓለማቀፋዊ ባለድርሻዎች የዓለም አቀፍ ማስረጃዎችን እና መረጃዎችን ተገኝነት እና ጥቅም ከፍ ለማድረግ ኢንቨስትመንቶችን ማሰባሰብ እና ማስተባበር አልቻሉም። ከዓለም አቀፍ ጤና በተቃራኒ፣ ዋና ዋና የባለብዙ ወገን ድርጅቶች ጥሩ ጥራት ያለው የክትትል መረጃን ለማምረት ሀብቶችን የሚያዋህዱበት፣ በተባበሩት መንግሥታት ኤጀንሲዎች መካከል የጋራ መደበኛ አቀማመጥ፣ ስታቲስቲካዊ እና ተዛማጅ የአቅም ግንባታ ሚናዎችን የሚደግፍ የትብብር ዝግጅት የለም። ውጤታማ መረጃዎችን ማሰባሰብ እና ማሰራጨት፣ በማስረጃ እና በምርምር ላይ ያሉ ክፍተቶችን መቅረፅ እና አቅምን ማጠናከር ከዓለም አቀፍ ተዋናዮች አዳዲስ የቅንጅት እና የፋይናንስ ደረጃዎችን ይጠይቃል።

ዕውቀትን፣ መረጃንና ማስረጃን የማመንጨትና የመጠቀም አቅምን ለማጠናከር የሚደረገው ድጋፍ በተሻለ የገንዘብ ድጋፍና የተቀናጀ መሆን አለበት። አንዳንድ ጊዜ የዕውቀት እና የምርምር ዓለም አቀፍ ጥረቶች የአንድ ወገን ውይይቶች ይመስላሉ። ይህ ተቀባይነት የለውም። ዓለም አቀፍ ትብብር ከግሎባል ደቡብ ለሚመጡ ሀገራት ለልዩ ሁኔታቸው ተስማሚ የሆኑ አዳዲስ እና ፈጠራዊ የምርምር ሞዴሎቻቸውን እንዲበይኑ ተጨማሪ ቦታ መስጠት አለበት። በጤና ረገድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተደረጉ ጥረቶች አገራዊና አካባቢያዊ አቅምን ማሳደግና አገሮች እርስበርሳቸው እንዲማማሩ ለማድረግ ያለመ ቅንጅታዊ መድረኮችን በመፍጠር ላይ ያተኮረ ነው። በትምህርት ችግር መፍታት ላይ ያተኮረ የደቡብ-ደቡብ ትብብር ላይ ኢንቨስት ለማድረግ አዳዲስ ሞዴሎች አስፈላጊ ናቸው። በምዕራፍ 8 ላይ እንደተገለጸው፣ ይህ አስተሳሰብን ለሚያበለጽጉ እና ሰፊ የፈጠራ መፍትሄዎችን ለሚደግፉ ለተለያዩ ሥነ ዕውቀቶች እና የማወቂያ መንገዶች ልዩ ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል።

ለዓለም አቀፍ ምርምር፣ ማስረጃ እና መረጃ ፋይናንስ ማግኘት ትልቁ የትምህርት ፈተና ነው። ለጤና ከሚመደበው ዓለም አቀፍ ኦዲኤ 25% የሚሆነው በእንደዚህ ዓይነቶቹ ዓለም አቀፍ ሀብቶች (7 ቢሊዮን ዶላር ገደማ) ላይ ይውላል። በ2015 ከ3 በመቶ ባነሰ ኦዲኤ (ወይም 200 ሚሊዮን ዶላር) መጠን ለጋራ ዕውቀት፣ ማስረጃ እና የውሂብ ሀብቶች የገንዘብ ድጋፍ መድቦ ነበር። ለምርምር፣ ዕውቀት እና ማስረጃዎች የሚደረገውን ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍን ለማሻሻል፣ በተባበሩት መንግሥታት ኤጀንሲዎች ቡድን ሥር ለትምህርት ዕውቀት እና ማስረጃ ለማመንጨት ሊመደብ የሚችል ተገማች ፈንድ መመሥረትን የመሳሰሉ አዳዲስ አማራጮች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

# የፋይናንስ ድጋፍ፣ የትምህርት ስጋት ባለበት

በትምህርት ዓለም አቀፍ ትብብርን በመሠረታዊነት እንደገና ማጤን እና በእርዳታ ላይ ካለው ጥገኝነት አመክንዮ መውጣት አስፈላጊ ቢሆንም፤ ከዓለም አቀፍ ዕርዳታ ጋር በትምህርት ላይ ያሉ አዳዲስ ግንኙነቶችን ሚና እና ትኩረት እንደገና መገምገምም አለብን።

ዕርዳታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የሚሄደውን የብሔራዊ ፍላጎቶች ድርሻ ያቀርባል፣ እና እንደዚሁ በዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ ያለው ተፅእኖ እና ጠቀሜታም እየቀነሰ ይሄዳል። ከቅኝ አገዛዝ የመነጨውን የኃይል ሚዛን መዛባት ከማጠናከሩም በላይ፣ የትምህርት ሥርዓቶችን ዘላቂነት ለማጠናከር ያደረገው ጥረት አነስተኛ ነው። በተመሳሳይ፣ ዝቅተኛ እና ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ያላቸውን አገሮች ለመደገፍ የሚያስችል የተመደበ ፋይናንስ ያስፈልጋል - በተለይም በሚቀጥሉት ዐሥርት ዓመታት አብዛኛው ነዋሪዎቿ ወጣቶች በሚሆኑባት አፍሪካ። ዛሬ ዝቅተኛ እና ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት 47 በመቶው እርዳታ ከቅድመ መደበኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚሰጠው ትምህርት ይመደባል። እንዲሁም የአየር ንብረት ቀውሱ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ቁጥራቸው እየጨመረ ለሚሄደው የተፈናቀሉ ሕዝቦች እና ያለፈቃቃድ ስደተኞች የትምህርት ፍላጎቶችን ለመደገፍ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍ መመደቡን ማረጋገጥ አለብን። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ እንደታየው፣ ከችግር እና ድንገተኛ አደጋዎች በኋላ ለአደጋ ምላሽ እና ትምህርታዊ መልሶ ግንባታ የሚሆን ዓለም አቀፍ መጠባበቂያ ፋይናንስ መያዝ ያስፈልገናል።

ከዚህ እስከ 2050 ለመድረስ፣ ሀገራዊ የሀብት አሰባሰብና አገራዊ አቅምን በማጠናከር አዳዲስ ግብአቶችን በማሰባሰብ ክፍተቶችን ለመሙላት እንዲችሉ አሁን ያለን የባለብዙ ወገን ቻናሎች ማሻሻል ይጠበቅብናል። ዓለም አቀፍ ለጋሾች በ2005 የፓሪስን የዕርዳታ ውጤታማነት ድንጋጌን ሲያፀድቁ እንደነበረው፣ በለጋሾች መካከል በአገር ባለቤትነት በተያዙ የትምህርት ዕቅዶች እና አገራዊ ሥርዓቶች ዙሪያ የሚደረግ የላቀ የዕርዳታ እና የማስተባበር ሂደት አሁንም ጠቃሚ ሆኖ ይቆያል።

ጎነ ብዙ ቻናሎች የእርዳታን ውጤታማነት ለማጎልበት የተሻሉ ዕድሎችን ስለሚሰጡ፣ ዕርዳታውን በጣም ለተቸገሩ ሀገራት እና ሕዝቦች የመምራት ዕድላቸው ሰፊ ነው። ነገር ግን እነሱም ፕሮጀክት ተኮር የሆነውን፤ ሳያስፈልግ ተበዳሪዎችን እና እርዳታ ተቀባዮችን በሚያመነጩት ዕውቀት እና መመሪያ ተገዢ የሚያደርገውን፤ እና አገራዊ አቅምን በመደገፍ ረገድ ደካማ ሪከርድ ያለውን አሠራራቸውን ማሻሻል ያስፈልጋቸዋል። በዓለም አቀፍ የሕብረተሰብ ጤና፣ ለምሳሌ፣ እነዚህን ውድቀቶች ለማስተካከል በቅርብ ጊዜ የቀረቡት ሐሳቦች ቴክኒካዊውን ድጋፍ ከፋይናንስ ድጋፍ በኤጀንሲዎች መለየትን እና በባለብዙ ወገን ድርጅቶች መካከል የጋራ የተጠያቂነት ዘዴዎችን ያካትታሉ።

# የዩኔስኮ ሚና

ዩኔስኮ ባለፉት 25 ዓመታት ብዙ ፈተናዎችን ተጋፍጧል። ዓለም አቀፋዊ ንግግሮችን እና የትምህርት ደረጃዎችን የማስተባበር እና የዘላቂ ልማት ግብ 4ን የትምህርት ስኬት የማረጋገጥ መደበኛ ኃላፊነቱን እንደጠበቀ፣ እነዚህን ግዴታዎች በብቃት ለመወጣት ሲታገል ቆይቷል። በትምህርት፣ በሳይንስ እና በባሕል ዙርያ የተሰጠው ኃላፊነት ሰፊ ቢሆንም፣ የዩኔስኮ አጠቃላይ በጀት ከብዙ የአውሮፓ ዩኒቨርስቲዎች ያነሰ መሆኑ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ነው። የዩኔስኮ አጠቃላይ የትምህርት ሴክተር በጀት በዓለም ባንክ ለዕውቀት እና ለትምህርት የአቅም ግንባታ ሥራዎች ከተሰበሰበው ውስጥ ሽራፊው ነው።

በወደፊት ዘላቂ ትምህርት ራዕያችን ላይ ውጤታማ ሚና ለመጫወት ዩኔስኮ የትምህርት ልማት አካሄዱን እንደገና ማጤን ይኖርበታል። የድጎማን መርህ መሠረት በማድረግ ድርሻው ክልላዊ እና ሀገራዊ ተቋማትን እና ሂደቶችን ማጠናከር አጋር አድርጎ ራሱን ማየት አለበት። በሁለተኛ ደረጃ፣ የማስረጃ አገናኝ እና የተጠናከረ መረጃ እና ተጠያቂነት ለዜጎች በሁሉም የትምህርት ሥርዓቶች እንዲቀርብ የሚሟገት ጠበቃ ነው። ለትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውል ውይይት እንዲፈጠር ልዩ ሚናውን እየጠበቀ ባለበት ወቅት፣ የዩኔስኮ አብዛኛው የገንዘብ እና የሰው ኃይል ሀብቱ የመማር መብት አደጋ ላይ የወደቀባቸው ቀጣናዎች፣ በተለይም በ2050 አብዛኞቹ የዓለም ወጣቶች በሚኖሩባት እና በሚማሩባት አፍሪካ ላይ ማተኮር ይኖርበታል።

ዩኔስኮ በትምህርታዊ ደንብ አወጣጥ፣ በፋይናንስ እና በዕውቀት ማሰባሰብ ላይ ዓለም አቀፍ እና ክልላዊ ተዋናዮች በሚሳተፉበት ውስብስብ ሥነ ምህዳር ውስጥ ስላለው አንጻራዊ ጥቅሙ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ይፈልጋል። እርግጠኛ ባልሆነው ክፍለ ዘመን ቁጥራቸው ሊበዛ ይችላል ተብሎ የሚጠበቀውን ያለፈቃድ ስደተኞች እና የተፈናቀሉ ሕዝቦችን የመማር መብት ለማረጋገጥ አዳዲስ መፍትሄዎችን ለማግኘት ከተባበሩት መንግሥታት አጋሮቹ ጋር መሥራት አለበት። እንደ ሰብአዊ መብት የተሻሻለ እና ፍትሐዊ የሆነ የዲጂታል መረጃ ተደራሽነትን ለማበረታታት ዓለም አቀፍ ተገኘነቱን ሊጠቀምበት ይገባል። ዩኔስኮ ትምህርት ከፍላጎታቸው ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ የዜጎች እና የሲቪል ማኅበረሰቡ በትምህርት አስተዳደር ውስጥ መሳተፋቸውን መደገፍ አለበት። ትምህርት ለሰላም፣ ብልጽግና እና ዘላቂነት የሚኖረውን ድርሻ ማጠናከርን ጨምሮ የጋራ የወደፊት ሕይወታችንን ለመገንባት ትምህርት የሚጫወተውን ሚና በማጉላት ረገድ ዩኔስኮ የተባበሩት መንግሥታት ፋና አብሪነቱን መቀጠል አለበት።

ዩኔስኮ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎችን እና ተቋማትን በመሰብሰብ እና በማሰባሰብ የጋራ የትምህርት የወደፊት እጣዎቻችንን ለመቅረጽ የሚያስችል ልዩ አቅም አለው። ታላቅ ጥንካሬውም እዚህ ላይ ነው። ደግሞም አዲስ፣ ዓለም አቀፍ ስምምነት ያለው ማኅበራዊ ውል ለትምህርት ለመቅረጽ እና በተለይም እሱን ለመተግበር አዲስ ስምምነት ለመገንባት የሚያስፈልገው ጥንካሬ ይኸው ነው።

# የውይይት እና የድርጊት መርሆዎች

ይህ ምዕራፍ ለወደፊት ፍላጎቶች፣ ተግዳሮቶች እና የትምህርት ዕድሎች ምላሽ ለመስጠት የታደሰ ዓለም አቀፍ ትብብር እንዲኖር ጥሪን ያቀርባል። ወደ 2050 ስናማትር፣ ለትምህርት ወደፊቶች ከሚያስፈልገው ከዓለም አቀፍ ትብብር ጋር የተገናኙ አራት ቁልፍ ቅድሚያዎች አሉ፦

- **ኮሚሽኑ ሁሉም የትምህርት ባለድርሻ አካላት በጋራ ዓላማዎች እና የትምህርት ተግዳሮቶች ላይ የጋራ መፍትሄዎችን ለመፍጠር በዓለም አቀፍ እና በክፍለ ዓለም ደረጃ እንዲሠሩ ጥሪውን ያቀርባል።** ለሁሉም የሰው ልጅ ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ የትምህርት ዕድልን ለመደገፍ የሚያስፈልገውን አዲስ ማኅበራዊ ውል መፍጠር፣ በተለይ በዓለም አቀፍ ፈተናዎች ምክንያት የመማር መብቶቻቸው ስጋት ውስጥ ለወደቀባቸው ወገኖች ጠቃሚ ነው። ተሳትፎው የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻዎችን እና አጋሮችን ማካተት፣ ከከላይ ወደ ታች ወደ ማዕከለ-ብዙነት መራመድ፤ እና አዲስ ቀጣናዊ ትብብር ዓይነቶች፣ በተለይም የደቡብ-ደቡብ እና የሦስት ማዕዘን ትብብርን ማካተት አለበት።
- **ዓለም አቀፍ ትብብር በድጎማ መርህ ላይ በመመሥረት፣ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ በአካባቢ፣ ብሔራዊ እና ቀጣናዊ ጥረቶችን መደገፍ እና አቅማቸውን መገንባት አለበት።** አዳዲስ የትምህርት ቃልኪዳኖችን፣ ደንቦችን እና ደረጃዎችን ለማጠናከር የተገቡትን ቃልኪዳኖችም ለማስፈጸም እና ለትምህርታዊ ማሻሻያዎች የተቀናጀ ድጋፍ ለማድረግ የተጠናከረ ተጠያቂነት ያስፈልጋል።
- **አነስተኛ ገቢ እና አነስተኛ መካከለኛ ገቢ ላላቸው አገሮች ለሚደረግ የዓለም አቀፍ ልማት የፋይናንስ ድጋፍ ትኩረት መስጠት አሁንም ጠቃሚ ነው።** ይህ በተለይ በአፍሪካ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የተገደበ ኢኮኖሚ ባላቸው አገሮች እና ወጣቶች ላይ ይሠራል። እንዲሁም በችግር እና በድንገተኛ አደጋ የመማር መብታቸው የተረበሸባቸውን ሕዝቦች ኢላማ ያደረገ ፋይናንስም ያስፈልገናል።
- **በማስረጃ፣ በውሂብ እና በዕውቀት ላይ የሚደረጉ የጋራ ኢንቨስትመንቶች የውጤታማ ዓለም አቀፍ ትብብር ወሳኝ አካላት ናቸው።** እዚህ ላይም ጥረታችን በድጎማ መርህ መመራት ያለበት ሲሆን፤ ይህም ዕውቀትን የማመንጨትና የመጠቀም አካባቢያዊ፣ አገራዊ እና ቀጣናዊ አቅምን ማዳበር ላይ ጉልሕ ትኩረት ያደርጋል። ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እርስበርስ መማማርን እና የዕውቀት ልውውጦችን በማኅበረሰቦች እና ድንበሮች ሁሉ ማጠናከር አለብን፤ ይህም እንደ የትምህርት አለመመጣጠንና እና ድህነትን ማቆም እና የሕዝብ አገልግሎቶችን ማሻሻል በመሳሰሉት ዋና ዋና ጉዳዮች እና በአውቶሜትድ እና ዲጂታይዜሽን፣ ፍልሰት እና ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃን በመሳሰሉ የረዥም ጊዜ ተግዳሮቶች ላይ ሊያተኩር ይችላል። ትምህርታዊ ዕድገትን በሁለንታዊ ዕውቀት እና መረጃ ለትምህርት ተለይተው የተመደቡ መድረኮች እና አዳዲስ የፋይናንስ ምንጮች ያስፈልጋሉ።

ይህ የዓለማቀፋዊ አጋርነት እና የተግባር አጀንዳ በጥንካሬ፣ በልበሙሉነት እና በቅንጅት እና ሁልጊዜም በ2050 እና ከዚያም ወዲያ በማየት መገንባት አለበት። በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ የጋራ ኃላፊነት እና የተሻሻለ ቅንጅት እንዲኖር እና የዩኔስኮ ሚና እንዲጠናከር ማስፈለጉን ያመለክታል። ይህ ከሌለ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተቀረጹት ሐሳቦች፣ ማለትም ትምህርትን እንደ ዓለም አቀፋዊ፣ ሕዝባዊ እና የጋራ ሀብት ተቀብሎ፣ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል የመቅረጽ ውጥኖች ዕውን ሊሆኑ አይችሉም። በአንድ ትውልድ ውስጥ፣ የትምህርት ሥርዓቶችን በዕውነት አካታች፣ ተገቢ እና ዓለም አቀፋዊ ፈተናዎቻችንን የመቋቋም አቅማችንን የሚያሳድጉ እንዲሆኑ ማድረግ እንችላለን።

# ማሳረጊያ ቃል እና ቀጣይነት

## የትምህርትን ወደፊቶች በጋራ መገንባት

የሰው ልጅ እና የፕላኔቷን የወደፊት ፍላጎቶች ሊያሟላ የሚችል አዲስ ማኅበራዊ ውል ለትምህርት ለመመሥረት በአስቸኳይ መሥራት አለብን። ይህ ሪፖርት ለአዲሱ ውል ግንባታ በሁለት መሠረታዊ መርሆች ላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እና ምክሮችን አቅርቧል፡- ዕድሜ ልክ የመማር መብት የተስፋፋ ራዕይ እና ትምህርትን እንደ ሕዝብ ሀብት እና የጋራ ጥቅም ማጠናከር።

በሪፖርቱ አስኳል ላይ የትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውል ምክረ ሐሳብ - በትምህርት ዙሪያ ማኅበራዊ ትስስርን የሚያነቃቁ እና የሚያነሳሱ እና ተዛማጅ ትምህርታዊ ዝግጅቶችን የሚያስገኙ ግልጽ ስምምነቶች እና መርሆዎች የተካተቱበት - ይገኛል። ይህ ማሳረጊያ አንባቢዎች ከሌሎች ጋር ተባብረው ለጋራ የትምህርት ወደፊቶች እንዲተረጉሟቸው እና መልሰው እንዲያጤኗቸው የሚጋበዙባቸውን ቅድሚያዎች እና ምክረ ሐሳቦች ጠቅልሎ ለማቅረብ የተዘጋጀ ነው።

አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል እና እስካሁን ድረስ ስለ ትምህርት በወል የተማርነውን እና በተመክሮ ያገኘነውን ሁሉ መተው አይደለም፤ ነገር ግን አስቀድሞ ተበይኖ እና የተቀመጠውን ሂደት አርሞ መቀጠል ብቻም አይደለም። አዲስ ማኅበራዊ ውል የነባር የትምህርት ሥርዓቶችን ውስንነቶች በትክክል ለይተው እና እነሱን ለማሸነፍ አዳዲስ ዘዴዎችን ባመነጩት - በትምህርት ባለሙያዎች፣ በማኅበረሰቦች፣ በወጣቶች እና በልጆች፣ በቤተሰቦች - ለረጅም ጊዜ ሲሠራ ቆይቷል።

> *አዲስ ማኅበራዊ ውል የነባር የትምህርት ሥርዓቶችን ውስንነቶች በትክክል ለይተው እና እነሱን ለማሸነፍ አዳዲስ ዘዴዎችን ባመነጩት - በትምህርት ባለሙያዎች፣ በማኅበረሰቦች፣ በወጣቶች እና በልጆች፣ በቤተሰቦች - ለረጅም ጊዜ ሲሠራ ቆይቷል።*

ነገር ግን ትምህርትን ለማደስ በምናደርገው ጥረት የተማርነውን ለማገናዘብ በጋራ ሳንገናኝ፣ ጥረቶቹ ብዙውን ጊዜ በተናጥል ወይም በትልልቅ ተቋማዊ ዘዴዎች ውሱን ማስተካከያዎች በማድረግ ይገለጣሉ። ፍትሐዊ፣ ተመጣጣኝ እና ዘላቂነት ያለው ወደፊትን ዕውን ለማድረግ ትምህርትን ማደስ የምንችለው በትምህርት አዲስ ማኅበራዊ ውል ግንባታ ውይይት እና ተግባር ላይ በንቃት በመሳተፍ ነው። ይህ ሪፖርት እነዚህን ሕዝባዊ ንግግሮች አውዳዊ አድርጎ ወደፊት ለማራመድ የቀረበ ግብዣ ነው። የትምህርት ማኅበራዊ ውል በተግባር እና በተለያዩ አውዶች ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት በዓለም ዙሪያ ለሚደረጉ ውይይቶች እንደ መተንኮሻ እና መቀስቀሻ እንዲያገለግል የታሰበ ነው። ስለዚህ ይህ ሪፖርት ወደ ወደፊት በተዘረጋው መንገድ ላይ ትልቅ ምዕራፍ ነው። በዓለም ዙሪያ ባሉ ሰዎች የበለጠ እንዲመረመሩ፣ እንዲጋሩ እና እንዲበለጽጉ ማዕቀፍን፣ መርሆችን እና ምክሮችን የሚያቀርብ ሕያው ሰነድ ነው። ዓላማው ትምህርትን ለማደስ እና ለመለወጥ ለሚያስችል የፖሊሲ ልማት አዳዲስ መንገዶችን በማነሳሳት ሁሉም ተማሪዎች የተሻለ የወደፊት ጊዜ ለመፍጠር በዕውነት ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ ያግዛል። መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ የመንግሥት ባለስልጣናት እና ሌሎች የትምህርት ባለድርሻ አካላት በተለይም ማኅበረሰቦች በሪፖርቱ ውስጥ ባሉት ሐሳቦች ላይ ሲሳተፉ እና በእነዚያ ማኅበረሰቦች ውስጥ ሐሳቦቹን በተግባር ለመተርጎም በጋራ ሲገነቡ ብቻ ትምህርትን በመቀየር ላይ ትርጉም ይኖረዋል።

ዩኔስኮ እዚህ ከቀረቡት በርካታ ሐሳቦች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የመወያያ፣ የመሳተፊያ እና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን እንዲያዘጋጅና እንዲቀጥል ኮሚሽኑ ጥሪውን ያቀርባል። የሪፖርቱ የወደፊት ስኬት ቀጣይነት ያለው የማሰላሰል እና የተግባር ሂደትን ለማነቃቃት ባለው ችሎታ ይወሰናል። የትምህርት ሥራ ሁሌም “በሂደት ላይ” ይሆናል፤ እዚህ የቀረቡት ምክሮችም በቀጣይነት መቀየር እና መሻሻል አለባቸው በሚል መነሻ ላይ የተመሠረተ ነው። እርስበርሳችን፣ ፕላኔታችንን ከሚለዩት አስደናቂ የሕይወት ስልቶች እና ሥርዓቶች፣ እና በፍጥነት አዳዲስ ቦታዎችን እና ለሰው ልጅ ዕድገት አቅምን ከሚከፍተውና እንዲሁም ወደር የለሽ አደጋዎችን ከሚጋርጠው ከቴክኖሎጂ ጋር ተስማምተን መኖርን ስንማር ትልቅ ትብብር ያስፈልገናል።

ዓለማችንን ለመሥራት እና እንደገና ለመሥራት በትምህርት ዋጋ ዙሪያ ያለው ዓለም አቀፋዊ መግባባት የጋራ መነሻ ነጥባችን ነው። ይህ የጋራ እምነት ጽኑ ነው፤ ብዙዎቹ ከዚህ በፊት ያልታዩ አዳዲስ ፈተናዎችን ስንጋፈጥ ቁርጠኝነታችንን ያጠናክራል።

ነገሮች በተለየ መንገድ እንዲከናወኑ፣ አሁን በተለየ መንገድ ማሰብ፣ መረዳት፣ መስማት እና ማለም አለብን። ስለ ትምህርት፣ ዕውቀት እና ትምህርት ያሉንን ሥር የያዙ የአስተሳሰብ መንገዶች የወደፊቱን ለመለወጥ አዳዲስ መንገዶችን ሊከፍቱ የሚችሉበት ግልጽ ምርመራ ማድረግ ያስፈልገናል።

# አዲስ ማኅበራዊ ውል የመገንባት ምክረ ሐሳቦች

ሪፖርቱ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ለመገንባት የሚያስፈልጉትን ለውጦች በአምስት አቅጣጫዎች መርምሯል። የእነዚህ አቅጣጫዎች ቁልፍ ሐሳቦች በዚህ ሪፖርት ክፍል ሁለት ውስጥ፣ እነሱን ወደፊት ለማስኬድ የሚረዱ መመሪያዎች ጋር ተብራርተዋል። እነዚህ ሁሉን አቀፍ ባይሆኑም፣ እዚህ ላይ እንደ መነሻ የተግባር ማዕቀፍ የተጠቃለሉ ሲሆን፤ ይህም እንደየዐውዱ ሊተረጎም እና በትምህርት አዳዲስ የወደፊት እጣዎችን ዕውን ለማድረግ ሊዳብር የሚችል ነው።

## የአጋርነት እና የትብብር ሥነ ትምህርቶች

ሥነ ትምህርት በትብብር እና በአጋርነት መርሆዎች ዙሪያ መለወጥ አለበት፤ ይህም ለረጅም ጊዜ የቆዩ የማግለል ዘዴዎችን እና ግላዊ ፉክክርን ይተካል። ትምህርት መተሳሰብን እና ርህራሄን ማጎልበት፤ እንዲሁም ግለሰቦች ራሳቸውን እና ዓለምን ለመለወጥ በጋራ የሚሠሩበትን አቅም መገንባት አለበት። ትምህርት የሚቀረፀው በመምህራን፣ በተማሪዎች እና በዕውቀት መካከል ባለው፣ ከመማሪያ ክፍል ደንቦች እና የስነምግባር ህጎች ገደብ ባለፈው ግንኙነት አማካይነት ነው። መማር ለምንጋራው የጋራ ዓለማችን ሀላፊነትን ለመሸከም በሚያስፈልገው ስነምግባር እና መተሳሰብ አማካይነት የተማሪዎችን ግንኙነት ያሰፋል። ሥነ ትምህርት ባለው እና በሚገነባው ላይ የተመሠረቱ የለውጥ ሁነቶችን የመፍጠር ሥራ ነው።

ወደ 2050 ስናማትር፣ ለግለሰባዊ እና ተወዳዳሪ የስኬት ትርጓሜዎች ቅድሚያ የሚሰጡ የትምህርት ዘዴዎችን፣ ትምህርቶችን እና መለኪያዎችን መተው አለብን። ይልቁንም፣ ለሚከተሉት የመመሪያ መርሆች ቅድሚያ መስጠት አለብን፦

አንደኛ፦ እርስበርስ መተሳሰር፣ መደጋገፍና መተሳሰብ በግለሰብም ሆነ በጋራ ለዋጭ ለሆነ ሥነ ትምህርት አስፈላጊ ናቸው። መምህራን በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ ትምህርታዊ ግንኙነቶችን እንዴት ማጎልበት እንደሚችሉ ሲማሩ፣ ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ሥርዓቶች እነዚህን ተግባራት በተቋም ደረጃ ለማካተት መንገዶችን መፈለግ አለባቸው። ተመክሮ እና ውይይት፣ አገልግሎት እና ትርጉም ያለው ተግባር፣ ምርምር እና ጽብረቃ፣ በገንቢ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች እና በማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ ተሳትፎ - እነዚህ ከብዙ ተስፋ ሰጭ አቀራረቦች ጥቂቶቹ ናቸው። ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ሥርዓቶች ቤተሰቦችን እና ማኅበረሰቦችን ለማዳመጥ እና ወደ ሌሎች የሕይወት ዘርፎች ለመዘርጋት ማኅበራዊ እና የዘርፍ ግድግዳዎችን በማፍረስ ከክፍል ውጭ አዲስ ትሥሥሮችን እና ትምህርታዊ ግንኙነቶችን መደገፍ አለባቸው።

ሁለተኛ፦ ሕብረት እና ትብብር፣ እንደ የጋራ፣ ተዛምዷዊ ሂደትነቱ የሥነ ትምህርት መሠረት መሆን አለባቸው። መምህራን በተለያዩ የመማሪያ ስልቶች ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ - ከአቻ ግብረመልስ፣ በፕሮጀክት ላይ የተመሠረተ ትምህርት፣ ችግር ፈቺ እና ጥያቄን መሠረት ያደረገ ትምህርት፣ የተማሪ ቤተ ሙከራ፣ የቴክኒክ እና የሙያ ወርክሾፖች፣ ሥነ ጥበባዊ ሥራ እና የፈጠራ ትብብር - ሁሉም የተማሪዎችን አዳዲስ ፈተናዎችን በፈጠራ እና ባልተጠበቁ መንገዶች በግል እና በጋራ የመጋፈጥ ችሎታ ለማሳደግ ያግዛሉ። ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ሥርዓቶች በዕድሜ ቡድኖች፣ ፍላጎቶች፣ ማኅበራዊ ዘርፎች፣ ቋንቋዎች እና የትምህርት ደረጃዎች ሰፋ ያሉ ግንኙነቶችን ለማመቻቸት መንገዶችን ማሰስ ይችላሉ።

> ሥነ ትምህርት ባለው እና በሚገነባው ላይ የተመሠረቱ የለውጥ ሁነቶችን የመፍጠር ሥራ ነው።

ሦስተኛ፡- አጋርነት፣ ርህራሄ እና መተሳሰብ በምንማርበት መንገድ ውስጥ ሥር ሊሰድዱ ይገባል። ሥነ ትምህርቶች ተማሪዎች ከራሳቸው ይልቅ ሰፋ ያሉ ልምዶችን እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል። ወላጆች እና ቤተሰቦች ከልጆቻቸው ጋር በመሆን ብዝሃነትን እና ብዝሃነትን በመጋራት እና በመመዘን እንዲሳተፉ እንኳን ደህና መጣችሁ። ትምህርት ቤቶች እና አስተማሪዎች ርህራሄን የሚያከብሩ እና የተለያዩ ታሪኮችን፣ ቋንቋዎችን እና ባሕሎችን የሚደግፉ አካባቢዎችን መፍጠር ይችላሉ፣ ከእነዚህም መካከል በተለይም ቀደምት ሕዝቦች እና ሰፊ የማኅበራዊ ንቅናቄዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

አራተኛ፡- ሁሉም ምዘና ሥነ ትምህርታዊ ነው። ስለሆነም ለተማሪዎች ዕድገትና ትምህርት ሰፋ ያሉ የትምህርታዊ ጉዳዮችን ለመደገፍ በጥንቃቄ ሊታሰብበት ይገባል። መምህራን፣ ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ሥርዓቶች በግል እና በጋራ መማርን በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍ ፈታኝ አካባቢዎችን በመለየት እና በመፍታት ቅድሚያ ለመስጠት ግምገማዎችን መጠቀም ይችላሉ። ግምገማ ለቅጣት ወይም 'አሸናፊዎች' እና 'የተሸናፊዎች' ምድቦችን ለመፍጠር ጥቅም ላይ መዋል የለበትም። የትምህርት ፖሊሲ አላስፈላጊና እጅግ ለተጋነነ ደረጃ ቅድሚያ በሚሰጡና አለአግባብ በሚደረጉ ሌሎች መመዘኛዎች ተጽዕኖ ሊደረግበት አይገባም። እንዲህ ያለው ትኩረት ያልተገባ ጫና በመፍጠር፣ በትምህርት ቤቶች ሊኖሩ የሚገባቸውን ትክክለኛ ተሞክሮዎች እና ልምምዶች ሊያሳጣ ይችላል።

# ሥርዓተ ትምህርት እና የጋራ ዕውቀት

በትምህርት እና በሚያሳድጋቸው እውቀቶች፣ አቅሞች እና እሴቶች መካከል አዲስ ግንኙነት መፈጠር አለበት። ሥርዓተ ትምህርት ትምህርትን ከሚደግፉ ሁለት ወሳኝ ሂደቶች ጋር ተዛምዶ ሊቀረጽ ይገባል፡- ዕውቀትን እንደ የሰው ልጅ የጋራ ቅርስ አካል አድርጎ መቀበል፣ እና በጋራ አዲስ ዕውቀት እና አዳዲስ የወደፊት ዕድሎችን መፍጠር። ወደ 2050 ስናማትር፣ ሥርዓተ ትምህርት እንደ የትምህርት አይነቶች ፍርግርግ ከሚታይባቸው ተለምዷዊ አመለካከቶች በዘለለ እና በምትኩ ተማሪዎችን እንዲማሩ እና ለሰው ልጅ የጋራ ዕውቀት እንዲሰጡ በሚያስችሏቸው በይነ-ዲሲፕሊናዊ እና በይነ-ባሕላዊ እይታዎች እንደገና ማጤን አለብን። የሚከተሉት የመመሪያ መርሆች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል፡-

አንደኛ፡- ሥርዓተ ትምህርት የተማሪዎችን የሁሉም የሰው ልጅ ውርስ የሆነውን የጋራ ዕውቀት የማግኘት እና ለእሱም የማዋጣት ችሎታ በማሳደግ እና የተለያዩ የዕውቀት እና የመግባቢያ መንገዶችን በማካተት በቀጣይነት መስፋፋት አለበት። የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ትግበራ ከመረጃና ከጠባብ ስርጭት በመራቅ ተማሪዎችን በልዩ ልዩ ዕውቀት ማግኛ፣ መተግበሪያ እና ማፍለቂያ መንገዶች መሳተፍ የሚያስችሏቸውን ፅንሰ ሐሳቦች፣ ክህሎት፣ እሴቶች እና አመለካከቶች በማሳደግ እንዲማሩ ማድረግ አለበት።

ሁለተኛ፡- በፍጥነት እየተለዋወጠ ያለው የአየር ንብረት እና የፕላኔታችን ሁኔታ የሰው ልጅ በዓለም ላይ ያለውን ቦታ መልሰው የሚቃኙ ሥርዓተ ትምህርቶች ያስፈልጋሉ። የማይለወጡ የፕላኔቶች ለውጦች እየፈጠኑ ናቸው፣ እና ትምህርት ለአካባቢያዊ፣ ማኅበረሰብ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ውስጣዊ ትስስር አድናቆትን ማዳበር አለበት። ሥርዓተ ትምህርት ከተለያየ የዕውቀት ዓይነቶች መሳል፣ ተማሪዎችን እና ማኅበረሰቦችን የአየር ንብረት ለውጥን እንዲለማመዱ፣ እንዲቀንሱ እና እንዲቀለብሱ በማዘጋጀት የሰው ልጅ ከሰው በላይ ከሆነው ዓለም ጋር የማይነጣጠል ትስስር እንዲኖረው ማድረግ አለበት። ሥርዓተ-ትምህርት የአየር ንብረት ለውጥ በማኅበረሰባቸው፣ በዓለም እና በተለይም ብዙ ጊዜ የተገለሉትን ለምሳሌ በድሆች፣ አነስተኛ ቁጥርና የእድገት ደረጃ ያላቸውን ብሄረሰቦች እና ሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ማገናኘት አለባቸው። የሥርዓተ ትምህርት ዕውቀት ትርጉም ላለው ተግባር እና ልጆች እና ወጣቶች በወደፊታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ የአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳ እና የአካባቢ ጥበቃ ጥረቶች ላይ እንዲቀጥሉ ለመርዳት ጠንካራ ማዕቀፍ ሊሰጥ ይችላል።

*ትምህርትን ከሚደግፉ ሁለት ወሳኝ ሂደቶች ጋር ተዛምዶ ሊቀረጽ ይገባል፡- ዕውቀትን እንደ የሰው ልጅ የጋራ ቅርስ አካል አድርጎ መቀበል፣ እና በጋራ አዲስ ዕውቀት እና አዳዲስ የወደፊት ዕድሎችን መፍጠር።*

ሦስተኛ፡- የተሳሳቱ መረጃዎችን በፍጥነት መስፋፋት እና ማጭበርበርን በበርካታ የትምህርት ክህሎቶች - ዲጂታል፣ ሳይንሳዊ፣ ጽሑፋዊ፣ ሥነ ምህዳራዊ፣ ሒሳባዊ - አማካይነት ግለሰቦች ዕውነተኛ እና ትክክለኛ ዕውቀት ማግኛ መንገዳቸውን እንዲያገኙ በሚያስችል መልኩ መከላከል አለባቸው። እንደዚህ ዓይነት መሠረታዊ ትምህርት በጋራ ዕውነቶች ላይ ለተመሠረተ ትርጉም ያለው እና ውጤታማ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። ውጤታማ መሠረታዊ ትምህርቶች የዕውነታዎችን፣ መረጃዎችን እና ውሂቦችን ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ትክክለኛ መደምደሚያ ለመድረስ፣ ግኝቶችን ለማረጋገጥ እና በትክክል ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉትን እንደ ምዘና እና ማጣቀስ ያሉ ሂደቶችን መገንዘብንም ማዳበር አለባቸው። ሥርዓተ ትምህርቶች የተማሪዎችን መረዳት፣ ትክክለኛነት፣ እቅጭነት እና ለዕውነት ያለ ቁርጠኝነት ለማዳበር በሰፊ ታሪካዊ፣ ባሕላዊ እና ሥነ ዘዴያዊ አቀራረቦች ላይ መመሥረት አለባቸው።

አራተኛ፡- የሰብአዊ መብቶች እና የዲሞክራሲ ተሳትፎ ሰዎችን እና ዓለምን የሚቀይሩ የሥርዓተ ትምህርት እና የትምህርት መሠረታዊ መርሆችን ማሳወቅ አለባቸው። ሰብአዊ መብቶች የሁሉም ሰዎች የማይነኩ መብቶች ሆነው መቀጠል አለባቸው፤ እንዲሁም ማኅበራዊ ውላችን እንደሚመሠረትበት የጋራ የመነሻ ነጥብ፣ መማርን ለሚቀርጹ ሥርዓተ ትምህርቶች መሠረት መሆን አለባቸው። ሥርዓተ ትምህርቶች የሁሉንም ሰዎች ተፈጥሯዊ መብትና ክብር መጠበቅ፣ እና ሁከትን አሸንፎ ሰላማዊ ማኅበረሰቦችን መገንባት አስፈላጊ መሆኑን ሊያጎላ ይገባል። ከማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች እና ከመሠረታዊ ማኅበረሰቦች ጋር ያለው መስተጋብር ሥርዓተ ትምህርትን በሥርዓተ ጾታ፣ በዘር፣ በቀደምት ሕዝብነት፣ በቋንቋ፣ በጾታዊ ዝንባሌ፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳት ወይም በዜግነት ሁኔታ ምክንያት ቡድኖች ላይ መድልዎ የሚፈጽሙ የኃይል አወቃቀሮችን ለመጠየቅ፣ ለመግለጥ እና ለመጋፈጥ የሚያስችል ትክክለኛ መንገዶች አሉት።

# መምህራን እና የመምህርነት ሙያ

መምህራን በሙያቸው አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ለመገንባት ልዩ ሚና አላቸው። የተማሪዎችን ዕውቀት እና አቅም ለማሳደግ በትብብር ሲሰሩ የተለያዩ አካላትን እና አካባቢዎችን የሚያሰባስቡ ቁልፍ አስተባባሪዎች ናቸው። የመልካም የሰው መምህራንን ፍላጎት ለመተካት ወይም ለመቀልበስ የሚያስችል ቴክኖሎጂ እስካሁን የለም። ወደ 2050 ስናማትር፣ ውጤታማ ትምህርትን ለማቀናጀት በአንድ ግለሰብ ላይ የሚደገፍ ትምህርትን እንደ ብቸኝነት ከመመልከት መራቅ አስፈላጊ ነው። ይልቁንም ማስተማር፣ የቡድን ሥራ ትርጉም ያለው የተማሪ ትምህርት የሚያረጋግጥበት የትብብር ሙያ መሆን አለበት። የሚከተሉት መርሆዎች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል፡-

አንደኛ፡- ትብብር እና የቡድን ሥራ የመምህራንን ሥራ መለያዎች መሆን አለባቸው። ለትምህርት ያለን ሰፊ ዓላማዎች በጣም ጎበዝ ከሆኑ መምህራን እንኳን ከሚጠበቀው በላይ ነው። መምህራን ከመምህራን ባልደረቦቻቸው፣ ከርእሰ ጉዳይ ስፔሻሊስቶች፣ ከመሠረተ ትምህርት ባለሙያዎች፣ እና የቤተ መጻህፍት ባለሙያዎች፣ የልዩ ፍላጎት አስተማሪዎች፣ የመመሪያ አማካሪዎች፣ የማኅበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች እና ሌሎች ጋር በቡድን እንዲሰሩ ያስፈልጋል። የሰውን ልጅ የሚያጋጥሙት ነውጦች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ በመምጣታቸው፣ የትብብር ሥራ አስፈላጊነት በመጪዎቹ አመታት የበለጠ አሳሳቢ ይሆናል። ስለዚህ መምህራን ሕፃናትን፣ ወጣቶችን እና ጎልማሶችን እንደየዕድሜያቸው በተለዋዋጩ ዓለም ውስጥ በአግባቡ እንዲጓዙ በመርዳት ረገድ ግንባር ቀደም ተሰላፊዎች ናቸው። የተማሪዎችን ደህንነት፣ ጤናማ ግንኙነት እና የአእምሮ ጤና በትምህርት ተቋማት ውስጥ መደገፍ እንዳለበት ሁሉ፤ መምህራንም ወሳኝ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ለኑሮ ምቹ የሆነ ደመወዝ፣ የሙያ ልህቀት፣ ቀጣይ ትምህርት፣ ሙያዊ ዕድገት እና ትብብራዊ የትምህርት አካባቢ ሊያገኙ ይገባል።

ሁለተኛ፦ ዕውቀትን፣ ጽብረቃን እና ምርምርን ማፍራት የማስተማር ዋና አካል እንደሆነ መታወቅ አለበት። ስለ ትምህርት የወደፊት ጊዜ ምርምር እና ዕውቀት የሚጀምረው አስተማሪዎች በሚያከናውኑት ሥራ ነው፤ ደግሞም ብዙዎቹ የአዲሱ የትምህርት ማኅበራዊ ውል አላባዎች ቀድሞውኑ መምህራን በሚሠሯቸው ለዋጭ የትምህርት ተግባራት ውስጥ ይችላሉ። የመምህራን ሥራ የዕውቀት አምራችነት እና የትምህርት አቅኚነት ሥራ ዕውቅና አግኝቶ፤ እና በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ተገቢ ምርምር እና ተመክሮዎቻቸውን እንዲሰንዱ፣ ከባልደረቦቻቸው ጋር እንዲጋሩዋቸው እና እንዲወያዩባቸው ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። ዩኒቨርስቲዎች እና ከፍተኛ ትምህርት መምህራን በሙያቸው ሰፊ የሆነ የዕውቀት ምርትን የሚደግፉበትን ቀጣይነት ያለው ምርምር እና ሙያዊ ግንኙነቶች እንዲያደርጉ የሚያግዙ አዳዲስ ተቋማዊ አወቃቀሮችን ማጤን ይችላሉ።

ሦስተኛ፦ የመምህራን ሙያዊ ራስገዝነት መከበር እና መጠበቅ አለበት። የመምህርነት ሙያ ሰፊ የላቁ ክህሎቶችን እና ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ዕድገትን ይጠይቃል። በሚቀጥሉት ዐሥርት አመታት ከፍተኛ ጥራት ያለው የቅድመ አገልግሎት የመምህርነት ትምህርትን ለማጠናከር እና ለማስፋት በተለይም የወጣቶች ቁጥር እየጨመረ በሚመጣበት ከሰሃራ በታች ባሉ አፍሪካ የትምህርት ፍላጎት የሰለጠነ የትምህርት አቅርቦትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ድጋፍ ያስፈልጋል። ለጀማሪ መምህራን ሙያዊ ዕድገት ቀጣይነት ባለው ትምህርት፣ ማማከር እና በትብብር አብሮ ማስተማር ሊሰጥ ይችላል። ለትምህርት ዝግጅት እና ለማሰላሰል በቂ ጊዜ መመደብ አለበት፤ መምህራንም ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ ክፍያ ማግኘት አለባቸው። ሙያዊ ራስገዝነት፣ ማኅበራዊ ክብር እና ጥሩ ደመወዝ ማረጋገጥ የሰለጠኑ አስተማሪዎች በሙያው እንዲቀጥሉ እና የሰለጠኑ እና ተነሳሽነት ያላቸው ግለሰቦች እንዲገቡበትም ያበረታታል።

> *የመልካም የሰው መምህራንን ፍላጎት ለመተካት ወይም ለመቅልበስ የሚያስችል ቴክኖሎጂ እስካሁን የለም።*

በትምህርት ሕዝባዊ ክርክር፣ ውይይት እና ትምህርት ፖሊሲ መሳተፍ የመምህራን ዋና ሥራ አካል ሆኖ መታወቅ አለበት። ብዙ ጊዜ፣ በትምህርት ቤቶች ወይም በክፍል ውስጥ ስለሚሆነው ነገር ውሳኔዎች የሚደረጉት ከነሱ ርቀው ባሉ፣ በትንሽ ውይይት፣ መስተጋብር ወይም ትርጉም ያለው የግብረመልስ ምልልስ ነው። ለወደፊት የትምህርት ዕድል፣ ይህ ሊለወጥ ይገባል፤ መምህራንም እንደ መሪ እና ጠቃሚ መረጃ ሰጪዎች በሕዝብ ክርክር፣ ፖሊሲ እና የወደፊት የትምህርት እጣ ፈንታችን ላይ ውይይት ላይ እንዲሳተፉ ሊጋበዙ ይገባል። በእነዚህ መስኮች የሚደረግ የመምህራን ተሳትፎ፣ የመምህርነትን ምንነት የሚገልጽ ዋና ተግባር መሆኑን በጋራ ግንዛቤ ውስጥ መካተት አለበት፤ እነሱም በትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውል ቀረጻ ውስጥ እንደ ቁልፍ ተሳታፊዎች መታየት አለባቸው።

# ትምህርት ቤቶችን መጠበቅ እና መለወጥ

ትምህርት ቤቶች፣ በሙሉ አቅማቸው እና ቁርጠኝነታቸው፣ ድክመቶቻቸው እና ውሱንነታቸው፣ ከሕብረተሰቡ በጣም አስፈላጊ የትምህርት መቼቶች መካከል እንደ አንዱ ሆነው ይቆያሉ። ትምህርት ቤቶች የትላልቅ የትምህርት ስነ ምህዳሮች ማእከላዊ ምሰሶዎች ናቸው፤ ህያውነታቸውም ሕብረተሰብ ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ ሰብአዊ እንቅስቃሴ በመቁጠር ለትምህርት እና ለሕፃናቱ እና ለወጣቶቹ ያለው ቁርጠኝነት መገለጫ ነው። ወደ 2050 ስናማትር፣ በምንም አውድ ቢሆን፣ ከእንግዲህ ወጥ በሆነ ሞዴል የተደራጁ ት/ቤቶች ሊኖሩን አይችሉም። አሁን ባሉት የኪነ ህንፃ፣ የአሰራር እና የአደረጃጀት ሞዴሎች ምትክ፣ የት/ቤቶችን ጊዜ እና ቦታዎችን ለመጠበቅ እና ለመለወጥ በሚያስችል መልኩ በአዲስ መልክ ለመንደፍ ትልቅ የሕዝብ ጥረት እንፈልጋለን። የሚከተሉት ቅድሚያዎች ይህንን አስፈላጊ ሥራ መምራት አለባቸው፦

አንደኛ፦ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ተግዳሮቶች የሚያጋጥሟቸው እና ሌላ ቦታ የማይገኙ ዕድሎች የሚያገኙባቸው ቦታዎች ተብለው ሊጠበቁ ይገባል። ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ቡድኖች እርስበርሳቸው የሚማሩበት የትብብር እና የእንክብካቤ

አካባቢዎችን ይፈልጋሉ። ልጆችን እና ወጣቶችን ለወደፊት ሕይወታቸው ፈታኝ ሁኔታዎችን ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን በሚኖሩበት በፍጥነት እየተለዋወጠ ካለው የሚኖሩበት ዓለም ጋር እንዲደራደሩ በመርዳት መምህራን እና ተማሪዎች ከአዳዲስ ሐሳቦች፣ ባሕሎች እና ዓለምን የሚያዩበት መንገዶች ጋር እንዲገናኙ ያስችላቸዋል።

ሁለተኛ፦ የት/ቤት ኪነ ሕንፃ፣ ቦታዎች፣ ጊዜዎች፣ የጊዜ ሰሌዳዎች እና የተማሪ ስብስብ እንደገና ሊታሰቡ እና የግለሰቦችን አብሮ የመሥራት አቅምን ለመገንባት በሚያስችል መልኩ ሊዘጋጁ ይገባል። የተገነባው አካባቢ እና አካታች ዲዛይን በራሳቸው ሥነ ትምህርታዊ ጠቀሜታ ያላቸው እና በጋራ የመማሪያ ቦታዎች ላይ በሚፈጠሩት ነገሮች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው። የትብብር ባሕሎች የት/ቤቶች አስተዳደር እና አመራር እንዲሁም በትምህርት ቤቶች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ወደ ጠንካራ የመማር፣ የማሰላሰል እና የፈጠራ ሥራዎችን ለማጎልበት መምራት አለባቸው።

ሦስተኛ፦ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚከናወኑትን ለመደገፍ ዓላማ ማድረግ አለባቸው፤ አሁን ባለው ሁኔታ እና ገና ሊታዩ በሚችሉ ድግግሞሾች መሠረት ለመደበኛ እና አካባቢያዊ የትምህርት ተቋማት በቂ መተኪያዎች አይደሉም። ዲጂታል መሳሪያዎችን መጠቀም በሚቀጥሉት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ የተማሪ ፈጠራን እና ግንኙነትን ለማጎልበት ጠቃሚ እና አስፈላጊ ይሆናል፤ ዲጂታል ቦታዎችን ማሰስም የጋራ ዕውቀትን እና የሰው ልምዶችን ለማግኘት እና ለመሳተፍ አዲስ ዕድሎችን ይከፍታል። በት/ቤቶች ውስጥ ሰው ሰራሽ አስተውሎት እና ዲጂታል ስልተ ቀመሮችን ለመተግበር የሚደረገው ጥረት ነባር የተዛቡ አስተሳሰቦች እና አግላይ ሥርዓቶች እንዳያባብሱ በጥንቃቄ ሊከወኑ ይገባል።

**ትምህርት ቤቶች የትላልቅ የትምህርት ስነ ምህዳሮች ማእከላዊ ምሰሶዎች ናቸው፤ ህያውነታቸውም ሕብረተሰብ ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ ሰብአዊ እንቅስቃሴ በመቁጠር ለትምህርት እና ለሕፃናቱ እና ለወጣቶቹ ያለው ቁርጠኝነት መገለጫ ነው።**

አራተኛ፦ ትምህርት ቤቶች ሰብአዊ መብቶችን በማረጋገጥ እና የዘላቂነት እና የካርበን ገለልተኝነት በማረጋገጥ ለምንመኘው ዓይነት ነገ ጊዜ አርአያ መሆን አለባቸው። የትምህርት ዘርፉን አረንጓዴ ለማድረግ ተማሪዎች እምነት ሊጣልባቸው እና ሊረዱ ይገባል። ለአካባቢያዊ ሁኔታዎች እና ለውጦች ምላሽ የሚሰጡ የአካባቢ እና አገር በቀል የንድፍ መርሆዎች ስለ መላመድ፣ ቅነሳ እና መከላከል የተሻለ የወደፊት ሁኔታን ለመገንባት እና ከተፈጥሮአዊው ዓለም እና እኛ አካል ከሆንንባቸው እና ከምንደገፍባቸው ሥርዓቶች ጋር የበለጠ ተደጋጋፊነትን ለመመስረት የመማሪያ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም በትምህርት እና ሌሎች ትምህርት ቤቶችን በሚመለከቱ ፖሊሲዎች ውስጥ በት/ቤቶች ውስጥው ይሁን ከዚያ ውጭ ያሉ ሰዎች ሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለብን።

# በትምህርት በተለያዩ ጊዜያት እና ቦታዎች

ከዋና ዋና ተግባሮቻችን አንዱ ትምህርት የትና መቼ እንደሚካሄድ ማሰብን እና ወደ ብዙ ጊዜያት፣ ቦታዎች እና የሕይወት ደረጃዎች ማስፋት ነው። ከልደት እስከ እርጅና በሕይወት እና በሕብረተሰብ ውስጥ ያለውን ሙሉ የትምህርት አቅም ተረድተን ትምህርትን ለማራመድ ብዙኃኑን ሥፍራዎች እና ብዙ ጊዜ ተደራራቢ የሚሆኑትን የባሕል፣ማህበራዊ እና የቴክኖሎጂ እድሎችን ማስተሣሠር አለብን። የወደፊት ማኅበረሰቦቻችን ከመደበኛ ትምህርት ቤቶች ባለፈ በበርካታ ሥፍራዎች እና በታቀዱ እና ባልታቀዱ ጊዜያት ትምህርት እንደሚሰጡ እና እንደሚያበረታቱ መገመት እንችላለን። ወደ 2050 ስናማትር ይህንን ምክረ ሐሳብ ወደፊት ለማራመድ የሚያስፈልጉትን ውይይቶች እና ድርጊቶች የሚመሩ አራት መርሆዎች አሉ።

አንደኛ፦ በሁሉም የሕይወት ደረጃዎች ውስጥ ሰዎች ትርጉም ያላቸው፣ ጥራታቸው የተጠበቀ የትምህርት ዕድሎች ሊያገኙ ይገባል። ትምህርት ዕድሜ ልክ እና የሕይወት ሙሉ ነው። የአዋቂዎች መማር እና ትምህርት በሁሉም የሕይወት ደረጃዎች ውስጥ የትምህርት ለውጦችን ዕድሎችን ለመቀበል ከ“ክህሎት” እና “የበቂ ችሎታ” ጉድለት ፅንሰ ሐሳቦች ባሻገር የበለጠ መጎልበት እና መደገፍ አለበት። በሕይወት ውስጥ ለትምህርት የሚሆን ማንኛውም እቅድ በጣም የተገለሉትን እና በጣም ደካማ

*የወደፊት ማኅበረሰቦቻችን ከመደበኛ ትምህርት ቤቶች ባለፈ በበርካታ ሥፍራዎች እና በታቀዱ እና ባልታቀዱ ጊዜያት ትምህርት እንደሚሰጡ እና እንደሚያበረታቱ መገመት እንችላለን።*

በሆኑ ቦታዎች ላይ ያሉትን በማገልገል ላይ፣ ተማሪዎችን ዕድሎችን እንዲገነዘቡ እና የአሁኑን እና የወደፊቱን ችግሮች ለመጋፈጥ በሚያስፈልጓቸው ዕውቀቶች፣ ፅንሰ ሐሳቦች፣ አመለካከቶች እና ክህሎት በማገዝ ላይ ማተኮር አለበት።

ሁለተኛ፡- ጤናማ የትምህርት ስነ-ምህዳሮች ተፈጥሯዊ፣ የተገነቡ እና ምናባዊ የመማሪያ ቦታዎችን ያገናኛሉ። ባዮስፌር - መሬቶቹ፣ ውሃዎቹ፣ ሕይወቱ፣ ማዕድኖቹ፣ ከባቢ አየር፣ ሥርዓቶቹ እና መስተጋብሩ - እንደ አስፈላጊ የመማሪያ ቦታ መታወቅ አለበት። ስለዚህ ከመጀመሪያዎቹ አስተማሪዎቻችን መካከል ነው። ከዚህ በትይዩ ዲጂታል የመማሪያ ቦታዎች በትምህርታዊ ሥነ-ምህዳሮች ውስጥ በይበልጥ መቀናጀት፤ እና ሕዝባዊነትን፣ አካታችነትን እና የትምህርትን የጋራ ጥቅምን ለመደገፍ መታገዝ አለባቸው። የክፍት ተደራሽነት እና የክፍት ምንጭ መድረኮች ለተማሪ እና አስተማሪ መረጃዎች ጠንካራ ጥበቃዎች ቅድሚያ ሊሰጡ ይገባል።

ሦስተኛ፡- የመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ እና የትምህርት ቁጥጥር አቅም መጠናከር አለበት። መንግሥታት ፈጥኖ መላሽ፣ ፍትሐዊ እና ሰብአዊ መብቶችን ለሚያከብሩ የትምህርት አቅርቦቶች ደረጃዎችን እና ደንቦችን የሚያወጡበትን እና የሚፈጽሙበትን ዐቅማቸውን መገንባት እና ማሳደግ አለብን። በአገር ውስጥ፣ በአገር አቀፍ፣ በክልላዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ፣ መንግሥታትና የሕዝብ ተቋማት የጋራ ወደፊታችንን እንደገና ለማጤን በእነዚህ መርሆች ዙሪያ ውይይት ለማድረግና ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆን አለባቸው።

አራተኛ፡- የመማር መብት መስፋት አለበት። የመማር መብትን የትምህርት ቤት ጉዳይ ብቻ ማድረጋችን ከእንግዲህ በቂ ውጤት አያስገኝልንም። የወደፊቱን ጊዜ ስንመለከት፣ መረጃ በማግኘት፣ በመተሳሰር እና በባሕል መብት አማካይነት የዕድሜ ልክ እና የሕይወት ሙሉ የመማር መብትን ማሳደግ አለብን።

# የተግባር ጥሪዎች

ሪፖርቱ ለትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውል ጥረቶችን ለማቀናጀት እና ለማስማማት ሁለት ጥሪዎችን አውጥቷል። እነሱም ለትምህርት አዲስ የጥናት አጀንዳ ጥሪ እና ትምህርትን እንደ የጋራ ሀብት ለመደገፍ የታደሰ የአጋርነት እና ትብብር ጥሪ ናቸው። ለእነዚህ ሁለት ጥሪዎች ምላሽ ለማግኘት የሚረዱ መርሆዎች በፍጥነት ለሚለዋወጡ ሁኔታዎች ምላሽ በመስጠት አዲስ የወደፊት የትምህርት ዕድል ለመፍጠር የምናደርገውን ጥረት ለማገዝ እና ለማጠናከር እዚህ ጠቅለል ተደርገው ቀርበዋል።

## ለትምህርት አዲስ የምርምር አጀንዳ

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተመለከቱት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ወጥነት ያለው እና የጋራ የምርምር አጀንዳን ፈጥረዋል። ከእንዲህ ዓይነቱ ሰፊ የምርምር አጀንዳ የሚመነጨው ትምህርት፣ ግንዛቤ እና ልምድ የትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውል በጋራ ለመሥራት አበረታች ይሆናል። ወደ 2050 ስናማትር፣ ለወደፊት የትምህርት ዕድል ምርምር እና ፈጠራን የሚመሩ አራት ቅድሚያዎች አሉ፡-

አንደኛ፡- በትምህርት የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ የሚካሄደው ዓለም አቀፍ የጋራ የምርምር መርሃ ግብር ወደፊት የሚገጥሙትን ችግሮች በመገመት እና የእነሱን አንድምታ ግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው የመማር መብት ማግኘታቸው ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። በዚህ ሪፖርት ውስጥ በቀረቡት የመመሪያ መርሆች እና የትምህርትን ዕድሳት ዕውን ለማድረግ ምርምር እንዲሁ ከመለካት እና ከትችት ማለፍ አለበት። ይህ የምርምር መርሐ ግብር ወደ አዲስ ማኅበራዊ

የትምህርት ውል እንድንሸጋገር ከወደፊት ዕውቀት እና ከወደፊት አስተሳሰብ አንጻር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እንደገና ማደራጀት አለበት።

ሁለተኛ፡- የትምህርት ወደፊቶች ዕውቀት፣ ውሂብ እና ማስረጃዎች ልዩ ልዩ የዕውቀት ምንጮችን እና የማወቅ መንገዶችን ማካተት አለባቸው። ከተለያየ አመለካከቶች የሚገኙ ግንዛቤዎች እርስበርስ ከመገፋፋት እና ከመተካካት ይልቅ፣ ስለ ስለ ትምህርት የጋራ ግንዛቤ መጨበጥ የሚያስችሉ አውታረ ብዙ ዕይታዎችን ያቀርቡልናል። ተመራማሪዎች፣ ዩኒቨርስቲዎች እና የምርምር ተቋማት ከቅኝ ግዛት ነፃ የሆኑ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ሰብአዊ መብቶችን ለመጠቀም እና ለማስተዋወቅ የሚያመቻቹ ስልታዊ ግምቶችን እና አቀራረቦችን መመርመር አለባቸው። ትምህርት ቤቶች፣ መምህራን፣ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች፣ የወጣቶች ንቅናቄዎች እና ማኅበረሰቦች ወሳኝ የዕውቀት እና የመረጃ ምንጮች ስለመሆናቸው በተመራማሪዎች ዘንድ ዕውቅና ሊሰጣቸው ይገባል። ከመማር ሳይንሶች፣ ከኒውሮሳይንስ፣ ከዲጂታል እና ከትልቅ ውሂብ እና ከስታቲስቲክስ አመላካቾች የተገኙ ግኝቶች፣ የጥራት እና ተግባራዊ ምርምርን ጨምሮ ከብዙ የተጨባጭ ግብአቶች ጋር ሲታዩ ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ሊሰጡ ይችላሉ።

> *በትምህርት የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ የሚካሄደው ዓለም አቀፍ የጋራ የምርምር መርሃ ግብር ሁሉም ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው የመማር መብት ማግኘታቸው ላይ ያተኮረ መሆን አለበት።*

ሦስተኛ፡- ትምህርታዊ ኢኖቬሽን በልዩ ልዩ ዐውዶች እና ቦታዎች ላይ በጣም ሰፊ ዕድሎችን የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት። ንጽጽር እና ተመክሮዎች እንደገና ሲጤኑ እና በተገቢው ዐውድ ማኅበራዊ እና ታሪካዊ ዕውነታዎች ውስጥ ሲከወኑ፣ ሰዎችን ሊያበረታቱ ይችላሉ። ትምህርታዊ ኢኖቬሽን አንዳንድ ጊዜ አሁን ያሉት መደበኛ ሥርዓቶች ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድር ተቋማዊ ውህደት ለመላቀቅ መሞከር አለበት። ግምገማ እና ጽብረቃ በአንድ ወገን ከመቀዛቀዝ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ማለቂያ ከሌለው የሥርዓት ለውጥ ዑደት በሚያላቅቅ የለውጥ ፅንሰ ሐሳብ መደበኛ ማሻሻያ እያደረገ ቀጣይነት ባለው እና በተቀናጀ መንገድ የትምህርት ፖሊሲዎችን መምራት አለበት።

አራተኛ፡- ስለ የትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውል በሚደረጉ ውይይቶች ላይ በመደበኛነት የማይገኙትን ያልሆኑትን ጨምሮ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ ብዙ ሰዎችን በሚያካትት መልኩ እንደገና መደራጀት አለበት። በተለይ በመምህራን፣ ተማሪዎች እና ትምህርት ቤቶች መካከል የአዲሱ የማኅበራዊ ውል ዘሮች በሕይወት አሉ። የትምህርት አዲስ የማኅበራዊ ውልን አብሮ ግንባታ የሚያፋጥን የምርምር አጀንዳን በመቅረጽ የመሳተፍ እና የመደገፍ ልዩ ኃላፊነቶች በምርምር ተቋማት፣ መንግሥታት እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ላይ ያርፋሉ። ዩኔስኮ ስለ ለጋራ የወደፊት የትምህርት እጣ ፈንታችን የዕውቀት፣ ራዕይ እና የሐሳብ ማፍለቂያ ቤት በመሆን ትልቅ ሚና ሊጫወት ይችላል።

# የታደሰ ዓለም አቀፍ አጋርነት እና ትብብር

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተገለፀው ታላቅ ራዕይ ያለ አጋርነት እና ትብብር በምንም መጠን ሊሳካ አይችልም - ከመማሪያ ክፍሎች እና ትምህርት ቤቶች አፋጣኝ አደረጃጀት ጀምሮ እስከ ሰፊ ሀገራዊ፣ ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ቁርጠኝነት እና የፖሊሲ ማዕቀፎች ድረስ። ሪፖርቱ ትምህርትን እንደ ሕዝብ እና የጋራ ሀብት በመደገፍ ለዓለም አቀፍ ትብብር አዲስ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ወደ 2050 ስናማትር፣ ከዓለም አቀፍ አብሮነት እና ለወደፊት የትምህርት ዕድል ትብብር ጋር የተያያዙ አራት መመሪያዎችን ማክበር አለብን።

አንደኛ፡- ኮሚሽኑ ሁሉም የትምህርት ባለድርሻ አካላት በጋራ ዓላማዎች እና የትምህርት ተግዳሮቶች ላይ የጋራ መፍትሄዎችን ለመፍጠር በዓለም አቀፍ እና በክፍለ ዓለም ደረጃ እንዲሠሩ ጥሪውን ያቀርባል። ጥረቶቹ በሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የመማር መብት እና በትምህርት የሕዝብ እና የጋራ ሀብትነት እሴት ላይ በመነሳት፣ ለሁሉም የሰው ልጅ ፍትሐዊ እና የተመጣጠነ የወደፊት ትምህርት ከመፍጠር ራዕይ ጋር ራሳቸውን ማስማማት እና አቅጣጫቸውን መቃኘት አለባቸው። የጋራ እርምጃዎች በተለይ በዓለም አቀፍ ነውጦች እና ለውጦች ምክንያት የመማር መብታቸው ላይ ስጋት ለተጋረጠባቸው

ተማሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። በሚቀጥሉት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ፣ ዓለም አቀፍ ትብብር የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻዎችን እና አጋሮችን ማካተት፣ ከከላይ ወደ ታች ወደ ማዕከለ-ብዙነት መራመድ፤ እና አዲስ ቀጣናዊ ትብብር ዓይነቶች፣ በተለይም የደቡብ-ደቡብ እና የሦስት ማዕዘን ትብብርን ማካተት አለበት።

*የጋራ እርምጃዎች በተለይ በዓለም አቀፍ ነውጦች እና ለውጦች ምክንያት የመማር መብታቸው ላይ ስጋት ለተጋረጠባቸው ተማሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።*

ሁለተኛ፡- ፣ ዓለም አቀፍ ትብብር በድኅማ መርህ ላይ በመመሥረት፣ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የአካባቢ፣ ብሔራዊ እና ቀጣናዊ ጥረቶችን መደገፍ እና አቅማቸውን መገንባት አለበት። አዳዲስ የትምህርት ቃል ኪዳኖችን፣ ደንቦችን እና ደረጃዎችን ለማጠናከር የተገቡትን ቃል ኪዳኖችም ለማስፈጸም እና ለትምህርታዊ ማሻሻያዎች የተቀናጀ ድጋፍ ለማድረግ የተጠናከረ ተጠያቂነት ያስፈልጋል። በወደፊት ዘላቂ ትምህርት ራዕያችን ላይ ውጤታማ ሚና ለመጫወት ዩኔስኮ የትምህርት ልማት አካሄዱን እንደገና ማጤን ይኖርበታል። በመጀመሪያ የድኅማን መርህ መሠረት በማድረግ ድርሻው ክልላዊ እና ሀገራዊ ተቋማትን እና ሂደቶችን ማጠናከር አጋር አድርጎ ራሱን ማየት አለበት። በሁለተኛ ደረጃ፣ የማስረጃ አገናኝ እና የተጠናከረ መረጃ እና ተጠያቂነት ለዜጎች በሁሉም የትምህርት ሥርዓቶች እንዲቀርብ የሚሟገት ጠበቃ መሆን አለበት።

ሦስተኛ፡- አነስተኛ ገቢ እና አነስተኛ መካከለኛ ገቢ ላላቸው አገሮች ለሚደረግ የዓለም አቀፍ ልማት የፋይናንስ ድጋፍ ትኩረት መስጠት አሁንም ጠቃሚ ነው። ዓለም አቀፍ ትብብር አብዛኛው የገንዘብ እና የሰው ኃይል ሀብቱ የመማር መብት አደጋ ላይ የወደቀባቸው ቀጣናዎች፣ በተለይም በ2050 አብዛኞቹ የዓለም ወጣቶች በሚኖሩባት እና በሚማሩባት አፍሪካ ላይ ማተኮር ይኖርበታል። እነዚህ ሀብቶች የአየር ንብረት ለውጡ ሲፋጠን በተደጋጋሚ ሊጨምሩ ወደሚችሉት የአደጋ ጊዜ ሁኔታዎች አቅጣጫ ይመራሉ።

አራተኛ፡- በማስረጃ፣ በውሂብ እና በዕውቀት ላይ የሚደረጉ የጋራ ኢንቨስትመንቶች የውጤታማ ዓለም አቀፍ ትብብር ወሳኝ አካላት ናቸው። በቀጣዮቹ ዐሥርት ዓመታት እርስበርስ መማማርን እና የዕውቀት ልውውጦችን በማኅበረሰቦች እና ድንበሮች ሁሉ ማጠናከር አለብን፤ ይህም እንደ የትምህርት አለመመጣጠንና እና ድህነትን ማቆም እና የሕዝብ አገልግሎቶችን ማሻሻል በመሳሰሉት ዋና ዋና ጉዳዮች እና በአውቶሜትድ እና ዲጂታይዜሽን፣ ፍልሰት እና ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃን በመሳሰሉ የረዥም ጊዜ ተግዳሮቶች ላይ ሊያተኩር ይችላል። ይህንን በአገሮች እና በቀጣናዎች መካከል ያለውን ልውውጥ ለማመቻቸት ዩኔስኮ ወሳኝ ሚና አለው።

# ውይይት እና ተሳትፎ

ለተስፋ የሚያበቃ ትልቅ ምክንያት አለ። በትምህርት ሥርዓቶች ንድፍ፣ በትምህርት ቤቶች እና በሌሎች የትምህርት ሥርዓቶች አደረጃጀት እና በሥርዓተ ትምህርት እና በሥነ ትምህርታዊ አቀራረቦች መጠነ ሰፊ ለውጥ እና ፈጠራ ማድረግ ይቻላል። ባለው ላይ በመመሥረት እና የሚያስፈልገውንም በመገንባት፣ በጋራ ፍትሐዊ፣ ተመጣጣኝ እና ዘላቂ የወደፊት እጣዎችን ለመገንባት ትምህርትን መለወጥ እንችላለን።ለውጥ እና ፈጠራ ማድረግ ይቻላል። ባለው ላይ በመመሥረት እና የሚያስፈልገውንም በመገንባት፣ በጋራ ፍትሐዊ፣ ተመጣጣኝ እና ዘላቂ የወደፊት እጣዎችን ለመገንባት ትምህርትን መለወጥ እንችላለን። በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ የግል እና የጋራ ቁርጠኝነት፣ አመራር፣ ጽናት፣ ፈጠራ እና የመተሳሰብ ተግባራት አማካኝነት አካሄዱን እንለውጣለን። የምንገነባባቸው ጥልቅ፣ የበለጸጉ እና ልዩ ልዩ ባሕላዊ ወጎች አሉን። ሰዎች ታላቅ የጋራ የመፈጸም ብቃት፣ ዕውቀት እና ፈጠራ አላቸው። ሁሉም አዳዲስ ዕድሎችን ሊፈጥሩ ስለሚችሉ ተስፋ ሰጪ ልምምዶች አዲስ ፈጠራ ወይም በትውፊት ላይ የተመሠረቱ ሊሆኑ ይችላሉ።

*በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ የግል እና የጋራ ቁርጠኝነት፣ አመራር፣ ጽናት፣ ፈጠራ እና የመተሳሰብ ተግባራት አማካኝነት አካሄዱን እንለውጣለን።*

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የቀረበው ውይይት በተቻለ መጠን ሰፊ ተሳትፎን ማካተት አለበት። ትምህርት በዜግነት፣ በአካባቢያዊ፣ በብሔራዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች ውስጥ ወሳኝ ነገር ነው። ሁሉንም ሰው ይመለከታል፣ እና ሁሉም ባሉበት በማንኛውም የተፅእኖ መስክ የወደፊት የትምህርት ዕድልን በመገንባት መሳተፍ ይችላሉ። ይህ ሪፖርት ወደፊት የሚጠብቀውን ውይይት እና ተግባር የበለጠ ለማስረጽ በተለይ የመምህራንን፣ የዩኒቨርስቲዎችን፣ የመንግሥታትን፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችን እና የወጣቶች ተሳትፎ የሚጠይቁ ሚናዎች እንዳሉ ሐሳብ አቅርቧል።

- ***መምህራን። መምህራን ለወደፊት የትምህርት ዕድል ዋና ተዋናዮች ሆነው ይቆያሉ።*** ከ20ሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሥራ ላይ ለነበረው የማኅበራዊ ውል መሠረት እንደነበሩ ሁሉ፣ በአዲሱ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ግንባታ ወሳኝ ሰብሳቢዎች፣ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች ይሆናሉ። ለዚህም ራስ ገዝነታቸውን እና ነጻነታቸውን ማረጋገጥ፣ በሙያዊ ሕይወታቸው በሙሉ ዕድገታቸውን መደገፍ እና በሕብረተሰቡ ውስጥ ላላቸው ሚና እና በመንግሥት ፖሊሲዎች ውስጥ ላላቸው ተሳትፎ ዕውቅና መስጠት ያስፈልጋል። መምህራን በውይይት እና በፈጠራ ሂደቶች ግንባታ፣ በማስተባበር እና ሌሎች ሰዎችን እና ቡድኖችን በማሰባሰብ ዋና ተዋናዮች ይሆናሉ።
- **ዩኒቨርስቲዎች እና ከፍተኛ ትምህርት።** በአዲሱ የትምህርት ማኅበራዊ ውል በሁሉም ዕውነታዎች ውስጥ እንደመገኘታቸው፣ በዚህ ሪፖርት በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ለዩኒቨርስቲዎች እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልዩ ጥሪዎች ቀርበዋል። ዛሬ ዩኒቨርስቲዎች እና ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዕውቀትን በመፍጠር እና በማሰራጨት ረገድ የሚጫወቱትን ወሳኝ ሚና የሚጠራጠሩ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው። ይህ በሁሉም ዘርፎች ውስጥ ቢሆንም፣ በተለይ ትምህርትን በተመለከተ ዕውነት ነው። አብዛኛው የመሠረታዊ ትምህርት የወደፊት ዕጣ የሚወሰነው በዩኒቨርስቲዎች በተሠራው ሥራ ላይ ነው። አብዛኛው የዩኒቨርስቲዎች የወደፊት እጣ ፈንታ ደግሞ በመሠረታዊ ትምህርት ውስጥ በተከናወነው ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው። ዩኒቨርስቲዎች ሕፃናትን እና ወጣቶችን በተለይም ትንንሽ ልጆችን ለማስተማር እና በጎልማሶች ትምህርት ተግባራት ላይ የበለጠ ለመሳተፍ አዳዲስ እና የበለጠ ውጤታማ መንገዶችን እንዲያገኙ ይጠበቃል። ከፍተኛ ትምህርት የበይነ-ትውልዳዊ እና የለዋጭ ውይይት ቦታ ነው፤ ስለዚህ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተገለጹት የወደፊት እጣዎች አብዛኛው ክፍል በእነሱ ላይ የተመሠረተ ነው። ጠንካራ፣ ራሱን የቻለ፣ ተዓማኒነት ያለው እና ፈጠራዊ ከፍተኛ ትምህርት ከሌለ፣ በዚህ ሪፖርት የታሰበውን የትምህርት ማኅበራዊ ውል መገንባት አይቻልም።
- ***መንግሥታት።*** ይህ ሪፖርት ለመንግሥታት የማይተካ ሚና አፅንዖት ሰጥቷል። ይህ ማለት ግን የውሳኔ ሐሳቦቹ በብሔራዊ የትምህርት ሥርዓቶች ደረጃ ብቻ የተቀመጡ ናቸው ማለት አይደለም። ስለ ትምህርታዊ ማሻሻያ ሪፖርቶች የተለመደውን መንግሥትን ያማከለ አመክንዮ ከመከተል ይልቅ፣ ይህ ሪፖርት ሰፋ ባለ መልኩ ባለድርሻ አካላት በምርምር፣ በዕውቀት፣ በፈጠራ፣ በመተንተን እና በተግባር እንዲሳተፉ ለማበረታታት ያለመ ነው። አነስ ባለ የተሃድሶ አመክንዮ፣ በሰፋፊ ተሳትፎ

አራማጆችነታቸው እና በፈጠራ አፋጣኞችነታቸው አንፃር የመንግሥታትን ተግባር በብዙ እርከኖች የመገምገም ጥያቄ ነው። በተጨማሪም፣ መንግሥታት በቁ እና ዘላቂ የሕዝብ የትምህርት ፋይናንስን በማረጋገጥ፣ የትምህርትን ሕዝባዊ ባሕርይ በመጠበቅ እና በማጠናከር እና ትምህርትን በአግባቡ የመቆጣጠር አቅምን በማሳደግ ልዩ ሚና አላቸው።

- **ዓለም አቀፍ እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች።** ይህ ሪፖርት በተለይም ትምህርትን እንደ ሕዝባዊ እና የጋራ ሀብት በተደጋጋሚ ለማረጋገጥ ዓለም አቀፍ እና ሲቪክ ማኅበራት ላላቸው አስፈላጊነት አፅንዖት ሰጥቷል። ድግግሞሹ በአገር ውስጥ፣ በአገር አቀፍ፣ በቀጣናዊ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ እና በተለያዩ ዘርፎች በትምህርት ትብብር ውስጥ ለአዳዲስ ድምፆች ቦታ በመስጠት፣ የአመለካከት ለውጥ ማስፈለጉን ለማሳየት የታሰበ ነው። የዓለም አቀፍ እና የሲቪክ ማኅበራት ንቅናቄ በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረበውን ውይይት እና ልዩ ዕውቀት፣ ሙያ እና የማሰባሰብ ዐቅማቸውን እንደሚጠቀሙ ይጠበቃል። እነዚህ ድርጅቶች በሐሳባቸው፣ በፆታ፣ በዘር ወይም በጎሳ፣ በባሕል፣ በሃይማኖታዊ እምነታቸው ወይም በፆታዊ ማንነታቸው ምክንያት አድሎ የሚደርስባቸው ሰዎች እንዲሰሙ፣ እንዲታዩ እና የመማር መብታቸው እንዲደገፍ በማድረግ ረገድ ልዩ ቦታ አላቸው።
- **ወጣቶች እና ሕፃናት።** በመጨረሻም እዚህ የቀረበው ውይይት ያለምንም ማመንታት ወጣቶችን ማካተት አለበት። መጪው ጊዜ ሸክም ሳይሆን የዕድሎች ስብስብ ሆኖ ሊቀረጽላቸው ይገባል። ይሄ እነሱን የማዳመጥ ወይም የማማከር ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የእነርሱ የሆነውን እና የሚሆነውን ነገ በመገንባት እንዲሳተፉ የማስተባበር እና የመደገፍ ጉዳይ ነው። በተለይ የአየር ንብረት ለውጥን በመዋጋት፣ የዘር መድልኦን በመቃወም፣ በአባዊ እና ገዳቢ የሥርዓተ ጾታ ደንቦች ላይ፣ እና ለባሕሎች ብዝሃነት እና ቀደምቶች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ሂደት ያደረጓቸው የወጣቶች የቅርብ ጊዜ ወሳኝ ንቅናቄዎች ለወደፊቱ አስፈላጊ መንገዶችን ያሳየናል። እነዚህን ንቅናቄዎች የሚመሩት ወጣቶች ፍቃድ አልጠየቁም። ይልቁንም ብዙ ጊዜ አዋቂዎችን ለሚያደክሙ ወይም ሽባ ለሚያደርጉ ጉዳዮች አስቸኳይ እና የሞራል ግልጽነት ያለው ምላሽ ሰጥተዋል። የእኛን እና የወደፊት እጣ ፈንታቸውን በመገንባት ረገድ ትልቅ እና መሪ ሚና አላቸው። የዚህ ሪፖርት ቀጣይነት በጣም አስፈላጊው ገጽታ በአዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ቀረጻ ወጣቶችን የማሳተፍ አቅሙ ነው።

በዓለም ዙሪያ ያሉ መምህራን፣ ማኅበረሰቦች፣ ድርጅቶች እና መንግሥታት አስፈላጊውን ለውጥ ለመፍጠር ብዙ ተስፋ ሰጭ ትምህርታዊ ውጥኖችን ጀምረዋል። ስፍር ቁጥር የሌላቸው ምሳሌዎች ዕውቀትን በጋራ መፍጠር እና በአደባባይ መካፈል የሚቻልባቸውን በርካታ መንገዶች ያሳዩናል። ሌሎች ምሳሌዎች ትምህርት እንዴት ትርጉም እንደሚፈጥር፣ እንደሚያበረታታ እና ነፃ እንደሚያወጣ፣ ከዚህም በተጨማሪ መማር ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለጋራ ጥቅም መደራጀት እንደሚያስችልም ያሳዩናል። እነዚህ ነባር ልምምዶች በተስፋ ለተሞሉ ወደፊቶች መንገድ ስለሚጠርጉ ሊበረታቱ ይገባል።

በዓለም ዙሪያ እየተካሄደ ያለው መልካም ሥራ በይበልጥ መታወቅ አለበት። ኮሚሽኑም ዩኔስኮ ተስፋ ሰጭዎቹን ልምምዶች ለማስቀጠል እና በዚህ ሪፖርት ውስጥ የቀረቡትን መሠረታዊ መርሆች ለመተግበር የለውጥ አፋጣኝነት እና የአሰባሳቢ መድረክነት ሚና እንዲጫወት ይመክራል።

# ለመቀጠል የቀረበ ግብዣ

በመሠረቱ ይህ ሪፖርት ስለ አስፈላጊ የወደፊት እጣዎች እና ትምህርት እነሱን ለመገንባት እንዴት እንደሚረዳቸው ማመቻቸት እና ሰፊ ማኅበራዊ ውይይቶችን ማመቻቸት እና ማነሳሳት ይፈልጋል። ሐሳቦቹ የሁለት ዓመት የውይይት እና የምክክር ሂደት ውጤትን በማጎልበት ትንሽ ጊዜ ውስጥ ያንፀባርቃሉ። የሪፖርቱ ሐሳቦች ወደፊት ብዙ ውይይቶችን፣ ትብብርን እና አጋርነቶችን ለመቀጠል በቀረቡ ግብዣዎች ይጠናቀቃሉ። ለወደፊት የትምህርት ጉዳይ በጣም አስፈላጊ የሆኑት እነዚያ ንግግሮች፣ ትብብር እና አጋርነቶች እንጂ ሪፖርቱ ራሱ አይደለም።

ሪፖርቱ ለወደፊት ለማስተማር የሚደረጉ ጥረቶችን እና ተግዳሮቶችን በተመለከተ ራዕይ ቢቀርጽ እና ይህንንም እንዴት ዕውን ማድረግ እንደሚቻል ሐሳቦችን ቢያስቀምጥም፣ አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል ራሱን በራሱ የሚያስፈጽም እንዳልሆነ በአንክሮ ገልጿል። ይልቁንም መልክ እንዲይዝ እና ተጽዕኖ እንዲያሳድር የተማሪዎችን እና የመምህራንን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እና ልምዶችን ወደሚቀይሩ መርሐ ግብሮች፣ ግብዓቶች፣ ሥርዓቶች እና ሂደቶች መተርጎም አለበት።

ትምህርት ብዙ ግለሰቦችን እና ቡድኖችን ውስብስብ በሆነ የግንኙነት መረብ ውስጥ ያሳትፋል። ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ ቤተሰቦችን፣ የትምህርት አስተዳዳሪዎችን እና በተለያዩ የመንግሥት እርከኖች ያሉ መሪዎችን ያካትታል፤ እንዲሁም በማኅበረሰቦች፣ በአውራጃዎች፣ በአገሮች፣ በቀጣና እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሕዝብ ሴክተርን እና የሲቪል ማኅበረሰብን ይነካል። የትምህርት ባሕል ለውጥ ብዙ ቡድኖች ከዳዲስ ሐሳቦች አንጻር እና ከሌሎች ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ እንደገና ለመመርመር ፍላጎቶቻቸውን እና ግንዛቤዎቻቸውን የሚያዋጡበት የአብሮ ግንባታ ሂደቶች ውጤት ነው። እዚህ የተነሡትን መርሆች፣ ሐሳቦች እና ስልቶች ወደ አዲስ ዕውነታዎች ለመተርጎም ትብብር አስፈላጊ ነው። እንዴት እንደምናስተምር እና እንደምንማር እና ውጤቱም ምን እንደሚሆን ሐሳቦችን አብሮ መገንባት በመጨረሻም ወደ ግልፅነት፣ ቁርጠኝነት እና የትምህርት ተግባራትን ሊለውጡ ወደሚችሉ ግብዓቶች እና እንቅስቃሴዎች ወደሚደረግ ድጋፍ ያመራል። ይህንን ለውጥ ሊደግፉ የሚችሉ ሁኔታዎችን በደንብ ስንረዳቸው፣ ስንቀበላቸው እና ስንተገብራቸው ልምምዶች ይለወጣሉ።

እያንዳንዳችን የምንኖርባቸውን ማኅበረሰቦች ማሻሻል እንችላለን። ሁላችንም ውይይት የማስተባበር ዕድሉ አለን። ይህ በተለይ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች በየቦታው ተገኝተው ለተርታ ሰዎች የመገናኘት እና የማደራጀት እና ጠንካራ ዓላማዎችን የማሳካት መድረክ በሚሰጡበት በዚህ ዘመን ዕውነት ነው። የቴክኖሎጂ እና የኢንተርኔት አገልግሎት ማግኘት በመምህራን፣ በትምህርት ተቋማት እና በማኅበረሰቦች መካከል ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ትብብር ፈጥሮ ለችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ያስችላል።

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በዚህ ሪፖርት መውጣት እና በሌሎችም በአብዛኛዎቹ ዝግጅቶቹ ላይ ጥላውን ጥሏል። ይህ ዓለም አቀፋዊ ክስተት ለሰፊ ትብብር እና አብሮ ግንባታ አስፈላጊነት ዕውቅናን አንቅቷል። በኮቪድ-19 ምክንያት የደረሰውን የትምህርት ጉዳት እና ኪሳራ ሙሉ በሙሉ መለካት ቢያስፈልግም፣ ነገር ግን ከባድ እንደሆነ እና የዓመታት ዕድገትን የመደምሰስ አደጋ እንዳለው እናውቃለን። ከሌሎች ተግዳሮቶች ጋር ተዳምሮ መዘዙ በበረታባቸው በድሆች እና የተገለሉ ሰዎች፣ በግሎባል ደቡብ በጣም ከባድ ሆኖ ተሰምቷቸዋል። የሞት እና የማጣት ዱካው፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ዕውነታዎች መፋጠን እና መጠናከር ጋር ተዳምሮ፣ በዚህች ፕላኔት ላይ ከሌሎች ጋር የተገናኘን መሆናችንን በጠንካራ ሁኔታ ያስታውሰናል። የኮቪድ-19 መከላከያ የክትባቶች ፈጠራ በዕውቀት፣ በሳይንስ እና በመማር ዙሪያ አንድ ላይ ስንሰባሰብ ምን በምን ፍጥነት እስከምን ድረስ ማድረግ እንደምንችል አሳይቷል። ይህ ሪፖርት አዲስ የተገኘ ዕውቅናን ለመሰብሰብ እና አዲስ እና ብሩህ ትምህርታዊ የወደፊት እጣዎችን ለመገንባት ለሚደረገው ጥሪ አበረታች እንደሚሆን ተስፋ ያደርጋል።

በዚህ አንገብጋቢ፣ ግን ደግሞ ታላላቅ ተስፋዎች ባሉት አውድ ውስጥ፣ በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተገለጹት ሐሳቦች የወደፊት ሕይወታችንን በጋራ እንድናስብ እና አዲስ የትምህርት ማኅበራዊ ውል እንድንገነባ ይረዱናል። ይህ ሪፖርት የትምህርት የወደፊት እጣዎችን በጋራ ለመገንባት በጋራ የማጤን እና የመተግበር ግብዣ ነው። መነሻ ነው፣ የውይይት እና የትብብር ሂደት መጀመሪያ ነው። ይህ ሪፖርት፣ ልክ እንደ ትምህርት አላለቀም። በተቃራኒው፣ ተግባራዊነቱ አሁን የሚጀምረው በዓለም ዙሪያ ባሉ አስተማሪዎች እና ከእነሱ ጋር በሚሠሩ ሰዎች ጉልበት ነው።

# አባሪዎች

# የተመረጡ ማጣቀሻዎችየተመረጡ ማጣቀሻዎች

## ገለልተኛ ሪፖርቶች

ዋና ዋና ተግዳሮቶችን እና ዕድሎችን ለመለየት እና ግብዓቶችን እና ምክሮችን ለዓለም አቀፍ የትምህርት ወደፊቶች ኮሚሽን ለማቅረብ ሴሚናሮችን እና የሥራ ቡድኖችን ለማዘጋጀት ለቀረበው ግልጽ ጥሪ በምላሽነት የሚከተሉት ሪፖርቶች ቀርበዋል። 200 የሚሆኑ ሌሎች ድርጅቶችም የትኩረት ቡድኖችን መሠረት በማድረግ ለዩኔስኮ የወደፊት የትምህርት ተነሳሽነት ሪፖርቶችን አቅርበዋል። እነዚህ አጋሮች "የዓለም አቀፍ ምክክር አስተዋጽኦ አበርካቾች" በሚለው ክፍል ከታች ተዘርዝረዋል።

Arab Campaign for Education for All. 2020. *Summary report on the Futures of Education in the Arab States: Building the future (2020-2050)*. Ramallah, Arab Campaign for Education for All. http://www.teachercc.org/articles/view/379

Asia South Pacific Association for Basic and Adult Education. 2021. *From the margins to the center: Youth informing the futures of education. Manila, Asia South Pacific Association for Basic and Adult Education*. http://www.aspbae.org/userfiles/2021/Futures_of_Education_Report.pdf.

Barber, P., Bertet, M., Choi, J., Czerwitzki, K., Njobati, F. F., Grau I Callizo, I., Hambrock, H., Herveau, J., Kastner, A., Laabs, J., Manalo, A., Mesa, J., Mutabazi, S., Muthigani, A., Richard, P., Scheunpflug, A., Sendler-Koschel, B., White, M., and Wodon, Q. 2020. *Christian schools and the futures of education: a contribution to UNESCO's Futures of Education Commission by the International Office of Catholic Education and the Global Pedagogical Network – Joining in Reformation. International Office of Catholic Education and Global Pedagogical Network – Joining in Reformation*. http://oiecinternational.com/wp-content/uploads/2020/12/OIEC-GPENR-contribution.pdf

Bridge 47. 2020. *The role of education in addressing future challenges*. Bridge 47. https://www.bridge47.org/sites/default/files/2020-12/bridge47_-_report_to_unesco_foe_international_commission_final.pdf

Éducation, Recherches et Actualités. 2021. *L'Éducation du futur - L'enseignement supérieur : défis et paradoxes*. Beirut et Paris, Université Saint Joseph et Université Gustave Eiffel. https://www.periodicos.ufam.edu.br/index.php/larecherche

Emmaüs International. *2020. Rapport à l'attention de la commission internationale de l'initiative de l'UNESCO : « Les futurs de l'éducation : apprendre à devenir »*. Montreuil, France, Emmaüs International. https://emmaus-international.org/images/actualites/2020/10/EMMAS_INTERNATIONAL_-_Contribution_Les_futurs_de_lducation__juillet_2020_003.pdf

Garcés, C. E. *2020. Aportación para la Comisión Internacional. Madrid.*

International Council for Adult Education (ICAE). *2020. Adult Learning and Education (ALE) – Because the future cannot wait*. International Council for Adult Education. https://en.unesco.org/futuresofeducation/sites/default/files/2020-10/ICAE%20-%20Futures%20of%20ALE%20FINAL.pdf

International Task Force on Teachers for Education 2030. 2021. *The futures of teaching: Background paper prepared for the Futures of Education Initiative*. Paris, UNESCO https://teachertaskforce.org/knowledge-hub/futures-teaching-background-paper-prepared-futures-education-initiative-0

International Union for Conservation of Nature (IUCN) Commission on Education and Communication (CEC). 2021. *Visions and Recommendations for the Futures of Education.* Gland, Switzerland, International Union for Conservation of Nature. https://www.iucn.org/sites/dev/files/content/documents/cec_report_to_unesco_foe_-_6.5.pdf

Mouvement International ATD Quart Monde. 2020. *Contribution du Mouvement International ATD Quart Monde aux Futurs de l'Éducation.* Pierrelaye, France, Mouvement ATD Quart Monde – Agir Tous pour la Dignité. https://nextcloud.atd-quartmonde.org/index.php/s/DzMMci4yqP6dkPA

Red Regional por la Educación Inclusiva de Latinoamérica. 2020. *Los futuros de la educación - Contribuciones de la Red Regional por la Educación Inclusiva de Latinoamérica. Buenos Aires, Red Regional por la Educación Inclusiva de Latinoamérica.* https://rededucacioninclusiva.org/wp-content/uploads/2020/09/Los-futuros-de-la-educaci%C3%B3n-Contribuciones-de-la-Red-Regional-por-la-Educaci%C3%B3n-Inclusiva-de-Latinoam%C3%A9rica.pdf

Schulte, D., Cendon, E. and Makoe, M. 2020. *Re-Visioning the Future of Teaching and Learning in Higher Education: Report on Focus Group Discussions for the UNESCO Futures of Education Initiative.* University of the Future Network. https://unifuture.network/wp-content/uploads/sites/2/2020/08/20200722_UFN_UNESCO-report_fin.pdf

SDG-Education 2030 Steering Committee. 2020. *Contribution to the Futures of Education. Paris,* UNESCO. https://sdg4education2030.org/sites/default/files/2020-07/Futures%20of%20Education%20SDG-Ed2030%20SC%20contribution%20July%202020.pdf

Sefton-Green, J., Erstad, O. and Nelligan, P. 2021. *Educational Futures Across Generations.* Centre for Research for Educational Impact (REDI) at Deakin University and Department of Education at the University of Oslo. https://www.deakin.edu.au/__data/assets/pdf_file/0005/2298551/Educational-Futures-Across-Generations.pdf

Seguy, F. 2021. *Penser l'avenir de l'éducation en contexte de pandémie.* Port-au-Prince, UNESCO. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000378392

UNESCO. 2020. *Humanistic Futures of Learning: Perspectives from UNESCO Chairs and UNITWIN Networks.* Paris, UNESCO. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000372577/PDF/372577eng.pdf.multi

UNESCO Institute for Lifelong Learning. 2020. *Embracing a culture of lifelong learning: Contribution to the Futures of Education Initiative.* Hamburg, UNESCO Institute for Lifelong Learning. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000374112/PDF/374112eng.pdf.multi

UNESCO International Institute for Higher Education in Latin America and the Caribbean (IESALC). 2021. *Thinking Higher and Beyond: Perspectives on the Futures of Higher Education to 2050.* UNESCO International Institute for Higher Education in Latin America and the Caribbean. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000377530

UNESCO. 2021. *Caribbean Futures of Education – Final Report*. Kingston, UNESCO. https://en.unesco.org/caribbean-futures-of-education

UNESCO's Collective Consultation of NGOs on Education 2030. 2021. *The role of Civil Society Organisations in 2050 and beyond.* Paris, UNESCO's Collective Consultation of NGOs on Education 2030. https://en.unesco.org/system/files/the_role_of_csos_in_2050_and_beyond.pdf

Unescocat and Fòrum Futurs de L'educació. 2020. How to Get to the Future of Education: Lessons Learned from the Escola Nova 21 Alliance in Catalonia. Unescocat-Center for UNESCO of Catalonia. https://catesco.org/wp-content/uploads/2020/10/Unescocat-contribution-to-Futures-of-Education.pdf

Wong, S., Kwok, V., Kwong, T. and Lau, R. 2020. Individuality, Accessibility, and Inclusivity: Applied Education and Lifelong Learning in Revolutionising Education for the 21st Century. Our Hong Kong Foundation. https://ourhkfoundation.org.hk/sites/default/files/media/pdf/UNESCO_submission_13102020.pdf

World Council on Intercultural and Global Competence. 2021. Contribution from the World Council on Intercultural and Global Competence to the UNESCO Futures of Education Initiative. https://iccglobal.org/wp-content/uploads/World-Council-Futures-of-Education-Learning-to-Become-Initiative_.pdf

Yidan Prize Foundation. 2021. Perspectives from the Yidan Prize Foundation Council of Luminaries on the Futures of Education.

# የዳራ ጥናቶች

የዓለም አቀፉ የትምህርት ወደፊቶች ኮሚሽን ባስቀመጣቸው ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ለማራመድ ይረዳ ዘንድ ዩኔስኮ የሚከተሉትን የዳራ ጥናቶች አሠርቷል።

Assié-Lumumba, N. T. 2020. *Gender, knowledge production, and transformative policy in Africa*. Paper commissioned for the UNESCO Futures of Education report. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000374154

Buchanan J., Allais S., Anderson M., Calvo R. A., Peter S. and Pietsch T. 2020. *The futures of work: what education can and can't do.* Paper commissioned for the UNESCO Futures of Education report. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000374435

Common Worlds Research Collective. 2020. Learning to become with the world: Education for future survival. *Education Research and Foresight Working Paper 28.* Paris, UNESCO

Corson, J. 2020. *Visibly ungoverned: strategies for welcoming diverse forms of knowledge.* Paper commissioned for the UNESCO Futures of Education report. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000374085

